


t.me/OLDBOOKSPDF

# I

ወሰኛው እሰጥ አገባ ሁለቱን ወጣቶች ሲያናቁር አረፈደ ። አጀማመሩ እንዲህ ነበር ።

የፈረንሳይዋ የወደብ ከተማ የማርሴል የመቆጣጠሪያ ሰገነት "ፋራኦን" የተባለችው የንግድ መርከብ በመምጣት ላይ መሆኗን የሚገልጽ ምልክት ይሰጣል ። ጊዜው ንጋት ላይ ነበር ፤ የካቲት 24 ቀን 1815 ።

የማርሴል ነዋሪ ወዲያውኑ ወደ ወደቡ ተመመ ። የአንድ መርከብ ወደ ማርሴል መምጣት ጥንቱንም በነዋሪው ሕዝብ ዘንድ እንደ ብርቅ ሲታይ የኖረ ሲሆን በተለይ ደግሞ ፋራኦን የአገር ውስጥ የሥራ ውጤት በመሆኗና ባለቤቷም የአካባቢው ተወላጅ ስለነበረ ሁኔታው የተለየ ክብደት ነበረው ።

ግዙፏ ፋራኦን ዝግ እያለች ለወደቡ በቀረበች መጠን ግን እንዳች አክል የደረሰባት ይመስል የውስጥ እንቅስቃሴዋና የሠራተኞቿ ሽርጉድ ያለወትሮው ጭር ማለቱ በግልጽ ያስታውቅ ጀመር ። በመርከቧ ውስጥ የተፈጠረውን አደጋ ለማወቅ የተቻኮለው ሕዝብ ማጉረምረም ያዘ ።

በተለይ ሁኔታው አላምርህ ያለው የፋራኦን ባለንብረት መርከቧ ከተወለደችባት ሥፍራ ደርሳ መልህቋን እስክትጥል አላስችል ብሎት በአንዲት ትንሽ ጀልባ ተሣፍሮ ወደ ፋራኦን አመራ ።

የፋራኦን ረዳት አዛዥ ይህ ሰው መምጣቱን ከሩቅ ይመለከት ኖሮ ባርኔጣውን በእጁ እንደያዘ ጀልባዋ ወደ ምትመጣበት አቅጣጫ ተጠጋ ። ረዳት አዛዡ ከከባድ ሥራና ከአደጋ ጋር የተላመደ ፤ ዕድሜው ከሃያ ዓመት የማይበልጥ ወጣት ለመሆኑ ቀልጣፋ እንቅስቃሴው ይመሰክራል ።

" እንኳ ገባችሁ ፤ መሴ ኤድመንድ " አለ ጀልባዋ ላይ ያለው የፋራኦን ጌታ ረዳት አዛዡን አንጋጦ እየተመለከተ ። " ምን ችግር ገጠማችሁ ፣ ምነው የመርከቤ እንቅስቃሴ ያለድሮው ጭር ብሏል ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ሚች ካፒቴን ሌክሌር የሰጠኝን ትዕዛዝ ለመፈጸም ነበር ጌታዬ ። በጣዕረ ሞት ላይ በነበረበት ወቅት ወደ ኢልባ ደሴት ሄጀ ለማርሻል በርትራንድ እንዳደርስ አንድ የታሸገ ነገር ሰጥቶኝ ነበር ።”

“ ታዲያ ማርሻሉን አገኘኸው ? ”

“ አዎ ፤ ጌታዬ ። ”

ሞሬል ብቻቸውን መሆናቸውን ለማረጋገጥ ዙሪያውን በአይኑ ከቃኘ በኋላ የኤድመንድን ክንድ ያዝ አድርጎ ወደ አንድ ጥግ ወሰደውና “ ለመሆኑ ናፖሊዮን እንዴት ናቸው ? ” ሲል ጠየቀ በሹክሹክታ ፤ መልሱን ለማወቅ ጓጉቶ ።

“ ለአጭር ጊዜ እንዳየሁዋቸው ደህና ይመስላሉ ። በማርሻሉ ክፍል ውስጥ እንደተቀመጥኩ መጥተው ነበር ።”

“ አነጋገርካቸው ?”

“የለም እሳቸው ነበሩ ያነጋገሩኝ” አለ ኤድመንድ፤ ባንድ ወቅት ‘ታላቁ ናፖሊዮን’ ይባል ከነበረ የፈረንሣይ መሪ ጋር በመነጋገሩ በኩራት ሳቅ ብሎ ።

“ ምን አሉህ ? ”

“ ስለመርከቧ ፤ ከማርሴል መቼ እንደተነሣን ፤ በየትኛው መሥመር እንደተጓዝንና ምን እንደጫን ጠየቁኝ ። የመርከቧ ባለቤት እኔ ብሆንና መርከቧ ጭነት ባይኖራት ኖሮ ሊገዙኝ ፈልገው ነበር መሰለኝ። ዳሩ ግን እኔ ተጠባባቂ አዛዥ መሆኔንና የመርከቧ ንብረትነት ‘ሞሬልና ልጆቹ’ ለተባለ ድርጅት መሆኑን ገለጽኩላቸው ። እሳቸውም ፤ ‘እሱን ድርጅት አውቀዋለሁ ። ሞሬል ከጥንት ጀምሮ የታወቀ የመርከብ ባለንብረት ሆኖ የኖረ የዘር ግንድ ነው’ አሉኝ ።”

“ እርግጥ ነው” አለ ሞሬልም በኩራት ። ቀጥሎም ኤድመንድን በጓደኝነት አስተያየት ከተመለከተው በኋላ ትከሻውን መታ መታ አደረገና እንዲህ አለ ። “ የካፒቴን ሌክሌርን መልዕክት ለማድረስ በኢልባ ደሴት መቆየትህ ትክክለኛ ተግባር ነው ። ለማርሻሉ የታሸገውን ነገር መስጠትህንና ከናፖሊዮን ጋር መነጋገርህን ያየ ሰው



t.me/OLDBOOKSPDF

ቢኖር ኖሮ ግን እንገትህን ለገመድ የሚዳርግ ቅጣት ይደርስብህ ነበር ። ”

“ እንዴ ፣ እንዴት ?” ሲል ጠየቀ ኤድመንድ ግንባሩን ቋጥር አድርጐ ።“በእሽጉ ውስጥ ያለው ነገር ምን እንደሆነ እንኳ አላውቅ ። በዚያ ላይ ንጉሡ ለማንኛውም እንግዳ ከሚቀርብ ጥያቄ የተለየ ሌላ ንግግር አላደረጉልኝ ። ግን አንድ ጊዜ ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ... የጤናና የቀረጥ ሠራተኞች ወደ ፋራኦን ሲገቡ ይታዩኛል ። ”

ኤድመንድ ፈቀቅ እንዳለ ዳንግላር ወደ ሞረል ተጠግቶ እጆቹን እያፍተለተለ ፣ “ ይኸ ጥጋበኛ መቸም አያፍር ፣ ይኸኔ በሥልጣኑ ላባከነው ጊዜ ዘጠኝ ምክንያት ደርድሮለዎ ይሆናል ” አለ ።

“ አጥጋቢ ምክንያት ነው ያቀረበልኝ መሴ ዳንግላር ” አለ ሞረል ተሰላችቶ ።

“ ኧረ እኔ ምን አግብቶኝ ፣ ባልንጀራ አደራውን ችላ ሲል መመልከቱ ለህሊናዬ ስለከበደው ነው እንጅ ።”

“ ተው አንጂ ዳንግላር ፣ ኤድመንድ አደራውን በመወጣቱ ተወቃሽ ሊሆን አይችልም ። የቆይታው ትዕዛዝ የተላለፈው በካፒቴን ሌክሌር ነበር ። ”

“ ስለካፒቴን ሌክሌር ከተናገረ አድርስልኝ የተባለውን ደብዳቤ ሰጥቶዎታል ?”

“ የምን ደብዳቤ ? ”

“ ካፒቴን ሌክሌር ከእሽጉ ጋር ደብዳቤ ጨምሮ የሰጠው መሰለኝ ።”

“ የምን እሽግ ዳንግላር ? ” ሞረል ሁኔታው ቢያስደነግጠውም የማያውቅ ለመምሰል ሞከረ ።

“ እንዴ ፣ ኤድመንድ ኢልባ ደሴት ላይ ለማርሻል በርትራንድ የሰጠው እሽግ ነዋ ! ”

“ ወደ ኢልባ የሄደው ለመዝናናት ነው ስትል አልነበረም ፣ እሽግ ማድረሱን እንዴት አወቅህ ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በኮሪደሩ በኩል አለፍ ስል የካፒቴኑ በር ሙሉ ለሙሉ አል ተዘጋም ነበር ፤ እሽግና ደብዳቤ ለኤድመንድ ሲሰጠው ተመለከትኩ ።”

“ ስለሱ ምንም አልነገረኝም ። ሆኖም ደብዳቤው በእጁ ካለ እንደሚሰጠኝ አልጠራጠርም ።”

ዳንግላር ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ “ ጌታዬ ፤ እባክዎ ይህን ጉዳይ በኤድመንድ ፊት አያንሱት... እኔ ተሳስቼ ይሆናል ?” አለ ።

በዚህ ቅጽበት ኤድመንድ እንደ ተመለሰ ዳንግላር ፈንጠር ብሎ ቆመ ።

“ ሥራህን ያገባደድህ ትመስላለህ ኤድመንድ ፤ ” ሞረል ነበር ።

“ ወይዚያው ነኝ ፤ ጌታዬ ። ”

“ መልካም ፤ እንግዲያው ራት ልጋብዝህ ? ”

“ ይቅርታ ይደረግልኝ ጌታዬ ፤ መጀመሪያ አባቴን ማየት አለብኝ ። ”

“ ትክክል ነህ ኤድመንድ... የተባረክህ ልጅ ነህ ። በል አባትህን ከጠየቅህ በኋላ እንጠብቅሃለን ። ”

“ አሁንም ታላቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ ሙሴ ሞረል ፤ ከዚያ በኋላም ቢሆን ከአባቴ የማላሳንሰው ሌላ ሰው በጉጉት ይጠብቀኛል ። ”

“ እሃ ፤ ልክ ነው ። ሜርሲደስ እንደአባትህ ትዕግሥቷን አጥታ እንደምትጠብቅህ ዘንግቻለሁ ። የታደልክ ነህ ኤድመንድ ፤ በጣም የተዋበች እመቤት አለችህ ።”

“ እመቤቴ እኮ አይደለችም ፤ ጌታዬ ” አለ ወጣቱ መርከበኛ ሲስቅ እየቃጣው ። “ እጮኛዬ ነች ። ”

“ ፍቅር እስካለ ሁለቱም ያው ናቸው ። ” አለ ሞረል እየሣቀ ፤ “ እሷ እመቤትህ ፤ አንተ ጌታዋ! . . . . በል ለማንኛውም ጊዜህን አል ግደልብህ ። የኔን ጉዳዮች በሰላምና በጥንቃቄ ስታከናውን በመስን በትህ ምሥጋናዬ የላቀ ነው ። ውለታ መላሽ ያድርገኝ ። አሁን ደግሞ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለታና የውለታ ተቀባይ ተ"ትሮ የለበትም ። ጉልበትህና ጥራልህ ጽት እስከሆነ የትም ቦታ ቢሆን ውጤቱ ይኸው ነው ። በል ሂድና አባትህንና ሚርሲደስን ካዩህ በኋላ ተመልሰህ ወደኔና ።"

" ወደ የብስ እንዳደርስዎ አይፈልጉም ?"

" የለም ፤ አመሰግናለሁ ።እዚሁ መርከቧ ላይ ከዳንግላር ጋር ሂሣብ ሣወራርድ እቆያለሁ ። በንገራችን ላይ በጉዞህ ወቅት በዳንግላርስ አልረካህበትም ?"

" መልሱ አስቸጋሪ ነው ጌታዬ። አጠያየቅዎ ወዳጅነትን በሚመለከት ከሆነ መልሱ አልረካሁበትም ይሆናል ። በእኔ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያለው ከመሆኑም በላይ የምኘነቴ ብዛት ምንቴ ክሪስቶ ደሴት ላይ እንደደረስን እርቅ ስጠይቀው እንኳ አሻፈረኝ አለ ። ሥራውን በሚመለከት የቀረበ ጥያቄ ከሆነ ግን እንከን የሚወጣለት አይመስለኝም ። ትጉህ ነው ።"

" የፋራኦን ካፒቴን ስትሆን በሥራው ላይ ቢቆይ ትፈቅዳለህ?"

" ካፒቴንም ሆንኩ ተጠባባቂ አዛዥ ጌታዬ " ሲል መለሰ ኢድመንድ ። " ምንጊዜም ባለመርከቡ ለሚያምንባቸው ሰዎች አክብሮት ማሳየቴን አልተውም ።"

" ጐሽ ጐሽ ፤ በሁሉም መንገድ የልብ የምታደርስ ወጣት መሆንህን ተረድቻለሁ ። በል ይልቅስ ጊዜህን አላባክንብህ ።"

"ይበሉ ደህና ይቆዩኝ ሙሴ ሞረል ፤ ከልቤ አመሰግንዎታለሁ ።"

ኢድመንድ ከመርከቧ ወርዶ ከባህሩ ከወጣ በኋላ በሕዝቡ መሐል ተቀላቅሎ ወደ አባቱ ቤት ሲጣደፍ ባለመርከቡና ዳንግላር ጐን ለጐን ቆመው አይናቸቸው ባንድ ላይ ተከተሉት ። ልቦቻቸው ግን ፍፁም በተለያየ ጐዳና ነጉደው ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 2

ኢድመንድ ከወደቡ ብዙም ሳይርቅ ወደሚገኘው ወደ አባቱ ቤት እንደደረሰ ጭለማ የዋጣቸውን ደረጃዎች ረግጦ ከወጣ በኋላ በከፊል ገርበብ ብሎ ከተዘጋ በር ላይ ሲደርስ ቆም ብሎ ሲመለከት የትንሿ ክፍል ውስጣዊ ገጽታ ታየው። የአባቱ የመኝታ ክፍል ነበረች።

" አባቴ ! አባ ! " ተንደርድሮ ከመግባቱ ሊስማቸው በርከክ አለ ። ሽማግሌው ግን ከመሃላቸው የተነሣ ጉልበታቸው ላይ የተደፋውን ልጃቸውን እንኳ ቀና ማድረግ አልቻሉም ።

" ምነው አባ!" አለ ኢድመንድ ተቻኩሎ፤ " ታመሃል ልበል?"

"የለም የለም፤ ኢድመንድ ልጄ፣ አዛኜ፣ እንዱ ልጄ፤ ደህና ነኝ። ትመጣለህ ብዬ ባላሰብኩበት ሰዓት ድንገት ሳይህ .... ደስታ አስደ ነገጠኝ ።"

" ደስታ ቀላል ነው ፤ መከራ ነው ከባድ ይባል አልነበር፣ . . . ልክ እንደደረስኩ አይንህን ላይ ፤ የገጠመኝንም ጥሩ ዕድል ልነግርህ ወዳንተ ሮጥኩ ። በል ይልቅስ በደህና መጥቻለሁና አብረን ደስ ይበለን ። በርታ በል ፤ አባ !"

" ግሩም ነው ልጄ ! " አሉ ሽማግሌው በረጅሙ ተንፍሰው " ግን እንዴት ነው አብረን ደስ የሚለን?ካሁን በኋላ ትቸህ አልሄድም ማለትህ ይሆን ? እስኪ ለማንኛውም ስለገጠመህ ጥሩ ዕድል አጫ ውተኝ ።"

" በሌላ ሰው ሞት ምክንያት በገጠመኝ ጥሩ ዕድል በደስታ በመ ፈንጠዜ ይቅር ይበለኝ ። ብቻ የሆነው ሆኗል፤እኔም ' ነፍስ ይማር ' ከማለት በስተቀር የተቆረጠ ዕድሜ የምቀጥልበት ኃይል አልነበረኝም። ይኸውልህ ፤ ካፒቴን ሌክሌር ከዚህ ዓለም በሞት በመለዩቱ ለተለ ቀቀው ቦታ እኔ ታጭቻለሁ ። ምን ይመስልሃል አባ ፤ገና ሃያ ዓመት እንኳ በቅጡ ሳይሞላ በካፒቴንነት ደረጃ ላይ መድረስ፣ የግዙፏ ፋራ ኦን ዋና አዛዥ መሆን ፤ ወፍራሙ ደመወዝ ፤ . . . . . እንደኔ ያለ ምስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኪን መርከበኛ በእውኑ ማግኘት ቀርቶ በሕልሙ ቢያየው እንኳ መታደል ነው ።”

“ በጣም ትልቅ እድል ነው ልጄ ።”

“ አባ ፤ ባጭር ጊዜ አንድ ቆንጆ የአትክልት ጓሮ ያለው መለስተኛ ቤት ልገዛልህ አስቤአለሁ ። . . . . ግን ከመምጣቴ በወሬ አለለቾሁህ መሰለኝ ፤ አንድ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ያስፈልግሃል ” አለ ኢድመንድ ፤ “ የት ነበር ወይን የምታስቀምጠው ? ”

“ ምንም አያስፈልገኝ ። ” አሉ ሽማግሌው ልጃቸውን ለመከልከል እየሞከሩ ።

“ የለም ያስፈልግሃል ። የት እንዳለ ንገረኝ ። ” ደምበጃኖችን እየከፈተ መፈለግ ጀመረ ።

“ አትድከም ልጄ ፤ ጭላጭም አታገኝ ።”

“ አታገኝም ?” በማለት ኢድመንድ ቃሉን ደገመው ፤ፊቱ ቀልቶ አንድ ጊዜ የአባቱን ጉድጓዳ ጉንጮች አንድ ጊዜ ደግሞ ባዶ ምቹን ደምበጃኖች እያፈራረቀ በመመልከት ። “ ገንዘብ ቸግሮህ ኖሯል አባ ?”

“አሁን አንተ እዚህ ከጐኔ አለህ ፤ አንድም ነገር አያስፈልገኝ።”

“ ግን . . . . .ግን ከዚህ ስሄድ ሁለት መቶ ፍራንክ እንደሰጠሁህ አስታውሳለሁ ።” አለ ኢድመንድ ፊርጠም ብሎ ።

“እውነት ነው ፤ ኢድመንድ ። ግን ጓደኛህ ካደሮስ ትንሽ ገንዘብ አበድሮህ እንደነበረ ዘንጋህ መሰለኝ ። ብድሩን አስታውሶኝ እኔ ካልከፈልኩት ለሞሬል ሄዶ እንደሚናገር አስጠነቀቀኝ ። ነገሩ አለቃህ ጆሮ መድረሱ ይጐዳሃል ብዬ ከፈልኩት ። ”

“ ከካደሮስ የተበደርኩትኮ አንድ መቶ አርባ ፍራንክ ነበር አባ! ከተውኩልህ ሁለት መቶ ፍራንክ ውስጥ ነው የከፈልከው ማለት ነው!”

ሽማግሌው በአዎንታ ራሣቸውን ከፍ ዝቅ አደረጉ ።

“ታዲያ ድፍን ሶስት ወር በስድሣ ፍራንክ ከረምህ? እግዚኦ! . . . ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ሜርሲዲሰን ማለትህ ነው?" አሉ ሽማግሌው ጣልቃ ገብተው።

"አዎ አባዬ፣" አለ ኢድመንድ ነጠቅ አድርጎ። "በል አሁን አን ተን ካዬሁ፣ ደህንነትህን ካረጋገጥኩ፣ የሚያስፈልግህ ነገር እንዲሟ ላልህ ማድረጌን ከተረዳሁ ዘንድ አንድ አፍታ ሜርሲደሰን ልጠይ ቃት ?" አባት ፈቃደኝነታቸውን ገልጸውለት ጐንበስ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ ካደሮስን ተሰናብቶ ወጣ ።

ካደሮስ ከአፍታ ቆይታ በኋላ ከኢድመንድ አባት ክፍል ወጥቶ ጥቂት እንደተጓዘ ከውጭ ሲጠባበቀው የነበረውን ዳንግላርን አገ ኘው ።

" እሽ " አለ ደንግላር ፤ " ስለካፒቴንነቱ ያለውን ተስፋ አሚወተህ ?"

" እንዳለቀለት ልቡን ሞልቶ ያናፋ የለም እንዴ ! እንዲያውም ይኸው ሹመት ማይሆን አይቀርም የጀነነው ። ሁኔታው ሁሉ የትልቅ ሰው ሆኗል ። " ካደሮስ ንግግሩን በደረቅ ሳቅ አጀበው ። " ቂቂቂቂ "

" አሁንም የሜርሲደስ ፍቅር አለው ?"

" ከግር ጥፍሩ እስከራስ ጸጉሩ ነዋ ! አባቱን እንኳ በቅጡ ሳያ ናግራቸው ወደሷ አልሄደ መሰለህ . . . . ግን ባልሳሳት ደንቃራ ሳያ ጋጥመው አይቀርም ።"

" የምን ደንቃራ ?"

" ውስጣቸውን አላውቅም ፤ ሁልጊዜ ሜርሲደስ ወደ ከተማ ስት ወጣ አንድ የካታላን ሰው አብሯት ሲጓዝ አያለሁ ።እንዲያውም ከጥ ቂት ጊዜ በፊት ወደሷ ቤት ሲገባ አይቻለሁ ።"

" እንግዲያውስ እስኪ ለማንኛውም በዚያው አቅጣጫ እንከተ ለውና አንድ ቤት አረፍ ብለን ጠርሙስ ወይን ጠጅ ይዘን መጨረሻ ውን እንስማ ።"

" ከማን አፍ ልንሰማ እንችላለን ? " አለ ካደሮስ

" ከመንገዱ ዳር እንሆንና የሆነውን ሁሉ ቀድሞ ከሚመጣው ሰው ገጽታ እናነባለን ። ወይ ከካታላኑ፤አለዚያም ከኢድመንድ ከራሱ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በሉ እንሂድ ” አለ ካደሮስ ። “ ልብ አድርግ ግን ለወይን ጠጁ ከፋይ አንተ ነህ ፤ አይደለም ? ቂ ቂ ቂ ቂ ”

“ እንዴታ ! ”

ሁለቱ ጓደኞች በፍጥነት ይራመዱ ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 3

ዳንግላርና ካደሮስ ወይን ጠጅ እየጠጡ ከተቀመጡበት ሥፍራ ብዙም ሳይርቅ ካታላን ተብሎ የሚጠራ ጉጣ የሚኖርበት መንደር ይገኛል ።

አንድ ቀን ማንነታቸው በውል የማይታወቅ ሰዎች ከማርሴል ዳርቻ እስካሁን ድረስ በያዙት ጠባብ ሥርጥ ላይ ሠፈሩ ። የተመዘገበ ታሪክ ባይኖርም እኒህ ሰዎች ከእስፓኝ እንደፈለሱ ይነገራል ። መሪያቸው የማርሴልን ነዋሪዎች ጀልባቸውን ያሳረፉበትን ትንሽ መሬት እንዲሰጧቸው ጥያቄ አቀረበ ። ጥያቄው እንደተሟላላቸውም እነዚህ የባህር ሰዎች በሶስት ወራት ውስጥ አነስተኛ መንደር ለመቆርቆር በቁ ። ይህ ከሆነ ሶስትና አራት መቶ ዓመታት አልፈዋል ፤ ካታላኖች ግን ከዚያች ምድር ጋር ተቆራኝተው ከመቅረታቸውም በላይ ከማርሴል ሕዝብ ጋር እምብዛም አይቀላቀሉም ። ጋብቻ የሚፈጽሙት እርስ በርሣቸው ሲሆን ጥንታዊ ቋንቋቸውንም ሆነ ባህልና ወጋቸውን እንደጠበቁ ናቸው ።

በዚህች መንደር መካከል አቋርጦ በሚያልፈው ብቸኛ አውራ ጎዳና ግራና ቀኝ ከሚገኙት መኖሪያ ቤቶች መካከል በአንዱ ውስጥ አንዲት ጸጉሯ ሽንጧን እየታከከ በዳሌዋ ትክክል እስኪደርስ ድረስ የወረደ ፤ ውብ ልጃገረድ ግድግዳውን ተደግፋ ቆማለች ። ከፊት ለፊቷ እድሜው በሃያ ዓመት አካባቢ የሚገኝ ወጣት የተቀመጠበትን ወንበር ወዲያ ወዲህ እየናጠ ልጅቷን ንዴትና ቁጣ በተቀላቀለበት አስተያየት ይመለከታታል ። አይኖቹ ለልጅቷ ጥያቄ እያቀረቡ ቢሆንም የልጅቷ ኮስታራና ጽኑ ሁኔታ የበላይነትን እንዳገናጸፏት በግልጽ ያስታውቃል ።

“ ስሚ ሜርሲደስ ፣” አለ ወጣቱ “ ዘንድሮም እንደገና ፋሲካ መድረሱ ነው። ለጋብቻ መቼም ከዚህ የበለጠ አመቺ ጊዜ አይገኝም። መልስ እፈልጋለሁ ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በዚያ ላይ ከፊት ለፊታቸው አግት የሚያስቆንጥጥ ወይን ጠጅ ጠርሙሱን አውርደው እያዩህ ? ” አለ ዳንግላር በግቅ ቀበል አድርጎ ።

ፈርናንድ ከቆመበት ግይነቃነቅ ሁለቱን ሰዎች በተለላቸ አለ ተያየት ከመመልከት በቀር የሚናገረው አልነበረውም ።

“ ቀንዷን የተመታች ላም ይመስላል !” አለ ዳንግላር ቀስ ብሎ ካደሮስን በክርኑ ጉሸም በማድረግ “ ሊድመንድ የበላይነቱን ግይ ቀዳጅ አልቀረም ።”

“ ልናይ አይደል” አለ ካደሮስ ቀጠል አደረገና ። ከዚያም ወደ ፈርናንድ ዞር ብሎ “ አትግደርደር እንጅ !” አለው ።

ፈርናንድ በግንባሩ የሚወርደውን ላብ ጠረግ አድርጎ በበረንዳው ላይ በዝግታ ወዲያ ወዲህ ይመላለስ ጀመር ።“ ታዲያስ ” አለ መጀመሪያ ። “የጠራችሁኝ ምስለኝ ።” ተቀመጠና ጠረጴዛው ላይ ደፋ ብሎ አረፋ የሚወጣው እስኪመስል ድረስ በረጅሙ ተነፈሰ ።

“ ምን ጉድ ፊትበህ ፈርናንድ ?” አለ ካደሮስ ። “ የተተፋ ፍቅረኛ ትመስላለህ ! ” ንግግሩን በተለመደው ሰላላ ሳቅ አደመቀው ። “ ቂ ቂ ቂ ቂ ”

“ ምንድን ነው የምታወራው ?” አለ ዳንግላር ቀበል አድርጎ “ ፈርናንድን የመሰለ ሸበላ የትኛዋ ልጅ ያበጠ ልጃገረድ ነች የምትተፋው ? . . . . ቀልደኛ ! ”

“ቀልድ አይደለም ። እስኪ ፈገግ ሲል እንኳ አስተውለው ። ና ወዲህ ፈርናንድ ፤ ነገርን አውጥተው ለወዳጅ ሲያጫውቱትኮ ቀለል ይላል ። በዚያ ላይ ባልንጀሮችህ ስለ ጤንነትህ ተጨንቀው ሲጠይቁህ ዝም ማለት ተገቢ አይደለም ። ”

“ ጤንነቴ እንኳ ደህና ነው ። ” አለ ፈርናንድ ከራሱ ቀና ግይል ጭኖቹን እያጋጨ ።

“ አሃ ፤ አሃ ! አዩህ ዳንግላር ? ” አለ ካደሮስ ወደ ዳንግላር መለስ ብሎ ። “ ገባኝ ፤ ገባኝ ። ፈርናንድ ሜርሲደስ ከተባለች ቆንጆ



t.me/OLDBOOKSPDF

" ይቅርታ ይቅርታ ፡" ሲል መለሰ ዳንግላር የደነገጠ በመም ሰል ። " ቸኩለሃል ለማለት ነበር የፈለግሁት ። ፋራኦን ጉዞዋን ለመ ጀመር ሶስት ወር ስለሚያስፈልጋት ሰፊ ጊዜ አለህ ለማለት ነበር ።"

" ሰው ሲባል ምን ጊዜም ለደስታ እንደተጣደፈ ነው ። የእኔው ጉዳይ ግን መስገብገብ ብቻ ሳይሆን ወደ ፓሪስ መሄድ ስላለብኝ ጭምር ነው ።"

" እረ ? እዚያ ጉዳይ አለህ እንዴ ?"

" እኔን የሚመለከት እንኳ አይደለም ። ካፒቴን ሌክሌር እዚያ አንድ ነገር እንዳደርስለት ጠይቆኝ ስለነበር ነው ። እንደምታው ቀው የሙትን አደራ መወጣት ትልቅ ተግባር ነው ። ግን አታስብ ፤ ቶሎ እመለሳለሁ ።"

" ገባኝ ገባኝ " አለ ዳንግላር ። ከዚያም በሃሳቡ እንዲህ ይል ጀመር ። ' ምናልባት ወደ ፓሪስ የሚሄደው ማርሻሉ የሰጠውን ደብ ዳቤ ሊያደርስ ይሆናል ። አሃ ! ያ ደብዳቤ ጥሩ ሃሳብ አመጣልኝ ፤ በጣም ጥሩ ሀሳብ ። አዬ ወዳጄ ኤድመንድ ፤ የፋራኦን ካፒቴን ሊኮን... አፈር ድሜ ። ' ብዙም ሳይቆይ ከሃሳቡ ተመለሰና " መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ ! " አለው ጥርሱን ብልጭ አድርጎ ።

" አሜን" ሲል መለሰ ኤድመንድ ጓደኛውን ፈገግ ብሎ እየ ተመለከተው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 4

በማግሥቱ ጸሐይዋ ገለጥለጥ ባለው ሰማይ ብሩህ ጨረሯን መፈንጠቅ እንደጀመረች ላ ሬዘርቫ በተባለው ሆቴል ሁለተኛ ፎቅ ላይ በኢድመንድ ዳንትና በሜርሲደስ ሄሬራ መካከል የሚፈረመው የጋብቻ ውል ቅድመ ዝግጅት በተሳካ ሁኔታ ይካሄድ ጀመር ። ሥነ-ሥርዓቱ የሚጀምረው ምሽት ላይ መሆኑ ቀደም ሲል የተገለጠ ቢሆንም ገና ጀምበር ማዘቅዘቅ እንደጀመረች ትዕግሥት አጥተው የሚቅበጠበጡ እንግዶች የሆቴሉን አዳራሽ አጣበቡት ። አብዛኞቹ እድምተኞች የኢድመንድ የልብ ወዳጆች የሆኑት የፋራኦን መርከበኞችና ወታደሮች ነበሩ ።

የፋራኦን ባለቤት ሞሬል ራሱ በግብዣው ላይ እንደሚገኝ ወሬው የሚናፈስ ቢሆንም ይህ ጉዳይ ለኢድመንድ ከሚገባው በላይ ታላቅ ክብር ከመሆኑ የተነሣ ማንም ሰው ሊያምን አልቻለም ። ይሁን እንጂ ባለመርከቡ ሞሬል በእርግጥም በሥነ ሥርዓቱ ሥፍራ ደረሰና የፋራኦን ሠራተኞች ከልብ በመነጨ የአፍቅሮት አቀባበል ሰላምታ ሊያቀርቡለት በቁ ። በሌላ በኩል ደግሞ የሞሬል በሥነ ሥርዓቱ መገኘት የኢድመንድን ሹመት የሚያረጋግጥ ምልክት በመሆኑ ኢድመንድን ያፈቅሩ የነበሩት የፋራኦን መርከበኞች የሞሬል ምርጫ የእነሱም በመሆኑ ደስታ ያስቦርቃቸው ጀመር ።

እውነትም የሞሬል አመጣጥ ዓላማው ከውሉ ሥነ ሥርዓት በኋላ ኢድመንድን ካፒቴን እንዳደረገው በእድምተኞቹ ፊት ለማስታወቅ መሆኑን ራሱ ሲናገር ተሰማ ። ሠርግና ሹመት ባንድ ምሽት ። የሜርሲደስ ገደ ቀናንነት የአዳራሹ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ቆየ ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሙሽሮቹና እድምተኞቻቸው ወደ ሆቴሉ ሲያመሩ ታዩ ። ኢድመንድና ሜርሲደስ በአራት ሚዜዎችና በኢድመንድ አባት ታጅበዋል ። ከጀርባቸው ፈርናንድ በፌዝ ሳቅ ፈገግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርምታና የመሣሪያዎች ድምጽ በሩ ላይ አስተጋቡ ። በሩ በተደጋጋሚ በኃይል ሲንኳኳ ቆይቶ ኖሯል ። ሁሉም ሰው ጸጥ አለ ።

"በሕግ አምላክ ክፈት" ሲል አንድ ድምጽ ጮኸ ። ወዲያው በሩ እንደተከፈተ አንድ የፖሊስ ኮሚሳር በአንድ ኦፊሰር አለቃ የሚመሩ አራት የታጠቁ ወታደሮችን አስከትሎ ዘው አለ ።

" ምንድን ነው ጉዳዩ ?" አለ ሞረል ባጋጣሚ ያውቀው ወደ ነበረው የፖሊስ ኮሚሳር እየተጠጋ ።" አንድ ስህተት ሳይፈጸም አል ቀረም ።"

" ስህተት ቢሠራ እንኳ መሴ ሞረል " አለ ኮሚሳሩ ፤ " በአፋጣኝ ይስተካከላል ። የማስገደድ ሥልጣን ተሰጥቶኛል ፤ ኃላፊነቴን የመወጣት ግዴታም አለብኝ ። ለመሆኑ የትኛው ነው ኤድመንድ ዳንት ?"

ሁሉም አይኖች ወደ ወጣቱ ሙሽራ አተኮሩ ። ኤድሙንድ ግን ነገሩ ቢያስቆጣውም ክብሩን ለመጠበቅ ራሱን እየተቆጣጠረ ወደ ፊት ሄደና፤" ኤድመንድ ዳንት ማለት እኔ ነኝ ጌታዬ! ምን ልታዘዝ?" አለ ።

" ኤድመንድ ዳንት ፤ ካሁኑ ደቂቃ ጀምሮ በቁጥጥር ሥር ውለሃል ።"

" በቁጥጥር ሥር ? " ሲል ኤድመንድ ቃሉን ደገመው ፊቱ ደም ለብሶ ፤ " ምን አጥፍቼ ?"

" በእውነቱ እኔ አላውቅም ፤ በመጀመሪያው ምርመራ ወቅት ይገለጽልሃል ። "

ነገሩ አሣዛኝም አስገራሚም ነበር ። ድንገተኛነቱም እንደ አንደርብ ነበር ። ከሙሽርነት ወደ እሥረኛነት ። ሜርሲደስ ሰውነቷ ከሁለት የተፈረፈ መሰላት ። ክርክር ማንሳቱ እርባና እንደሌለው ሞረል ወዲያውኑ ተረዳ ። የማስገደድ ሥልጣን የተሰጠው ኮሚሳር በድርድር የሚያምን ሰው ሳይሆን ለሕግ የቆመ ሐውልት ነው ። ወለም ዘለም የለም ። ይሁን እንጂ የኤድመንድ አባት ወደ ኮሚሳሩ ተንደርድሮ ተጠጋ ። ምንጊዜም የእናትና የአባት ልቦች የማይገነዘቧቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

አንዳንድ ነገሮች አይታጡም ። የኢድመንድ አባት ከመለመን አል ፈው ተማጸኑ ። እንባና መማጸን የሚፈይዱት ነገር ባይኖርም የሽማ ግሌው ሐዘን ግን እጅግ ያሳዝን ስለነበረ ኮሚሳሩም ልቡ ሣይነካ አልቀረም ። "ረጋ በሉ አባቴ ፤" አለ ኮሚሳሩ፤ "ልጅዎ ምናልባት አንዳንድ የቀረጥ ደንቦችን ተላልፎ ይሆናል ። ተፈላጊውን መረጃ ከሰጠ የማይለቀቅበት ምክንያት የለም ።"

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢድመንድ ከጓደኞቹ ጋር እጅ ለእጅ ተጨ ባብጦ ሲሰናበታቸው ፤ "ከዚህ ሥነ ሥርዓት ስንሣ ምን እንደተሰ ማኝ በቃላት ልገልጸው ባልችልም ፤ አይዟችሁ ። የተፈጠረው ስህተት በአስቸኳይ — እንዲያውም እሥር ቤት ከመድረሴ ቀደም ብሎ — እንደ ሚስተካከልና አሁኑኑ እንደምመለስ እርግጠኛ ነኝ ።" አላቸው ። ከዚ ያም ኮሚሳሩን ከፊቱ አስቀድሞ በወታደሮቹ እንደተከበበ ከሆቴሉ ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 5

የኤድመንድ ዳንት የጋብቻ ውል ሥነ ሥርዓት ሲከናወን በነበረበት ሰዓት ማርሴል ከተማ ውስጥ ከሚገኙት የመሳፍንት ሕንጻ የሚመሳሰሉ ግምቦች መካከል በአንዱ ሌላ የጋብቻ ውል ይፈረም ነበር ። ይሁን እንጅ በዚህኛው ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙት እንግዶች እንደ ኤድመንድ እድምተኞች ተራ መርከበኞች ሳይሆኑ እንደተኮለኮሉበት ሕንጻ በማርሴል የታወቁ ሰዎች ነበሩ ። ከመካከላቸውም በናፖሊዮን ዘመነ መንግሥት ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁ የቀድሞ የሕግ ሰዎች ፤ የጦር መኮንኖችና ወጣት ከበርቴዎች ይገኙባቸዋል ።

ጊዜው በመላው ዓለም ዱካውን ትቶ ባለፈው የፈረንሳይ አብዮት ማግሥት የተነሣው ናፖሊዮን ፈረንሣይን ከመግዛት አልፎ አለምን እያንቀጠቀጠ በተለያዩ የአውሮፓ ቋንቋዎች ‘ ናፖሊዮን ለዘላለም ይኑር ! ’ እያሰኘ ያዘምር እንዳልነበረ ሁሉ ንጉሣዊው አገዛዝ እንደገና የናፖሊዮንን መንግሥት ገልብጦ ዙፋን ላይ በመውጣቱ ናፖሊዮን ኢልባ ወደ ተባለችው የአምስትና የስድስት ሺህ ሰዎች መኖሪያ ደሴት ሸሽቶ በስደተኛ ሽፍትነት መንግሥትን ሲፈታተን የነበረበት ዘመን ነበር ። ይህ ውድቀቱ እንደማይቀርለትም እነዚህ በድግሱ የተጠሩ እንግዶች ጠንቅቀው ያውቁ ነበር ። ናፖሊዮን ያሸቀነጠራቸው ንጉሥ እንደገና ወደ ሥልጣን በመመለሳቸው በደስታ የፈነደቁት እነዚህ እንግዶች ሕይወት በድል ስላሸበረቀችላቸው ወደሕጻንነት የተመለሱ እስኪመስላቸው ድረስ እንደ ፀደይ እምቡጳ ይፈነጫሉ ። ከእስፈሪ ቅዠት እንደ ባነኑ ነበር የሚሰማቸው ።

የድግሱ ሥነ ሥርዓት እንደጀመረ አንድ መስቀል ባንገቱ ያደረገ ሽማግሌ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ለንጉስ ሉዊስ አሥራ ስምንተኛ ጤንነት ጽዋቸውን እንዲያነሱ ጠየቀ ። ምላሹ ፈ



t.me/OLDBOOKSPDF

" አዎ ፤ ግን ለማንኛውም መጀመሪያ ደብዳቤውን ስጠኝና ፈርም ።"

"አንተ ጋ መሆን አለበት ፤ ከሌሎች ደብዳቤዎቹ ጋር ነው የወሰድኸው ።"

" ቆይ እስኪ " አለ ቪልፎርት ኢድመንድ ባርኔጣውንና የእጅ ጓንቱን ሲያነሣ ተመልክቶ " ደብዳቤው ለማን የሚሰጥ ነበር ?"

" ኖርቴር ለተባለ ፓሪስ የሚኖር ሰው ነው ጌታዬ ።"

ከፊት ለፊቱ መብረቅ ቢጥል እንኳ ቪልፎርት እንደዚያ ሊደነግጥ አይችልም ። ከኢድመንድ የተወሰዱትን ደብዳቤዎች ለማንሣት ብድግ ከማለቱ በድንጋጤ ክው ብሎ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ።ደብዳቤውን አንስቶ በቃላት ሊገልጹት በማይቻል ፍርሃት እየተርበደበደ አስተዋለው ። " ለኖርቴር . . . ፓሪስ " ይላል አድራሻው ። ቪልፎርት ፊቱ ገረጣ ። የተጻፈው ለአባቱ ኖሯል ።

" ደብዳቤው የተጻፈለትን ሰው ታውቀዋለህ መሰለኝ ።" አለ ኢድመንድ ።

"ኧረ የለም !" በማለት ካደ ቪልፎርት ፤"አንድ ታማኝ የንጉሥ ሎሌ እንዴት ከሴረኞች ጋር ትውውቅ ሊኖረው ይችላል ?"

" ደብዳቤው ስለ ሴራ ነው እንዴ ?" ሲል ጠየቀ ኢድመንድ ራሱ ነጻ መሆኑን ማሳመኑን ካመነ በኋላ ከመጀመሪያው የበለጠ ተቆጥቶ "ያም ሆነ ይህ እኔ ቀደም ብዬ ነግሬሃለሁ ። ስለ ደብዳቤው ይዘት ምንም ነገር አላውቅም ።"

" አዎ" ሲል አጉረመረመ ቪልፎርት " ግን ደብዳቤው የተጻፈለትን ሰው ስም ታውቃለህ ።"

" እንዴ ፤ ደብዳቤውን ለማድረስ ስሙን ማጥናት የለብኝም እንዴ ?" ሲል በጥያቄ መለሰ ኢድመንድ ።

" ለመሆኑ ይህንን ፖስታ ለሰው አሳይተሃል ?" አለ ቪልፎርት ደብዳቤውን ከፍቶ እያነበበ ።

" ለአንድም ሰው አለማሳየቴን እምላለሁ ።" ነበር የኢድመንድ መልስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍርጥርጥ አድርገህ ትናገራለህ ፡፡የተቃጠለውን ደብዳቤ በሚመለከት ግን እንዲትም ቃል እንዳትተነፍስ ፡፡"

" ቃል እገባለሁ ፤ ጌታዬ " አለ ኢድመንድ ፡፡

" ምናልባት የሰማ ሰው ቢጠይቅህ እንኳ የሚያዋጣህ መካድ ነው ፡፡ ራስህን ለማትረፍ ከፈለግህ ልምጥ አድርገህ ካድ ፡፡"

" እሺ እክዳለሁ ጌታዬ !"

" ጥሩ " አለና ቪልፎርት ደወል ደውሎ የፖሊሱን ኮሚሳር ጠራ ፡፡

" ይህንን ሰው ተከትለህ ሂድ ፡፡" አለ ቪልፎርት ለኢድመንድ፡፡ ኢድመንድ በምሥጋና አስተያየት ቪልፎርትን ተመልክቶ በትህትና እጅ ከንሣ በኋላ ወጣ ፡፡

ልክ በሩ እንደተዘጋ ቪልፎርት ኃይሉ ከድቶት በከፊል ራሱን ስቶ ወንበሩ ላይ ተዘረረ ፡፡ " አቤት አምላኬ " አለ እንደተጋደመ ፡፡

" ዋናው አቃቤ ሕግ ማርሴል አለመኖሩ በጀ እንጅ ያንን ደብ ዳቤ ያገኘው ነበር ፤እኔም ጉል ገብቼ ነበር ፡፡ አይ አባቴ ፤ እስከ መቼ የደስታዬ እንቅፋት እንደሆንህ ትኖራለህ ? ምን ፍርጃ ነው አንተ ሲያቀብጥህ ጥንት የሠራሃቸው ጥፋቶች ጠስ ሲፈታተኑኝ የሚኖረው፣ ምን ርግማን ነው ካንተ የፈጠረኝ ?"

ወዲያውኑ ግን ያልጠበቀው ነገር ትዝ ብሎት በደስታ ፈካ ፡፡ አይኖቹ አንድ ቦታ ላይ እንደተተከሉ በሃሣብ ተዋጠ ፡፡" አዎ !"አለ ሃሣቡን እንደ ቋጨ ፡፡ " ያ እኔን ሊያጠፋ የነበረ ደብዳቤ ምናልባት የዕድሌ በር ከፋች ይሆን ይሆናል ፡፡ግሩም !"

እሥረኛው በረንዳው አካባቢ አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ቪል ፎርት ወደ እጮኛው ቤት ይጣደፍ ጀመር ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# 6

ኢድመንድ ዳንትና ኮሚሳሩ የኢንግዳ ግረሬያውን ክፍል እንዳ ለቁ ሁለት ወታደሮች ከኢድመንድ ጐን ቆሙ ። ወዲያውም ወደ ፍርድ ቤት የሚያስገባው በር ተከፍቶ እጅግ የሚያስፈሩትን ረጅምና ጨለማ የዋጣቸው መተላለፊያዎች ተጓዙ ።

የቪልፎርት አፓርትማ ከፍርድ ቤቱ ጋር የተገናኘ የመሆኑን ያህል ፍርድ ቤቱ እንደገና ከእሥር ቤቱ ጋር የተያያዘ ነበር ። ብዙ መተላለፊያዎችን ካለፉ በኋላ ኢድመንድና አጃቢዎቹ በመጨረሻው ከአንድ የብረት በር ላይ ሲደርሱ ቆሙ ። በሩ ወዲያውኑ ተከፈተና እንደገባ ከጀርባው ተዘጋ ። ኢድመንድ አሁን የታመቀና ከባድ አየር መተንፈስ ጀመረ ። በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እሥር ቤት ገባ ።

ይሁን እንጂ እሥር ቤቱ ውስጥ በተለይ ለሱ የተሰጠችው ክፍል ንፁህና ቀለል ያለች በመሆኗ ፍርሃቱ ከመቀነሱም በላይ የቪልፎርት የማፅናኛ ቃላትና የሰጠው ተስፋ ጆሮው ውስጥ ያቃጭልበት ነበር ። ብዙም ሳይቆይ ቀኑ መሽቶ ክፍሉን ጭለማ ዋጠው ። በጭለማው የተነሣ አይኑ ማየት ሲሳነው የመስማት ችሎታው ጨመረ ። ትንሽም ድምጽ ሲሰማ መፈታቱን የሚያበስርለት ወታደር የመጣለት እየመሰለው ከተቀመጠበት ቦታ ብድግ ብሎ ወደ በሩ ይሄድና ቆሞ በጉጉት ያዳምጣል ። ድምፁ ግን ወደ ሌላ አቅጣጫ ይሄድና ይጠፋል ፤ እሱም ተመልሶ በርጩማው ላይ ይቀመጣል ።

በመጨረሻ ከምሽቱ አራት ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ኢድመንድ ተስፋ በመቁረጥ ላይ እንዳለ በመተላለፊያው አካባቢ የእርምጃ ድምፅ ሰማ ። እርምጃውም እሱ ከታጐረበት ክፍል ሲደርስ ቆመ ። ቁልፉ ተከፍቶ ግዙፉ በር እንደተበረገደ የሁለት ጧፎች ብርሃን ይታይ ጀመር ። አራት ወታደሮች ገቡ ። “ እሰይ ! ” አለ ኢድመንድ በረ ጅሙ ተንፍሶ ። ልቡ በደስታ ደለቀ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ወደኔ ነው የመጣችሁት አይደል ?" ሲል ጠየቀ ፈጠን ብሎ።

" አዎ ! "

" ረዳት እቃቤ ሕግ ነው የላካችሁ አይደል ?"

" ልክ ነው ።"

የላካቸው ቪልፎርት መሆኑን ማረጋገጡ ለዕድለቢሱ ወጣት ትልቅ እፎይታ ሆኖ ነበር የተሰማው ። መፈታቱን አልተጠራጠረም።

ወደበሩ ሊያመራ ቃጣው ። አራቱ ወታደሮች ግን ከመካከላቸው አድርገውታል ። መንገድ ላይ የእሥረኛ ማሸጊያ ቁም ሣጥን የመሰለ ሠረገላ ይጠብቀዋል ።

የሠረገላው በር ተከፈተ ። ኢድመንድ ነገሩ ሳይገባውና አን ድም ቃል ለመናገር እንኳ ፋታ ሳያገኝ ከኋላው ሲገፈትሩት ተሰማው። የመታገል ፍላጐት አልነበረውም ። ከአፍታ በኋላ ሠረገላው ውስጥ ገብቶ ሁለት ወታደሮች ከጐናቸው ሁለት ደግሞ ከፊት ለፊታቸው አድርገውት ተቀምጧል ። ግዙፉ ሠረገላ ወደ ማይታወቀው አቅጣጫ ጉዞውን ቀጠለ ።

ድፍኑ ሠረገላ እንደቆመ ኢድመንድ ቢመለከት ወደብ ላይ መድ ረሳቸውን ተረዳ ። አንድ የቀረጥ መኰንን በባህሩ ዳርቻ በሰንሰለት አያይዞ ካቆማት ጀልባ ላይ ከአራቱ ወታደሮች ጋር ወጣ ። አንድ ሌላ የፖሊስ መኰንንም ጠርዙ አካባቢ ተቀመጠ። ሌሎች አራት ቀዛፊዎች ባለ በሌለ ኃይላቸው እየቀዘፉ የባህሩን ጉዞ ተያያዙት ።

" ወዴት ነው የምትወስዱኝ ?" ሲል ጠየቀ ኢድመንድ አን ደኛውን ወታደር በዝግታ ።

" ምን አስቸኰለህ ፤አሁን ታውቀው የለ ?"

" ግን . . . . . . "

" ምንም ዓይነት መረጃ እንዳንሰጥ ተከልክለናል ።" ኢድመንድ ሌላ አልተናገረም ። ፀጥ ብሎ በሃሣብ እንደ ተዋጠ ከጭለማ ጋር የተ ላመዱትን የመርከበኛ አይኖቹን እያንከራተተ ዙሪያ ገባውን በመ መልከት የጭለማውን ግርዶሽ ሊሰነጥቅ ይሞክር ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ለዛሬ ሌሊት እዚህ ታድራለህ” አለ ዘበኛው ፤ “ሌሊቱ በመግፋቱ አስተዳዳሪው ተኝቷል ። ምናልባት ነገ ስላንተ የተጻፈውን መመሪያ ካነበበ በኋላ ሌላ ክፍል እንዲሰጥህ ያደርግ ይሆናል ። ይኸውልህ ዳቦ ። ኩባያው ላይ ውሃ አለልህ ። እዚያ ጥግ አካባቢ ደግሞ ለመኝታህ ጥቂት ገለባ ቢጤ አይጠፋም ። ለአንድ እሥረኛ የሚያስፈልጉ ነገሮች ተሟልተውልሃል ። ደህና እደር ። ” እሥረኛው አንድ ቃል እንኳ ለመመለስ ጊዜ ሳይሰጠው ዘበኛው ኩራዟን አንስቶ ከክፍሉ ወጣና በሩን ዘግቶ በውጭ ቆለፈበት ። ኢድመንድ ጥቅጥቅ ካለው ጭለማ ጋር ተፋጠጠ ።

ዘበኛው ተመልሶ የመጣው ጐህ ቀድዶ የመጀመሪያው የንጋት ብርሃን መፈንጠቅ ሲጀምር ነበር ። ዘበኛው ኢድመንድ ከነበረበት ክፍል እንዲቆይ ትዕዛዝ ተቀብሏል ። ኢድመንድ አልተንቀሳቀሰም ። በምስማር የቸነከሩት ይመስል ማታ እንደገባ ከቆመበት ሥፍራ ላይ ሣይንቀሳቀስ ነበር ሌሊቱን ያነጋው ። በዚህም የተነሣ ለአፍታ እንኳ እንቅልፍ አልዞረበትም ። ዘበኛው ወደ ኢድመንድ ጠጋ አለ ፤ኢድመንድ ግን የሚያየው አይመስልም ። ጀርባው ላይ ቸብ አደረገው ። ኢድመንድ ዞር ብሎ ራሱን በፍጥነት አነቃነቀ ።

“ እንቅልፍ አልተኛህም ?” ሲል ጠየቀ ዘበኛው ።

“ እኔ እንጃ ! ”

“ አልራበህም ?”

“ ምን አውቃለሁ ።”

“ ምን የሚያስፈልግህ ነገር አለ ?”

“ አስተዳዳሪውን ማነጋገር እፈልጋለሁ ።”

“ ያ እንኳ አይቻልም ።”

“ ለምን ?”

“ ምክንያቱም የወህኒ ቤቱ ደንብ እሥረኞች እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ እንዳያነሱ ይከለክላል ።”

“ ታዲያ ምንድን ነው የተፈቀደው ?”

“ መክፈል ከቻልህ የተሻለ ምግብ ፤ ከክፍልህ ወጣ ብለህ ወዲያ ወዲህ መንቀሳቀስ ፤ አንዳንዴም መጻህፍትን ማንበብ ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ቸገረኝ ! ምን ቸገረኝ !" አለ ዘበኛው ። " እንዲህ ካሁኑ ጩርቅህን ከፍ ከፍ ማድረግ ከጀመርክ ለአስተዳዳሪው እናገራለሁ ።"

" ጥሩ" አለ ኢድመንድ ። ከዚያም ባርጩማውን ወለሉ ላይ መልሶ ካስቀመጠ በኋላ እሱም ተቀምጦ አንገቱን ደፋ በማድረግ አይኖቹን እያጉረጠረጠ ያበዱ ለመምሰል ሞከረ ። አስተዳዳሪው መጥቶ እንዲያነጋግረው የሚያደርገው ጥረት ነበር ።

ዘበኛው በርግጎ ከወጣ በኋላ በቅጽበት አራት ወታደሮችና አንድ አሥር አለቃ አስከትሎ ተመለሰ ።" በአስተዳዳሪው ትዕዛዝ መሠረት " አለ ዘበኛው ፤ " ይህንን እሥረኛ ምድር ቤት ወዳለው ክፍል ይዛችሁልኝ ውረዱ ።"

" ወደ ጨለማ ቤቱ ?" ሲል ጠየቀ አሥር አለቃው ።

" አዎ ! እብዶች የሚታሠሩት ከእብዶች ጋር ነው ።"

ነገር ገንተረ ።አራቱ ወታደሮች ኢድመንድን አፈፍ አድርገው ያዙት ። ኢድመንድ ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ወታደሮቹን ያለ ተቃውሞ ተከትሎ ወረደ ። በመሬት ውስጥ አሥራ አምስት ደረጃዎችን እንደወረደ የአንድ ክፍል በር ተከፍቶለት ሲገባ " አልተሳሳቱም " አለ ለራሱ ፤ " እብዶች የሚታሠሩት ከእብዶች ጋር ነው !"



t.me/OLDBOOKSPDF

# 7

ንጉሥ ሉዊስ አሥራ ስምንተኛ ፓሪስ ከተማ በሚገኘው ቤተ መንግሥታቸው በተለይ በትንሿ የጥናት ክፍላቸው ውስጥ ምንጊዜም በማትለያቸውና አሁንም ከስደት ወደ ሥልጣን ሲመለሱ ይዘዋት በመጡት ወንበራቸው ላይ ተቀምጠው አንድ እድሜው በግምት አምሳ ዓመት የሚሆን ግማሽ ፀጉሩን ሽበት የወረሰው ሰው የሚያደርግላቸውን ንግግር በግማሽ ልብ ያዳምጣሉ።ከንግግሩ ጠቃሚ ጠቃሚውን ነጥብም በማስታወሻቸው ላይ ለማስፈር ይሞክራሉ ።

" ምንድን ነበር ያልከኝ ?" አሉ ንጉሡ። "እስኪ እጠር አድርገህ ንገረኝ ።"

" ከወደ ደቡብ አደገኛ መብረቅ በማጉረምረም ላይ መሆኑን በመስማቴ በጣም ተጨንቄያለሁ ነው የምለው ፣ጃንሆይ ።"

" የሰም መስፍን ፤ የተሳሳተ መረጃ ሳትቀበል አልቀረህም ። በስተደቡብ ያለው የአየር ሁኔታ መልካም መሆኑን አውቃለሁ ።" ንጉሡና እንግዳቸው የሚናገሩት ቁም ነገር ቢሆንም ቃላት አጣጣላቸው ግን እንደ ቀልድ ነበር ።

"ግርማዊነትዎ የፈረንሣይ ሕዝብን መልካም አመለካከት ማጤኑ ተገቢ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን እኔም አንድ የጣዕረ ሞት ሙከራ ሣይከጀልብን እንደማይቀር መፍራቴ ስህተት ነው አልልም ።"

" ለመሆኑ በማን ነው ሙከራው የሚከጀለው ?"

" በእምባገነኑ ናፖሊዮን ፤ ወይም በጀሌዎቹ ።"

" ህም !" አሉ ንጉሡ በታከተ ሁኔታ ፣" ባዶ ጭንቀትህ ሥራ አስፈታኝኮ ።"

" የርስዎ ችላ ማለት ደግሞ እኔን ሰላም አሳጣኝ ፤ ጃንሆይ ። የኔ ፍርሀት የመነጨው ከሚዳ ወይም ከተራ አሉባልታ ሣይሆን ' ግር



t.me/OLDBOOKSPDF

ማዊነታቸውን ታላቅ አደጋ ያስጋቸዋል ’ በማለት ከጥቂት ጊዜ በፊት ከማርሴል የደረሰ ታማኝና ጨዋ ሰው ከነገረኝ ጥቆማ ነው ። በዚህ ምክንያት ነው ተጣድፌ የመጣሁት ፤ ጌታዬ ። መሬ ቪልፎርትን ቢያነጋግሩት እጅግ በጣም ጠቃሚ ይመስለኛል ።”

“ ቪልፎርት ! ” ሲሉ ንጉሡ ስሙን ሜን አድርገው ደገሙት።

“ ከጥቂት ጊዜ በፊት ከማርሴል መጣ የምትለኝ ሰው ቪልፎርት ነውን ለምን ስሙን ቀደም ብለህ አልነገርከኝም ?”

“ ክቡርነትዎ ስሙን የማያውቁው ስላልመሰለኝ ነው ። ”

“ እንዴት ሆኖ ። ቪልፎርት ጠንቃቃ ፤ የተከበረ ፤ ጨዋና ከሁሉም በላይ ተፍጨርጫሪ ሰው ነው ። በዚያ ላይ አባቱን እጣርቼ አውቃቸዋለሁ ።”

“ አባቱን ?”

“ አዎ ፤ ኖርቲርን በደንብ አውቃቸዋለሁ ።”

“ ኖርቴር የናፖሊዮን ጀሌ ? ቪልፎርት የኖርቴር ልጅ ነው እንዴ?”

“ ልክ ነህ ። ”

“ እና ግርማዊነትዎ ይህን ጉድ እያወቁ የጠላትዎ ልጅ የርስዎን መንግሥት ያገለግላል ?”

“ የኔ ወዳጅ ፤ እንዴት አይገባህም ? ቪልፎርት ተፍጨርጫሪ ሰው ነው ነውኮ የምልህ ። ምኞቱን የሚያሳካለት ከሆነ ወላጅ አባቱን ጨምሮ ማንኛውንም ነገር መስዋዕት ያደርጋል ።”

“ ታዲያ ባቀርበው ይሻላል ጃንሆይ ? ”

“ አዎ ። አሁኑኑ !”

መሥፍኑ በፍጥነት ከክፍሉ ወጥቶ አፍታ ከቆየ በኋላ ከቪልፎርት ጋር ተመለሰ ።

“ ግባ ቪልፎርት ፤ ወዲህ ቀረብ በል” አሉ ንጉሡ ።

ቪልፎርት ለጥ ብሎ እጅ ከነሣ በኋላ እጆቹን እንዲጠጣመረ ወደ ፊት ቀረብ ብሎ የሚቀርብለትን ጥያቄ ይጠባበቅ ጀመር ።

“ ቪልፎርት ” አሉ ሉዊስ አሥራ ስምንተኛ ፤“ የምታስረዳኝ አሳሳቢ ጉዳይ እንዳለህ መሥፍኑ የነገረኝ ነገር እውነት ነውን ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

የቪልፎርት አይኖች በኩራትና በደስታ እንባ ተሞሉ ። ሜዳሊያውን በሁለት እጁ በጥንቃቄ እንደያዘ ሳመው ።

“ በል ሂድ ፤” አሉ ንጉሡ ፤“ ንጉሥ ሁሉንም ነገር አስታውሶ አይዘልቀውምና ብረሳህ እንኳ መልሼ እንዳስታውስህ ያለምንም ፍርሃት እንድታሳስበኝ ።”

“ እንጀራህን አበሰልህ ቪልፎርት ። የዕድልህ መቃናት አሁንገና ተረጋገጠ።” አለው የፖሊስ አዛዡ ከቪልፎርት ጋር ሆነው ከቤተ መንግሥት እንደወጡ ።

‘ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅ ይሆን ? ’ ሲል ቪልፎርት በልቡ ራሱን ጠየቀ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 8

ነገሮች እየተደራረቡ ተከሰቱ ። ናፖሊዮን ከኢልባ ደሴት ወደ ፓሪስ ያደረገውን የማይታመንና ተአምረኛ ጉዞ ታሪክ የሚያውቀው ነው ።

ንጉሥ ሊዊስ አሥራ ስምንተኛ የናፖሊዮንን ጥቃት ለመከላከል ያደረጉት ጥረት ፋይዳ አልነበረውም ። መልሶ በመቋቋም ላይ የነበረው ንጉሣዊ አገዛዝ ገና መሠረቱን.በማጠናከር ካስማውን ቸክሎ ሚዛኑን አ ስተካክሎ መቆም ሳይጀምር ኃያሉ የናፖሊዮን ክንድ እንደገና ደቆሰው ።

በዚህም የተነሣ ቪልፎርት ከንጉሡ የጠበቀውን ውለታ ማይቀ በል ቀረ ። ያተረፈው ነገር ቢኖር የንጉሡ ምሥጋና ብቻ ሲሆን እሱም ቢሆን ለሕይወቱ አደገኛ ከመሆን ሌላ ጥቅም አላስገኘለትም ። እን ዲያውም ናፖሊዮን ቪልፎርትን ከሥልጣን አውርዶ በቅጣት ሊያስ ቀምጠው የከጀለ ሲሆን ከዚህ መአት ሊያመልጥ የቻለውም በናፖ ሊዮን ፍርድ ቤት ታላቅ ተደማጭነት ባለው አባቱ በኖርቴር ጥብ ቅና ነበር ።

ቪልፎርት የረዳት ዓቃቤ ሕግ ሥልጣኑን ከመነጠቅ ዳነ ። ጋብ ቻው ግን አማቶቹ ሌላ “ የደስታ ዘመን ”እስኪመጣላቸው ተላለፈ ። ናፖሊዮን በሥልጣኑ የሚቆይ ከሆነ ቪልፎርት ሌላ ሚስት ለማጨት አይኑን አያሽም ። በሌላ በኩል ግን ንጉሡ ሉዊስ አሥራ ስምንተኛ እንደገና አልጋቸውን ከያዙ የቀድሞዋ ወላጆቿ በቤተ መንግሥት ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ሰዎች ልጅ ሬኒ የሚስትነቱን ሥፍራ ትይዛለች ።

ኢድመንድ ግን እሥረኛ እንደሆነ ቀረ ። መሬት ውስጥ በሚገ ኘው የጨለማ ክፍል እንደታጐረ የተረሣው ኢድመንድ ስለሉዊስ አሥራ ስምንተኛ ከሥልጣን መውረድም ሆነ ስለሌላው ሁኔታ የሚያ ውቀው ነገር አልነበረም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሜርሲደስ ያለው ፍቅር፣በሃዘኗም ሆነ በጭንቀቷ ወቅት አሉን የሚሰማው ሐዘንና ጭንቀት ፣ ለፍላጐቷ መሟላት የሚያደርገው መዋተት በሜርሲደስ ልብ ውስጥ መሥረጻቸውን አላቋረጡም ። ሜርሲደስ ወትሮም በፈርናንድ ወንድምነት ስትመካ የኖረች ሴት ነበረች ። አሁን ደግሞ ልቧ ውስጥ አንድ ሌላ ነገር መስመጥ ጀመረ ፣ ውለታ ። ይህንን የተረዳው ፈርናንድ ወደ ዘመቻ ሲሄድ ኤድመንድ ካልተመለሰ በስተቀር ሜርሲደስ አንድ ቀን የእሱ እንደምትሆን ተስፋ እያደረገ ነበር ።

ሜርሲደስ ብቻዋን ቀረች ። ያለመታከት በካታላኖች መንደር ስትዘዋወር ፤አንዳንድ ጊዜ ኃይለኛው ፀሐይ እየወረደባት ሳትንቀሳቀስ ተገትራ ስትውል ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከባህሩ ዳርቻ በመቀመጥ ሙሾዋን የሚያስተጋባ የሚመስላትን የውሃ እንቅስቃሴ እያዳመጠች ተስፋ የሌለውን ጨለማ ሕይወት ከመግፋት ይልቅ ባህሩ ውስጥ መስጠምን ስትመኝ በእንባ እየታጠበች ታሳልፋለች ። ባህር ውስጥ እንዳትገባ የሚያግዳት የመኖር ፍላጐቷ ወይም የወኔ መጥፋት አልነበረም ፣ ራሷን ከማጥፋት የሚመልሳት የሃይማኖቷ ሕግ ነበር ።

የናፖሊዮን መንግሥት ሲገረሰስ የኤድመንድ አባት የነበራቸው የመጨረሻ ተስፋ ተሟጠጠ ። ከልጃቸው ከተለያዩ ከአምስት ወራት-በኋላ የሜርሲደስን ክንድ እንደ ተደገፉ የመጨረሻዋን ትንፋሻቸውን ውጠው የዘለዓለም እንቅልፋቸውን ተኙ ። ለቀብራቸው ሥነ ሥርዓትና በሕመማቸው ወቅት የገቡትን እዳ ከፍሎ የሰላም እንቅልፍ ያስተኛቸው ሞረል ነበር ። ይህንን ማድረግ ራሱ ራስን ከመግደል የማይተናነስ ወኔ ነበር ። በናፖሊዮን ደጋፊነት የተወነጀለ እሥረኛን አባት መርዳት የወንጀሉ ተባባሪ እንደመሆን ይቆጠር ነበርና ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 9

ኢድመንድ ከምድረ ገጽ በታች ጭለማ ቤት ውስጥ እንደ ቆሻሻ የተጣሉ እሥረኞች በሚዳከሩበት የኑሮ አርንቃ ይዛቅጥ ጀመር ። በመጀመሪያ አካባቢ የተከፋ ጭላንጭልና የንፅህና ልበ ሙሉነት ልቡን እንጠርብበውት ሥቃዩን ሁሉ በወኔ ይጋፈጠው ነበር ። ጊዜ እየተገጉተተ ሲሄድ ግን ተስፋውን ማጣት ብቻ ሣይሆን የግል ንጽህናውን እንኳ እየተጠራጠረ መጣ ። በመጨረሻም ወደ መማፀን እዘነበለ ። የሚማፀነው አምላኩን ሣይሆን ሰዎችን ነበር ። ከዚያ አስቃቂ ክፍል አውጥተው የበለጠ ጭለማና የበለጠ ምሬት ውስጥ የጠለቀ ቢሆንም እንኳ ሌላ ክፍል ውስጥ እንዲያዛውሩት ተማፀነ ። የባሰ የሚያስከፋ ቢሆንም ለውጥ ለተወሰነ ጊዜ መንፈስን ዘና ሊያዶርግ ይችላል ። መጺሕፍት እንዲሰጡትና ወጣ ብሎ ሰውነቱን እንዲያንቀሳቅስ ለመነ ። ይሁን እንጅ እብድ ነውና መልእክቱን የሚያመላል ስለት ዘበኛ እንኳ ከልቡ አላዳመጠውም ። እሱ ግን ልመናውን አላሰለሰም ።

በመጨረሻው በሰው በኩል ያለው ተስፋ ሲሟጠጥ ኢድመንድ ወደ ፀሎት ገባ ። በልጅነቱ ያጠናውን ፀሎት እየደጋገመ ሲናገር በቃላቱ ውስጥ ከዚህ በፊት ያልታወቀው ትርጉም ይከሰትለት ጀመር ። ከብሶቱ ጋር የሚነጋገርበትን ጣፋጭ ቋንቋ ምንነት የሚያስረዳው መራራ ዘመን እስካልደረሰበት ድረስ ለደስተኛ ሰው መዝሙርም ቢሆን የቃላት ጥሻ ፤ የጩኸት ዋሻ ነው ።

ግን አልሆነም ። ፀሎቱም ቢሆን ከወህኒ አላወጣውም ። እንደ ሚኖርበት ክፍል መንፈሱም ጨለመ ። ቀኑን ከሌሊት መለየት ባለ መቻሉ የጊዜ ምንነት ጠፋበት ። መኖር አለመኖር ፤ ጣዕም ምሬት ለሱ ልዩነት አልነበራቸውም ። አእምሮው የተላበሰውና ዙሪያውን የወረሰው አንድ ነገር ብቻ ነበር ፤ ውስጣዊ ባዶነት . . . . ዳፍንት !



t.me/OLDBOOKSPDF

ለአዲሱ መግረፊያው ምሥጋና ይድረሰውና ምሽት ላይ እሥር እፍኝ የሚሆን አሸዋና አፈር ከግድግዳው አውጥቷል። ዘበኛው የማታ ጉብኝቱን የሚያደርስበት ሰዓት እንደደረሰ ሥራውን አቋርጦ የተወላገመውን የብረት ድስት እጀታ በማቃናት ባርጩማው ላይ ተቀምጦ ጠበቀው ።

ዘበኛው ከሄደ በኋላ ሥራውን እንደገና ተያይዞት ሁለት ወይም ሦስት ሰዓት ያህል እንደፈቀፈቀ አንድ እንቅፋት ገጠመው ። በሥርሡሩ የጐደጐደውን ግድግዳ በእጁ ሲዳስስ ከዚያ ሁሉ ልፋት በኋላ ሥርሰራው ግድግዳውን በመቅደድ ፋንታ አንድ ትልቅ ማገር ላይ እንዳደረሰው ተረዳ ። ይህንን ማገር በምንም ተአምር ሊሰረስረው አይችልም ።

" አንተ አምላኬ !" አለ ኢድመንድ ወለሉ ላይ ተንበርክኮ በታከተ ድምፅ ። " ይህን ያህል ዘመን ፀልይኩልህ ፤ በመጨረሻውም ብሶቴን የሰማኸኝ መስሎኝ ነበር ። እባክህ በቃህ በለኝ ። እረ እባክህ እንደማቀቅሁ አትግደለኝ ? "

" ማነው እሱ ደሞ ስለአምላክና ስለብሶት የሚያወራው ?" ሲል አዝገመገመ አንድ ከወደ ሰማይ የሚመጣ የሚመስል ድምፅ ።

ኢድመንድ ፀጉሩ የቆመ መሰለው ። ጆሮዎቹን ማመን አቅቶት ኮረኮራቸው ። ራሱን ለመቆጣጠር ግን ጊዜ አልወሰደበትም ። " በፈጠረህ እስኪ እንደገና ተናገር ፤ ማነህ አንተ ?" አለ ።

" አንተስ ማነህ? " ሲል መልሶ ጠየቀ ያው ድምፅ ።

"ዕድለ ጐደሉ እሥረኛ ፤ " ነበር በእንባ የታጀበው የኢድመንድ መልስ ።

" እዚህ ምን ያህል ጊዜ ታሥረሃል ?"
" ከየካቲት 28 ቀን 1815 ጀምሮ ።"
" የሠራኸው ወንጀል ምንድን ነበር ?"
" እረ ምንም ወንጀል አልሠራሁም ።"
" ታዲያ በምን ተወነጀልህ ?"
" ናፖሊዮንን ወደ ስልጣን ለመመለስ ዶልተሃል ተብዬ ።"
" ምን ? ለመሆኑ ናፖሊዮን ከሥልጣን ወርዷል ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በ1814 ሥልጣኑን ለቆ በኢልባ ደሴት በስደት ይኖር ነበር። ግን እንትብ ይህን ሁሉ የማታውቅ ከመቼ ጀምሮ ብትታሠር ነውን” ሲል ጠየቀ ኢድመንድ

“ ከ1811 ጀምሮ ። ”

ኢድመንድ ሰውነቱን ወረረው ። ጉረቤቱ ከሱ በፊት አራት ዓመታት ቀደም ብሎ ኖሯል የታጐረው ። የባሰም አለ ።

“ በጣም ጥሩ ፤ መቆፈሩን አቁም ” አለ ድምፁ በፍጥነት እየ ተናገረ ።“ ለመሆኑ የቆፈርከው ከምን ያህል ከፍታ ነው ?”

“ ከወለሉ ትይዩ ።”

“ እንዴት ነው የተደበቀው ?”

“ አልጋዬ ይጋርደዋል ።”

“ ከታሠርክ ጀምሮ አልጋህን ሰው አንቀሳቅሶት፤አያውቅምን”

“ በጭራሽ ! ”

“ ከክፍልህ ውጭ ምን አለ ?”

“ መተላለፊያ ኮሪደር ።”

“ ኮሪደሩ ወዴት ይወስዳል ?”

“ ወደ በረንዳ ።”

“ ወይኔ” ሲል ድምጹ አዝገመገመ ።

“ ምነው ? ” በማለት ጠየቀ ኢድመንድ ።

“ ተሳስቼ ኖሯል . . . የነደፍኩት ንድፍ በተሳሳተ አቅጣጫ ወስ ዶኛል ። የምሠረሥረው የምሽጉን ግድግዳ መስሎኝ ነበር ።”

“ ግን እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ወደ ባሕር አቅጣጫ ነበር የምትቆ ፍረው ማለት ነው ።”

“ እሱን ነበር የፈለግሁት ! ወደ ባህር ተወርውሬ ለመዋኘትና ወዳንዱ ደሴት ለመጓዝ ።”

“ ያን ያህል ርቀት መዋኘት እችላለሁ ብለህ ትገምታለህ ?”

“ አምላኬ ጉልበቱን ይሰጠኝ ነበር ። ግን ምን ያደርጋል ፤አሁን ሁሉም መና ቀረ ። በል መተላለፊያህን በጥንቃቄ ግጥም አድርገህ ምንም ሥርሠራ ሳታደርግ እኔ ድምጽ እስካሰማህ ጠብቅ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ጩረስ ግድግዳው ሦስት ጊዜ ሲንኳኳ ተሰማው። “አንተ ነህ?አለሁ!” አለ ኢድመንድ ደስታ እያስቸቅለው ።

“ ዘበኛህ ሄዷል ?” ሲል ጠየቀ ድምፁ ።

“ አዎ ! እስከማታ ድረስ አይመጣም ። የአሥራ ሁለት ሰዓት ነፃነት አለን ።”

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትልልቅ ድንጋዮችና አፈር ሲወድቅ ይሰማ ጀመር ። ኢድመንድ ሲቆፍረው ከነበረው መተላለፊያ ጐን አንድ ቀዳዳ ታየው ። ከዚህ ቀዳዳም የሰው ራስ ብቅ አለ ። ብዙም ሳይቆይ እንድ ሰው በቀዳዳው ሾልኮ በመውጣት ከፊት ለፊቱ ዱብ አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲

ኢድመንድ በጉጉት ሲጠባበቀው በኖረው ጓደኛው ላይ ዘሎ ከተጠመጠመበት በኋላ ወደ እንዲት የብርሃን ጭላንጭል የምታሳይ ቀዳዳ ወስዶ ይመለከተው ጀመር ።

ጓደኛው ቁመቱ ከእሱ ጥቂት አጠር ያለና በእርጅና ሳይሆን በሥቃይ ፀጉሩን ሽበት የወረሰው ሰው ነበር ። ንቁዎቹ አይኖቹ በረጃጅሞቹ ቅንድቦች ውስጥ ተቀብረዋል ። ጥቁሩ ፂሙ ደረቱ ድረስ ተንዠርግጓል ። በመሥመር ከተተበተበው ቀጭን ፊቱ ላይ ከጉልበቱ ይልቅ አእምሮውን የሚያንቀሳቅስ ሰው ገጽታ ይታይበታል ። ልብሶቹ ከመቀደድ አልፈው በሰውነቱ ላይ እንደ እንቀልባ ስለሚንዘላዘሉ አይነታቸውን እንኳ መለየት ያዳግታል ።

ዕድሜው ቢያንስ ስድሣ እምስት ዓመት ቢመስልም ፤ የሰውነቱ እንቅስቃሴ ብርቱነት የስድሣ እምስት ዓመት እዛውንት ያስመሰለው የረጅም ዘመናት እሥር መሆኑን ይመሰክራል ።

የኢድመንድን ሰላምታ እጁኑ በደስታ በመመለስ እሱም ተጠመጠመበት ። ለረጅም ጊዜ ተለያይተው እንደቆዩ ወንድማማቾች ተቃቅፈው ይሳሳሙ ጀመር ። የእንግዳው በሕይወት የተሰላቸ አእምሮም ኢድመንድን በመሰለው ወጣት ፊት ሲቆም በአዲስ የተስፋ ባህር ይዋኝ ገባ ። ወደውጭው ዓለም ያደርሰኛል ብሎ ለረጅም ጊዜ ሲቦረቡረው የነበረው አፈርና ድንጋይ በመጨረሻው ከሌላ እሥረኛ ክፍል ውስጥ ስለጣለው የተሰማው ቅሬታ እንዳለ ቢሆንም አዲስ ጓደኛ የማግኘቱ ነገር ሊያካክስለት ሞክሯል ። ሁለቱም ማይታወቃቸው እንባቸውን አወረዱ ።

"ከሁሉ አስቀድሞ" አለ እንግዳው ፤ "እስኪ ይህንን ቀዳዳ ዘበኛህ እንዳያዬው ለማድረግ እንችል እንደሆነ እንሞክር ። " ድን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋዩን ገፋ አድርጐ ወደ ቀዳዳው መለሰው ። “ ይህ ድንጋይ የተነሣው በከፍተኛ ጥንቃቄ ነበር ።” አለ፤ “ሊመሆኑ መሣሪያዎች የሉህም ?”

“ አንተ አሉህ ?”

“ እኔ እንኳ ራሴ ሠርቻለሁ ። የምፈልገው ነገር ሁሉ አለኝ ። ለምሳሌ መሮ ፤ መቆንጠጫ ፤ ቢላዋ ” ካለ በኋላ እንግዳው የእንጨት እጀታ ያለው ጠንካራና በደንብ የተሳለ ቢላዋ አሳዩው ።

“ ክምን ልትሠራው ቻልክ ?”

“ ከአልጋዬ የማያያዣ ሽቦ ። በዚህ ስለት ነው ከእኔ ክፍል እዚህ ድረስ ያለውን ወደ ሃምሣ ጫማ የሚደርስ ርቀት በሙሉ ልሰረስር የቻልኩት ።”

“ ሃምሣ ጫማ !” አለ ኢድመንድ ርዝመቱ ከማስገረም አልፎ አስደንግጦት ።

“ አዎ ፤ ግን ምን ያደርጋል ፤ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ ሆነ ። ከዚህ ክፍል ፊት ለፊት ያለው መተላለፊያ ኮሪደር የሚወስደው በዘቦች ወደተጨናነቀው በረንዳ ነው ፡ ምንም የማምለጫ መንገድ የለም ። ብቻ እም ላክ ያውቃል ።” የሽማግሌው ፊት የተስፋ መቁረጥ ምልክት ይነበብበት ጀመር ። ኢድመንድ መገረምና አድናቆት በተቀላቀለበት ስሜት ይህንን የረጅም ጊዜ ተስፋውና ጥረቱ በመጨረሻው ሲበላሽበት እርጋታ ያልተለየው ሰው በተመስጦ አስተዋለው ።

“ አሁንስ ማን እንደሆንክ አትነግረኝም ?” በማለት ጠየቀ ኢድመንድ ።

“ጉንግዳይ ምንም ጥቅም የማልሰጥህ ደካማ መሆኔን አይተሃል ። እንዲሁ ልወቅህ ካልክ ምን ቸገረኝ ። እኔ ቄስ ነኝ ፤ስሜም ፋሪያ ይባላል ። እዚህ እሥር ቤት የገባሁት በ1811 ቢሆንም ከዚያ ቀደም ብሎም በኢጣሊያ ግዛት ሦስት የእሥር ዓመታት አሳልፌአለሁ ።”

“ ግን የታሰርክበት ምክንያት ምንድን ነበር ?”

“ ምክንያቱማ በ1811 ፈረንሣይ ውስጥ ናፖሊዮን ያካሄደውን ዓይነት ተግባር እኔም ጣሊያን አገር በ1807 መወጠኔ ፤ በጥቃቅን



t.me/OLDBOOKSPDF

ኖብኛልና ካሁን በኋላ ነፃነቴን እቀዳጃለሁ ብዬ የምጥረው ነገር አይኖርም ።"

ኢድመንድ ጓደኛ በማግኘቱ የተሰማው ደስታ የሽማግሌው ሐዘን ሙሉ ለሙሉ እንዳይሰማው ማድረጉ እንዳይታወቅበት አንገቱን አቀረቀረ ።

" በእሥር ቤት ባሳለፍኳቸው አሥራ ሁለት ዓመታት " በማለት ፋሪያ ንግግሩን ቀጠለ ፤ " በታሪክ የታወቁ ዝነኛ የማምለጫ ዘዴዎችን ሁሉ በጥንቃቄ አስቤአለሁ ። በተሳካ ሁኔታ የተከናወኑ የማምለጫ ዘዴዎች እጅግ በጣም ጥቂት ሲሆን እነሱም ቢሆኑ ብዙዎቻቸው በጥልቀት የተቀናጁና በትዕግሥትና በጥንቃቄ የተዘጋጁ ነበሩ። እንደዚያም ሆኖ እንዳንዶቹ ከፍጻሜ ሊደርሱ የበቁት በአጋጣሚ ነው ። እኛም ብንሆን የቀረን አማራጭ አጋጣሚን መጠባበቅና ከሆነልን በዚያ አጋጣሚ መጠቀም ብቻ ነው ።"

" አንተ እንኳ ለመጠባበቅም ትችል ነበር ፤" አለ ኢድመንድ ፈገግ እያለ ። " አስቸጋሪው ሥራህ ብዙውን ጊዜህን ይገድልልሃል፤ የምትሠራው ሥራ ሳይኖር ደግሞ ተስፋህን ማሰላሰሉ እርካታ እየሰጠህ ኖረሀል ።"

"ስርሰራ ብቻ አልነበረም ሥራዬ ፤ " አለ ቄሱ ።

" ሌላስ ምን ታደርግ ኖሯል ?"

" እጽፋለሁ ፤ አጠናለሁ ።"

" ወረቀት ፤ ብዕርና ቀለም ይሰጡሀል ?"

" የለም ፤ ራሴ እሠራ ነበር ።"

" ወረቀት ፤ ብዕርና ቀለም ?" ሲል ኢድመንድ በመገረም ጠበቅ አድርጐ ጠየቀ ።

" አዎ ! "

ኢድመንድ በአድናቆት ፈዞ ቀረ ። የሽማግሌውን ንግግር ማመን አስቸጋሪ ነበር ።

ቄስ ፋሪያ ግን የወጣቱን ጥርጣሬ አስተውሎ እንዲህ አለው ።

" ወደኔ ክፍል በምትመጣበት ጊዜ አንድ የተሟላ መጽሐፍ አሳይሃለሁ ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእኔ እውቀት ፤ ምርምርና ጥናት



t.me/OLDBOOKSPDF

በሙሉ ተጠቃሏል ። ርዕሱም ‘ አሃዳዊ መስተዳድር በኢጣሊያ ’ የሚል ነው ።

“ እና እዚህ እሥር ቤት ውስጥ ሆነህ ጻፍከው ?”

“ አዎና ! በሁለት ሸሚዞች ላይ ። ልብስን እንደብራና ለስላሳና ግትር የሚያደርግ ዘዴ ፈልስፌአለሁ ። አንዳንድ ጊዜ ከሚጥሉልን አጥንት ደግሞ ድንቅ የሆኑ ብዕሮች እሠራለሁ ።”

“ ቀለሙስ ?” ሲል ጠየቀ ኢድመንድ ።

“ እኔ ክፍል ውስጥ ጥንት የእሳት ምድጃ ነበረ ። እኔ ከመምጣቴ በፊት ቢደፈንም ውስጡ በጥቀርሻ የተሞላ መሆኑን አወቅሁ ።ጥቀ ርሻውን እሁድ እሁድ በሚሰጡኝ ወይንጠጅ በመበጥበጥ ግሩም ቀለም አገኘሁ ። በሆነ ርዕስ ወይም ምዕራፍ ላይ ልዩ ትኩረት ልሰጥ ስፈ ልግ እንዱን ጣቴን እቆርጥና በራሴ ደም በቀይ ቀለም እጽፋለሁ ወይም አሰምርበታለሁ ። ”

“ ይህን ሁሉ መቼ ማዬት እችላለሁ ?” በማለት ጠየቀ ኢድመን ድ ።

“ በምትፈልግበት ጊዜ ። ”

“ አሁኑኑ ልዬው ። ”

“ ተከተለኝ !” ካለ በኋላ ቄሱ በቀዳዳዋ ሲሾልክ ኢድመንድ ም ተከተለው ። በዚህ መተላለፊያ ካለፉ በኋላ ያለችግር ታጠፉና በተቃራኒው አቅጣጫ ወደሚገኘው ክፍል ደረሱ ። የክፍሉ ወለል የድንጋይ ንጣፍ የተደረገበት ሲሆን በአንድ በኩል ያለውን ድንጋይ በማንሳት ነበር ቄስ ፋሪያ ያን ትዕግሥት አስጨራሽ ሥራ ሲሠራ የኖረው ።

ኢድመንድ ቄሱ ክፍል ውስጥ እንደገባ ዙሪያውን በጥንቃቄ መረመረ ፤ በመጀመሪያ እይታ ግን ክፍሉ ከሌሎች የተለዬ ነገር የሚ ታይበት አልነበረም ። “ ሥራዎችህን ለማዬት በጣም ጓጉቻለሁ ።” አለው ኢድመንድ ቄሱን ።

ፋሪያ ወደ ምድጃው ሄደና ጥንት ጉልቻ የነበረውን ድንጋይ ወደጐን ሲያደርገው አንድ ጥልቅ ጉድጓድ ታዬ ። ለኢድመንድ የተ ነገሩት እቃዎች የተደበቁት እዚህ ጉድጓድ ውስጥ ኖሯል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በጣም ጥሩ ፤ከሁሉ አስቀድሞ የአንተ ካፒቴን መሆን የሚ ከነክነው ሰው አልነበረም ?”

“ ኧረ በጭራሽም ፤ ሁሉም ሠራተኛ ይወደኛል ። እንደእውነቱ ከሆነ ካፒቴኑን ራሳችሁ ምረጡ ቢባሉ እንኳ እኔን እንደሚመርጡ አልጠራጠርም ። አንድ ጓደኛዬ ብቻ በማይረባ ምክንያት ይጠላኝ ነበር ። አንድ ጊዜ በትንሽ ነገር ተጣላንና እንድንታረቅ ብጠይቀው እምቢ አለኝ። በኋላም ፍልሚያ ጠየቅሁት ። እሱንም እምቢ አለ ።”

“ አሃ ! ይኽ ጓደኛ ተብዬው ሰው ማን ነበር ?” አለ ቄስ ፋሪያ።

“ ዳንግላር ። የመርከቧ የኢቃ ግምጃ ቤትና የሂሳብ ሹም ነበር ።”

“ ካፒቴን ብትሆን ኖሮ ሥራው ላይ ታቆየው ኖሯል ?”

“ በጭራሽ ። የሆነ ሰቡብ ፈጥሬ አስወጣው ነበር ።”

“ ጥሩ ። ከሚቹ ከካፒቴን ሌክለር ጋር ስትነጋገሩስ ሌላ ሰው አብሯችሁ አልነበረም ?”

“ የለም ፤ ብቻችንን ነበርን ።”

“ ከውጭ ሰው ሊሰማችሁ አይችልም ?”

“ ምናልባት ፤ በሩ ክፍት ስለነበረ ። በእርግጥ . . . . ቆይ ቆይ . . . . እዎ ልክ ነው ! ልክ ካፒቴን ሌክለር እሽጉን ሲሰጠኝ ዳንግላር በበሩ በኩል ማለፉ ትዝ ይለኛል ።”

“ጥሩ” አለ ቄሱ ፤ “ አሁን ነገራችን መልክ መልክ እየያዘልን ነው ። በኢልባ ደሴት ከመርከቧ ወርደህ መልእክትህን ስታደርስ ሌላ ሰው አላሰከተልህም ?”

“ ብቻዬን ነበርኩ ።”

“ እዚያ የተቀበልከውን ደብዳቤስ ምን አደረግኸው ?”

“ በቢሮ ቦርሳዬ ውስጥ አስቀመጥኩት ።”

“ የቢሮ ቦርሳህን በዚያ ወቅት ይዘኸው ነበር ?”

“ አይ መርከቧ ላይ ትቼው ነበር ።መርከቧ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ደብዳቢውን ቦርሳው ውስጥ አልከተትኩትም ።”

“ ከደሴቷ ወደ መርከቧ ስትመጣ ደብዳቤውን በምን ይዘህ መጣህ ? ”

“ በእጄ ነዋ ! ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ስለዚህ ደብዳቤ ይዘህ መመለስህን ማንም ሰው ሊረዳ ይችል ነበር ማለት ነው ።”

“ እዎ ። ”

“ ዳንግላርም ጭምር ?”

“ እዎ ። ”

“እንግዲህ” አሉ ቄስ ፋሪያ ፤“በጥሞና አዳምጠኝና በምትችለው መጠን በግልጽ ለማስታወስ ሞክር ። የተወነጀልህበት ደብዳቤ ቃላት ምን እንደሚመስሉ ልትነግረኝ ትችላለህ ?”

“ በደንብ እንጅ ፤ሦስት ጊዜ አንብቤዋለሁ ፤ እያንዳንዱ ቃልም አእምሮዬ ውስጥ እንደተቀረፀች ናት ። ” ካለ በኋላ ስሙን ካልገለፀ ሰው ለአቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት የተጻፈበትን ወንጀላ ቃል በቃል አሰማው ።

ቄስ ፋሪያ ትክሻቸውን ነቅነቅ ካደረጉ በኋላ እንዲህ በማለት ተናገሩ ።

“ ነገሩ እንደቀን ብርሃን ግልጽ ነው ። ነገሮችን ቶሎ ለማገናዘብ የተሳነህም ልብህ ሲበዛ የዋህ በመሆኑ መሆን አለበት ። የዳንግላር የእጅ ጽሑፍ ምን ይመስላል ?”

ኢድመንድ አይነቱን በምልክት ለማሳየት ሞከረ ። የዳንግላር የእጅ ጽሁፍ ከወንጀላው ደብዳቤ የበለጠ የሚያምር መሆኑንም ተናገረ ።

“ ያ ደብዳቤስ እንዴት ነበር የተጻፈው ?”

“ ፊደሎቹ ወደ ፊት የተንጋደዱ ነበሩ ።”

ፋሪያ ለአፍታ ክት ብሎ ከሳቀ በኋላ “ የእጅ ጽሁፉ የዳንግላር የማሳሳቻ ዘዴ ነበር ፤ አይደለም? ” አለ ።

“ እኔ እንጃ ” በማለት መለሰ ኢድመንድ ።

“ ቆይ ፤ ” አለና ፋሪያ አንደኛውን ብዕሩን አንስቶ በተለይ በተዘጋጀው ጨርቅ ላይ በግራ እጁ ጥቂት መሥመሮች ጻፈ ። ኢድመንድ ወደ ኋላው አፈግፍጐ ቄሱን በጥርጣሬ ተመለከተው ። “በጣም ይገርማል።እንዴት የዚያ ደብዳቤ አጻጻፍና ይኸኛው ሊመሳሰሉ ቻሉ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ፆ ማለት ውንጀላው የተጻፈው በግራ እጁ ነበር ማለት ነው። በግራ እጅ የተጻፉ የእጅ ጽሁፎች ሁሉ በአብዛኛው አንድ ዓይነት መሆናቸውን አስተውያለሁ ። አሁን ወደ ሁለተኛው ጥያቄህ እንመለስ ። ሜርሲዴስን ማግባትህ የሚያስከፋው ሰው አልነበረም ?”

“አዎ! ፈርናንድ የተባለ ካታላን አሣ አስጋሪ ያፈቅራት ነበር።”

“ ደብዳቤውን ለመጻፍ የሚችል ይመስልሃል ?”

“ ምንም እንኳ እሱን ለመተናኮል ባይተኛም ጽሑፉን ለማቀናጀት ልብ ያለው አይመስለኝም ። ከዚያም በላይ በውንጀላው ደብዳቤ ላይ ስለተገለጹት ነገሮች የሚያውቀው ነገር የለም ። ስለደብዳቤው ለማንም ሰው ፤ ለሜርሲዴስ እንኳ አልተናገርኩም ። ”

“ ፈርናንድ ዳንግላርን ያውቀዋል ? ”

“ አዎ ! ሠርጉን ሊፈጽም ሁለት ቀን ሲቀረኝ ከሆቴል በረንዳ ላይ አብረው ሲጠጡ አይቻቸዋለሁ ። ዳንግላር ፊቱ ያልጠቆረና ጥርሱ ያልተከደነ ሲሆን ፈርናንድ ግን ተቆጥቷል ፤ ፊቱም በርበሬ መስሎ ነበር ። ከሁለቱም ጋር ካደሮስ የተባለ የአባቴ ጎረቤት የሆነ ልብስ ሰፊ አብሮአቸው ነበረ ፤ እሱ ግን ራሱን እስኪስት ድረስ ሰክሮ ነበር ።”

“ እስካሁን ስለ ሁለቱ ጓደኞችህ የወሰድነው ማጠቃለያ የማያምታታ ነው ። ግን አሁን አንዳንድ ይበልጥ ቁልጭ ያሉ ማብራሪያዎችን እንድትገልጽልኝ እፈልጋለሁ ። ”

“ መቼም ሕይወቴ ከራሴ የበለጠ ላንተ ግልፅ ሆኖ እየታዬ ነውና ጠይቀኝ አስረዳለሁ ።”

“ ከታሠርክ በኋላ ቃልህን የተቀበለህ ማን ነበር ?”
“ ምክትል አቃቤ ሕግ ።”
“ እንዴት ነበር ያስተናገደህ ?”
“ በጣም ትሁት ሆኖ ።”
“ ሁሉንም ነገር አስረዳኸው ?”
“ አዎ ። ”

“ በቃለ መጠይቁ ወቅት ሁኔታው ለውጥ ያሳዬበት ጊዜ አልነበረም ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ነበረ ፤ ከኢ.ልባ ደቤት የተቀበልኩትን ደብዳቤ ካነበበ በኋላ በእኔ ላይ ለደረሰው መጥፎ አጋጣሚ ከፍተኛ አዘኔታ ተሰምቶት ነበር ። "

" ያሳዘነው ምንቱ መጥፎ አጋጣሚ ለመሆኑ እርግጠኛ ነህ ?"

" መቼም ለአዘኔታው እንደ ትልቅ ግስረጃ ሰጥቶኛል ። በአይኔ እያየሁ ደብዳቤውን ካቃጠለልኝ በኋላ ' ባንተ ላይ የሚጠቀሰው ማስረጃ ይህ ብቻ ነበር ፤ ግን እንደምታየው አቃጥዬልሃለሁ ። ' ብሎ ኛል ።

"ያልተለመደና ከሚገመተው ውጭ የሆነ ድርጊት ነው" አለ ፋሪያ ።

" እንደዚያ ነው ትላለህ ?"

" ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም ። ለመሆኑ የደብዳቤው ተቀባይ ስም ማን ይባላል ?"

" ፓሪስ የሚኖር ኖርቴር የተባለ ሰው ነው ።"

" ምክትል ዓቃቤ ሕጉ ደብዳቤውን ለማቃጠል የፈለገበት ሌላ ምክንያት እንደሚኖረው አትገምትም ?"

" ራስህን ለማዳን ነው ብሎ ስለደብዳቤው ለማንም እንዳልና ገር ሁለትና ሦስት ጊዜ ቃል አስገብቶኛል ፤ የደብዳቤውን ተቀባይ ስምም እንዳላወጣ አስምሎኛል ።"

" ኖርቴር አልከኝ ? . . . . ኖርቴር . . . . " በማለት ፋሪያ ስሙን በሃሳብ እንደተመሰጠ ደጋገመው ። " ይህንን ስም በአደባ ባይ ላይ አውቀዋለሁ ፤ እንዲያውም ኖርቴር የሚባል በንቅናቄው ወቅት ስሙ ገኖ ይጠራ የነበረ ሰው አስታውሳለሁ ። . . . . . ቃል ሀን የተቀበለው ምክትል ዓቃቤ ሕግስ ማን ይባላል ?"

" ቪልፎርት ። "

ቄስ ፋሪያ በኃይል ሳቀ ። " ምስኪን ወንድሜ " አለ በምፀት ከንፈሩን በመምጠጥ ፤ "እውነትም ሩህሩህ ቃል ተቀባይ አጋጥሞህ ኖሯል ፤ እ ?"

" አዎ " ሲል መለሰ ኢድመንድ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘግሙም እያንዳንዳቸው በኢድመንድ አእምሮ ውስጥ የእውቀት አሻራቸውን ይጥሉ ስለነበረ በዓመቱ መጨረሻ ኢድመንድ ፍጹም ሌላ ሰው ሆነ ።

ፋሪያን በሚመለከት ግን ከጓደኛው ጋር በመጥሉ በየቀኑ እየተጽናና የሚሄድ ይመስላል ። ሕይወቱን የተቆራኘው የግፍ ገጠመኝ ግን በምንም መንገድ ከአእምሮው የሚፋቅ አለመሆኑ ግልጽ ነው ። አእምሮው በአንድና በማያቋርጥ ሃሳብ የተወጠረ መሆኑ ያስታውቅበታል ። ብዙ ጊዜ አንድ ሃሳብ ውስጥ ጥልቅ ብሎ ይሰምጥና ሳይታወቀው ይሥቃል ፤ ወዲያው ደግሞ ብድግ ብሎ በክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ይንጐራደዳል ። አንድ ቀን ድንገት መንጐራደዱን አቆመና ።

“ እህ ፤ ዘበኛ ባይኖር ኖሮ !” አለ ።

“ የማምለጫ መንገድ አግኝተሃል ? ” ሲል ጠየቀ ኢድመንድ መልሱን ለማወቅ ተቻኩሎ ።

“ አዎ ፤ ዘበኛው እውርና ደንቆሮ ቢሆን ኖሮ ” !

“ እኔ እውርና ደንቆሮ አደርገዋለሁ !” አለ ኢድመንድ ፋሪያን ጭምር በሚያስፈራራ ሁኔታ ።

“የለም የለም ! ” አለ ፋሪያ፤ “ ደም እንዲፋሰስ እንኳ አልፈቅድም !”

ኢድመንድ በጉዳዩ ላይ መወያየታቸውን እንዲገፋበት ፈልጐ ነበር ፤ ፋሪያ ግን ራሱን በመነቅነቅ ሌላ ነገር እንደማይናገር አስታወቀ ። ሌሎች ሶስት ወራት አለፉ ።

“ ጉልበትህ ምን ያህል ጠንካራ ነው?” ሲል ጠየቀ ፋሪያ አንድ ቀን ። ኢድመንድ መልሱን በቃላት ሊደረድር አልፈለገም ። ጠንካራውን መሮ አነሳና ያለምንም ችግር ካጠፈው በኋላ መልሶ ዘረጋው ።

“ አግራጭ ካልጠፋ በስተቀር ዘበኛውን ላለመግደል ትስማማለህ?”

“ እረ እስማማለሁ ። ”
“ እንግዲያውስ የማምለጫ እቅድ ማውጣት እንችላለን ።”
“ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ግን ሁለታችንም የማንጠቀምበት ከሆነ የማስነውን ቦይ መድፈን አለብን ። ዘበኛው በቦዩ አካባቢ በሚራመድበት ጊዜ በእግሩ ድምጽ የቦዩን መቀደድ ሊያውቅ ይችላል ። ከዚያም ክትትል እንዲደረግብን ያደርግና እንለያያለን ። አስፈላጊ ከሆነ ሌሊቱን ሙሉ ተጠቅመህ ድፈነው ። ነገ ዘበኛው የጧት ጉብኝቱን ጨርሶ ከመመለሱ በፊት ወደኔ እንዳትመጣ ። ነገ ስትመለስ አንድ የምነግርህ ቁም ነገር አለኝ ።”

ኢድመንድ የፋሪያን እጅ ወደ ደረቱ በመውሰድ ታማኝነቱን ከገለጸ በኋላ አሥራ አምስት ወር የተቆፈረውን ቦይ ባንድ ሌሊት ለመድፈን ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፱

በማግሥቱ ጧት ኢድመንድ ፋሪያ ክፍል ሲገባ ቄሱ ባልሰለሰው እጁ ቁራጭ ወረቀት ይዞ ተቀምጦ አገኘው ። ፋሪያ አንድም ቃል ሳይ ናገር ወረቀቱን ለኢድመንድ አሳየው ።

" ምንድን ነው እሱ ?" ሲል ጠየቀ ኢድመንድ ፤ ግራ ተጋብቶ።

" በደንብ ተመልከተው እስኪ " አለ ፋሪያ ፤ ፈገግ ብሎ ።

" ምን ነካህ ? አይቸው በማላውቀው ቀለም የተጻፉ ፊደላት ካሉበት ቡሜቂ ወረቀት በስተቀር የሚታዩኝ ነገር የለም ።"

"ይህ ቡሜቂ ወረቀት የኔ ልጅ" አለ ፋሪያ ሳቅ ብሎ ፤ "የኔ ንብ ረት ሲሆን ከዛሬ ጀምሮ ግማሹን አውርሼሃለሁ ። "

ኢድመንድ ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ቆረር ብሎ ሲወርድ ተሰ ማው ። ፋሪያን ካዩበት ጊዜ ጀምሮ በቻቲዩዲፍ እብድ ስላሰኘው ንብ ረት ማንሳትእ ይፈልግም ነበር ።

ፋሪያ ግን ነገሩ ስለገባው እንደመሳቅ ብሎ እንዲህ አለ ። "ከአደ ነጋገርህ ምን እንደተሰማህ ገብቶኛል ። ግን አይዞህ አትፍራ ፤ እብድ ባለመሆኔ ራስህ ዋቢ ነህ ። ይህ ንብረት በርግጥ አለ ። እድሉ እንዳገ ኘው ከፈቀደልኝ አንተም ታገኘዋለህና በጥሞና አዳምጠኝ ። ከዚያ በኋላ ማመን አለማመኑ ያንተ ፋንታ ነው ። "

" ሰማኸኝ ወይ" አለ ኢድመንድ ቀበል አድርጐ ፤ "ሕመሙ በጣም አድቅቆሃል።ትንሽ ብታርፍ አይሻልህም ? ታሪኩን ነገ ትነግረ ኛለህ ። ዛሬ ግን እኔ የምፈልገው አንተን ማስታመም ብቻ ነው ። በዚያ ላይ " አለ ኢድመንድ ፈገግ ብሎ " አሁን እኛን የሚያሳስበን የንብረት ጉዳይ አይደለም ። ነው እንዴ ?"

"ነው ! . . . . በጣም ሊያሳስበን ይገባል ! " አለ ሽማግሌው ነጠቅ አድርጐ ፤ " ሶስተኛው ሕመሜ ነገ ይነሳ እንደሁ በምን እናው



t.me/OLDBOOKSPDF

ታቸው ለሊክሳንደር ስድስተኛ
ሰኩት ገንዘብ ያላረካቸው ጳጳስ ከወ
ፈልገ ስለተጠራጠርኩ የወንደ ሚ
ክረስቶ ደሴት ዋሻ ለብ
ል መልክ የቀበር
የው ቀዳዳ ተነስቶ በቀጥታው
ስቶ ሊያገኘው መቻሉን እየገለ
ዳ ያወረስኩት መሆኔን አስታውቃ

ቹ የተሠሩ ሲሆን ንብረቱ የሚገኘው
ኩል ባለው ጠርዝ ነው ።
ባር ስፓዳ
፯ ቀን ፲፬፻፲

"እስኪ ሁሉቱን ቁራጮች ባንድ ላይ አስቀምጥና ራስህ ፍረድ" አለ ቄስ ፋሪያ ኢድመንድ ማንበቡን እንደ ጨረሰ ። ሁለቱ ቁራጮች ሲገናኙ እንደሚከተለው ይነበቡ ነበር ።

ዛሬ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፬፻፲ በብፁዕነታቸው ለሊክሳንደር ስድስተኛ ቤት ለራት ግብዣ ስጠራ ለሹመቱ የከፈልኩት ገንዘብ ያላረካቸው ጳጳስ ከወ ላጆቼ የወረስኩትን ሃብት ሊገፉኝ እንደሚፈልጉ ስለተጠራጠርኩ የወንደ ሚ ልጅ ጊዮዶ ስፓዳ ከኔው ጋር ባንድ ወቀት በሞንቴ ክረስቶ ደሴት ዋሻ ለብ ርኝ ሂዶ የጉበኘውን በወርቅ ፣ በአልማዝ ፣ በእንቁና በሉል መልክ የቀበር ኩትን ንብረት በስተምሥራቅ በኩል ከሚታየው ቀዳዳ ተነስቶ በቀጥታው መሥመር በመጓዝ ሃያኛውን ድንጋይ ለንስቶ ሊያገኘው መቻሉን እየገለ ፅኩ ይህንኑ ሀብቴን ለዚሁ ለጊዮዶ ስፓዳ ያወረስኩት መሆኔን አስታውቃ ለሁ ።

በዋሻዎቹ ውስጥ ሁለት መግቢያዎች የተሠሩ ሲሆን ንብረቱ የሚገኘው በሁለተኛው መግቢያ ላይ በዳር በኩል ባለው ጠርዝ ነው ።

ቄሳር ስፓዳ

ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፬፻፲

"እሺ ፤ አሁንስ ገባህ ?" ሲል ጠየቀ ቄስ ፋሪያ ።

" ይህ ማለት የመስፍኑ ኑዛዜ መሆኑ ነውን" በማለት ጠየቀ ኢድመንድ ፤ አሁንም ግራ ተጋብቶ ።

" አዎ ! አዎ ! "

" የተቃጠለውን ክፍል ማን መልሶ በዚህ መልክ አስቀመጠው ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

አምላክ ግን አባት መሆንም ሆነ ነጻ መውጣት የማልችለውን እድለ ቢስ ለመካስ ብሎ አንተን ላከልኝ ።”

ቄስ ፋሪያ ያልሰለለውን ግራ እጁን ሰጣቱ ሲዘረጋለት ወጣቱ ከንዱን በሽማግሌው አንገት ዙሪያ ጠምጥሞ ሁለቱም በእንባ ዶፍ ይጠመቁ ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 12

እብድ ያሰኘው ንብረት አሁን ግን እንደ ልጁ የሚወደውን ወጣት የወደፊት ሕይወት ሲያረካ መቻሉ እየታዩው በቄስ ፋሪያ ዓይነ ህሊና የንብረቱ ጠቀሜታ እጥፍ ድርብ ሆነበት ። ሁልጊዜ የንብረቱን ብዛት ለኤድመንድ እያስረዳ በእንዶዚያ ዓይነቱ የተትረፈረፈ ሃብት ሊሠሩ ስለሚገባቸው መልካም ተግባራት ይመክረዋል ። በዚህ ጊዜ ኤድመንድ ለራሱ የገባውን የብቀላ ቃል ኪዳን በማስታወስ ፊቱን የሐዘን ጭጋግ ያለብሰውና በበኩሉ ሃብት የተትረፈረፈው ሰው በባላጋራዎቹ ላይ ምን ያህል ከባድ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል በአንክሮ በማሰላሰል ይደነቃል ።

የሞንቴ ክሪስቶን ደሴት ቄስ ፋሪያ አያውቃትም ። ኤድመንድ ግን በዚያች ትንሽ ደሴት በኩል በተደጋጋሚ ያለፈ ሲሆን ባንድ ወቅትም በእግሩ ረግጧታል ። ሞንቴ ክሪስቶ የሰው ዘር የማይኖርባት የጐጆ ቤት ከዳን ቅርጽ ያላት የድንጋይ ደሴት ስትሆን በእሳተ ገሞራ እማካኝነት ከባህሩ ወለል የተነሳች እንደሆነች ይነገርላታል ።

ቄስ ፋሪያ እንደፈራው እግርና እጁ እንደሰለለ በመቅረቱ ወደ ደሴቷ ሄዶ ንብረቱን የማግኘቱ ተስፋ ጨርሶ ቢጨልምበትም ለወጣት ወዳጁ ማምለጥ ሴት ተቀን ይመኝ ነበር ። ምናልባት ወረቀቷ ልትጠፋ እንደምትችል በመፍራት ኤድመንድ ኑዛዜውን ቃል በቃል በአእምሮው እንዲቀርጸው አደረገ ።

አንድ ቀን ኤድመንድ ድንገት ባንድ ድምጽ ከእንቅልፉ ባነነ። አይኖቹን ገለጥ አድርጎ ጨለማውን በእይታው ሊበሳ ሞከረ ። የሰውን ስም የሚጠራ የሚመስል ድምጽ በድጋሚ ጆሮው ውስጥ ገባ ። ከአልጋው ብድግ ብሎ በጸጥታ ማዳመጡን ቀጠለ ። ያለ ጥርጥር ድምጹ የሚመጣው ከፋሪያ ክፍል ነበር ።

እንደተለመደው አልጋውን ወደ መሐል ከንፏቀቀ በኋላ በውስጥ ለውስጡ መተላለፊያ በቅልጥፍና ሾልኮ ከሽማግሌው ክፍል ሲገባ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኸቱ ሊቆይ አልቻለም ። ውሃው ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ሰመጠ ። ከአግሩ ጋር የታሠረው ትልቅ የመድፍ ጥይት ቀለህ ቁልቁል ይዞት ይወርድ ጀመር ።

የቻ·ቲዩዲፍ የመቃብር ሥፍራ ባህሩ ኖሯል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህም ልክ ከመርከቧ ካፒቴን ጋር የተዋዋለው የኮንትራት ቅጥር እንደተፈጸመ አንድ ሰበብ ፈጥሮ አነስተኛ ታንኳ ከተከራዩ በኋላ ወደ ሞንቴ ክሪስቶ ለመጓዝ ወሰነ ። የተቀበረውን ንብረት ለማየት በሚሄድበት ጊዜ ማንንም ማስከተል እንደሌለበትም ያውቃል ። ይሁን እንጅ ብቻውን የሚሄድበትን የማሳመኛ ምክንያት ሊያገኝ አልቻለም።

ይህንን ችግር በማሰላሰል ላይ እንዳለ አንድ ምሽት በኢድመንድ ላይ ባደረበት ጠንካራ እምነት የተነሳ በጆሚኒት ሊያሠራው የሚፈልገው የጂዩን ካፒቴን ወደ አንድ የሌጉርን ወደብ ዋና የመገናኛ ሥፍራ የነበረ ሆቴል ወሰደው ። በዚያ ምሽት በታወቁ የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች መካከል ስለአንድ ሚስጥራዊ ተግባር ውይይት ይካሄዳል ። ውይይቱም የቱርክ መጋረጃዎች ፤ ሱፍና ሌሎች ጨርቆች ስለተጫነች መርከብ የሚመለከት ነበር ። የሸቀጡ ልውውጥ ሊካሄድበት ስለሚችል ሰዋራ ሥፍራና ይህንኑ ሸቀጥ ወደ ፈረንሳይ ማስገባት ስለሚቻልበት ዘዴ መፍትሔ መገኘት ነበረበት ። ሙከራው ከተሳካ ወደር የማይገኝለት ትርፍ ይዛቃል ። በተግባሩ የተሳተፉ ሰዎችም ፣ ተራ ሠራተኞች ሳይቀሩ የትርፍ ተካፋይ ይሆናሉ ። የጂዩን ካፒቴን በሞንቴ ክሪስቶ ደሴት ሰው ስለማይኖርና ወታደሮችም ሆኑ የቀረጥ ወኪሎች ስለማይገኙ ጭነቱን ለማራገፍአመቺ ስለመሆኗአስተያየት ሰጠ ። ስለ ሞንቴ ክሪስቶ ሲወራ በመስማቱ ኢድመንድ በደስታ ፈነደቀ ። ደስታው ከፊቱ ላይ በግልጽ ይነበብ ስለነበር ሰዎች እንዳያውቁበት ከውይይቱ ሥፍራ ተነስቶ በሆቴሉ በረንዳ ከዳር ዳር ይንጐራደድ ጀመር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ውይይቱ ሲመለስ ነጋዴዎቹ በሚቀጥለው ምሽት ከሌጉርን ተነስተው ወደ ሞንቴ ክሪስቶ ለማምራት ተስማምተዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኢድመንድ በወርቁና በከበሩት ድንጋዮች ላይ እጁን እያሳወሰ ከዳሰሳቸው ፤ የሚንቀጠቀጡ እጆቹን በውስጣቸው ቀብሮ ከቆዩ በኋላ እንደ እብደት አድርጎት ከዋሻው ወጥቶ ይሮጥ ጀመር ።

ዙሪያውን የከበበውን ባህር ማዩት ወደሚችልበት ግዙፍ ድንጋይ ላይ ዘሎ ወጣ ። ለመገመትም ሆነ ለማመን ከሚያዳግተው ፤ ተሰምቶ ከማይታወቀው ፤ የተትረፈረፈ ሃብት ጋር ብቻውን መሆኑን አረጋገጠ። ያሁሉ ንብረት የእሱ ፣ የብቻው መሆኑን አመነ ። ግን ሕልም ይሆን ወይስ ዕውነት ? ጸጋውን በድጋሚ ለመመልከት ቢፈልግም በወቅቱ የሚራመድበት ጉልበት ፣ የሚያይበት አይንም ሆነ የሚያመዛዝንበት ሕሊና እንደሌለው ተሰማው ። አእምሮውን እንዳይስት ፈርቶ ራሱን በሁለት እጆቹ አድርጎ ከቆዩ በኋላ ድንገት እንደበረገገ አውሬ በደሴቷ ዙሪያ ሲሮጥ የሚያሰማው ጩኸትና መወራጨት የተራራ ፍየሎቹንና ዳክየዎቹን ሳይቀር ያስፈራ ነበር ።

ከረጅም ጊዜ በኋላ ወደ ዋሻው ሲመለስ እንኳ ገና ጥርጣሬው አል ለቀቀውም ። በዋሻው ውስጥ በፍጥነት ቁልቁል ወረደና ከዚያ ሀብት ፊት ተንበረከከ ። እጆቹን በኃይል በሚመታው ልቡ ላይ አስቀምጦ እሥር ቤት እስኪወርድ ያሳለፈው ደስታ ፣ እሥራ አራቱ የጨለማ ዓመ ታትና አሁን ደግሞ ከፊቱ ሆጨጭ ያለው ቁጥር ሥፍር የሌለው ሀብት በአእምሮው ተደበላለቀ ። ከእንግዲህ ሁሉም በእጁ ፣ ሁሉም በደጁ ነው ። እንደተንበረከከ ጸሎት ሊያደርስ ሞከረ ፣ የሚያቀርበው የምሥ ጋና ቃል ግን አልመጣልህ አለው ። ሁሉም ነገር ከሚያምነው በላይ ሆነበት ። የደስታው ብዛት በልቡ እንጅ በአንደበቱ የሚገለጽ አልነበ ረም ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

# 15

በሚቀጥለው ቀን ኢድመንድ ኪሶቹን በአልማዝና በእንቁ ከሞላ ቻው በኋላ ካዝናውን በጥንቃቄ ቀብሮ የዋሻውን መግቢያ በፍጹም መለየት እስኪያዳግት ድረስ ሸፈንና የጓደኞቹን መመለስ እየተቅበጠበጠ ይጠባበቅ ጀመር ። በደሴቷ ተቀምጦ ንብረቱን የመጠበቅ ፍላጎት አላደረበትም ። ከህብረተሰብ ጋር ተቀላቅሎ በዚህች አለም ሃብት በሕዝብ በራት የሚሰጠውን ታላቅ ማዕረግ ፡ ተደማጭነትና ኃይል የሚጨብጥበት ጊዜ ደርሷል ።

የኮንትሮባንድ ነጋዴዎቹ በስድስተኛው ቀን ተመለሱ ። ጓደኞቹ ወደ ደሴቷ እንደመጡ ህመሙ ሙሉ ለሙሉ ባይለቀውም በመጠኑ እንደተሻለው ነግሯቸው እነሱ በጉዟቸው ላይ ምን እንዳጋጠማቸው ያዳምጥ ጀመር ። ጉዟቸው የተሳካ ከመሆኑም በላይ በተለይ ጃኮፖ ኢድመንድ ከትርፍ ሊካፈል አለመታደሉን በቁጭት እያነሳ ደጋግሞ ኃዘኑን ይገልጽ ነበር ። ኢድመንድ ሳቁን እንደ ምንም ተቆጣጠረ ። ጂዩን ወደ ሞንቴ ክሪስቶ የመጣችው ለኢድመንድ ስትል ብቻ ስለነበር ወዲያውኑ ተሳፍሮ ወደ ሌጎርን ጉዟቸውን ቀጠሉ ።

ሌጎርን እንደደረሱ ኢድመንድ ኪሱን ካጣበበት አልማዞች ውስጥ አራቱን ትናንሽ እንክብሎች ብቻ በሃያ ሺህ ፍራንክ ከሸጠ በኋላ በማግስቱ ለጃኮፖ ትንሽ መርከብ ገዝቶ ሰራተኞች የሚቀጥርበት ገንዘብ ጨምሮ ሰጠውና ወደ ማርሴል ሄዶ ሉዊስ ዳንት ስለሚባል ሽማግሌና ሚርሲደስ ስለምትባል ሴት ሁኔታ እንዲያጠያይቅ ላከው ። ጃኮፖ ነገሩ ሁሉ ህልም መሰለው ። ይሁንና ኢድመንድ ሌጎርን እንደ ደረሱ ከአጎቱ ውርስ እንደተረከበ ለጃኮፓ ተረከለት ። የኢድመንድ እውቀት ትረካውን ትክክለኛ አስመስሎ ስላስቀመጠው ጃኮፖ ለቅጽበት እንኳ አልተጠራጠረም ። በሞንቴ ክሪስቶ ደሴት ለመገኘት ተቃጣጥረው በሚቀጥለው ቀን ጃኮፖ ወደ ማርሴል ጉዞውን ቀጠለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የአባቱ ሞት ያልተጠበቀ አልነበረም ። ግን ሜርሲደስ የት ደረሰች ? ሌሎች ማንንም አምኖ የማይጠይቃቸው ፡ ግን በአእምሮው የሚጉላሉ ጥያቄዎችም ነበሩ ። ሌጎርን ላይ ፊቱን በመስታወት በተመለከተበት ወቅት ማንም ሊያውቀው እንደማይችል ተረድቷል ። በዚያ ላይ ራሱን ሌላ ሰው ለማስመሰል ሁሉም ነገር በእጁ ነው ። ይህንን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ የጃኮፖን መርከብ እያስከተለ በድፍረት ወደ ማርሴል ወደብ ከተጓ። በኋላ ከአስራ አራት አመት በፊት ወደ ቻቲዩዲፍ ሲወሰድ በተሳፈረበት ቦታ ትይዩ አቆማት ።

ወታደሩ በመቃኛ ጀልባ ሆኖ ወደሱ ሲጠጋ ኢድመንድ አንዳችም ድንጋጤ አልተሰማውም ። ይልቁንም ከራት ባንጠረበበው ልበሙሉነት ሌጎርን ላይ የገዛውን ፓስፖርት አሳይቶ ያለምንም ችግር የወደቧን ከተማ ማርሴልን በእግሩ ረገጠ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፮

በደቡባዊው የፈረንሳይ ክፍል በእግር የተጓዘ ሰው ሁሉ በሊጋርድና በካይር በተባሉት ትናንሽ ከተሞች መካከል በመንገዱ ዳር አንዷት ትንሽ የገጠር ሆቴል ማየቱን ያስታውሳል ። ላለፉት ሰባትና ስምንት ዓመታት የዚህች ሆቴል ባለቤት ካደሮስ የተባለ የማርሴል ልብስ ሰፊ ነበር ። ሆቴሏ የይስሙላ ስም ትያዝ እንጅ በውስጧ ያሉትን ባልና ሚስት አስተዳዳሪዎቿን የሚያኖር ገቢ እንኳ አልነበራትም ።

የካደሮስ ባለቤት በንዳድ በሽታ ቀጫጭና ገርጥታ ለብዙ ዓመታት የአልጋ ቁራኛ ሆና የኖረች ደቃቃ ሴት ናት ። ሁልጊዜ በሽታዋንና የባሏን ድህነት ስታማርር ካደሮስ የሚሰጣት መልስ ፤ " ይብስ እያምጣ ! የእሱ ትዕዛዝ ነው " የሚል ቃል ብቻ ነበር ።

አንድ ቀን ረፋዱ ላይ ካደሮስ በሆቴሉ በረንዳ ላይ ቆሞ እንቅስቃሴው የተዳከመውን ጐዳና በትካዜ በመመልከት ላይ እንዳለ አንድ ፈረሰኛ ከሩቅ ወደ ሆቴሉ ሲገሰግስ ታዩው ። ፈረሰኛው ለአይን እየቀረበ በመጣ መጠን ካባ የለበሱ ኢጣሊያዊ ቄስ መሆናቸው ተለዩ ። የበሐይዋ ሙቀት ኃይለኛ ቢሆንም ቄሱ ወፈር ያለ ጥምጣም በራሣቸው ዙሪያ አስረዋል ። ቀጠን ብለው ረዘም ያሉት ፈረሰኛ ቄስ ከሆቴሉ በረንዳ አጠገብ ሲደርሱ ዱብ ብለው ወረዱና በግንባራቸው ላይ የተንቸረፈፈውን ላብ በመሐረብ ጠረግ ጠረግ እያደረጉ በቀጥታ ወደ ካደሮስ ያመሩ ጀመር ።

ቄሱ ከካደሮስ ፊት ለፊት እንደደረሱ ለአፍታ በልዩ አትኩሮት ከተመለከቱት በኋላ ጥርት ባለ ጣሊያንኛ ፤ " ካደሮስ ማለት አንተ አይደለህም ? " አሉ ።

" አዎ ፤ አባታችን " አለ ካደሮስ " ምን ልርዳዎ ? "

" ቄስ ቡሶኒ እባላለሁ ። ለመሆኑ አንተ ባንድ ወቅት ማርሴል ላይ ልብስ ሰፊ አልነበርክም ? "



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት ለአምስት ክፈል ይላል ?" ሲል ጠየቀ ካደሮስ ። "እር ስዎ የጠቀሱት አራት ሰዎችን ብቻ ነው ። "

"አምስተኛውማ አባቴ ነበር ፤ ሞቷል እሉ ። የሰማሁትም ማር ሴል ነው ። " በማለት ቄስ ቡሶኒ ለሁኔታው የማይጨነቁ ለመምሰል እየሞከሩ ንግግራቸውን ቀጠሉ ። " ግን አባቴ ከሞተ ረጅም ጊዜ ስለ ሆነው ስለአሟሟቱ ዝርዝሩን የሚነግረኝ አላገኘሁም ። አንተ የምታውቀው ነገር ይኖራል ? "

"ከማንም የበለጠ ነኖ ! " አለ ካደሮስ ፤ "ከእሳቸው መኖሪያ ምድር ቤቱን ተከራይቸ ነበር የምኖረው ። . . . ልጃቸው ከጠፋ በኋላ አንድ ዓመት እንኳ አልቆዩም ። እዬ ምስኪን ሽማግሌ ! "

" እንዴት ነበር የሞተው ? "

" ዶክተሮች ጨጓራቸው እንደተላጠ ነበር የሚናገሩት ፤ በደንብ የሚያውቋቸው ግን የሞቱት በሐዘን ነው ይላሉ ። ይሁን እንጂ እኔ ልክ ነፍሳቸው ስትወጣ አይቻቸዋለሁ ። የሞቱትም በ . . . . " ካደሮስ ንግግሩን ገታ ።

" በምን ? " አለ ቄስ ቡሶኒ ለመነሳት እየቃጣቸው ።

" በረሃብ ! "

"በረሃብ ? " ሲሉ ጮሁ ቄስ ቡሶኒ ከባርጩማው ፈንጠር ብለው እየተነሱ ። ቀጥሎም ራሳቸውን ለመቆጣጠር እየታገሉ " እንዴት ? " አሉ ፤ "ፈረንሳይ የጥጋብ አገር ናት ፤ እንስሳት እንኳ በረሃብ አይሞቱም ትላላችሁ ። በየትም አገር ቢሆን ፤ በመንገድ የሚዘዋወር ውሻ እንኳ ቁራሽ ቂጣ የሚወረውርለት አያጣም ! አንተ ግን ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች ዙሪያውን የሚያጕራብቱት ሽማግሌ በረሃብ እንደሞተ ታወራለህ ። አይደረግም ! በፍጹም አይታመንም ! "

" የምነግርዎትኮ የሆነውን ነው ። " አለ ካደሮስ ።

በዚህ ጊዜ " ምን ያስለፈልፍሃል ? " የሚል የሴት ድምጽ ከደረጃው ላይ ተሰማ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" አሳምሬ ነኛ ። "

" በላ ንገረኝ ። "

"ካደርስ" አለች እመቤት ካደርስ ፤ " እረ እባክህ ተለመነኝ ?"

" እረ አሁንስ እውነትሽን ነው ፣ ፈተፈትኩት " አለ ካደርስ ቀበል አድርጎ ።

" ልትነግረኝ አትፈልግም ? " ሲሉ ጠየቁ ቄሱ ።

" እንዲያውስ ለምን ይበጃል ? ኢድመንድ በሕይወት ቢኖርና ወደኔ መጥቶ ጠላቶቹንና እውነተኛ ወዳጆቹን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመለየት ቢጠይቀኝ ኖር አፍረጥርጬ በነገርኩት ነበር ። እርስዎ እንደ ነገሩኝ ግን የሞተ ፣ የተቀበረ ስለሆነ ማንንም ሰው ሊጠላ ፣ በማንም ሰው ላይ የበቀል ርምጃ ሊወስድ የሚችል አይደለም ። በቃ ያለፈውን እንዳለፈ ቆጥረን እንለፈው ። "

" ታዲያ ለእነዚህ ተንኮለኛ ጓደኞች ለታማኝነታቸው የተዘጋጀ ውን ኑዛዜ ስጣቸው ትለኛለህ ? "

"እረ በፍጹም " አለ ካደርስ ። " ደግሞስ የምስኪኑ ኢድመንድ ኑዛዜ ለነሱ ምን እርባና አለው ? በውቅያኖስ ላይ የተጨመረች አንዲት ጠብታ ውሃ ! "

" አዎ ፣ እነዚያ ሰዎች ከፈለጉ በትንሽዋ ጣታቸው ድምጥማጥህን ሊያጠፉት እንደሚችሉም አትርሳ " አለች እመቤት ካደርስ ።

" እስከዚህ ከበርቴና ኃይለኞች ሆነዋል ወይ ? " ሲሉ ጠየቁ ቄስ ቡሶኒ ።

" እስካሁን የነሱንም ታሪክ አያውቁ ፣ አባታችን ? "

" በጭራሽ ፣ እስኪ ንገረኝ ። "

ካደርስ ለአፍታ አሰበና " አይሆንም " አለ ፣ " ታሪኩ ረጅም ነው ። "

" የሚያስገድድህ የለም ። " አሉ ቄስ ቡሶኒ ግድ የለሽነት የተቀ ሃደው በሚመስል ቀዝቃዛ የአነጋገር ቃና ። "ምርጫህን እቀበላለሁ። በቃ ፣ እዚህ ላይ እንዝጋውና እኔም አልማዜን ልሽጥ ። " አልማዙን ከ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኪሳቸው አወጡና በሚቅለጨለጨው የካዶርስ አይኖች ፊት እንዲፍ ለቀለቅ አደረጉት ።

“ ታያለሽ ? ” ሲል ካዶርስ ወደሚስቱ ባረቀ ።

“ አልማዝ ! ” በማለት እመቤት ካዶርስ ብድግ ብላ በደረጃው ወደታች ወረደች ። “ የት ተገኘ ? ”

“ አልሰማሽም እንዴ ? ኤድመንድ ዳንት ለአባቱ ፤ ለእጮኛው ፤ ለፈርናንድ ፤ ለዳንግላርና ለእኔ የተናዘዘው እኮ ነው ። ”

“ጉድ አያልቅምኮ ! ከሃዲ ሰው ደግሞ በዮት ሀገር ነው ኑዛዜ ተካፋይ የሚሆነው ? ” አለች እመቤት ካዶርስ “ በደቦ የወቱት አል በቃ ብሏቸው ዶልተው ያስገደሉት እንዷቸው ፤ ደሞ ኑዛዜ ይካፈሉ ? ”

“ እኔስ ይኸንኑ አልነበር የምናገረው ” አለ ካዶርስ ፤ “ ምህረት ለማያሻው ሃጢአት የኑዛዜ ቃልን መዳረግ አብሮ የሐጢአቱ ተሳታፊ መሆን ነው ። ”

“ እሱ የራስህ ችግር ነው ፣ ” አሉ ቄሱ ረጋ ብለው ፣ አልማዙን ወደ ኪሳቸው እየመለሱ ። “ አሁን እባካችሁ የኤድመንድን ጓደኞች አድራሻ ንገሩኝና የሙት አደራዬን ከላዬ አስወርጄ ኸሁ ልበል ።”

የካዶርስ ግንባር በላብ ይታጠብ ጀመር ። ቄስ ቡሶኒ ከተቀመጡ በት ተነስተው ወደ ፈረሳቸው እንደሚመለከቱ ሁሉ ወጣ አሉ ። ካዶር ስና ሚስቱ ግራ ተጋብተው እርስ በርሳቸው ተያዩ ።

“ አልማዙ በሙሉ የኛ ይሆናል ። ” አለ ካዶርስ ።

“ ምን ትቀልዳለህ ? ”

“ መቼም ቄስ ይኸን ያህል አይዋሽም ። ”

“ እንግዲያስ አደራህ በርታ ” አለች እመቤት ካዶርስ ። “ ዘዴ ውን ላንተ ትቸዋለሁ ። ” ቀስ ብላ በደረጃው ወደፎቅ ወጣች ። በመ ጨረሻው ደረጃ ላይ እንደደረሰች ለአፍታ ቆም አለችና ቁልቁል እየተ መለከተች ። “ በደንብ አስብበት ካዶርስ ! ” አለች ።

“ እሱን ለእኔ አትንገሪኝም ” አለ ካዶርስ በልበሙሉነት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ምን ወሰናችሁ ? » ሲሉ ጠየቁ ቄሱ ፤ አመቺውን ጊዜ በመጠቀም ተመልሰው እንደመጡ ።

« አንድ ባንድ ለማስረዳት » ነበር መልሱ ።

« እሱ የሚሻል ይመስለኛል ። መናገር የማይገባችሁን ነገር እያስለፈለፍኩ የወሬ ጥማቴን ለማርካት ፈልጌ እንዳይመስላችሁ ፤ የኢድመንድን ቅርስ በአግባቡ ማከፋፈል ግን የሰማይ ቤት አደራዬ ነው ። »

« እርግጥ ነው ፤ በአግባቡ መሰጠት አለበት ! » አለ ካደሮስ ጉንጮቹ በተስፋ እየቀሉ ።

« ቀጥል ። »

« በመጀመሪያ » ሲል ጀመረ ካደሮስ ፤ « ለአንድ ነገር ቃል እንዲገቡልኝ እጠይቅዎታለሁ ። »

« ምንድን ነው እሱ ? »

« በምንግርዎ ነገር ላይ አንድ ርምጃ የሚወስዱ ከሆነ ነገሩን ከእኔ መስማትዎን መናገር የለብዎትም ፤ ምክንያቱም ሰዎቹ ከሐብታቸውና ከሥልጣናቸው የተነሳ ብርጭቆ የመስበር ያህል በቀላሉ ሊያጠፉኝ ይችላሉ ። »

« አይዞህ አትፍራ ወዳጄ ፤ ቄስ እንደመሆኔ መጠን የተነገረኝን ኑዛዜ የትም እንዳላባክን ሙያዬ ያግደኛል ። ዋናው ዓላማችን የወዳጃችንን ኑዛዜ በትክክል መፈጸም ነው ። ይልቅስ ያለምንም ጥላቻና ፍርሃት በግልፅ ተናገር ። ምናልባት የምትጠቅሳቸውን ሰዎች ማንነት ሳላውቅ እችላለሁ ። በዚያ ላይ እኔ ኢጣሊያዊ እንጅ ፈረንሳይዊ አይደለሁም። የሟቹን ኑዛዜ እንደፈጸምኩ ወደነበርኩበት ገዳም እመለሳለሁ።»

የካደሮስ ጥርጣሬ እየቀነሰ ፤ ልቡ ረጋ እያለ መጣ ። « እንግዲያውስ » አለ ፤ « ምስኪኑ ኢድመንድ እውነተኛና የልብ ወዳጆቼ ብሎ የሚጠራቸውን ሰዎች እውነተኛ ታሪክ ልንገርዎ ። መቼም ላፍ የሚከብድ አሳዛኝ ታሪክ ነው ። መጀመሪያውን የሚያውቁት ይመስለኛል ። »

« አዎ ፤ ሟቹ በሠርጉ ዋዜማ መታሠሩን አጫውቶኛል ፤ ውል ሊፈረም ሥነ ሥርዓቱን እንደጀመረ ። »



t.me/OLDBOOKSPDF

" የበለጠ የሚያስቅቀው ደግሞ ይህ ሁሉ ነገር የታዘዘው ከእምላክ ሳይሆን በሰው መሆኑ ነው ። "

" አሁን ደግሞ ስለነዚያ ሰዎች ልስማ " አሉ ፡ ቄስ ቡሶኒ ። ቀጥሎም ፤ " ግን ልብ አድርግ " በማለት ቄሱ ሳይታወቃቸው እንደመቆጣት ቃጣቸው ። " ምንም ነገር ሳትደብቀኝ ተስማምተሃል ። ልጁን በትካዜ ፡ አባቱን በረሃብ የገደሉት እነሱ እነማን ናቸው ? ሳትቀላምድ ንገረኝ ! "

" ቅናት ያሳረራቸው ሁለት ከይሲዎች " አለ ካድሮስ የቄሱ የሚያንገራግር ትዕዛዝ አስፈርቶት ። " አንደኛው በፍቅር የቀናበት ፈርናንድ ፡ ሌላው በሥልጣን የተመቀኘው ዳንግላር ። "

" እኮ እንዴት ? ቀንተውና ተመቅኝተው ምን አደረጉት ? "

"በመንግሥት ግልበጣ ላይ እንደሚካፈል አድርገው ወነጀሉት ።"

" ግን ከሁለቱ የትኛው ነው ይህንን ወንጀል ያሳበቀበት ? የትኛው ነው ትክክለኛው ሃጢአተኛ ? "

" ሁለቱም ። አንደኛው ደብዳቤውን ጻፈ ፡ ሌላው ላከው ። "

" ደብዳቤው የተጻፈው የት ቦታ ነበር ? "

" ሆቴል በረንዳ ላይ ። ከኢድመንድ ውል ማሰሪያ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ።

" ግን አንተስ እዚያ አልነበርክም ? " ሲሉ ባረቁ ቄሱ ቀበል አድርገው ።

" እዚያ እንደነበርኩ ማን ነገረዎ ? " በማለት ጠየቀ ካድሮስ ግራ ተጋብቶ ።

ቄስ ቡሶኒ ታሪኩን አበክረው ማውጣታቸው ትዝ አላቸው ። "ማንም ፤ " አሉ ፈጠን ብለው ፤ " ግን ዝርዝሩን በደንብ ልታውቅ ከቻልክ በሥፍራው ሳትኖር አትቀርም ብዬ ነው ። "

" እውነት ነው " አለ ካድሮስ በታፈነ ድምጽ ። " ነበርኩ ። "

" ታዲያ ያንን ተንኮል ሲተበትቡ አልተቃወምሃቸውም ። ያ ደግሞ አባሪ ተባባሪ ያደርግሃል ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

ካደሮስ ሽምቅቅ አለ ። " አርቲፊሻል ?" ሲል አጉረመረመ ፤"እ ታመጭው የለሽ ! ለምን አርቲፊሻል ይሰጡኛል ? "

" ሚስጥርህን በነፃ ለማስለፍለፍ ነዋ ! "

ካደሮስ የሚስቱ ጥርጣሬ ጭንቅላቱን መታው ። "እግዚኦ!" አለ ራሱን ይዞ " አታድርስ ነው ማለት ። "

ከጥቂት ጊዜ የትካዜ ፀጥታ በኋላ ካደሮስ ባርኔጣውን አንስቶ አል ማዙን በራሱ ዙሪያ ባሠራት መሃረብ እየጠቀለለ " አሁኑኑ ማጣራት አለብን ። " አለ ።

" በምን መንገድ ? "

" ወደ ከተማ ጐራ ብዬ ለደህና እንጥረኛ አሳያለሁ ። ቤቱን ጠብ ቂ ። በሁለት ሰዓት ውስጥ እመለሳለሁ ። " ያን ያህል የተቅመደመደ በት አልማዝ አሁን ደግሞ ያሽመደምደው ጀመር ። ከቤት ወጥቶ መን ገዱን እንደያዘ በሶምሶማ ይሮጥ ገባ ።

" ሃምሣ ሺ ፍራንክ " አለች እመቤት ካደሮስ ባሏን በአይኗ እየ ተከተለች ። " ብዙ ነው . . . . ሃብታም አያሰኝም እንጅ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

# 17

ካደሮስ የአምሳ ሺ ፍራንክ አልማዝ በተቀበለ ማግሥት በአነጋገሩም ሆነ በአረማመዱ እንግሊዛዊ የሚመስል ዕድሜው በሰላሳዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የሚገመት ሰው ወደ ማርሴል ከተማ ከንቲባ ቢሮ ጐራ ብሎ ነበር ። ይህ ጸጉረ ልውጥ በመጀመሪያ ራሱን ከከንቲባው ጋር በማስተዋወቅ ሮም የሚገኘው ‘ ቶምሶንና ጓደኞቹ ’ የተባለው የንግድ ድርጅት ዋና ሒሣብ ሹም መሆኑን ከገለጸ በኋላ ጊዜ ሳያባክን የመጣበትን ጉዳይ በዝርዝር አብራራ ።

“ ባለፉት አሥር ዓመታት እዚህ ማርሴል ከሚገኘው ‘ ሞሬልና ልጆቹ ’ ከተሰኘው ድርጅት ጋር የሸርክና ንግድ ስናካሂድ ቆይተናል ። ከድርጅቱ ጋር ለከፈትነው ንግድ አንድ መቶ ሺህ ፍራንክ የሚሆን ገንዘብ ያወጣን ሲሆን አሁን ግን የሞሬል ድርጅት እየከሰረ መሆኑን በመስማታችን ገንዘባችን አሳስቦናል ። ከሮም ባስቸኳይ የመጣሁት በጉዳዩ ላይ የበኩልዎን አስተያየት ለመጠየቅ ነው ። ” ሲል ተናገረ እንግሊዛዊው በተጀነነ አንደበት ።

“የተከበሩ እንግዳዬ” አለ ከንቲባው፤ “ ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት ሞሬልን ክፉ እጣ እንደገጠመው አውቃለሁ ። ሆኖም ምንም እንኳ ራሱም በድርጅቱ ላይ አሥር ሺ ፍራንክ የሚደርስ ገንዘብ ያፈሰስኩ ቢሆንም የሞሬልን ድርጅት ካፒታል መጠን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ ልሰጥዎ አልችልም ። በርግጥ ስለ ሰውዬው የግል አስተያየቴን እንድሰጥዎ የሚጠይቁኝ ከሆነ ሞሬል ማለት ግዴታዎቹን በወቅቱና በአግባቡ የሚወጣ ንጹህ ሰው ሲሆን ልነግርዎ የምችለውም ይህንኑ ብቻ ነው ። የበለጠ ልወቅ ካሉ ግን የወህኒ ቤቶች ተቆጣጣሪ የሆነውን ቦቪልን ማነጋገር ይችላሉ ። ቦቪል በሞሬል ድርጅት ላይ የሁለት መቶ ሺህ ፍራንክ ካፒታል ማፍሰሱን አውቃለሁ ። ስለዚህ በድርጅቱ ላይ የሚያሰጋ ነገር ካለ የበለጠ የሚያስጨንቀው እሱን ነውና ዝርዝሩን ሊያውቅ ይችላል ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

# 18

የሞረልና ልጆቹ ድርጅት በጥቂት ዓመታት ውስጥ እጅግ ተለ ውጧል ። ከባለጸጋ መኖሪያ ቤት በሚታየው የቤት ሠራተኞች ትርም ስና ሞቅ ያለ ኸር ጉድ ፣ በኮሪደሮች ወዲያ ወዲህ በሚጣደፉ በሥራ የተ ወጠሩ የሂሣብ ሠራተኞች ፣ በንግድ ልውውጥ በተጨናነቀው በረንዳ ፣ በወደብ ሠራተኞች ጫጫታና ሳቅ በተሞላው ግቢ ፋንታ የሐዘንና የጸ ጥታ አየር ይነፍሳል ። ቢሮዎችን አጣበው ከነበሩት ብዙ ሠራተኞች ውስጥ አሁን የቀሩት ሁለት ብቻ ናቸው ። አንደኛው አማኑኤል የተ ባለ የሞረልን ልጅ በማፍቀሩ ወላጆቹ ከሥራ እንዲሰናበት ቢገፋፉት እምቢ ብሎ የቀረ የሃያ አራት ዓመት ወጣት ሲሆን ሌላው ደግሞ ኮክል የተባለው በሂሣብ አያያዝ በኩል ካለው ጠንካራና ግትር አቋም ጋር በታማኝነቱና በታጋሽነቱ የታወቀው ግንዘብ ያዥ ነው ። ኮክል በድር ጅቱ ለሃያ ዓመታት በማገልገሉ አሁን እምነቱን መለወጡ አልዋጥልህ ስላለው ከሥራ ሊሰናበት አልፈቀደም ። ያለፈው ወር የሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ በወቅቱና ሙሉ ለሙሉ ተከፍሏል ። ይሁን እንጅ ከዚያ ወር መጨረሻ ጀምሮ ሞረል ብዙ እስከፊ ሰዓቶችን አሳልፏል ። የሠ ራተኞውን ክፍያ ለማሟላት የተረፈውን ጥሪት በሙሉ ማሰባሰብ ነበረ በት ። የመደህየቱ ወሬ በማርሴል ለሐሜታ እንዳይዳርገው ፈርቶ የባለ ቤቱን ጌጣጌጦች ወደ ሌላ ከተማ ሄዶ ከሸጠ በኋላ ነበር የሠራተኞቹ ደመወዝ የተከፈለው ። ይህ መስዋዕትነት የድርጅቱ ክብር ተጠብቆ እንዲቆይ ቢያደርግም ገንዘቡ ግን ጭራሹን ተሟጠጠ ። በወሩ አጋማሽ ላይ ለቦቪል አንድ መቶ ሺህ ፍራንክ ለመክፈልና በሚቀጥለው ወር አጋ ማሽ ላይም በድምሩ ሶስት መቶ ሺህ ፍራንክ የሚደርሱ እዳዎችን ለመሸፈን የቀረችው አንድ ተስፋ የፈራኦን ከሕንድ መመለስ ነበር ። ነገር ግን ከፋራኦን ጋር ካልካታ ከተባለችው የሕንድ ወደብ የተነሳች መርከብ ባሁለት ሣምንት በፊት ወደሚርሴል ስትመለስ የፋራኦን ወሬ አልሰማ አለ ። ዳናዋ ጠፋ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሞረል በዚህ አጉል ግልጽኝነት ፊቱ ከሐፍረት አልፎ በብሽቀት በርበሬ መሰለ ። " ይህ ድርጅት አባቴ ለሰላሣ አምስት ዓመታት ያህል ሲያንቀሳቅሰው ከኖረ በኋላ ያወረሰኝ ድርጅት ነበር ። " አለ ፤ " ያን ያህል ጊዜ አንድም ደረሰኝ ቀርቦበት ክፍያ አልተጠየቀም ። "

" አውቃለሁ " አለ እንግሊዛዊው ። " ግን በግልጽ ይንገሩኝና እነዚህን ደረሰኞች በወቅቱ ያወራርዱልኛል ? ። "

" እንዲህ ዓይነቱ ግልጽ ጥያቄ ግልጽ መልስ ያስፈልገዋል ። " አለ ሞረል ፤ " በርግጥ መርከቧ በደህና ከተመለሰች ይህንን ደረሰኝ ማወራረድ ብቻ ሳይሆን በተከታታይ የደረሰብኝን ክስረት ሁሉ መሸፈን እችላለሁ ። ነገር ግን የመጨረሻዋ ንብረቴ የሆነችው ፋራኦን በደህና ካልተመለሰች የክፍያዎችን ጊዜ ለማራዘም እንድምገደድ ስገልጽ ከፍተኛ ቅሬታ እየተሰማኝ ነው ። "

" ወደዚህ በመምጣት ላይ እንዳለሁ " አለ እንግሊዛዊው ፤ "አንዲት መርከብ ወደ ወደቡ ስትገባ አይቻለሁ ። "

" አውቃለሁ ፣ የመጣችው ከሕንድ ቢሆንም የእኔዋ አይደለችም ።" አለ ሞረል ። ከዚያም ለስለስ ባለ አንደበት ፤" እንዲህ ዘግይታ አታውቅም ። ፋራኦን ከካልካታ የተነሳችው የካቲት አሥራ አምስት ቀን ሲሆን ከወር በፊት መድረስ ነበረባት ። "

" የምን ድምጽ ነው የምሰማው ? " አለ እንግሊዛዊው ጆሮ ብሎ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ ። አካባቢውን ሁከት የረበሸው ይመስላል ።

" እግዚአ ፈጣሪዬ ! " አለ ሞረል ፤ " ደግሞ ምን መዓት መጣ ይሆን ? "

በደረጃዎቹ ላይ ከባድ ርምጃ ይሰማ ጀመር ። የሐዘን ጫጫታም ይሰማል ። ሞረል ሊወጣ ፈልጐ በሩን ከከፈተው በኋላ ጉልበቱ ከድቶት ተመልሶ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ።

ከአፍታ በኋላ ድምጹ ጋብ ቢልም ሞረል ግን አንድ ነገር የሚጠባበቅ ይመስላል ። ።

የውጭው በር በቁልፍ ሲከፈት ተሰማ ።

" የዚያ በር ቁልፍ ያላቸው ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው ፣ ኮክልና ዡሲዬ" ሲል አጉረመረመ ፤ሞረል ። ብዙም ሳይቆይ ሁለተኛው በር


t.me/OLDBOOKSPDF

ተክፍቶ ዡሊዬ ጉንጮቿ በእንባ እየታጠቡ ከገባች በኋላ አባቷ እንገት ላይ ተጠምጥማ "አባዬ ፣ አባዬ ፣ ምን በጀን ?" ስትል ጮኸች ።

"ፋራኦን ሰጠመች አይደለም ?" ሲል ጠየቀ ሞረል በታከተ ደ ካማ ድምጽ ። ልጅቷ የምትናገረው አልነበራትም ፣ የአዎንታ ምልክት ሰጥታ ራሷን አባቷ ደረት ላይ ለጠፈች ።

" ሠራተኞቹስ ? "

"ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የደረሰችው መርከብ ሁሉንም አተረ ፈቻቸው ።"

ሞረል በእርይታና በምሥጋና አይነት አስተያየት ወደ ላይ አን ጋጠ "ተመስገን" አለ ፤ "የፈረድከው በሌሎች ላይ ሣይሆን በእኔ ላይ ብቻ ነው ።"

በዚህ ቅጽበት እመቤት ሞረል ሲቃ እንደተናነቃት ገባች ፣ ከኋ ላዋ እማኑኤል ተከትሏታል ። መተላለፊያው ላይ ስምንት የሚሆኑ ከወ ገባቸው በላይ እርቃናቸውን የሆኑ መርከበኞች ይታያሉ ። እንግሊዛ ዊው እንግዳ እነዚህን ሰዎች ሲያይ ብድግ ብሎ ወደነሱ ሊሄድ ከከጀለ በኋላ ወዲያውኑ መለስ ብሎ ወደ ጥግ ቆመ ።

"ነገሩ እንዴት ነው የሆነው ?" ሲል ጠየቀ ሞረል ።

"ና ወዲህ ፔኔሎን" አለ እማኑኤል ፣ "እስኪ አስረዳን ?"

ፀሐይ ያበረናው ሽማግሌ መርከበኛ የተበጣጠሰች ባርኔጣ በእጁ እንደያዘ ወደፊት ከተራመደ በኋላ ፤ "ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ" አለ ፣ ሩቅ ቦታ የሰነበተ መንገደኛ ሳይመስል ።

"እንኳን ገባችሁ ፣" አለ ሞረል ። እንባው እየወረደ ቢሆንም ፈገግ ማለቱን ግን አልተወም ። "ካፒቴን ጋውማርድ የታለ ?"

"መንገድ ላይ ታሞ ቀርቷል ጌታዬ ፣ ከተሻለው በጥቂት ቀናት ውስጥ ይመለሳል ።"

"እሺ . . . እስኪ በል አስረዳን ፣ ፔኔሎን ?"

ፔኔሎን የቶምባሆውን ፒፓ ከከንፈሩ ካላቀቀ በኋላ አፉን በእጁ አበሰና ንግግሩን ጀመረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" የሂሣቡን ማወራረጃ ጊዜ እንዳራዝምልዎ ይፈልጋሉ ? "

" ማራዘሙ ክብሬንና ፤ በኋላም ሕይወቴን ያድናል ። "

" ለምን ያህል ጊዜ ላራዝምልዎ ? "

ሞረል ጥቂት ካቅማማ በኋላ " ለሁለት ወራት ያህል የሚቻል ከሆነ ፤ " አለ ።

" ይቻላል ፤ እንዲያውም ሶስት ወር ይሁንልዎ ። "

" ግን ድርጅትህ የሚፈቅድልህ ይመስልሃል ? " ከማለቱ እንግሊዛዊው ቀበል አድርጎ ፤ " አይጨነቁ ፤ ሙሉ ኃላፊነት ተሰጥቶኛል ። ዛሬ ሰኔ አምስት ነው ። ደረሰኞቹን ለመስከረም አምስት ያድሱና ይፈርሙ ። መስከረም አምስት ቀን ልክ ባሁኑ ሰዓትና ደቂቃ ማለትም ከጧቱ አምስት ሰዓት ላይ እመጣለሁ ። " አለ ።

አሮጌዎቹ ደረሰኞች ተቀደው አዳዲስ ደረሰኞች ከተሠሩና ከተፈረሙ በኋላ እንግሊዛዊው በተለመደው ቆጠብ ያለ አነጋገር ፤ " ልክ የዛሬ ሶስት ወር መስከረም አምስት ቀን ከጧቱ ልክ በአምስት ሰዓት እ ? " በማለት ምስኪኑን ባለመርከብ ተሰናብቶ ወጣ ። ሞረል የመጨረሻውን ንብረቱን የሚያሰባስብበት ሶስት ወር በማግኘቱ መጠነኛ እፎይታ ተሰማው ።

እንግሊዛዊው ደረጃዎቹን በመውረድ ላይ እንዳለ ዡሊዬን አገኛት ። እሷም ወደታች በመውረድ ላይ ያለች ብትመስልም ዓላማዋ ግን እንግዳውን ማግኘት ነበር ።

" እ ! ውድ . . . " በማለት እጆቿን እንዳጣመረች ስሙን መጥራት ባለመቻሏ አፈር አለች ።

" ወይዘሪት " አለ እንግዳው ። ' መርከበኛው ሲንባድ ' የሚል ፊርማ ያለበት ደብዳቤ ይደርስሻል ። ምንም ያህል ግራ ብትጋቢ እንኳ ደብዳቢው እንድታደርጊ የሚጠይቅሽን በትክክል ፈጽሚ ። እሺ ? "

" እሺ ! "

" ደብዳቤው የሚለውን ለመፈጸም ቃል ትገቢያለሽ ? "

" እምላለሁ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ መልካም ። ደህና ሁኚ እንግዲህ ወይዘሪት ። ልክ እንዳሁኑ ትክ ክለኛ ልጃገረድ ሆነሽ ከቆየሽ አምላክ አማኑኤልን በማጋባት እንደሚ ያስደስትሽ እርግጠኛ ነኝ ። ” ከዚህ አነጋገር ጋር እንግሊዛዊው አን ዳች መልእክት ባዘለ ሁኔታ የገቦሊዩን እጅ ጭምቅ አድርጉ ጨበጠው።

ገቦሊዩ እንባዋ እየተናነቃት ፊቷ ቲማቲም እ፣ኪመስል ድረስ ቀላ ። “ መርከበኛው ሲንባድ ” አለች እንዳይረሳት ። እንግዳው መን ገዱን እንደቀጠለ በረንዳው ላይ ፔኔሎንን አገኘው ። ፔኔሎን በሁ ለት እጁ የያዘውን የሶስት ወር ደመወዙን ጥቅል ብር ምን እንደሚያ ደርገው መወሰን አቅቶት የሚያሰላስል ይመስላል ። “እስኪ ተከተለኝ፣ መሴ? ” አለ እንግሊዛዊው እንግዳ ። “ ሳነጋግርህ እፈልጋለሁ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፲፱

በቶምሶንና ጓደኞቹ ወኪል የተደረገው ያልተጠበቀ የክፍያ ማራዘም እንደ ተዓምር ይቆጠር ጀመር ። ሞረል ግን የቶምሶንና ጓደኞቹ ወኪል ስለት ወደ ሶስት መቶ ሺህ ፍራንክ የሚጠጋ እዳ የተቆለለበትን ሰው አስቸኳይ ክፍያ በመጠየቅ ውድቀቱን አፋጥኖ ጭራሹን መክፈል እንዳይችል ከማድረግ ይልቅ ጊዜ ሰጥቶ በርጋታ እዳውን በሙሉ እንዲሸፍን ማድረግ ይሻላል ከሚል መርህ የመነጨ አድርጐ ነበር የገመተው ።

ይሁንና ሌሎቹ የሞረል አበዳሪዎች ከዚህ አስተሳሰብ የራቁና እንዲያውም በተቃራኒው የሚያስቡ ነበሩ ። እናም ደረሰኞቻቸውን ይዘው ልክ በማወራረጃው ጊዜ ይደርሱ ጀመር ። እንግሊዛዊው ጊዜውን ባያራዝም ኖሮ ሌሎቹን እዳዎች መክፈል ባልተቻለ ነበር ።

የእንግሊዛዊው ወሬ ጠፋ ። ከሞረል ጋር ውይይቱን ካካሄደ በኋላ ሁለት ቀን የሞላ ጊዜ እንኳ በማርሴል ከተማ አልታየም ። የፋራኦን መርከበኞችም ቢሆኑ በሌላ መርከብ ላይ ሳይቀጠሩ አልቀሩም ፡ ሁሉም የሄዱበት አልታወቅ አለ ።

ሞረል ከሁለት ወራት ለበለጠ ጊዜ ዕዳዎቹን ለማደስ ሲፍጨረጨር ቢከርምም አልተሳካለትም ። ነሐሴ 20 ቀን ከማርሴል ለመውጣት ሠረገላ ላይ ተቀምጦ ታዬ ። አነሳሱ ወደ ፓሪስ ነበር ። ጉዞው በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ክስረቱ ይፋ ከመውጣቱ በፊት ከአካባቢው ለመሠወር ፈልጐ ያደረገው ጉዞ መሆኑ ተወራ ። ይሁን እንጅ በነሐሴ ወር የመጨረሻ ቀን ኮክል የቀረበለትን ደረሰኝ በሙሉ ከፍሎ ሊያወራርድ ቢቃ ። ይህ ጉዳይ የሞረልን መውደቅ ሲ ተነብዩ የነበሩትን ሁሉ በእጅጉ ያስገረመቢሆንም ይኸው ውድቀት ወደመስከረም ወር መጨረሻ ይሸጋገር እንጅ እንደማይቀር መገመታቸውን አላቋረጡም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ናለች ። መርከቧ ጭንቷን ለማራገፍ በመዘጋጀት ላይ እንዳለች ካፒቴን ጋውማርድ በአንድ ጫፍ በኩል ቆሞ ትዕዛዝ ሲሰጥ ፔኔሎን ደግሞ ለሞሬል ምልክት ያሳይ ጀመር ።

ሕዝቡ በመገረም በሚያውካካበት ወደብ ሞሬልና ማክሲሚለን እርስ በርሳቸው የደስታ ቃል በመለዋወጥ ላይ እንዳሉ ግማሽ ፊቱን ጥቁር ጺም የሸፈነው ሰው ራቅ ብሎ ሁኔታውን ይከታተል ነበር ፡ "ደስ ይበላችሁ እናንት ንጹህ ልቦች ! " አለ ሰውዬው በዝግታ ለራሱ ፡ "ላደረጋችሁትና ለምታደርጉት ሁሉ ካሣው ተከፍሏችኋል ። "

ከዚያም ፊቱ በእርካታና በደስታ ፈገግ ብሎ ከተሰወረበት ሥፍራ ተነሳና ማንም ሳያስተውለው በሕዝቡ መሐል ወደ ውሃው ጫፍ ሄዶ " ጃኮፖ ! ጃኮፖ ! " ሲል ተጣራ ።

አንዲት ታንኳ ቀርባ ተቀበለችውና በረቀቀ ጥበብ ወደተሠራችው ውብ የቅንጦት ባርካ ወሰደችው ። ባርካዋ ላይ በጠንካራው የመርከበኛ ጉልበት ዘሎ ከወጣ በኋላ በደስታ ዙሪያውን ከከበበው ሕዝብ ጋር እየተጨባበጠ ባለውለታውን ከሰማይ ያገኘው ይመስል አንጋጦ የሚመለከተውን ሞሬልን ለመጨረሻ ጊዜ ተመለከተው ።

" ከእንግዲህ ወዲያ " አለ በቅንጦት ባርካዋ የተቀመጠው ሰው ፊቱን ክስክስ አድርጎ ። " ደግነት ፣ ርህራሄና ፣ ባለውለታነት ደህና ሁኑ ፤ ልቤን በሃሴት የምታስፈነድቁ ስሜቶች ሁሉ ከአእምሮዬ ጥፉ ። ለበጎ አሳቢዎች ውለታ በመክፈል እንደረካህ ሁሉ የሸረኞችን ተንኮል ለመበቀል ደግሞ ልቤ ደንድንልኝ ! " እንዲህ ከተናገረ በኋላ ባርካዋ የባህሩን ጉዞ ተያያዘችው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደራሴው ንግግሩን ቀጠለ ። ዛሬ ከበዓሉ መከፈቻ ቀደም ብሎ በአ ደባባዩ ላይ የሞት ፍርድ ይፈጸማል ። አደባባዩን በደንብ የሚያሣይ መ ስኮት ያለበት ሆቴል እንዲይዝልኝ ትናንት ለባለሟሌ ነግሬዋለሁ ። ምናልባት ያንንም ሥነ ሥርዓት አብረን ልንመለከት እንችላለን ። ” እጁን ዘርግቶ መጥሪያውን ደወለ ።

ወዲያውኑ ዕድሜው አርባ አምስት ወይም አምሳ የሚሆን ሰው መጣ ። የእንደራሴው ልዩ ባለሟል ነበር ።

“ ቤርቱሲዮ ” አለ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ፤ “ አደባባዩን የሚ ያሣይ መስኮት ያለበትን ክፍል አገኘህ ? ”

“ አዎ ጌታዬ ” ሲል መለሰ ቤርቱሲዮ ፤ “ ሦስተኛ ፎቅ ላይ አግኝ ቻለሁ ። ”

“ በጣም ጥሩ ቤርቱሲዮ ፤ በል ምሣ እንደደረሰ አስታውቀን ። ወን ድሞቼ ምሳ አብረን እንድንበላ ልትችገሩልኝ ትችላላችሁ ? ”

“ ባናስቸግር እንመርጣለን ፤ ክቡር እንደራሴ ” አለ አልበርት ።

“ ምን ችግር አለው ? ባይሆን ውለታዬን አንድ ቀን ፓሪስ ላይ ትመልሳላችሁ ። ቤርቱሲዮ ፤ ማዕድ ለሦስት ሰው ይዘጋጅ ። ”

ቤርቱሲዮ እንደወጣ እንደራሴው የሞት ቅጣቱ የሚፈጸምበትን ፕሮግራም ከማስታወሻ ላይ ያነብላቸው ጀመር ። በቅጣቱ መሠረት አንድሪያ የተባለ ወንጀለኛ በስለት እንዲገደል ፤ ፔፒኖ የተባለ ደግሞ እንዲሰቀል ተፈርዶባቸዋል ።

“ ግን ” አለ እንደራሴው ማንበቡን እንደጨረሰ ፤ “ ትናንት ማታ በመስፍኑ ቤት ውስጥ ነበርኩ ፤ ከሁለቱ አንደኛው እሥረኛ ወ ሣኔው እንደተሻረለት አረጋግጫለሁ ። ”

“ የትኛው ? ” ሲል ጠየቀ ፍራንዝ ።

“ ፔፒኖ የተባለው ” ሲል መለሰ እንደራሴው ፤ “ ያ ማለት የስቅ ላት ፍርድ ሲፈጸም ለማዩት አልታደላችሁም ማለት ነው ። ይሁን እ ንጅ የስለት ቅጣቱ በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለተመለከተው በጣም የ ሚማርክ ትዕይንት ነው ። ስቅላት በጣም ቀላል ነገር ነው ፤ ምንም አዲስ ነገር አይታይበትም ። ይገርማችኋል . . . ስቅላትንና ግርፋትን በሚመ ለከት አውሮፓውያን ምንም አያውቁም ። ” በማለት እንደራሴው ከንፈ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮቹን በሽሙጥ ወደአንድ ጐን አጣመመ ። “ ስለጭካኔ ሲወሳ አውሮፓውያን በሕፃንነት ወይም ደግሞ በአዛውንት ዕድሜ ክልል ላይ ያሉ ይመስላል ። ”

“ በመላው ዓለም እየተዘዋወሩ በቅጣት አይነቶች ላይ ዝርዝር ጥናት ያካሄዱ ይመስላሉ ፤ ጌታዬ ” በማለት ተናገረ ፍራንዝ የእንደራሴው አነጋገር እንግዳ ሆኖበት ።

“ ያላየሁዋቸው የቅጣት አይነቶች ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ። ” ነበር እንደራሴው ቀዝቀዝ ብሎ የሰጠው መልስ ።

“ እንደዚህ አይነቶቹን አሰቃቂ ድርጊቶች መመልከት ያስደስትዎታል ? ”

“ መጀመሪያ በርግጥ ይረብሸኝ ነበር ። በኋላ ግን ግድየለሽ ሆንኩ። አሁን እንዲያውም ሱስ ይዞኛል ። ”

“ ሱስ ! ለመናገር ቀርቶ ለመስማት የሚቀፍ ቃል ነው ። ” አል በርት ነበር ።

“ ይገርማችኋል በሕይወት ውስጥ ትልቁ ትርኢት አሟሟትን መመልከት ነው ። ነፍስ ከሥጋ የምትነጠልባቸውን የተለያዩ መንገዶች ማጥናትና የተለያዩ ግለሰቦች በግል ባህርያቸው ወይም በአካባቢያቸው ወግ አማካኝነት ይህን ከሕይወት ወደሞት ፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የሚደረግ ሽግግር እንዴት እንደሚፈጽሙ ማስተዋል ጠቃሚ አይደለም ‘ትላላችሁ ? በበኩሌ ግን አንድ ነገር ልጠቁማችሁ እወዳለሁ ፤ አንድ ሰው ሌሎች ሲሞቱ አዘውትሮ የሚመለከት ከሆነ ራሱ ሞትን ለመጋፈጥ ደፋር ሰው ይሆናል ። እንደእኔ አስተሳሰብ ሞት የሚያስጨንቅ ነገር ቢሆንም ብዙዎች የሚፈሩትን ያህል የሚፈራ አይደለም ። ፍርድ የሚበይነው ቅጣትም የተፈፀመ ወንጀልን ያህል አይከብድም ። ”

“ግልጽ አልሆነልኝም ። ” አለ ፍራንዝ በተመስጦ ሲያሰላስል ቆይቶ ፤ “እባክዎ በደንብ ያብራሩልኝ ፣ ስሜቴን እጅግ ኮረኮሩት ። ”

“ እንግዲያውስ እንደማመጥ ” አለ እንደራሴው ። “ ለምሳሌ አንድ ሰው አባትህን አሰቃይቶ ቢገድልብህ ፣ ወይም እጮኛህን በግፍ ቢነጥቅህ፣ አለዚያም የአንተን የወደፊት ብሩህ ዕድል ቢያጨልምብህ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

# 21

የሞት ቅጣት በሚፈጸምበት አደባባይ የሮም ከተማ ዓመታዊ ፌስቲቫል እንደተጀመረ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ከሁለቱ ወጣቶች ጋር በመሆን እንደሌላው ሕዝብ በትርኢቱ ለመሳተፍ በሠረገላ ከአደባባዩ ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው ጥቂት እንደተጓዙ ኢንደራሴው ወጣቶቹን ፈቃድ በመጠየቅ ሊለያቸው እንደሚፈልግ ገለጸላቸው ። " ወንድሞቼ " አለ ከሠረገላው እንደወረደ ። " አደባባዩን መዞር ሲደክማችሁና ትርኢቱን በተመልካችነት ለመከታተል ስትፈልጉ ፎቅ ላይ ያለውን ክፍሌን ልትጠቀሙ ትችላላችሁ ። ሠረገላዬንና ሾፌሩንም እንደፈለጋችሁ ልታዝዙ ፈቅጄላችኋለሁ ። "

ፍራንዝ እንደራሴውን ከልብ አመስግኖ ሁለቱ ወጣቶች አደባባዩን መዞር ቀጠሉ ።

" ታያለህ ? " አለ የእንደራሴውን መውረድ ያስተዋለው አልበርት ከጓደኛው ጋር የሚስጥር ጭውውት ማድረግ እንደሚችሉ ተረድቶ።

" ምኑን ? " ሲል ጠየቀ ፍራንዝ ።

" ተመልከት ፣ እዚያ ሠረገላ ላይ የሚታዩት ቆንጃጅት ! "

" ጣሊያን አገር አንድ ድል ሳትቀዳጅ መሄድ የለብህም " አለ ፍራንዝ ' ከቆንጃጅቱ አንዷን ተዋወቅ ' የሚል አስተያየት ባዘለ አነጋገር ።

" አዎ ፣ " አለ አልበርት ፣ " በሞት ቅጣቱ የተሸማቀቀው ሰውነቴ አሁን በደንብ እንዲካስ ማድረግ አለብኝ ። " እንዲህ እንዳለ አልበርት ወደ ቆንጃጅቱ ሠረገላ አንድ የታሸገ የሽቶ ጠርሙስ ወረወረ ። ይህንን ያስተዋለችው አንዲት ውብ ሴት ብዙም ሳትቆይ ወደ አልበርት የሚያማምሩ አበቦች መልሳ ወረወረች ። አልበርት ከአበቦቹ መካከል ብዙዎቹን ከአየር ላይ ከቀለባቸው በኋላ በኩራት በኮቱ ቁልፍ አገዛሩ ላይ ሰካቸው ። አንድ ጊዜ የነአልበርት ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የቆንጃጅቱ ሠረገላ እየቀደሙ አደባባዩን መዞራቸውን ቀጠሉ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ቢላ እንግዲህ ” አለ ፍራንዝ አበቦቹን እያስተዋለ ። “ መድረኩ የተከፈተ ይመስላል ። ” ልጅቷ ፈቃደኝነቷን ስለገለጸችልህ ግፋበት ለማለት የቀረበ አባባል ነበር ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሠረገላቸው ፍጥነቱን ጨምሮ የቆነጃጅቱን ሠረገላ መቅደም እንደጀመረ የወረወረቻቸው አባቦች በአልበርትኮት ቁልፍ አዝራር ላይ እንደተሰኩ የተመለከተችው ኮረዳ እጆችዋን በማጨብጨብ ፈገግ ስትል አልበርት ተመለከታት ።

በማግሥቱ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ራሱ ወደ ወጣቶቹ ክፍል በመሄድ ፤ “ ወንድሞቼ ፤ የመጣሁት ካሁን ጀምር በዓሉ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ ሠረገላዩን እንደፈቀድኩላችሁ ለመግለጽ ነው ። ” በማለት ገለጸላቸው ።

ሁለቱ ወጣቶች ጥቂት ከተግደረደሩ በኋላ በሠረገላው ለመጠቀም ፍቃደኞች ሆኑ ። እንደራሴው ለሩብ ሰዓት ያህል የተለያዩ ጉዳዮችን ሲያጫውታቸው ቆየ ። አነጋገሩ ከሁሉም አገሮች ሥነጽሁፍ ጋር በደንብ እንደሚተዋወቅ ይመሰክራል ። በሥነጥበብ በኩልም ጥልቅ እውቀት እንዳለው አልበርትና ፍራንዝ የቤቱን ግድግዳ ተመልክተው አረጋግጠዋል ። በውይይታቸው ወቅት እንደራሴው የሚወረውራቸው ቃላት በሣይንስ መስክ ሰፊ ግንዛቤ እንዳለው ይመሰክራሉ ። በተለይ ኬሚስትሪን በሚመለከት ከፍተኛ ጥናት ሳያደርግ የቀረ አይመስልም ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፍራንዝና አልበርት ወደሠረገላቸው ሄዱ ። አልበርት ትናንት የተወረወሩለትን አበቦች ሆን ብሎ አሁንም በቁልፉ አዝራር ላይ አስቀመጣቸው ።

አደባባዩ ውስጥ እንደገቡ አልበርት የቆነጃጅቱን ሠረገላ ሲያይ አበባዎቹን ከኮቱ በማንሳት ወደ ከንፈሮቹ አስጠጋቸው ። አበባዎቹን የወረወረችው ኮረዳ ዛሬም ሌሎች አበቦችን አከታትላ ወረወረችለት። በዚህ ሁኔታ ሁለተኛው ቀን አለፈ ።

በሶስተኛው ቀን ፍራንዝ የተለዩ ጥሪ ስለነበረበት ከጓደኛው ጋር በአደባባዩ ሲዞር ለመዋል አልቻለም ። ሁለቱ ጓደኞች ማታ በመኝታ ክፍላቸው ለመገናኘት ተቀጣጥረው ተለያዩ ። በዚህም መሠረት አልበርት በዚያ ዕለት ብቻውን በሠረገላ ውስጥ ለመቀመጥ ተገዶ ነበር የዋለው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ልቦ የቀረበለትን ራት ተመገበ ። አልበርት ሊቆይ እንደሚችል ስለነ ገረው እስኪመለስ መጠበቅ አልነበረበትም ።

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ፍራንዝ ብንን ሲልም አልበርት አል ተመለሰም ። ወዲያውኑ ግን የሆቴሉ ሠራተኛ ወደ ክፍሉ ገበቶ “ ጌታ ዬ ፣ ከአልበርት የተላከ ደብዳቤ የያዘ ሰው ሆቴሉ በረንዳ ላይ ይጠብቅ ዎታል ! ” አለው ።

ፍራንዝ ጊዜ ሳያባክን ወደ በረንዳው ወጣ ። በእርግጥም አንድ ሰው ቆሟል ። ፍራንዝ ከአልበርት የተላከው ሰው እሱ ለመሆኑ ጥርጣሬ አል ነበረውም ። ሲያነጋግረው ጠጋ ከማለቱ ሰውየው ቀልጠፍ ብሎ ፤ “ ከእኔ ምን ትፈልጋለህ ? ” ሲል ጠየቀ ወደኋላው በማፈግፈግ።

“ ከአልበርት ደብዳቤ ያመጣኸው አንተ አይደለህም እንዴ ? ” ሲል ጠየቀ ፍራንዝ ።

“ ስምህ ማነው ? ” በማለት ጠየቀ መልዕክተኛው ።

“ ፍራንዝ ። ”

“ ደብዳቤው የተላከው ላንተ ነው ። ”

“ መልስ ያስፈልገዋል ? ” ሲል ጠየቀ ፍራንዝ ደብዳቤውን እየ ተቀበለ ።

“ አዎ ፣ ጓደኛህ መልስ እንደምትሰጥ ተስፋ ያደርጋል ። ”

“ ና ፣ ከእኔ ጋር እንግባና መልሱን እሰጥሃለሁ ። ”

“ የለም ፣ እዚሁ መቆዬትን እመርጣለሁ ። ” አለ መልእክተኛው እየሳቀ ።

“ ለምን ? ”

“ ምክንያቱን ደብዳቤውን ስታነብ ትረዳዋለህ ። ”

ፍራንዝ በፍጥነት ወደክፍሉ እንደገባ ደብዳቤውን ገልጦ ያነብ ጀመር ።

<u>ውድ ፍራንዝ</u> — ይህንን ደብዳቤ እንዳነበብህ በጠረጴዛዬ መሣቢያ ከሚ ገኘው ቦርሣዬ ውስጥ የፈረምኩበት ቼክ ታገኛለህ ። ወደ ባንክ ሄደህ አርባ ሺህ ፍራንክ ካወጣህ በኋላ ይህንን ደብዳቤ ለሰጠህ ሰው ስጥልኝ ። የእኔ የባንክ ገንዘብ በቂ ካልሆነ ከራህስ ጨምርበት ። በአስቸኳይ ገንዘቡን ማግኘት ስላለብኝ ቸል እንዳትል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላ የምለው የለኝም ። ያለሁህ እኔ እንደመሆኔ ለእኔም ያለኸኝ አንተ ነህ ።

ሉልበርት

ከእነዚህ ቃላት በታች ደግሞ በሌላ ዓይነት የእጅ ጽሁፍ የሚከተለው ተጽፏል ።

የተጠቀሰው ገንዘብ ልክ ከቢቱ ለሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ካልደረሰለት ሉልበርት የተባለውን ጓደኛህን በሕይወት አታገኘውም ።

ሉዊጊ ቫምፓ ።

ሁለተኛው መልእክትና ፊርማ ሚሥጥሩን ከመገላለጡም በላይ መልእክተኛው ለምን ሆቴሉ ውስጥ እንዳልገባ ያስረዳል ። አልበርት በመላው አውሮፓ በዝና በሚታወቀው ሉዊጊ ቫምፓ በተባለው የኢጣሊያ ሽፍታ እጅ ወድቋል ።

የሚባክን ጊዜ አልነበረም ። ፍራንዝ ወደ አልበርት ጠረጴዛ ሮጦ ከሄደ በኋላ ከመሣቢያ ቦርሣውን አውጥቶ ቼኩን ሲመለከት አልበርት የነበረው ስድሳ ሺህ ፍራንክ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ግማሹን አጥፍቶለታል ። ፍራንዝ ራሱ የባንክ ተቀማጭ አልነበረውም ። ወደ አሥር ሺህ ፍራንክ የሚደርስ ገንዘብ ያስፈልገዋል ። ጥቂት እንዳሰበ የምንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ትዝ አለው ። በዚያ ቅጽበት ፓስቲሪኒ ወደ ክፍሉ ገባ ።

“ ፓስቲሪኒ ! ” አለ ፍራንዝ ተቻኩሎ ፤ “ እንደራሲው ክፍላቸው ውስጥ መኖራቸውን ታውቃለህ ? ”

“ አዎ ጌታዬ ፤ አሁን ሲገቡ አይቻቸዋለሁ ። ”

“ እንግዲያውስ እስኪ እባክህ ላነጋግራቸው እችል እንደሁ ጠይቅልኝ ? ”

ፓስቲሪኒ በፍጥነት ወደ እንደራሴው መኖሪያ ከሄደ በኋላ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ተመለሰ ። “ እንደራሴው ይጠብቁሃል ። ” አለ።

እንደራሴው ፍራንዝ ከዚህ በፊት አይቶት በማያውቀውና ዙሪያውን ባርጩማዎች በሞሉት ትንሽ ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ነበር ።

“ ምን የተመረቀ ነፋስ በዚህ ሰዓት እዚህ ሥፍራ ጣለህ እባክህ ?” አለ እንደራሴው ፤ “ ራት ልትጋብዘኝ ፈልገህ ከሆነ በደስታ እቀበላለሁ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እሽ " አለ ፔፒኖ ፣ " ይጠይቁኝና ልመልሳ . . . ? "

" አልበርት እንዴት ነው በሉዊጊ ቫምፓ እጅ የወደቀው ? "

" ጌታዬ ፣ የፈረንሳዊው ሠረገላ በተደጋጋሚ የእመቤት ቴሬዛን ሠረገላ ይከታተል ነበር ። "

" ቴሬዛ ማለት የሉዊጊ ቫምፓ ባለቤት ? "

" አዎ ፣ በወቅቱ ባለቤቷም አብረው ነበሩ ፣ ፈረንሣዊው አይኑን በሷ ላይ ሲጥል ባልና ሚስት ከፈረንሣዊው ጋር አበባ በመወራወር ይቀልዱ ነበር ። "

" ምን ? " አለ ፍራንዝ ። " ሉዊጊ ቫምፓ ራሱ እዚያ ሠረገላ ውስጥ ነበረ ? "

"ራሳቸውን ሾፌር አስመስለው ይነዱ ነበር ።" ሲል መለሰ ፔፒኖ፣ " ታዲያ በእሳቸውና በቴሬሳ ምክክር ለፈረንሣዊው የቀጠሮ ደብዳቤ ተወረወረለት ። ነገር ግን በቀጠሮው ቦታ ጊያኮሞ ቤተክርስቲያን ለፈረንሣዊው ቀጠሮ የተሳከችው ቴሬዛ ሳትሆን ቤፓ የተባለው ወጠምሻ ነበር ። "

" ምን ? " አለ ፍራንዝ እንደገና ፤ " ሻማውን የነጠቀችው የሮም ገበሬ ልብስ የለበሰች ሴት . . . . . "

" የአሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ነበር ። " አለ ፔፒኖ ቀበል አድርጎ ። " ሆኖም ጓደኛህ ይህን ያህል ሃፍረት እንዲሰማው አያስፈልግም ። ቤፓ የምልህ ልጅ ሌሎችንም ማርኮ ወስዷል ። "

" ታዲያ ቤፓ ከከተማ ውጭ ወሰደው ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው ጣልቃ ገብቶ ።

" አዎ ጌታዬ ! " በማለት ፔፒኖ በመጀመሪያ ቤፓ አልበርትን እንዴት ልጃገረድ መስሎ እንደወሰደውና በመጨረሻ ግን ከከተማ ውጭ ሲደርሱ ሽጉጥ ግንባሩ ላይ እንደደቀነበት ፣ አልበርት ራሱን ለመከላከል በመሞከር ላይ እንዳለ ሌሎች የቤፓ ጓዶች መድረሳቸውንና ተባብረው አልበርትን ቴሬሳና ሉዊጊ ቫምፓ ወደሚገኙበት ምሽግ መውሰዳቸውን አብራራ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ልክ የዛሬ ሶስት ወር ፈረንሣይ መጥተው በሬን ያንኳኳሉ ?" ሲል ጠየቀ አልበርት ፤ የቀጠሮው ርዝማኔ እያሳቀው ።

" ቀኑንና ሰዓቱን መወሰን ትፈልጋለህ ? በበኩሌ የተመሰከረ ልኝ ቀጠሮ አክባሪ መሆኔን ላስጠነቅቅህ እወዳለሁ ። "

" ቀኑንና ሰዓቱን እንወስን ። " አለ አልበርት ፤ " በጣም ደስ ይለኛል ። "

"ጥሩ ፤ እንግዲህ አሁን የካቲት ሃያ አንድ ቀን ከጧቱ አራት ሰዓት ተኩል ነው ። ግንቦት ሃያ አንድ ቀን ልክ ከጧቱ አራት ሰዓት ተኩል ይመችሃል ?"

" ምጣ አዘጋጅቼ እጠባበቃለሁ ።"

" በል አድራሻህን ስጠኝ ? "

" አልበርት የመኖሪያ ቤቱን አድራሻ ሰጠ ። እንደራሴው አድራ ሻውን በማስታወሻው ካሰፈረ በኋላ በዚያው አጋጣሚ ኔፕልስ ወደተባ ለችው የኢጣሊያ ከተማ የሚሄድበት ጉዳይ እንዳለው ለወጣቶቹ ነገር የሶስት ወር ሰንብት አደረጉ ።

ፍራንዝ የእንደራሴውን እጅ ሲጨብጥ ይህ የመጀመሪያው ነበር። የእንደራሴው እጅ እንደሬሳ ሰውነት ስለቀዘቀዘው ሰውነቱ ሽምቅቅ አለ ።

አልበርትና የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ የቀጠሮአቸውን ቀንና ሰዓት በድጋሚ ከተነጋገሩ በኋላ ሁለቱ ወጣቶች እጅ ነስተው ወጡ ።

" ምን ነካህ ?" አለ አልበርት ፍራንዝን ወደ ክፍላቸው በመግባት ላይ እንዳሉ ፤ " የተሸበርክ ትመስላለህ ።"

" አዎ በጣም እንጅ ፤ " አለ ፍራንዝ ፤ " እንደራሴው ግራ የሚያ ጋቡ አይነት ሰው ናቸው ። የፓሪሱ ቀጠሮአቸው አስጨንቆኛል ። "

" ምን ? አብደሃል ?"

"አበድኩም አላበድኩ አስጨንቆኛል ። ባዩሁዋቸው ቁጥር ሆዴ ን ብራሽ ብራሽ ይለኛል ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

# 22

ግንቦት ሃያ አንድ ቀን ጧት ለሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ጥሪ ባደ ረገበት ቤቱ ውስጥ አልበርት እንግዳውን ለመቀበል ዝግጅቱን ማጠ ናቀቅ ጀመረ ።

አልበርት ከወላጆቹ ከቤተና ጄኔራል ሞርስፍና ከእናቱ ጋር ባንድ ግቢ ውስጥ ይኖራል ። ይሁን እንጂ እመቤት ሞርስፍ የምትወደው ልጅዋ ከአጠገቧ እንዳይርቅ ብታደርግም የአንድ ወጣት ወንደላጤን ነጻነት ልትነፍገው ስላልፈለገች ቤቱን ስታሰራለት የመግቢያው በር ከቅጥር ግቢው ወደ ውጭ ስለተደረገለት የራሱ ግለኝነት ይሰማው ነበር ።

አልበርት ጧት ምድር ቤት ላይ ባለው ሳሎኑ እንደተቀመጠ የቤት ሠራተኛው የተለያዩ ጋዜጦችን ካመጣለት በኋላ፤ "ምሣ በስንት ሰዓት ነው እንዲቀርብ ያዘዙት ጌታዬ ?" ሲል ጠየቀው ።

" ልክ በአራት ሰዓት ተኩል ። በእንደራሴው ቀጠሮ እንኳ ሙሉ እምነት የለኝም ፤ ሆኖም ቀጠሮው በእኔ መፍረስ የለበትም።"

አራት ሰዓት አካባቢ ጥሪ የተደረገላቸው የአልበርት ጓደኞች መድረስ ጀመሩ ። በመጀመሪያ የመጣው ደብራይ የተባለው የአ ገር አስተዳደር ሚኒስትር ዋና ጸሐፊ ነበር ፤ ቀጥሎም ቡቻምፕ የተ ባለው እውቅ የፈረንሣይ ጋዜጠኛ ገባ ።

" ሬናውድና ማክሲሚሊን ሞረል መጥተዋል ። " አለ አስተና ጋጁ ።

"ማክሲሚሊን ሞረል . . . " አለ አልበርት ግራ ተጋብቶ፤ "ማነው ደግሞ ማክሲሚሊን ?"

ግን አልበርት ንግግሩን ገና ሳይጨርስ ሬናውድ ከተባለው እን ግዳ ጋር እጅግ ረጋ ያለ ወጣት ገባ ። ሬናውድ ሰላምታውን ከተለዋወጠ በኋላ ፤ " ሻለቃ ማክሲሚለን ሞረልን ላስተዋውቃችሁ ፤ የልብ ጓደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኛዬና ከሁሉም በላይ ሕይወቴን ያተረፈ ጀግና ነው ። ” በማለት እንግዳውን መኮንን ያስተዋውቅ ጀመር ። ይኸው እንግዳ ቁመቱ ረጅም ከመሆኑም በላይ ሰፋ ባለው ደረቱ ላይ የጅብዱ ሜዳይ የተንጠለጠለበት ማራኪ የወታደር ዩኒፎርም ለብሷል ።

“ የሬናውድ የልብ ጓደኛ የእኔም ነው ። ” አለ አልበርት የማክሲሚለንን እጅ እየጨበጠ ።

“ አዎ ፤ ምናልባት ደግሞ አንድ ቀን ለእኔ ያደረገልኝን ለአንተም ያደርግልህ ይሆናል ። ” አለ ሬናውድ

“ ላንተ ምን አደረገልህ ?” ሲል ጠየቀ አልበርት ።

ሬናውድ ታሪኩን ያጫውታቸው ጀመር ። ሬናውድ ባንድ ወቅት ወደ አፍሪካ በተደረገ ዘመቻ ተካፍሎ ነበር ። አንድ ውግያ ላይ አረቦች በፈጸሙት ጥቃት ፈረንሣዮች መሸሽ ሲጀምሩ የሬናውድን አንገት ሁለት አረቦች ሊቀንጥሱ ረጅም ጸጉሩን ጨምድደው እንደያዙ ማክሲሚለን ምረል አከታትሎ በመተኮስ ይጥላቸዋል ። “ ይገርማችኋል ” አለ ሬናውድ ገለጻውን ሲያገባድድ ። “ በዚያ ቀን ሻምበል ማክሲሚለን ከምሽጉ የተነሣው ጠላቶቹን ለማሳደድ ብቻ ሳይሆን የሰው ሕይወት ለማዳንም ጭምር ነበር ፤በአጋጣሚ የሚያድነው ሰው እኔ ሆንኩ ።”

“ አዎ” አለ ማክሲሚለን ቀበል አድርጐ ። “ ዕለቱ መስከረም አምስት ቀን ነበረ ። ያ ዕለት አባቴ በአንድ ባልታወቀ ተዓምር ከሞት የተረፈበት እለት ስለነበር በየዓመቱ እኔም የሰው ሕይወት በማትረፍ ሳከብረው ቆይቻለሁ ።”

“ ይህን የአባቱን ታሪክ ብትሰሙት ደግሞ እጅግ ይገርማችኋል ። ግን አሁን የምግብ ሰዓት ነው ። ስንት ሰዓት ላይ ነው ምሣ የሚቀርብ ልን አልበርት ?” ሲል ጠየቀ ሬናውድ ።

“ በአራት ተኩል ። ”

“ ልክ በአራት ተኩል ?” ሲል ጠየቀ የአገር አስተዳደር ሚኒስቴሩ ዋና ጸሐፊ ደብራይ ሰዓቱን እየተመለከተ ።

“ አምስት ደቂቃ ያህል ትታገሱኛላችሁ ፤ ” አለ አልበርት ፤ “ምክንያቱም እኔም ሕይወቴን ያተረፈኝን ሰው እየተጠባበቅሁ ነው።”

“ የማንን ሕይወት ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ከምላ ጐደል ። ”

“ የእንቅልፍ መድኃኒት ይጠቀማሉ ? ”

“ አልፎ አልፎ ። ”

“ መድኃኒቱን ሲንግሩን ይችላሉ ? ” ሲል ጠየቀ የሚኒስትሩ ጸሐፊ ።

“ እንዴታ ! ” ካለ በኋላ እንደራሴው መድኃኒቱ እንዴት እንደሚቀመም አስረዳቸው ።

“ ግን ” አለ ጋዜጠኛው ፤ “ ሁል ጊዜም መድኃኒቱን ከኪስዎ አይለዩትም ? ”

“ ምንጊዜም ከኪሴ አይጠፋም ። ”

እንደራሴው የመድሃኒቱን እንክብሎች እንዲያሣያቸው ሁሉም ስለጠየቁት ከኪሱ ውስጥ አንድ ወጥ ከሆነ እንቁ ተቦርቡሮ የተሠራ የመድሃኒት ሙያግ ነገር አውጥቶ ስድስት ያህል ሰማያዊ ቀለም ያላቸው አተር የሚያካክሉ እንክብሎችን አሳያቸው ። በደንብ እንዲያዩትም ከነ መያዣው እየተቀባበሉ እንዲያሆሩት ፈቀደላቸው ።

እንግዶቹ ግን ከመድሃኒቱ ይልቅ ይበልጥ ያስገረማቸውና አፋቸውን እንደከፈቱ ያስቀራቸው መያዣው ነበር ።

“ በጣም የሚያስገርምና ካየሁዋቸው የእንቁ መያዣዎች ሁሉ ትልቁ ይህ ነው ። ” አለ አንደኛው ።

“ እንዲህ ያሉ ሶስት መያዣዎች ነበሩኝ ። ” አለ እንደራሴው ፤ “ አንደኛውን ለኢጣሊያ ንጉሥ ሰጥቻቸው በጦራቸው ጫፍ ላይ ሰክተውት ይገኛል ። ሁለተኛው ደግሞ ለብፁዕነታቸው ለጳጳሱ አበርክቻላቸው በአክሊላቸው ላይ እንደኔው ባያምርም ለበፊቱ ጳጳስ ከንጉሥ ናፖሊዮን ተሰጥቶ ከነበረው ሌላ እንቁ ጋር አድርገውታል።ይህንን ሶስኛውን ደግሞ በእውቅ አስቦርቡሬ ለራሴ አደረግሁት ። ሲቦረቦር ግማሹ ያህል ቢወጣለትም ለምፈልገው ጥቅም በመዋሉ ደስ ብሎኛል ።”

እንግዶችና አልበርት እንደራሴውን በአድናቆት ተመለከቱት ። አነጋገሩ ያለመጨነቅ በመሆኑ ንግግሩ እውነት ነው ወይም ሰውዬው አብድ ነው ከሚል ጥርጣሬ ላይ ይጥላል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ስንነጋገር የቆየነው ። በሉ ጉበዝ እኒህን አዲስ የፓሪስ እንግዳ የት እናግርፋቸው ?”

በዚህ ንግግር መንስኤነት በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ሠፈሮች ሁሉ እየተጠቀሱ ለውይይት ቀርበው እንግዳውን በምቾት ለማሳረፍ ይችሉ እንደሁ ያነጋግሩ ጀመር ።

“ አንተስ ማክሲሚለን ፤” አለ ሬናውድ ፤ “ በዚህ ጉዳይ ላይ የምትለው የለህም ?”

“እረ አለኝ” አለ ወጣቱ ሻለቃ ፈገግ ብሎ ፤ “እንደራሴው ካቀ ረባችሁላቸው አካባቢዎች ሁሉ እንዱን ይመርጡ ይሆናል ብዬ ስጠ ባበቅ ነበር ። ግን እስካሁን ባለመርካታቸው እኔ በበኩሌ እህቴ ባለ ፈው ዓመት ተከራይታው የነበረውን ቤት እጠቁማቸዋለሁ ።”

“ እህት አለችህ ?” ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

“ አዎ ። ”

“ አግብታለች ?”

“ ዘጠኝ ዓመት በትዳር ቆይታለች ። ”

“ ደስተኛ ነች ?”

“ ወሰን የሌለው የደስታ ኑሮ ትመራለች ። የምታፈቅረውንና በች ግራችን ጊዜ እንኳ ከአጠገባችን ያልተለየውን አማኑኤል ኸርባውት የተባለ ሰው አገባች ።እኔም እረፍት ሳገኝ ከእነሱ ጋር ነው የምኖረው። እኔና የእህቴ ባል ለሚያስፈልግዎ ሁሉ አለንልዎ ። ”

“ አመሰግናለሁ ሻለቃዬ ። ፍላጐቱ ካለህ ላስቸግርህ የምፈልገው ከእህትህና ከባሏ ጋር እንድታስተዋውቀኝ ብቻ ነው ። ስለቤት አንስ ታችሁ ሁላችሁም ያቀረባችኋቸውን አማራጮች ያልተቀበልኩበት ምክንያት ግን ሠራተኛዬን ከእኔ አስቀድሜ ከሮም ወደዚህ በመላክ ቤት ገዝቶ እንዲቆዩኝ ስላዘዝኩት ነው ። እስካሁን እንዲያውም የቤት እቃውን እንኳ ሳይቀር አሟልቶ እንደሚጠብቀኝ አምናለሁ ። ”

“ ያ ከሆነ ሠራተኛዎ ፓሪስን ያውቃታል ማለት ነው ። ” አለ ጋዜጠኛው ቡቻምፕ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ችሁ እንዴት በባርነት ገዝተዋት የነበረች የቆንጆዎች ቆንጆ ሸጡልኝ ለማለት ፈልጌ ነበር ።"

"ግን አንድ የረሱት ነገር አለ" አለ የሚኒስትሩ ጸሐፊ እየሣቀ ፣ "የተሸጠችልዎን ሴት በባርነት መያዝ የሚችሉትበገ ዘብት አገር ብቻ በመሆኑ ልክ የፈረንሣይን ምድር ስትረግጥ ነጻነቷ የተጠበቀ ነው ።"

"ፈረንሳይ ትሁን ማሌያን ግን ይነግራታል ?" ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

"መጀመሪያ የምታገኘው ፈረንሣዊ ነዋ !"

"በምን ቋንቋ ? እሷ እንደሆነች አንዱንም የአውሮፓ ቋንቋ አት ሰማም ። "

"እሃ ፣ እዚህ ላይ አገኙኝ" አለ የሚኒስትሩ ጸሐፊ ።

"ልናያት እንችላለን ?" ሲል ጠየቀ ጋዜጠኛው ፣ "ወይስ እን ደሷ ዓይነት ዱዳ እመቤት ከለችዎ ስልብስ ቤትዎ ውስጥ አይገኝም ?"

"የለም ፣ ያን ያህል ወግ አጥባቂ አይደለሁም ።" አለ እንደራ ሴው ፣ "ሴትን በጠባቂ የማኖር ፍላጐት ሊኖረኝ አይችልም ። ሁሉም የቤቱ ሰዎች ነጻነታቸው የተጠበቀ ነው ። ከፈለጉ ቤቱን ትተው ለመሄድ ይችላሉ ። እንዲያውም ያ ነጻነት ይመስለኛል ከቤቱ እን ዳይወጡ ሕሊናቸውን ተብትቦ የሚያስቀራቸው ።"

በዚህ ሁኔታ ጨዋታው ሞቅ ብሎ ከቆየ በኋላ ወጣቶቹ አንድ ባንድ እየተሰናበቱ መውጣት ጀመሩ ። ጋዜጠኛው ቡቻምፕ ከበሩ ሲወጣ አልበርትን በጥቅሻ እንዲከተለው ካደረገ በኋላ "ዛሬ ወደ ምክር ቤት የምሄድ አይመስለኝም ።ስለ እንደራሴው እንግዳህ በጋ ዜጣዬ ማስፈር አለብኝ ።" አለው ።

"በጋዜጣ ከሚገልጹት በላይ ነው ።" አለ ሬናውድ ፣ "እስካሁን ካየሁዋቸው ልዩ ሰዎች የበለጠ ሰው ነው ።"

"ልክ ለእንደራሴው አድራሻዬን እንደሰጠሁዋቸው ቤቱን ለማዩት እንደሚፈቅዱ ገለጹልኝ ።" አለ ማክሲሚለን ሞረል በኩራት።

በመጨረሻም እንደራሴውና አልበርት ብቻ ቀሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብትዎ ታላቅነት ሊኩራሩ ሲገባዎ በውትድርና ዓለም ተሰልፈው አገርዎን ማገልገልዎና ከዚያም በጄኔራልነት ማዕረግ ከደረሱ ፤ የፈረንሣይ እውቅ የጦር መሪ ከሆኑና የክብር ሜዳይ ከተሸለሙ በኋላ ይህንን ሁሉ ከምንም ሳይቆጥሩ ወደ ሌላ ሙያ ማዘንበልዎ እጅግ የሚደንቅ ነው ። ”

አልበርት እንግዳው እንዲህ ያለ የአድናቆት አነጋገር ሲናገር ሰምቶት ስለማያውቅ በአትኩሮት ተመለከተው ።

“ አሰለችዎታለሁ ብዬ ባልሠጋ ኖሮ” አለ ሞርስፍ እንግዳው ባደረገለት የአድናቆት ንግግር ተደስቶ ፤ “ ከእኔ ጋር ወደ ምክር ቤት በወሰድኩዎ ነበር ። ከአገራችን ዓቃቤ ሕጎች ጋር ሳልተዋወቁ ሰዎች ዛሬ በምክር ቤቱ የሚደረገው ክርክር በጣም የሚስብ ነው ።”

“ ይህንን ግብዣዎን ሌላ ቀን ቢያደርሱት በደስታ እቀበለዋለሁ። ዛሬ ግን እመቤት ሞርስፍን ለመተዋወቅ የተሰጠኝ ዕድል እንዲያመልጠኝ ስለማልፈልግ እሣቸውን እጠብቃለሁ ።” አለ እንግዳው ።

“ ያው እንዲያውም መጣች” አለ አልበርት ። እንግዳው በፍጥነት ዞር ሲል ከሣሎኑ በር ላይ ቆማ ከነበረችው እመቤት ሞርስፍ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ ። እመቤት ሞርስፍ ፊቷ ከመገርጣቱም በላይ እንግዳው ወደሷ ዞር ብሎ ሲመለከታት በሚንቀጠቀጥ እጅዋ ይዛው የነበረው የሻይ ሲኒ እንዴት እንደሆነ ሳይታወቃት ከእጅዋ ላይ አምልጦ ተከሰከሰ ።

እንግዳው ጥቂት ወደፊት ራመድ ብሎ ለእመቤቷ ከአንገቱ ጐንበስ በማለት በአክብሮት እጅ ነሣ ። እርሷም እንደምንም አጸፋውን መለሰች ።

“ ምንድን ነው ነገሩ ?” አለ ሌተና ጄኔራል ሞርስፍ ፤ “ የሣሎኑ ሙቀት አልተስማማሽም ?”

“ አመመሽ . . . . እናቴ ?” አለ አልበርትም በበኩሉ ወደ እናቱ እየተንደረደረ ።

ሁለቱንም ፈገግ ብላ “ ደህና ነኝ” የሚል ዓይነት የጥቅሻ መልስ ከሰጠቻቸው በኋላ ፤ “ የእሣቸው ደግነት ባይኖር ኖሮ ቤታችን ይሄኔ ቤሐዘን ተውጦ ነበር በማለት እኚህን ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ስመለከት



t.me/OLDBOOKSPDF

ችን ላይ አባትህ በደንብ የተቀበለውና ያስተናገደው ይመስልሃል ? በጣም ሥራ ስለሚበዛበትና አንዳንድም ጊዜም የሚጨነቀው ለራሱ ጉዳይ ብቻ በመሆኑ ምናልባት ሳይታወቀው . . .”

“ እረረ . . . አባባ በአግባቡ ነበር የተቀበለው” አለ አልበርት ነጠቅ አድርጎ ።“ በዚያ ላይ እንግዳው ስለ አባባ ጀግንነትና ክብር እያሞገሰ ሲናገር ሰላሣ ዓመት የሚያውቀው ይመስል ነበር ። አባባም ደስ ብሎታል ። በጣም እንደሚዋደዱ ጓደኞች ሆነው ነበር የተለያዩት ።” አባባ እንዲያውም ወደ ምክር ቤት ሊወስደው ፈልጎ ነበር ።”

ከዚህ በኋላ እናት ምንም አልተናገረችም ። በራሷ ሃሳብ ከመመስጧ የተነሣ ማይታወቃት ቀስ በቀስ አይኖቿ ተከደኑ ። አልበርት ቆንጆና ወጣት እናቶቻቸውን በፍቅር አይን እንደሚያዩት ልጆች በአትኩሮት አስተዋላት ። ከዚያም እንቅልፍ እንደ ጣላት ገምቶ እንዳይቀሰቀሳት በእግሩ ጣቶች እየተራመደ ከክፍሉ ወጣና በሩን ዘጋው ። ሜርሲደስ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነበር ከተኛችበት ስመመን የባነነችው ። ከሮም ከረጅም ጊዜ በኋላ ነበር ከተኛችበት ስመመን የባነነችው ። ከሮም መልስ ልጅዋ እንደራቢው ስለብቀላ እንስቶ አጫውተኝ ያላት ቃል ትዝ ብሏት ደጋግማ አማተበች ። “ ለአይን አይን ፤ ለጥርስ ጥርስ !”



t.me/OLDBOOKSPDF

# 23

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ከአገልጋዮቹ ጋር በተቀጣጠረበት ቦታ ደርሶ እንዲገዙለት ያዘዘውን ቤት ባለንብረት ከተገናኘ በኋላ የግዢውን ውል በመፈረም የገንዘብ ክፍያውን ፈጸመ ። ቤቱ አውቴል በተባለው ከፓሪስ ወጣ ያለ ሠፈር ውስጥ ይገኛል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን እንደራሴው መሃል ከተማ ላይ ሌላ ቤት በመግዛቱ ይህን ቤት አልፎ አልፎ ንጹህ አየር ለመቀበል ብቻ ይጠቀምበት ጀመር።

" ሰማኸኝ ዎይ ቤርቱሲዮ " አለ እንደራሴው ቤቱን በገዛበት እለት ፤ በጣም የሚያቀርበውን አገልጋዩን ፤ " ባንድ ወቅት ፈረንሣይን ካሁን በፊት እንደምታውቃት አልነገርከኝም ? "

" አዎ ጌታዬ ፤ ግን ፈረንሣይን ዳር እስከ ዳር አላውቃትም ።"

" የፓሪስን ዳርቻስ ?"

" እረ የለም ጌታዬ ፤" በማለት ሲመልስ ቤርቱሲዮ ከሰውነቱ ሽምቅቅ በማለቱ አንድ ነገር እንዳስደነገጠው ለእንደራሴው ግልጽ ሆኖለት ነበር ።

" ያሳዝናል " አለ እንደራሴው ፤ " ምክንያቱም አሁን የገዛሁትን ቤት ዛሬ አመሻሽ ላይ ሄጄ ለማየት ስለፈለግሁ ስለሠፈሩ አንዳንድ መረጃዎችን ትሰጠኛለህ ብዬ ነበር ።"

" ስለ ሠፈሩ ?ስለአውቴል ?" ነሐስ የመሰለው የቤርቱሲዮ የፊት ቀለም በጭንቀት በርበሬመሰለ ። " ወደ አውቴል እንድገኄድ ይፈልጋሉ ?"

"ምን የሚያስደንቅ ነገር አለው?የቤተሰቢ አባል ነህ፣አይደለም?"

ቤርቱሲዮ በእንደራሴው ቁጣ ያዘለ አስተያዬት ተደናግጦ አንገቱን ደፋ አደረገ ። መልስ ግን አልሰጠም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ሆነሃል ?" አለ እንደራሴው ፤ " ሠረገላዬ እንዲዘጋጅ ሁለ ተኛ ጊዜ ትዕዛዝ እንድሰጥ ትፈልጋለህ ?"

ቤርቱሲዮ ወደ ውጭ ሮጦ ከሄደ በኋላ ፤ " የክቡርነታቸውን ሠረ ገላ " በማለት ጮሀ ብሎ ተናገረ ።

በዚህ ጊዜ እንደራሴው ቁጭ ብሎ ሁለት ደብዳቤዎችን ይጽፍ ነበር ። ሁለተኛውን ደብዳቤ በማሸግ ላይ እንዳለ ቤርቱሲዮ ተመልሶ በመምጣት " ሠረገላው ተዘጋጅቷል ፤ጌታዬ " አለ ።

" መልካም ፤ ቢል ባርኔጣህንና ጓንትህን አዘጋጅ ። "

" እኔም ከእርስዎ ጋር ልሄድ ነው ጌታዬ ?"

" አዎ ፤ መኖሪያዬን በዚያ ቤት ለማድረግ ስለፈለግሁ አንዳንድ ነገሮችን እንድትሠራ እሳይሃለሁ ።"

ቤርቱሲዮ ያለአንዳች ተቃውሞ እንደራሴውን ቢከተልም እንደ ራሴው ግን ቤርቱሲዮ ሲያማትብና እንዲያውም ሠረገላው ላይ በተቀ መጠበት ወቅት ጸሎት ቢጤ ሲያደርስ ሳያስተውለው አልቀረም ።

አውቲል በተባለው ሠፈር እንደደረሱ ከቤርቱሲዮ ግንባር ላብ ፥ ንቆረቆር ጀመር ። እንደራሴው ሁሉንም ነገር በጥሞና ይከታተላል ።

ፀሐይ ጠልቃ ለአይን ያዝ ማድረግ ጀምሯል ።

" አንኳኳና መምጣቴን ንገር" አለ እንደራሴው ።ቤርቱሲዮ እንዳ ንኳኳ በሩ ተከፍቶ አንድ የቤት ሠራተኛ ብቅ አለ ።

" ይኸው ፤ አዲሱ ባለንብረት " አለ ቤርቱሲዮ ውሉን ለሠራ ተኛው እያሳዬ ።

" ቤቱ ተሸጠ እንዴ ?" ሲል ጠየቀ ሠራተኛው ።

" አዎ " አለ እንደራሴው ፤ " የቀድሞውን ባለ ንብረት በማጣታ ችሁ ቅሬታ እንዳይሰማችሁ ለማድረግ እሞክራለሁ ።"

" እረ ምንም ቅሬታ አይሰማኝም ጌታዬ ፤ እንዲያውስ ሙቹ ብቅ ብሎ ጠይቆን ያውቃል ?ይህንን ቤት ካዬው ይኸው አምስት ዓመት ሆነው ።"

" ስሙ ማን ነበር ?" ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሠራተኛው የሰውዬውን ስም ተናገረ ።

" ይህንን ስም ቀደም ብዬ የማውቀው ይመስለኛል " ካለ በኋላ እንደራሴው የሰውዬውን ማንነት በሚመራመር አይነት ሃሳብ ተውጦ ቆየ ።

" የሉዊስ አ/ሥራ ስድስተኛ ደጋፊ የነበረ ሽማግሌ ሲሆን ልጁም አንድ ጥንት የማርሴል ፣ በሁዋላም የቨርሳይል ዓቃቤ ሕግ ሆኖ ያገለገለ ቪልፎርት የተባለ ሰው አግብታለች ። " አለ ሠራተኛው ።

በዚህ ወቅት እንደራሴው ቤርቱሲዮን በጨረፍታ ሲመለከተው ከመውደቅ እንዲከላከለው እንደተደገፈው ግድግዳ ደርቆ መትረቱን አስተዋለ ።

" አሃ ፣ ታዲያ ያች ቪልፎርትን ያገባች ልጅ ሞታ የለም እንዴ?"
ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

" አዎ ጌታዬ ፣ ከሞተች ብዙ ዓመታት አልፈዋል ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አባቷ ወደዚህ ቤት ከሶስት ጊዜ በላይ አልመጡም ።"

" አመሰግናለሁ " ካለ በኋላ እንደራሴው ለቤቱ ሠራተኛ ሁለት የወርቅ ሣንቲሞች ሲሰጠው ሠራተኛው ማመን አቅቶት ፈዞ ቀረ ።

" እስኪ ከሠረገላው መብራት ቢጤ አምጣና በደንብ እንጎብኘው ፣ቤርቱሲዮ " በማለት እንደራሴው ሲናገር የቤርቱሲዮ የሚንቀጠቀጡ እጆች ምን ያህል እንደተናገጠ ያመለክቱ ነበር ።

የመጀመሪያውን ፎቅ ከጐበኙ በኋላ ወደ ሁለተኛው ወጡ ።በሁለተኛው ፎቅ ላይ ከሚገኙት የመኝታ ክፍሎች በአንዱ ወደ ታች የሚያስወርድ ደረጃ መኖሩን እንደራሴው አስተዋለ ። " እዚህ አንድ የግል ደረጃ ይታያል " አለ ፣ " እስኪ አብራልኝ ቤርቱሲዮ ፣ ወዴት እንደሚወስድ እንመልከት ።"

" ወደጓሮ ነው የሚወስደው ጌታዬ !" አለ ቤርቱሲዮ ሣይታወቀው

" እንዴ ፣ እንዴት አወቅህ ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ኧ . . . . . ሸ . . . . ምናልባት ወደዚያ ሳይወስድ አይቀርም ለማለት ፈልጌ ነው ፤ ጌታዬ ።”

“ በላ ፤ አስኪ እንይ ።”

ቤርቱሲዮ ደረቅ ፈገግታ እያሳዩ መንገዱን ይመራ ጀመር ።በእር ግጥም ደረጃውን ወርደው እንደጨረሱ ወደ ጓሮ ደረሱ ። ልክ የውጭ ውን በር እንደከፈቱ ቤርቱሲዮ ራሱን ስቶ ሊወድቅ እስኪደርስ ድረስ እንደመገዝለፍለፍ ስላደረገው መራመድ ተሣነው ።

“ ደህናም አይደለህ ?” አለ እንደራሴው ።

“ኧረ ፤ ኧረ ” አለ ቤርቱሲዮ “ የለም ጌታዬ ፤ ከዚህ በኋላ መራ መድ አልችልም !”

“ ምን ማለትህ ነው?” ሲል ጠየቀ እንደራሴው ረጋ ብሎ ።

“ በጣም እንግዳ ነገር ነው ጌታዬ ፤ ፓሪስ ውስጥ ከሚገኙ ሠፈ ሮች ሁሉ አውቲልን መረጡ፤ አውቲል ውስጥ ከሚገኙት ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ቤቶች ውስጥ ደግሞ ይህንን ግድያ የተፈጸመበትን ቤት መረጡ ።”

“ እውነትም የኮርሲካ ሰው ነህ ቤርቱሲዮ ፤ ሁልጊዜ ሚስጥርና እምልኮት የተጠናወታችሁ ! ናባክህ መብራቱን ያዝና ጓሮውን እን ጎብኝ ።”

ቤርቱሲዮ መብራቱን አንስቶ መራመድ ጀመረ ። እንደራሴው ግን ዛፎች ችፍግ ብለው ከተተከሉበት ሥፍራ ሲደርስ ቆመ ። ቤርቱ ሲዮ ትዕግሥቱ ተሟጠጠ ። “ ፈቀቅ ይበሉ ጌታዬ ፤ እባክዎ ይለመ ኑኝ !” ሲል ጮኸ ፤ “ በትክክለኛው ቦታ ነው የቆሙት ።”

“ ምን ይቀባዠርራል ?የምን ትክክለኛ ቦታ ነው ?”

“ ሰውዬው የወደቀበት ቦታ ።”

“ ሳታብድ አልቀረህም ቤርቱሲዮ የማን ሰውዬ ? ” አለ እንደ ራሴው ቆጣ ሊል እየሞከረ ። “ እባክህ ይልቅስ አንተ ተለመነኝና ምን ለማውራት እንደፈለግህረጋ ብለህ አብራራልኝ ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

በእሥር ቤት ሞተ ። ልክ ከመሞቱ በፊት ዛሬ ወደ ቤታችን በመጡት ቄስ በኩል ለእኛ እንዲሰጥ ተናዘዘ ። '

« 'ጓንግዲህ በዋጋው እንስማማ' አለ እንጥረኛው በባልና ሚስት ትረካ መመሳሰል ረክቶ ።

« 'ጅረግ እድሌ ' አለ ካደርስ ፤ 'ቀደም ብለን ተነጋግረን አልነበር ? '

« 'እይ አርባ ሺ ይበቃችኋል ' አለ እንጥረኛው ።

« 'አርባ ሺ ? ' ስትል ጮኸች ወይዘሮ ካደሮስ ፤ ' ዋጋው አምሳ ሺህ መሆኑን ቄሱ ነግረውናል ። አንድ ፍራንክ አይነቅስም '

«' በሉ አርባ አምስት ይሁንላችሁ ፤ ከዚያ በላይ አንዲት ማንቲም ከፍ አልልም ። ' አለ እንጥረኛው ።

« 'የራስህ ጉዳይ ፤ ለሌላ ሰው እንሸጠዋለን ። ' አለ ካደሮስ ።

« 'እንደፈለጋችሁ ማን እንደምታዩት ገንዘቡ በእጀ ነበር ።' በማለት ብሎጡ እንጥረኛ የእህያ ጆሮ የመሳሰለውን ኖትና እፍኝ የሚሞላ ወርቅ አውጥቶ በካደሮስ አይን ላይ ሲያብለጨልጨው ባልና ሚስት ውሳኔ ላይ መድረስ አቅቷቸው ያወላውሉ ጀመር ። ካደሮስ ወደ ሚስቱ ዞር ብሎ በሹክሹክታ ' ምን ይመስልሻል ? ' ሲላት ይሰ ማኝ ነበር ።

« 'በል ስጠዋ መቼስ ምን ይደረግ ' ስትል መለሰች ወይዘሮ ካደ ሮስ ፤ ' ባዶ እጁን ከተማ ገብቶ ስማችንን ቢያጠፋው ታሪኩን ለማስ መስከር ቄስ ቡሶኒን እንኳ ማግኘት አንችልም ። '

« 'በል እስኪ ቁጠር ' አለ ካደሮስ ወደ እንጥረኛው መለስ ብሎ። 'እዚህ ድረስ ካደከምኩህ በኋላ አላስቀይምህም ። '

እንጥረኛው ሰላሣ ሺህ ፍራንክ በጥሬ ገንዘብና አሥራ አምስት ሺህ በወርቅ መቁጠር ጀመረ ።

በዚህ ወቅት ለካስ ሁሉም የቀኑን መምሸትና መብረቅ ያዘለ ዝናብ በመጣል ላይ መሆኑን ዘንግተው ኖሯል ።

« 'ለምን ራት አይቀርብልንም ?' አለ ካደሮስ ከርክክቡ በኋላ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንጥረኛው ‘ የሰም የሰም ፤ መሄድ አለብኝ፤ባለቤቴ ታስባለች’። ከማለቱ ኃይለኛ መብረቅ ሲጥል ብልጭታውም ቤቱ ውስጥ ገባ ።

“‘በእንዲህ ዓይነቱ ዝናም ነው ልሂድ የምትለው ?’ ሲል ጠየቀ ካደሮስ ።

“‘ እዬ ፤ እኔ መብረቅ አልፈራ ፤’

“‘ሌባስ ትደፍራለህ?ይኸ መንገድ እንደሆነ ጤና ካጣ ቆይቷል ።’

“‘ ለሌባ ይኸ ይበቃዋል ፤’ በማለት እንጥረኛው የጐረሰ ሽጉጥ አወጣ ።

“ ‘በል እንግዲያውስ ፣ መልካም ጉዞ ’ አለ ካደሮስ ።

“‘ አመሰግናለሁ ’ ካለ በኋላ እንጥረኛው በትሩን አንስቶ በሩን እንደከፈተ ወደ ውስጥ የገባው ኃይለኛ ነፋስ የፋኖሱን ብርሃን ሊያ ጠፋው ምንም አልቀረውም ።

“ ‘ ወይ ጣጣ ፤ ይኸን ረጅም መንገድ ከዚህ ንፋስ ጋር እየታገልኩ እዘልቀዋለሁ ? ’ አለ እንጥረኛው ።

“ ‘ ለምን የዛሬን እዚህ አታድርም ’ አለ ካደሮስ ።

“ እረ ግዴለህም ሥጋት አይደርብህ ! ” አለች ወይዘሮ ካደሮስ በሚንቀጠቀጥ ድምጽ ።

“ ‘ አይሆንም ፤ ቤቱ ሳልገባስ አላድርም ። ደህና እደሩ ። ’ እንጥረኛው ወጥቶ ተፈተለከ ።

“ ‘ለምን ነበር እዚህ እንዲያድር የጐተጐትከው ?’ ስትል ጠየ ቀች ሚስት እንጥረኛው እንደወጣ ።

“‘ እንዴ ፤ በዚህ ብርድና ዝናብ በሌሊት ከሚጓዝ ብዬ ነዋ ’ አለ ካደሮስ ግራ ተጋብቶ ።።

“‘እሃ!’ አለች ወይዘሮ ካደሮስ ‘ እኔ ደግሞ ለሌላ ጉዳይ መስሎኝ።’

“ ‘እረ ተይኝ አንቺ ሴትዮ ፤ እንዲህ ያለው ርኩስ አስተሳሰብ ምን ያደርግልሻል ? ደግሞም ይህን አይነቱን ተንኮል ለኔ እንድትነግ ሪኝ አልፈልግም ፤ ለራስሽ አምስልስይው ። ልብ አድርጊ ፤ እግዚአብ ሔርን እያስቀየምሽው ነው ! ’ ልክ እንዲህ ሲናገር ኃይለኛ ነጐድ ጓድና ብልጭታ ጸጥታውንና ጨለማውን ሰነጠቀት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 24

በተከታዩ ቀን ስምንት ሰዓት ገደማ በሁለት ምርጥ የእንግሊዝ ፈረሶችየሚሳብ ሠረገላ ከሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ቅጥር ግቢ በር ፊት ለፊት ቆመ ። በውስጡም ሰማያዊ ኮት ፤ ቡናማ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ የለበሰ አጭር ፤ ከመጠን ያለፈ ወፍራም ሰው ይታያል ። ሰውዬው ከጸጉር እበጣጠሩ ጀምሮ እለባበሱና ጠቅላላ ሁኔታው ወጣት ሊመስል የሚጥር የአርባ አምስት ዓመት ጉልማሣ ነው ። አንገቱን በመስኮት በኩል ብቅ አድረገና የሠረገላው ሾፌር የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ቤቱ ውስጥ መኖር አለመኖሩን እንዲያጣራ አዘዘው ።

የሠረገላው ሾፌር የግቢውን ዘበኛ መስኮት ካንኳኳበኋላ ፤ “ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ መኖሪያ ይህ ይሆን ?” ሲል ጠየቀ ።

“ ክቡርነታቸው በርግጥ የሚኖሩት እዚህ ነው ። ሆኖም አሁን ሥራ ላይ ናቸው ። ” ሲል መለሰ ዘበኛው ።

“ እንግዲያውስ ይኸው የአሊቃዬ የባሮን ዳንግላር ካርድ ። ውሰድና አሳይተህ አሊቃዬ ወደ ምክር ቤት ሲሄዱ እግረ መንገዳቸውን ሊያነጋግሩዋቸው እንደፈለጉ ንገርልኝ ።”

“ እኔ ከክቡርነታቸው ጋር ለመነጋገር አልችልም ፤ መልዕክቱን ግን ባለሟላቸው ሊያደርስ ይችል ይሆናል ።”

የሠረገላው ሾፌር ወደ ዳንግላር ተመልሶ የተሰጠውን መልስ ተናገረ ። “ ይኼ ክቡርነታቸው እያሉ የሚጠሩትና ከባለሟሉ በስተቀር ማንም ሊያነጋግረው የማይችል ሰው መሥፍን መሆን አለበት ። ”አለ ዳንግላር ። “ ግን ምን ቸገረኝ ፤ ከእኔ ጋር የከፈተው ሂሣብ እስካለው ድረስ ገንዘብ ሲፈልግ የግዱን ራሱ ወደኔ ይመጣል ። ” ከዚህ በኋላ ዳንግላር ወደ ምክር ቤት ሙንገዱን ቀጠለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የዳንግላር መምጣት የተገለጸለት እንደራሴ ግን በመስኮት ጠኩል ኃይለኛ የማቅረቢያ መነጽሮችን በመጠቀም ሲመለከተው ቆይቶ ኖሮ ወዲያውኑ ቤርቱሲዮን አስጠራው ።

“ ከደቂቃ በፊት ከአጥሩ በር ትይዩ ቆመው የነበሩትን ፈረሶች አይተሃቸዋል ፣ ቤርቱሲዮ ?” ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

“አይቻቸዋለሁ ጌታዬ ። በጣም የሚያማምሩ ፈረሶች ናቸው ።” አለ ቤርቱሲዮ ።

“ እኮ እንዴት ? ” አለ እንደራሴው ግንባሩን ሸብሸብ አድርጎ፣ “ ፓሪስ ውስጥ ከሚገኙት ፈረሶች ሁሉ የበለጠ የሚያምሩትን መር ጠህ እንድትገዛ አልነበረም ያዘዝኩልህ ? እንዴት እንዲህ ያማሩ ፈረ ሶች በሌላ በሰው እጅ አያለሁ ?”

“ ጌታዬ ” አለ ቤርቱሲዮ ፣ “ ያዩዋቸው ፈረሶችኮ የሚሸጡ አይ ደሉም ። ”

እንደራሴው ከትከሻው ነቅነቅ ብሎ ፤ “ የመግዛት አቅም ላለው ሁሉም ነገር ሸቀጥ ነው ። ” አለው ።

“ መሴ ዳንግላር ሁለቱን ፈረሶች በአሥራ ስድስት ሺህ ፍራ ንክ ነው አሉ የገዙዋቸው ጌታዬ ።”

“ ይሁና ፤ ሰላሳሁለት ሺህ ፍራንክ እንደምትከፍለው ንገረው። የባንክ ነጋዴ እስከሆነ ድረስ ካፒታሉን የሚያዳብርለት እድል እንዲ ያመልጠው ስለማይፈልግ ያለ ጥርጥር ይሸጥልሃል ።”

“ እውነትዎን ነው የሚናገሩት ጌታዬ ?” ሲል ጠየቀ ቤርቱሲዮ ግራ ተጋብቶ ።

“ ይልቁንስ በአሥራ አንድ ሰዓት ቀጠሮ አለብኝ ፣ ሠረገላዬ የሚንቀሳቀሰው በነዚያ ፈረሶች መሆን አለበት ።”

“ ይቅርታ ያድርጉልኝና አሁንኮ ስምንት ሰዓት ሆኗል ጌታዬ ።” አለ ቤርቱሲዮ እንደማፈር ብሎ ።

“ አውቃለሁ ! ” ነበር የእንደራሴው መልስ ።

* * *

አሥር ሰዓት ተኩል ላይ እንደራሴው ከክፍሉ ወጣ ሲል ከሁለት ሰዓት በፊት በዳንግላር ሠረገላ ላይ አይቶ ያደነቃቸው ፈረሶች ከራሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

" ጥሩ ! የበረገገ በሬ በሸምቀቆ ጠልፈህ ማቆም ትችላለህ ?"
አሉ. አሁንም በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ።

" ነብርስ ?"

ሌላ አዎንታ ።

" አንበሳ ?"

አሊ ሸምቀቆ እንደሚወረውር ሰው እጁን ካወናጨፈ በኋላ የቀጠሰፈ አንበሳ እንዴት ድምጽ አሰማ ።

" ገባኝ ! ለመሆኑ አንበሳ አድነህ ታውቃለህ ?"

አሊ እንደገና በኩራት የአዎንታ ምልክት ሰጠ ።

" እሺ ሁለት የሚሰግሩ ፈረሶችስ ማቆም ትችላለህ ?"
አሊ በንቀት ከት ብሎ ሳቀ ።

" በጣም ጥሩ ! እንግዲህ አዳምጠኝ ። በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሁለት ጥቁር ግራጫ ፈረሶች የሚጎተት ሠረገላ በዚህ መንገድ ያልፋል ። ፈረሶቹ ትናንት የገዛሁዋቸውና መልሼ የሳከሁዋቸው ናቸው ። እንደ ምንም ብለህ ከአጥር ግቢዬ በር ትይዩ ሲደርሱ በሸምቀቆ ጠልፈህ ትጥልልኛለህ ።"

በእንደራሴው ትዕዛዝ መሠረት ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቆ አሊ ከጥሻው ውስጥ ተደበቀ ።

ብዙም ሳይቆይ ከሩቅ በፍጥነት የሚመጣ የፈረስ ኮቴ ይሰማ ጀመር ። ወዲያውኑ ሠረገላ ታዬ ። የሠረገላው አሽከርካሪ በኃይል የሚሠግሩትን ፈረሶች ለመግታት ይታገላል ። ሠረገላው ውስጥ አንዲት ልጅ እግር የቤት እመቤትና የስምንት ዓመት ልጅ እርስ በርሳቸው ተቃቅፈው ለመጮህ እንኳ ቀልብ አጥተው በመደናገጥ በደመነፍስ የሚንደረደሩትን ፈረሶች አፍጥጠው ይመለከታሉ።መጠኗ ትንሽ ከፍ ያለ ድንጋይ እንኳ የሠረገላውን ጎማ ብታገኘው የምትገለብጠው ይመስላል ።

ሠረገላው ከታቀደለት ሥፍራ ሲደርስ አሊ ሸምቀቆውን ከኪሱ አውጥቶ በመወርወር በግራ በኩል ያለውን ፈረስ የፊት እግር ጠፍሮ ከያዘ በኋላ በቅጽበት ሲጎትተው ፈረሱ በራሱ ኃይል መሬት ላይ ሲወድቅ በቀኝ በኩል ያለው ፈረስም ከሩጫው ከቆመ በኋላ ከጓደኛው ላይ ተደርቦ ዘጭ አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የተዋጠ ቅጽበት እንደራሴው እናቱ እያገላበጠች የምትስመውን ሕጻን ኤድዋርድን አስተዋለው ። ልጁ ለውነቱ የቀጨጨ ሲሆን ጸጉሩ ከፊት ለፊቱ ግንባሩን በሥርዓት እንደከበበ ወደ ትከሻው ወርዷል ። ሳምባ ከሚመስለው የፊቱ ቀለም ጋር ጥቁሩ ጸጉሩና ቅንድቦቹ ሥዕል አስመስለውታል ። የመጀመሪያው እንቅስቃሴው ራሱን ከእናቱ እቅፍ አላቆ እንደራሴው መድሃኒቱን ያወጣበትን ሳጥን መክፈት ነበር ። ሳጥኑን እንደከፈተ በሕጻንነት መንፈሱ የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቅ የብልቃጦችን ክዳኖች መንቀል ጀመረ ።

“ ተው የኔ ልጅ ።” አለ እንደራሴው ፈጠን ብሎ ፤ “ አንዳንዶቹ ፈሳሾች ለመቅመስ ቀርቶ ለማሽተትም አደገኞች ናቸው ።”

እመቤት ቪልፎርት በድንጋጤ ልጅዋን ጐትታ በእቅፏ ሥር ሸጐጠችው ። ፍርሃቷ ቀለል ሲልላት የመድሃኒቱን ሳጥን በጨረፍታ ገልመጥ አደረገች ።

“ መኖሪያ ቤትዎ ይህ መሆኑ ነው ክቡር እንደራሴ ?” ስትል ጠየቀች እመቤት ቪልፎርት ከተጋደመችበት እየተነሳች ።

“ አይደለም እመቤት ፤ ለሳምባዬ ንጹህ አየር ፤ ለአይኖቼ የገጠር ልምላሜና ለመንፈሴ ጸጥታ በምፈልግበት ወቅት የማርፍበት ቤት ነው ። ዋና መኖሪያዬ መሐል ከተማ ላይ ይገኛል ። ግን . . . ሙሉ ለሙሉ የተሻለሽና ለመሄድ የተዘጋጀሽ ትመስያለሽ ። እነዚያው ፈረሶች በእኔ ሠረገላ ላይ ተለጉመው አሊ እንዲያደርስሽ ፤ ያንቺው ሾፌር ደግሞ እዚሁ ቆይቶ ሠረገላሽን እንዲጠግንና ሲጨርስ በእኔ ፈረሶች ወደ እመቤት ዳንግላር እንዲላክ ማድረግ አለብኝ ።”

“ ግን እንዴት በእነዚያ ፈረሶች እንደገና እሳፈራለሁ ?”

“ በእኔ ይሁንብሽ እመቤት ” አለ እንደራሴው ።“ በአሊ እጅ እንደ ማገልገል በግ ይታዘዛሉ ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

በምወጣበት ጊዜ ስለኔ የበለጠ ሲያውቁና ተራ ሰው አለመሆኔን ሲረዱ ግንኙነታችን ሚዛኑን እንደሚጠብቅ እርግጠኛ ነኝ ። በተለይም የባለቤቱ ባለውለታ በመሆንዎ ። ”

አቃቤ ህጉ ከክፍሉ እንደወጣ እንደራሴው ለራሱ እንዲህ አለ፣ “ አሁን ገና ልቤ በመርገዝ ተሞላ፣ ከእንግዲህ የቀረው ማርከሻውን መጋት ነው ። ”

ከዚያም ደወል ደውሎ አሊን ካስቀረበ በኋላ “ ሰረገላዩ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ዝግጁ እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ ። ” አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 26

መሸትሸት ብሏል ። የምንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ከኢጣሊያውንጉሥ ከተረከባት የግሪክ ባሪያው ከሃይዲ ጋር አንድ ሰዓት ያህል ለማሳለፍ ወስኖ ነበር ።

ወጣቷ ግሪክ ከእንደራሴው ክፍል ሙሉ ለሙሉ በተለዩ ክፍል ውስጥ ትኖራለች ። በመካከለኛው ምሥራቅ ባህል መሰረት የተቀመጡት እቃዎቿና ጌጣጌጦቿ ለክፍሏ ልዩ ውስጥ ሰጥተውታል ። መኖሪያዋን ለማድነቅ ወለሉን የሸፈነውን የቱርክ ምንጣፍ መመልከቱ ብቻ ይበቃል ። የቆዳዋ ጥራት በጣት ቢነኳት የምታድፍ ፣ የሰውነቷ ጥብቅነት በጥፍር ጠቆም ሲያደርጓት የምትፈርጥ የምትመስለው ሃይዲ በሰማያዊ የአልጋ ምንጣፍ ከተዋበችው ድንክ አልጋዋ ላይ ለሰላሳ ከንዶቿን ተንተርሳ ተጋድማለች ። ከአለባበሷ ጀምሮ እስከ አስተኛኘቷ ድረስ መላ ሁኔታዋ ለሠዓሊ እይታ የተዘጋጀች አስመስሏታል ። ትላልቆቹና ጥቋቁሮቹ አይኖቿ ፣ ቀጥ ብሎ ወርዶ ከታች ቀና ያለው አፍንጫዋ ፣ ስስ ከንፈሮቿና ችምችም ብለው የሚታዩት ጥርሶቿ ፍጹም ያልተቀየጠ የግሪክ ኮረዳ ውበት ያንጸባርቃሉ ። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የወጣትነት ግለትና ደስተኛነት ይታያል ። ሃይዲ እድሜዋ ከአሥራዘጠኝና ከሃያ ዓመት የሚበልጥ አልነበረም ።

እንደራሴው የግሪክ ባለሟሉን ጠርቶ ሃይዲ ልታነጋግረው ትችል እንደሆን እንዲጠይቃት ላከው ። ወዲያውኑ ፈቃደኛ መሆኗ ተገልጾለት ወደ ክፍሏ ጐራ አለ ።

ሃይዲ እንደራሴው እንደገባ ራሷን ቀና በማድረግ በግራ ክንዷ አስደግፋ ቀኝ እጅዋን ከፈገግታ ጋር ለሰላምታ በመዘርጋት " ለምንድን ነው እዚህ ለመምጣት ፈቃድ የጠየቅኸው ? " አለች እጅግ በለሰለሰ አነጋገር፤" ጌታዬ መሆንህ አበቃ ? ባሪያህ መሆኔ አከተመ ? "

" ሃይዲ " አለ እንደራሴው ፤ "እሁን ያለነው ፈረንሳይ ውስጥ ስለሆነ ሙሉ ለሙሉ ነጻ ሰው ነሽ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ለመሆን ነው ነጻነቴ ? "

" ከዚህ ለመሄድ ? "

" ካንተ ለመለዩት ? ለምን እለይሃለሁ ? "

" እየሽ፤ እዚህ ከብዙ ሰዎች ጋር እንገናኛለን፣ እንጠያየቃለን ። ከምታያቸው ወጣቶች መካከል አንደኛው ቆንጆ ላይ አይንሽ ቢያርፍ በእኔ ምክንያት መብትሽ ተገፎ ማየት አልፈልግም ። "

" ካንተ የበለጠ ቆንጆ አይቼ እንደማላውቅም ሆነ ልመለከት እንደማልችል ፣ እንደማልፈቅድ ታውቅልኛለህ ? እንዳንተና እንዳባቴ ሰው ወድጄ እንደማላውቅም ሆነ ልወድም እንደማልችል ታውቅልኛለህ ? "

" አባትሽን ታስታውሻቸዋለሽ ፣ ሃይዲ ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

ሐይዲ ፈገግ ካለች በኋላ " አባቴ እዚህና እዚህ ላይ አለ " በማለት በእጅዋ አይኖቿንና ልቧን አመለከተች ።

" እኔስ የት ነኝ ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው እየሣቀ ።

" በሥራ አካላቴ " አለች ሃይዲ ፣ አሁንም ከእግር ጣቷ እስከ ራሷ በእጅዋ እያመለከተች ።

እንደራሴው እጅዋን ሳብ አድርጐ በዝግታ ሳመው ። ሃይዲ ግን እጅዋን ነጠቀችውና ግንባሯን አስጠጋችለት ።

" አሁን እንግዲህ ሃይዲ " አለ እንደራሴው፤ " ነጻ መሆንሽን፣ ለዚህ ግቢም እመቤትና ንግሥት መሆንሽን ካወቅሽ ዘንድ ባገርሽ ባህል ወይም በፈለግሽው ዓይነት አለባበስ ፣ እዚህ የመሆንም ሆነ ወደ ፈለግሽው ሥፍራ የመንቀሳቀስ መብትሽ የተጠበቀ ነው ። በጉዞሽ ወቅትም ሆነ ግቢ ውስጥ ትዕዛዝሽን የሚፈጽሙ ሁለት ባለሟሎች እመድብልሻለሁ ። ግን ካንቺ አንድ የምጠይቀው ነገር ይኖራል ። "

" ንገረኝ! "

" ከማን እንደተወለድሽም ሆነ ያለፈውን ታሪክሽን በተመለከተ ለማንም እንዳትነግሪ ። የታላቁ አባትሽም ሆነ የምስኪኗ እናትሽ ስም ካፍሽ እንዳይወጣ ፣ አደራ ! "



t.me/OLDBOOKSPDF

# 27

“ አ ! ክቡር የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ” አለ ማክሲሚለን ሞረል እንደራሴው ቃል በገባው መሰረት ሲጠይቀው መምጣቱን እንደሰማ ወደ በሩ እየሮጠ ። “ ቃልዎን ባለማጠፍዎ በጣም አመሰግናለሁ ፤ ክቡር እንደራሴ ! ” በማለት ሻለቃ ማክሲሚለን የእንደራሴውን እጅ ጨብጦ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረበ ። ወዲያውኑ ወደ ክፍል መግባት ጀመሩ ።

የቶምሶንና ጓደኞቹ ወኪል እንደተነበዩው እመቤት አማኑኤል ለመባል የበቃችው ዡሊዬ እንግዳቸውን ስትመለከት ጨኸት ቃጣት ።

“ ፔኔሎን ” አለች ዡሊዬ የአባቷ መርከብ የነበረችው የፋራኦንን መርከበኛ በመጣራት ፤ “ፈጠን በልና እንግዳው መምጣታቸውን ለአማኑኤል ንገር ። ”

የዡሊዬ ግቢ በአበባ ያሸበረቀ ነበር ። ከትላልቆቹ ዛፎች ላይ የሚሰማው የወፎች ዝማሬና የመስኩቶችን መጋረጃዎችን እየመቱ የሚወድቁት የግራር ቅጠሎች ግቢውን ከማስዋብ ጋር መንፈስን ያድሳሉ ። ከዚህ የተፈጥሮ ውበት ጋር የተቀላቀለው የዡሊዬ ፤ የአማኑኤልና የማክሲሚለን ትህትና እንግዳን ያፈዛል ።

እንደራሴው በክፍሉ እንደገባ ይህንን በትህትና የተሞላ የደስታ አየር ለመረዳት ጊዜ አልወሰደበትም ። ከመጀመሪያው የሰላምታ ልውውጥ በኋላ የሚቀጥል ጭውውት እንደሌለ ሁሉ እንደራሴው ዝም ብሎ በሃሳብ እንደተዋጠ ከቆየ በኋላ በመጨረሻው የሰፈነው ጸጥታ በሱ የተነሳ መሆኑን ሲረዳ አእምሮው የመነጋገሪያ ርዕስ ፍለጋ ይጣደፍ ጀመር ። “ እመቤት ” አለ ፤ “ ሊያስገርምሽ የሚችል የዝምታ ሁኔታ በመፍጠሬ ይቅርታ እጠይቅሻለሁ ። ለዝምታዬ መንስኤው ልክ ግቢው ውስጥ ሲገባ ያስተዋልኩት ከብዙ ቤተሰቦች መካከል የማይታይ የደስተኛ ቤተሰብ መልክ አይኔን ከአንችና ከባለቤትሽ እንዳነሳ አለማድረጉ ነው ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

# 28

የሞንት፡ ክሪስቶ እንደራሴ ለተደረገለት ጉብኝት አጸፋ ለመ መለስ ወደ ቪልፎርት መኖሪያ ቤት እንደሄደ እመቤት ቪልፎርትን ሳሎን ውስጥ አገኘት ። የመጀመሪያው የሰላምታ ልውውጥ ከተካ ሄደ በኋላ እንደራሴው ስለ ቪልፎርት ጠየቀ ።

" ባለቤቴ ራት ተጠርቶ ሄዷል ። እርስዎን ሲያገኝ ባለመቻሉ ሲያዝን ነበር " አለች እመቤት ቪልፎርት ፤" ኤድዋርድ ፤ ቫለንቲን የታለች ? ሄድ ጥራት ፡ ከክቡር እንደራሴ ጋር ትተዋወቅ ። "

" ሴት ልጅም አለችሽ '' እንዴ እመቤት ?" ሲል ጠየቀ እን ደራሴው ።

" አዎ ፡ ከቪልፎርት የመጀመሪያ ሚስት የምትወለድ ናት " ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቫላንቲን ወደ ሳሉኑ ገባች ። ረዘም ያለች ለግላጋ ወጣት ነበረች ። የእንጀራ እናቷን ብዙ ሲወራለት ከሰማ ችው እንግዳ ሰው ጋር ስትመለከት የልጃገረድ መሽኮርመም በማ ይታይበት ግልጽ ሁኔታ ዝቅ ብላ ሰላምታ ስትሰጥ ከፊቷ ላይ የሚ ነበበው ደስተኛ አስተያየት የእንደራሴውን ትኩረት ሳበው ።

" ይቅርታ አድርጊልኝና እመቤት " አለ እንደራሴው እመ ቤት ቪልፎርትንና ቫለንቲንን እያፈራረቀ በመመልከት ፤ " እን ቺንና ይህችን ወጣት ልጃገረድ ከዚህ በፊት አይቻችኋለሁ ልበል? ቀደም ሲልም ስለዚህ ጉዳይ ሳስብ ነበር ። አሁን ግን ወይዘሪት ቫለ ንቲንን ስመለከት የጊዜ ርዝመት ባደበዘዘው ትውስታዬ ላይ የብ ርሃን ጨረር ፈነጠቀበት ። "

" ሊሆን አይችልም ክቡር እንደራሴ ፡ ከቫለንቲን ጋር ብዙ ጊዜ አብረን አንወጣም ። " አለች እመቤት ቪልፎርት ።

"የለም ፓሪስ ውስጥ ማለቴ ሳይሆን ባንድ የሃይማኖት ክብረ በዓል . . . . ቦታው ጠፋኝ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" ምናልባት ጣሊያን አገር አይተውን ይሆናል።" አለች ቫለ ንቲን ።

" አ . . . ዎ! ልክነሽ ወይዘሪት፣ ሮም ውስጥ ባንድ ሆቴል በመ ናፈሻ ስፍራ . . . "

" አሃ ፣ አሃ ፣ አስታወስኩ።" አለች እመቤት ቪልፎርት " እር ስዎ ትዝ አላሉኝም እንጂ ቦታው ይታወሰኛል ። "

" እስኪ ላስታውስሽ እመቤት ። ቀኑ በጣም ሞቃት ነበር ። በበአሉ ምክንያት ሰረገላሽ ዘግይቶብሽ እየተቅበጠበጥሽ ትጠብቂ ያለሽ ። ቫለንቲን በአትክልቱ ሥፍራ ስትንሸራሸር ኤድዋርድ ደግሞ ከወፍ ጋር ይጫወት ነበር ። እዚያ ቦታ በድንጋይ ወንበር ላይ ተቀ ምጠሽ ከአንድ ሰው ጋር መነጋገርሽ ትዝ አይልሽም ? "

" እንዴ ፣ እንዴ ፣ ልክ ነዎ " ካለች ወጣቷ እመቤት ተከ ስኩሶ የነበረው ፊቷ ፈክቶ " ካንድ ረጅም ኩፍያ ካደረገ ሰው ጋር ማውራቴ ትዝ አለኝ ፣ ዶክተር ሳይሆን አይቀርም ። " አለች ።

" ያ ሰው እኔ ነበርኩ ፣ እመቤት ። በዚያ ሆቴል ሁለት ሳም ንት ተቀምጫለሁ ። በዚያ እለትም አንድ ባለሟሌን ከንዳድ ፣ የሆ ቴሉን ተቆጣጣሪ ደግሞ ከተቅማጥ ፈውሻቸዋለሁ ። በዚህም ምክ ንያት ነው በአካባቢው እውቅ ዶክተር መሆኔ ሲነገር የነበረው ።"

" ግን ያን ሁሉ ህመም ያዳኑት ዶክተር ነዎት ማለት ነው ። አይደለም ? "

" አይደለሁም እመቤት ፣ በኬሚስትሪና በተፈጥሮ ሳይንሶች ላይ ጥልቅ ጥናት ባካሂድም የህክምና ዶክተር አይደለሁም ። ኬሚ ስትሪንም ቢሆን ላጠና የበቃሁት በመካከለኛው ምሥራቅ ጉብኝት አዘወትር ስለነበር የንጉሥ ሚትሪዴትስን ምሳሌ ለመከተል ብዬ ነው ። "

" ሚትሪዴትስ " አለ ህጻኑ ኤድዋርድ ከእንደራሴው ነጥቆ "ሁልጊዜ ቁርሱን መርዝ በክሬም እየቀላቀለ የሚበላው ንጉሥ ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

" አንተ ቀልባጣ " በማለት እመቤት ቪልፎርት ልጇን ገሰጸች ። " አሁንስ አልተቻልክም ! ሂድ ውጣ ። "

እመቤት ቪልፎርት ለኤድዋርድ የሚጫወትበት ነገር ከሰጠችው በኋላ ወደ ውጭ ትመራው ጀመር ።

" እስኪ ትዘጋበት እንደሆነ እንይ ! " አለ እንደራሴው ለራሱ።እመቤት ቪልፎርት ሀጹሩን አስወጥታ ብሩን ስትዘጋ እንደራሴው አላማው መሳካቱ ውስጥ ውስጡን ቢያስፈነድቀውም ሁኔታውን የማይከታተል ለመምሰል ይሞክር ነበር ። በክፍሉ ውስጥ ብቻቸውን ቀሩ ፤ ሁለቱ ።

" የልጅሽ እውቀት ከእድሜው የቀደመ ይመስላል ። " አለ እንደራሴው እንደገባች ።

" አዎ ፡ የነገሩትን ቀብ ሲያደርግ አንዲት ቃል አታመልጠውም . . . . ለመሆኑ ሜትሪዴትስ የተባለው ንጉስ እውነት ምግብ ከመርዝ ጋር ቀላቅሎ ይወስዳል ? "

" እኔ ራሴ እንደዚያ አደርጋለሁ እመቤት ። አይነተኛ የመርዝ ማርከሻ በመሆኑ ሁለት ጊዜ ከሞት አድኖኛል ። "

" አሃ ! ሮም በተገናኘንበት ጊዜ እንዳጫወቱኝ አስታውሳለሁ።"

" እረ ? " አለ እንደራሴው እጅግ የተገረመ በመምሰል ። "እሱ እንኳ ብዙም ትዝ አይለኝም ። "

" ታዲያ እንዴት አድርገው ነው ሰውነትዎን ከመርዝ ጋር ያለማመዱት ?"

" በጣም ቀላል ነው ። መጀመሪያ የሚያስጋሽን የመርዝ አይነት ማወቅ አለብሽ ። በመጀመሪያው ቀን ከዚያ መርዝ አንድ ሚሊግራም ትወስጃለሽ ። በማግሥቱ ሁለት ሚሊግራም ፤ ቀጥሎ ሶስት እያልሽ ባስረኛው ቀን አሥር ሚሊግራም መርዝ እስከምትወስጅ ድረስ ትለማመጃለሽ ። ከዚያም በየቀኑ ሁለት ሚሊግራም መውሰድ ትጀምሪና በሃያኛው ቀን ሰላሳ ሚሊግራም ትደርሻለሽ ፤ ሰላሳ ሚሊግራም መርዝ ያለ ልምምድ ለሚወስደው ሰው እጅግ አደገኛ ሲሆን ላንቺ ግን ምንም ጉዳት አያስከትልም ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ልንባቸው እጅግ አደገኛ መርዞች የሚባሉት እንኳ ፍቱን መድሃኒ ቶች ሊሆኑ ይችላሉና !"

" ታዲያ መርዝ ካልሆነ ምንድን ነው ?"

" እጅግ የተራቀቀ ጓደኛዬ አጠቃቀሙን ጭምር አስረድቶ የቀመመልኝ ነገር ነው ።"

" እሃ ፤ እንግዲያውስ ግሩም የሆነ የድንገተኛ መድሃኒት ነው።"

" እንከን የማይወጣለት እመቤት ፤ ራስሽ እንዳየሽው ። አስፈ ላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ለራሴም እጠቀምበታለሁ ። " አለ እንደ ራሴው ከፈገግታ ጋር ።

" እንደሚጠቀሙበትስ እርግጠኛ ነኝ።" አለች እመቤት ቪል ፎርት በተመሳሳይ ፈገግታ ። " በበኩሌ ግን ብዙ ጊዜ ራሴን የመሳት ህመም ያጠቃኛል ፤ ታዲያ እንደርስዎ የተማረ ወዳጅ ስለሌለኝ ተራ የሃኪም መድሃኒት ነው የምጠቀመው ። "

" የእኔው ይመረጣል ።"

" ያለጥርጥር ፤ " አለች እመቤት ቪልፎርት ። " በተለይ እኔ ልጄን ከሞት ካተረፈልኝ ወዲህ ከእርስዎው የተሻለ መድሃኒት አለ እልልም ። ግን የሚስጥር መድሃኒት ስለመስለኝ ስጡኝ ብዬ ልጠይቅ ቀርቶ ወሬውን ማንሳት እንኳ ይከብደኝ ነበር ።"

" አይ፤ምንም አይደለም። እንዳስፈላጊነቱ ልሰጥሽ እችላለሁ ።" አለ እንደራሴው ከተቀመጠበት እየተነሳ ።

" እረረ . . . " አለች ወጣቷ እመቤት ማመን አቅቷት ።

" አንድ ነገር እንዳትረሺ ። በትንሹ ሲወሰዱት መድሀኒት ቢሆ ንም በዛ ካለ መርዝነት አለው ። አንድ ጠብታ እንዳዬሽው ከሞት ያስ ነሳል ፤ አምስትና ስድስት ጠብታዎች ግን ለሞት ይዳረጋሉ ። እጅግ አደገኛ የሚያደርገው ደግሞ እነዚያ አምስትና ስድስት ጠብታዎች ካንድ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ጋር ቢቀላቀሉ የወይን ጠጁን ጣዕም ሆነ ቀለም ሊለውጡ አለመቻላቸው ነው ። " ሆን ተብሎ የተቀናበረ ገለጻ ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የማድግዳው ሰዓት አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ እንደደወለ አንዷት የቤት ሠራተኛ ለራት ግብዣ የተጠራች እንግዳ መግባቷን አስታወቀች ።

“ ይህ የዛሬው ለሁለተኛ ሳይሆን ለሶስተኛ ወይም ለአራተኛ ጊዜ መገናኘታችን ቢሆን ኖሮ”አለች እመቤት ቪልፎርት፣“ በተለይም ከውለታ ተቀባይ ይልቅ ባለዕዳ ለመሆን ብታደል ኖሮ ራት ሳይበሉ አልለዩዎትም ነበር ።”

“ በጣም አመሰግናለሁ እመቤት ” ሲል መለሰ እንደራሴው “ ሆኖም እኔም የማልሰርዘው አንድ ቀጠሮ ይጠብቀኛል ።”

“ የመድሃኒቱን ነገር እንግዲህ አደራ እንዳይረሱብኝ ። ”

“ በጭራሽ እመቤት ፤ እሱን መርሳት ማለትኮ የዛሬውን ጭውውታችንንና የበፊቱንም መርሳት ማለት ነው ።”

እንደራሴው ተረናብቶ ወጣ ። ያገኘው ውጤት ከጠበቀው በላይ ነበር። “የዘራሁት ዘር ቦዳ መሬት ላይ እንዳልወደቀ እርግጠኛ ነኝ።” አለ ለራሱ ከግቢው ከወጣ በኋላ ።

በማግስቱ በገባው ቃል መሠረት እመቤት ቪልፎርት የጠየቀችውን መድሃኒት ላከላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 29

ከብዙ ቀናት በኋላ አልበርት የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴን ለመ ጠየቅ መሐል ከተማ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ጉራ አለ ።

አልበርት ወደ እንደራሴው ቤት ሲሄድ ደብራይ የተባለው የሚ ኒስትር ጸሐፊ ኋደኛውን አስከትሎ ነበር ። የሚኒስትሩ ጸሐፊ ወደ እንደ ራሴው ቤት እንዲመጣ የተደረገው የዳንግላር ባለቤት በሰላሣ ሁለት ሺ ፍራንክ የገዛቻቸውን ፈረሶች መልሶ የሚልክና በሌላ በኩልም በሚ ሊዮን ፍራንክ በሚቆጠር የአልማዝ ጌጣጌጥ ከተንቆጠቆጠች የግሪክ ባሪያ ጋር ወደ ቲያትር ቤት የሚሄደው ሰው ቤት ምን ዓይነት እንደ ሆነ አይቶ እንዲመለስ ስለላከችው መሆኑን እንደራሴው ጠርጥሯል። ይሁን እንጅ እንደራሴው በሚኒስትሩ ፀሐፊና በኢመቤት ዳንግላር መካከል ያለውን ግንኙነት እንደማያውቅ ሆኖ ነበር የቀረበው።ሆኖም የሚኒስትሩ ጸሐፊ ብዙም ሳይቆይ ይቅርታ ጠይቆ ከቤት ወጣ ።

“ ከዳንግላር ጋር በተደጋጋሚ ትገናኛላችሁ ፤ አይደለም ?” ሲል እንደራሴው አልበርትን ጠየቀው ።

“ በሚገባ ፤ የነገርኩዎን ያስታውሱ የለም ።”

“ ታዲያ ነገሮች እያስተካከሉ ናቸው ማለት ነዋ ?”

“ አዎ ፤ ያለቀለት ጉዳይ ነው ። ”

“ ቆንጆ ናት ?”

“ እጅግ በጣም ታምራለች ። ግን ቁንጅናዋ እኔ የማደንቀው ዓይነት አይደለም ። አትስበኝም ።”

“ የምትናገረው እንዳገባሃት ሆነህ ነው ። ” አለ እንደራሴው “ በጋብቻው ብዙም አልተደሰትህበትም መሰለኝ ።”

“ ወይዘሪት ኢዩጊን ዳንግላር ከምፈልገው በላይ ሃብታም ነች ። ያ ደግሞ እጅግ ያስፈራኛል ።” አለ አልበርት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሃብት ወደ ፓሪስ ሲመጣ ከሚፈልግ እንድሪያ ከተባለ ልጁ ጋር ጥብቅ ቀጠሮ አለብኝ ። ለሻለቃው የራት ግብዣ አደርግለትና ልጁን ለእኔ ትቶልኝ ይሄዳል ።”

“ በኑ ጋጣሚ ሻለቃ ባርቶሎሚዮ ለልጃቸው ሚስት ከፈለጉ…” አለ አልበርት ፤ “ በአባቷ ባሮን ፤ በእናቷ የመሳፍንት ዘር የሆነች ሃብታም ልጃገረድ እንዲያገባ ለመርዳት ዝግጁ ነኝ ። ”

“ እስከዚህ ተከፍተሃል ?”

“ አዎ ከቡር እንደራሴ ፤ ወንደላጤ ሆኘ እንድቀር ቢረዱኝ እንዴት ባመሰግንኩዎ ነበር ።”

“ የማይቻል ነገር የለም !” አለ እንደራሴው ፈርጠም ብሎ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 30

እንደራሴው ሻሊቃ ባርቶሎሚዮ የተባለ ኢጣሊያዊ ወደቤቱ እንደሚመጣ አስታውቆ የአልበርትን ጥሪ ለመቀበል አለመቻሉን የገለጸው በትክክል ነበር ።

የግድግዳው ሰዓት አንድ ሰዓት ላይ ደወለ ። እንደራሴው ባዘዘው መሠረት ቢርቱሲዮ አውቲል ወደሚገኘው ቤት ከሄደ ሁለት ሰዓት አልፎታል ። መሐል ከተማ ከሚገኘው የእንደራሴው ቤት ፊት ለፊት አንድ ሠረገላ እንደ ቆመ ዕድሜው ሃምሳ ዓመት አካባቢ የሚሆነው ሰው ወረደ ።

ነገሩ እንቆቅልሽ ነበር ። የዚያ ዕለቱን ትርኢት ሚስጥር የሚያውቀው እንደራሴው ብቻ ነው ።

እንግዳው ወደ ሳሎን ሲገባ እንደሚችል ተነግሮት ሲጠባበቀው ከነበረው እንደራሴ ጋር የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጡ ።

" እንኳን ደህና መጣህ ወዳጄ ፤ " አለ እንደራሴው " ስጠብቅህ ነበር ። "

" እረረ . . . ? በርግጥ የሚጠብቁት ሰው እኔ ለመሆኔ እርግጠኛ ነዎ ?"

" በሚገባ ። ግን ከፈለግህ የበለጠ ማረጋገጥ እንችላለን ።"

" አይ ፤ እርስዎ እርግጠኛ ከሆኑ በቂ ነው ። " እንግዳው በመጠኑ የተረበሸ ይመስላል ።

" የለም ፤ የለም ፤ " አለ እንደራሴው ፤ " ለማንኛውም ሁለታችንም እርግጠኞች መሆን አለብን ፤ ባርቶሎሚዮ ማለት አንተ ነህ አይደለም ? "

" ባርቶሎሚዮ ፤" አለ እንግዳው በደስታ ተውጦ ፤ " አዎ እኔ ነኝ ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በአውስትሪያ ዘመቻ ወቅት ሻለቃ አልነበርህም ?”

“ ሻለቃ ነበርኩ አንዴ ?” ሲል ጠየቀ ሽማግሌው ወታደር እንደ ማፈር ብሎ ።

“ አዎ ሻለቃ ነበርህ ። ኢጣሊያ ውስጥ ለነበረህ ማዕረግ በፈረንሣይ የሚሰጠው አቻ ስም ሻለቅነት ነው ።”

“ በጣም ግሩም ነው ! ” አለ እንግዳው ።

“ በተጨማሪም ወደኔ የመጣኸው ከአንድ ሰው ተልከህ ነው።”

“ አዎ ። ”

“ የሰውዬው ስም ቄስ ቡሶኒ አይደለም ?”

“ ትክክል ነው !” አለ ሻለቃው በደስታ እየፈነደቀ ።

“ ደብዳቤ ይዘሃል ?”

“ ይኸው ። ”

“ እንደራሲው ደብዳቤውን ተቀብሎ ካነበበው በኋላ “ አዎ ፤ ልክ ነው ። ” አለ ።

ሻለቃ ባርተሎሚዮ ፤ ገቢው ግማሽ ሚሊዮን ። ስመጥር የኢጣሊያ መኳንንት ዘር ።

“ ግማሽ ሚሊዮን ነው ያሉት ?” ሲል ጠየቀ ሻለቃው ።

“ አዎና ! ይኸው ፤ በደብዳቤው ላይ ከመጻፉም በላይ ከቄስ ቡሶኒ የበለጠ ስለ አውሮፓ ሃብት የሚያውቅ ስለሌለ ውሸት ሊሆን አይችልም ።”

“ግን ይህን ያህል ብዙ መሆኑን አላውቅም ነበር ። ”

እንደራሲውዝም ብሎ ማንበቡን ቀጠለ ።

ደስተኛ ለመሆን አንድ ነገር ብቻ ይጉድለዋል ፤ በሕፃንነቱ በቤተሰቦቹ ጠላቶች ይሁን በቀማኞች በውል በማይታወቅ ሁኔታ የተነጠቀውን ውዳጁን ልጁን ማግኘት ። ክቡር እንደራሲ ፤ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያለ መታከት ሲፈልገው የነበረውን ልጁን እንዲያገኝ ሊረዱት እንደሚችሉ ተስፋ ስለሰጠሁት እንዲረዱት ፤ አደራ ።

ሻለቃው አይኑ በማይታወቅ አትኩሮት እንደራሲውን ተመለከተው ።

“ እንድታገኘው ልረዳህ እችላለሁ ። ” አለ እንደራሲው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ታዲያ ደብዳቤው ትክክለኛ ነው ማለት ነው ?"

" ትጠራጠረዋለህ ፤ሻለቃ ?"

"ኧረ በጭራሽም ! እንደ ቄስ ቡሶኒ ያለ ቁምነገረኛ ሰው እንዲህ ያለ ቀልድ አይቃጣውም ። . . . ግን ደብዳቤውንኮ እንብበው አልጨ ረሱም ፤ ክቡር እንደራሴ ?"

" አ! አዎ ሌላ ማሳሰቢያም አለው ።" ካለ በኋላ እንደራሴው ንባ ቡን ቀጠለ ።

ሻለቃ ባርቶሎሚዮ ገንዘቡን በማዛወር በኩል ችግር እንዳይገጥመው በማለት ከተበደሩት አርባ ስምንት ሺህ ፍራንክ በተጨማሪ ለመጓጓዣ ወጪ እንዲሆነው ሁለት ሺ ፍራንክ ልኪለሁ ።

ሻለቃው ማሳሰቢያውን በታላቅ ተመስጦ ነበር የሚከታተለው።

" መልካም ።" ብቻ ነበር እንደራሴው የሰጠው አስተያየት ።

" ማሳሰቢያው . . . " አለ ሻለቃው ።

" ምን ሆነ ?"

" ትክክል ነው አይደለም ?" ሲል ጠየቀ ሻለቃ ባርቶሎሚዮ ።

" ልክ ነው ። እኔና ቄስ ቡሶኒ አንድ የሽርክና ሂሳብ ከፍተናል ።"

" ታዲያ አርባ ስምንቱን ሺህ ፍራንክ ይሰጡኛል ?"

" በፈለግህ ጊዜ ።"

የሻለቃው አይኖች በአድናቆት ፈጠጡ ።

" እንግዲህ ሻለቃ " አለ እንደራሴው ፤ " በትውልድህም ሆነ በሃ ብትህ የምትከራ ሆነህ እያለ ደስተኛ ለመሆን አንድ ነገር ብቻ ይጐ ድልሃል ፣ አ ? "

" አንድ ነገር ብቻ ፤ ክቡር እንደራሴ ። "

" ያ አንድ ነገርም ልጅህን ማግኘት ነው ፤ አይደለም ?"

"አዎ ፤እንዲያውም በጣም የሚያንገበግበኝ ጉዳይ ይኸው ነው።" አለ ሻለቃው አይኖቹን በኃይል በመግለጥ ።

" ይህ ከሆነ ሻለቃ ባርቶሎሚዮ ፤ ስለዚህ ልጅ አንዳንድ ነገ ሮችን ለማወቅ እፈልጋለሁ ፤ ዕድሜ ልክህን ወንደላጤ እንደነበርህ ስለሰማሁ ግራ ገብቶኛል ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" ሰዎች እንደዚያ ይመስላቸዋል ፤ እኔ ግን . . . "

" አንተም ራስህ ይህንኑ ነገር ነው የምታስተጋባው ፤ በወጣትነትህ አንድ ወንጀል ስለፈጸምህ የልጅ እናትህ እንዳያስጠይቃት ፈርተህ ወንጀሉን ለመደበቅ ትሞክራለህ ። "

" አዎ ፤ የልጅ እናቷን እንዳያስጠይቃት "

" የልጅ እናትህ ኢጣሊያ ውስጥ ከታወቁ የመሳፍንት ዘሮች ትወለዳለች ፤ አይደለም ?"

" ትክክል ነው ፤ ጌታዬ ። "

" ስሟ ማን ነበር ?"

" ስሟን ማወቅ ይፈልጋሉ ?"

" አ ! ብትነግረኝም ዋጋ የለውም ። " አለ እንደራሴው ፤ " ቀደም ሲል አውቀዋለሁ ።"

" ሁሉንም ነገር ያውቁታላ ፤ ክቡር እንደራሴ " ቫለቃው አንገቱን አቀረቀረ ።

" ስሟ ኦሊቫ ነበር ፤ አይደለም ? "

" እውነት ነው ፤ ኦሊቫ ።"

" የቤተሰብ ተቃውሞ ችላ ብለህ ነው ያገባሃት አይደለም ?"

" አዎ ፤ ቢቃወሙኝም በመጨረሻው አገባሁዋት ።"

" ማስረጃዎችህን አምጥተሃል ?"

" የምን ማስረጃዎች ? " ሲል ጠየቀ ቫለቃ ባርቶሎሚዮ ።

" የጋብቻና የልጁ የልደት የምስክር ወረቀት ። በነገራችን ላይ የልጁ ስም አንድሪያ አይደለም ?"

" ይመስለኛል ።"

" ይመስልሃል ?"

" እርግጡን ለመናገር ያዳግተኛል . . . ካየሁት ረጅም ጊዜ አልፏል ።"

" እሱስ ይሁን " አለ እንደራሴው ፤ " ግን የምስክር ወረቀቶቹን ይዘሃል ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

" በጣም አዝናለሁ ። አስፈላጊ መሆናቸውን የነገረኝ አልነበረም ፤ ትቻቸው መጣሁ ፤ ለመሆኑ ያስፈልጉ ኖሯል ?"

" በጥብቅ ያስፈልጋሉ ። የማስረጃዎቹ አለመኖር ምናልባት ከአንድ ጥሩ ጋብቻ ሳያግደው አይቀርም ። ፈረንሳይ ውስጥ እንደ ኢጣሊያው ባህል ወደቄስ ሄዶ ፤ ' እርስ በርሳችን እንፋቀራለን ፤ እባክዎ አጋቡን ' ማለት በቂ አይደለም ። ማንኛውም ሰው ማንነቱን የሚያረጋግጥበት የልማት ማስረጃ መያዝ አለበት ። ያም ሆነ ይህ የጠየቅሁህ ማስረጃዎች እኔ ዘንድ ይገኛሉ ። "

" እርስዎ ይዘዋቸዋል ?"

" አዎ ። "

" በጣም ግሩም " አለ ቫለቃው ፤ የማስረጃዎቹ አለመኖር በአርባ ስምንቱ ሺህ ፍራንክ ላይ ችግር እንዳያስከትል ሲፈራ በመቆየቱ እፎይታ እየተሰማው ። " እርስዎ ማስረጃዎቹ ይኖሩዎታል ብዬ አላሰብ ኩም ነበር ። "

" አንድ ሰው ሁሉንም አስቦ አይችልም ። እንደ እድል ሆኖ ቄስ ቡሶኒ ሁሉንም አዘጋጅተውልህ ኖሯል ። "

" እንዴት የሚደነቁ ሰው ናቸው ፤ ለእርስዎ ላኩልዎ ?"

" እኚሁልህ ። በጥንቃቄ እንዲይዛቸው ነግረህ ለልጅህ ስጥ ። የእነዚህ ማስረጃዎች ጠቀሜታ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ሳታውቅ አልቀረህም ። "

" ጥቅማቸው በምንም ሊገመት አይችልም ። "

" አሁን ስለልጅህ እናት . . . "

" ያንት ያለህ ! " አለ ቫለቃው ። " እርሷም ታስፈልገናለች ?"

" አይ አታስፈልገንም ። " በማለት መለሰ እንደራሴው ፤ " ብታ ስፈልገንስ . . . የተፈጥሮ . . . "

" አዎ ጌታዬ የተፈጥሮ . . . ."

" ግዴታዋን በመወጣት ከዚህች ዓለም ተሰናብታ የለም ።"

" እህ ፤ ልክ ነው ። "

"ከሞተች አሥር ዓመት አካባቢ ሆኗታል ሲሉ ነው የሰማሁት ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እስካሁን አልረሣህ ኦለችኝ ” በማለት ቫለቃው ከኪሱ መሐ ረብ አውጥቶ አይኖቹን ይጠራርግ ጀመር ።

“ መርሳት ነው እንጂ ቫለቃ ፤ ሁላችንስ ከሞት መች እንቀራለን ። በንግራችን ላይ ትዝታህን ከቀሰቀስኩት አይቀር አንድ የቆጠብኩት አዲስ ዜና እንዳዘጋጀሁልህ ሳትገምት አትቀርም ።”

“ ወይ እድሌ ! ጥሩ ዜና ይሆን ?”

“ መቼም የአባትን አይንና ልብ ማታለል አይቻልም ። እዚህ እንዳስቀመጥኩት ታውቀዋለህ አይደለም ?”

“ ማንን ነው ያስቀመጡት ?”

“ ልጅህን ነዋ ! አንዱን ልጅህን ፤ አንድሪያን !”

“ ኧረረ . . . . ?”

“ ስሜትህ ገብቶኛል ። ራስህን እስከታረጋጋ ጊዜ መስጠት አለ ብኝ ። ከዚያም በተጨማሪ አንዳንት ትዕግሥት አጥቶ የሚቅበጠበጠ ውን ወጣት ልጅህንም ለዚሁ ደስታ እንዲዘጋጅ እፈልጋለሁ ። ወደ ዚህ ክፍል የምልክልህ ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ይሆናል ።”

“ በንግራችን ላይ ” አለ ቫለቃው ፤ “የንበረኝ ሁለት ሺህ ፍራንክ ብቻ ሲሆን አሁን . . . .”

“ አሁን ገንዘብ ትፈልጋለህ ፤ አይደለም ? በርግጥ ያስፈልግሃል ። እንካ ስምንት ሺህ ። አርባ ሺህ ፍራንክ ይቀርሃል ።”

“ ደረሰኝ ይፈልጋሉ ፤ ክቡር እንደራሴ ?” አለ ቫለቃው አይ ኖቹ እያበሩ ።

“ ደረሰኙን የምትሰጠኝ ሁሉንም ወስደህ ስትጨርስ ይሆናል ። በሚተማመኑ ሰዎች መካከል እንዲህ ያለ ነገር ጥሩ አይደለም ።”

“ አዎ ፤ እሱስ ልክ ነው ።”

“ በል እንግዲህ ቫለቃ ባርቶሎሚዮ ” አለ እንደራሴው ፤ “ ልጅ ህን አንድሪያን ለማዬት ራስህን አዘጋጅ ።” እንደራሴው ከክፍሉ ወጥቶ ሄደ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

‘ አባትህ አቤቱ በመጣበት ሰዓት ’ የሚለውን ንግግር ሲሰማ ግን ወጣቱ አንድሪያ እንደመንግስት እየታጣው ፤ “ አባቴ ! የኔ አባት እዚህ አለ ?” ሲል ጮኸ ።

“ አዎ” ሲል መለሰ እንደራሴው ፤ “ አባትህ ሻለቃ ባርቶሎሚዮ እዚህ አለ ። ”

የአንድሪያ የተሸበረ መንፈስ ወዲያውኑ ተረጋጋ ። “ በርግጥ የእኔ አባት ያሉት ሻለቃ ባርቶሎሚዮ አሁን እዚህ ግቢ አለ ፤ ክቡር እንደ ራሴ ?”

“ አዎ ፤ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ታገኘዋለህ ። ምናልባት ሁኔታው ኩሩና ግድየለሽ ይመስልህ ይሆናል ፤ ተፈጥሮ ሆኖ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ በውትድርና በመቆየቱ ነው ። በዚያ ላይ መቸስ ሐብት ብዙ ነገ ሮችን ችላ እንድንል ማድረጉ የተለመደ ነው ።”

“ አባቴ ሐብታም ነው ማለት ነዋ ?”

“ ሐብቱ በቁጥር የሚቀመጥ አይምሰልህ ። የትዬለሌ ነው ።”

“ እንግዲያውማ አልከፋም ማለት ነዋ ። ” አለ ወጣቱ አንድሪያ በጉጉት ።

“ እጅግ ደስተኛ ትሆናለህ ። ፓሪስ ውስጥ እስከቆዩህ ጊዜ ድረስ የአምሳ ሺህ ፍራንክ አበል ሊያስብልህ አቅዷል ። ”

“ እሱም ፓሪስ ውስጥ ረጅም ጊዜ የመቆየት ዓላማ አለው ?”

“ ሥራ ስለሚበዛበት ጥቂት ጊዜ ከሰነበተ በኋላ ይሄዳል ።”

“ ወይኔ አባቴ ” አለ አንድሪያ ፤ በምጸት ።

“ መልካም ” አለ እንደራሴው የአንድሪያ አነጋገር ያልገባው ለመምሰል እየጣረ ። “ ብዙ እንድትቆይ አላደርግህም ።ተቻኩለሃልና ወደሚቀጥለው ክፍል ሄደህ ከአባትህ ተገናኝ ። ”

አንድሪያ ወደሚቀጥለው ክፍል እንደገባ እንደራሴው አንድ የተሰወረ ስፕሪንግ ነካ ሲያደርግ በግድግዳው ላይ ያለው ሥዕል ወደ ጐን በመንሸራተት የተገለጠው ቀዳዳ የሚቀጥለውን ክፍል ያሳይ ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንድሪያ በሩን ዘግቶ ወደ ቫለቃው ተራመደ ። ቫለቃው የእንድሪያን የእግር እርምጃ እንደሰማ ከተቀመጠበት ተነስቶ ይጠባበቀው ኖሯል ።

" አባቴ ! " አለ እንድሪያ ድምጹን ለእንደራሲው እንዲሰማ ከፍ አድርጎ ! " በርግጥ አንተ ነህ ?"

" አዎ ልጄ ። " አለ ቫለቃው ።

" ከብዙ ዘመናት መለያዬት በኋላ ምን የተባረከ ቀን አገናኘን ?" በማለት እንድሪያ ወደ በሩ እየተመለከተ ንግግሩን ቀጠለ ።

" አዎ ልጄ ! ረጅም ዘመናት ተለያይተን ቆየን ። "

" አሁንስ እንደገና እንለያያለን ?"

" ይመስለኛል ልጄ ። አንተ ፈረንሣይ ውስጥ ሳትቆይ አትቀርም አይደለም ? "

" እውነቱን ለመናገር ከፓሪስ ከምወጣ የዕለት ሞቴን ቢሰጠኝ ይቫለኛል ። " አለ እንድሪያ ።

" እኔ ደግሞ ከኢጣሊያ ውጭ መኖር አልችልም ፤ አሁንም ቢሆን ቶሎ ለመመለስ እፈልጋለሁ ።"

" ግን ከመሄድህ በፊት አባባ ፤ ካንተ መወለዴን እንዳስመሰከር ርበት የልደት ማስረጃዬን ትሰጠኛለህ ።እሽ ?"

"አዎ ! ተጣድፌ የመጣሁትም ማስረጃውን ልሰጥህ ነው ። እንካ ።"

እንድሪያ ወረቀቶቹን በአትኩሮትና ልምድ ያላቸውን አይኖች በሚያስመሰክር ፍጥነት መረመራቸው ። ከዚያም ቫለቃውን ግራ በሚያጋባ ፈገግታ በመመልከት በጠራ ኢጣሊያኛ " ኢጣሊያ ውስጥ እሥር ቤት የለም እንዴ ?" አለው ።

" ምን ማለትህ ነው ?"

" ፈረንሣይ ውስጥ እንዲህ ያለው ውስልትና አምስት ዓመት ያስቀፈድዳል ።"

"እባክህ ቀልዱን እናቁም ።" አለ ቫለቃው እንደመኩራት እያለ



t.me/OLDBOOKSPDF

" የእኔ አባት በመሆንህ ስንት ይከፈልሃል ?" ሲል ጠየቀ አን ድሪያ የሻለቃውን ክንድ ጭምቅ እያደረገ ። ሻለቃው ሊናገር ሲጀምር አንድሪያ " ሽ . . . ." አለ ድምጹን ዝቅ አድርጐ ፤ " አዬህ ፤ የሚስ ጥር ተካፋይህ ለመሆኔ አንድ ምሳሌ ልስጥህ ። እኔ የአንተ ልጅ በመ ሆኔ በዓመት አምሳ ሺህ ፍራንክ ሊያስቡልኝ ነው ።"

ሻለቃው ዙሪያውን በጥርጣሬ ተመለከተ ።

" አ! አትጨነቅ . . . ማንም የለም " አለ አንድሪያ ፤ " በዚያ ላይ አሁን የምንነጋገረው በኢጣሊያኛ ነው ። "

" እ . . . . . እኔም አምሳ ሺ የተጣራ ፍራንክ ሊከፈለኝ ነው ።"

" ሻለቃ ባርቶሎሚዮ ፤ በእፈ ታሪክ ታምናለህ ? "

" በፊት አላምንም ነበር ፤ አሁን ግን ወደዚያው ነኝ ።"

" ታዲያ የእንደራሴውን ቃል እመን ትለኛለህ ?"

" አዎ ፤ ግን እኔ የአንተ አባት እንድሆን እስከጠየቁ ድረስ እኛም የበኩላችንን ተግባር ማከናወን አለብን ።"

" እነማን ናቸው እነሱ ?"

" እኔ እንጃ . . . . .ደብዳቤውን የጻፉልን ናቸዋ !"

" ደብዳቤ ደርሶሃል ? "

" አዎ ። " አለ ሻለቃው ።

" ከማን ?"

" ቄስ ቡሶኒ ከተባለ ሰው ። "

" ታውቀዋለህ ?"

" ኧረ አላውቀውም ።"

" ደብዳቤው ላይ ምን ተጽፎ ነበር ?"

" ለማንም አትናገርም ?"

" ለምን ብዬ ነው የምናገረው ፤ ፍላጐታችን ተመሳሳይ አይደ ለም ?"

" በል አንብብ እንግዲያውስ ።"

አንድሪያ ደብዳቤውን ያነብ ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በሁሉም ነገር ። ”

“ እረ ለመሆኑ ስለዚህ ሁሉ ነገር የገባህ ሚስጥር አለ ? ”

“ ምንም አልገባኝ ። ብቻ እስከመጨረሻው ጉዳን ማየት ነው የሚሻለን ።”

“ እንደራሴው ይህች ቅጽበት አመቺ መሆኗን መርጦ ሁለቱ ሰዎች ወደሚነጋገሩበት ክፍል ገባ ። የእግሩን እርምጃ ሲሰሙ ሰዎቹ እርስ በርሳቸው ተቃቀፉ ።

“ ልጅህን በፈለግኸው መሠረት ያገኘኸው ትመስላለህ ፤ ሻለቃ ።” አለ እንደራሴው ።

“ ደስታዬን መቆጣጠር አልቻልኩም ።” አለ ሻለቃው ።

“ አንተስ አንድሪያ ?”

“ ክቡር እንደራሴ ፤ ደስታ ሊያሳብደኝ ነው ።”

“ በጣም ጥሩ “ አለ እንደራሴው ።“ አሁን እንግዲህ ልትሄዱ ትችላላችሁ ።”

“ መቼ ይሆን እንደገና ተመልሰን የምንጠይቅዎ ?” ሲል ጠየቀ ሻለቃው ። አንድሪያም ይህንኑ ጥያቄ በመድገም አስተጋባ ።

“ ከፈለጋችሁ በመጭው ቅዳሜ ይመቻል ። ከከተማ ውጭ ባለው ቤቴ ብዙ ሰዎችን ለራት ግብዣ ጠርቻለሁ ።”

“ ምን ሰዓት ብንመጣ ይሻላል ?” በማለት ጠየቀ አንድሪያ ።

“ ወደ አሥራ ሁለት ተኩል ገደማ ።”

“ እንቀርም ! ” አለ ሻለቃው ባርኔጣውን እያነሣ ።

ሁለቱ ሰዎች እጅ ነስተው ወጡ ። እንደራሴው ወደ መስኮቱ ተጠግቶ እጅ ለእጅ ተያይዘው መንገዱን ሲያቋርጡ አያቸው ።“ጥን ድ ወረበሎች !” አለ ለራሱ ፤ “ በእርግጥ አባትና ልጅ አለመሆናቸውን እያወቁ ሲያስመስሉ የማያፍሩ ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

# 31

ማክሲሚለን ጥሪል የቪልፎትን መኖሪያ ቤት አጥር ተደግፎ በንቁ አይኖቹ አሾልኮ እየተመለከተ ያዳምጣል ። በሥፍራው ደርሶ ብዙም ሳይቆይ ነበር በአሸዋ ላይ የሚራመድ የነጠላ ጫማ ድምጽ ዓይነት ርምጃ የተሰማው ።

እርምጃው እየቀረበ በመጣ መጠን ግን የአንድ ሣይሆን የሁለት ሰው ጥላ ታየው ። ማክሲሚለን በሰዓቱ ልትደርስለት ያልቻለ ችበትን ምክንያት እንዲረዳላት በማለት ቫለንቲን ወይዘሮት ኢዩጊንን ስበብ ፈጥራ በጓሮው በኩል ይዛት በመውጣት የሆነ ያልሆነውን እያ ወራችላት ወዲያ ወዲህ ይመላለሳሉ ። እመቤት ዳንግላርና ወይዘሮት ኢዩጊን ከቪልፎርት ቤት በማምሸታቸው ቫለንቲን በቀጠሮው ሰዓት ልትመጣ አለመቻሏን የተረዳው በዚህ ወቅት ነበር ።

ማክሲሚለን በፍቅረኛ ፈጣን ልቡና ሁሉንም ነገር ተገንዝቦ እፎይታ ተሰማው ። ሁለቱ ልጃገረዶች ግማሽ ሰዓት ያህል በጓሮው ሲመላለሱ ከቆዩ በኋላ ወደ ቤት ሲመለሱ ማክሲሚለን የእንግዶቹ ቆይታ በመገባደድ ላይ መሆኑን ገመተ ።

ከብዙ ቆይታ በኋላ ቫለንቲን ብቻዋን ብቅ አለች ። ሆኖም ፡ ተመልሳ ወደጓሮ መሄዷ እንዳይታወቅባት ቀስ ብላ በመንዝ በቀጥታ ወደ ማክሲሚለን ከማምራት ይልቅ በዛፎች መካከል ከሚገኝ ወንበር ላይ ተቀምጣ ዙሪያዋን ተመለከተች ። ከዚያም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካደረገች በኋላ ወደ ማክሲሚለን ሮጣ ሄደች ።

“ ታዲያስ ቫለንቲን ። ” አለ የፍቅረኛዋ ድምጽ ።

“ ታዲያስ ማክሲሚለን ፡ አስጠበቅሁህ ። ግን ምክንያቱን አውቀሃል አይደል ?”

“ አዎ ! ኢዩጊንን አየሁአት ። ሁለታችሁ እንዲህ የምትቀራረቡ ጓደኞች መሆናችሁን አላውቅም ነበር ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እህ . . . " አለ ማክሲሚለን በትዝብት ራሱን እየነቀነቀ ፣ " በእንዲት ውብና ለግላጋ እመቤት ላይ እንዲህ ዓይነቱ ስግብግብነት ሲታይ ያስገርማል ።"

" ለእርሷ ግድ፡ሆነ ልጅዋ መሆኑን አትርሳ ። የኮንንከው ስግብግ ብነቷ እንደ አምልኮ ኃያል ከሆነ የእናት ፍቅር የመነጨ ነው ።"

" ግን ለምን ከራሉን ሃብትሽን ዝም ብለሽ ለልጅዋ አትሰጭውም? ለዚያውም ወንድምሽ ነው ።"

" ስለ ራሷ ስሜት የለሽነት ከምታወራ ሴት ጋር እንዴት አድርጌ ይህን አስተያየት ማቅረብ እችላለሁ ? . . . ስማ እየተጠራሁ ነው ። "

" ቫለንቲን " አለ ማክሲሚለን ፣ " እባክሽ በቀዳዳው በኩል ትንሿን ጣትሽን አሳልፊልኝና ልሳማት ?!"

" ትንሿን ጣቱን መሣም ያስደስትሃል ? "

" አ . . . . አዎ ። "

ቫለንቲን ከእጥሩ ተጠግቶ በተሠራው ወንበር ላይ ቆማ ከፍ ብሎ በሚታየው ቀዳዳ በኩል ትንሿን ጣቷን ብቻ ሳይሆን እጅዋን ሙሉ ለሙሉ አሳለፈችለት ። ማክሲሚለን ተወዳጁን እጅ ያዝ አድርጐ በጉጉት ወደ ከንፈሩ ከማስጠጋቱ ያ እጅ ድንገት ተመልሶ በቀዳዳው ውስጥ ገባ ። ወዲያውም ቫለንቲን በራሷ ስሜት ተደናግጣ ሣይሆን አይቀርም ወደ ቤቷ ስትሮጥ ታየው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኖርቴር አልሃቸው ቢያልቅም ከውስጥ የታመቀው ሃይልና ወኔ ወደ ውጭ በመገንፈል ውጤት ሲያሳይ እንደማይችል ያውቃሉ ። “ ገብቶኛል” አሉ በዓይኖቻቸው ታላቅ ቁጣን በሚገልጽ ምልክት። ቪልፎርት ምልክቱን ስለተረዳ በተራው ክትክሻው በጥቂቱ ነቅንቆ በማለት መልስ ሰጠ፡ከዚያም ሚስቱን እንድትነሳ ጠቆም አደረጋት ።

“ አሁን መሄድ አለብኝ።” አለች እመቤት ቪልፎርት ፤“ ኤድዋርድን እጅ እንዲነሣ ልላከው ?”

ሽማግሌው ዓይኖቻቸውን አንድ ጊዜ ብቻ ሲከድኑ በነገር እንደ ተስማሙ ፤ ደጋግመው ሲጨፍኑ እንደ ተቃወሙ ፤ ወደ ጣራ ሲመለከቱ አንድ ነገር እንዳስፈለጋቸው ይተረጎማል ። ቫለንቲንን አፈልጋ ሲሁ ካሉ የቀኝ ዓይናቸውን ብቻ ይከድናሉ፤ አሽከራቸውን ባሮይስን ከፈለጉ ደግሞ የግራ ዓይናቸውን ።

እመቤት ቪልፎርት ኤድዋርድን ለመላክ ላቀረበችው ጥያቄ ኖርቲር የሰጡት መልስ ዓይናቸውን በችኩላ ደጋግመው መጨፈን ነበር ። ተቃውሞ ! እመቤት ቪልፎርት በዚህ ተቃውሞ ከንፈሯን ከነከሰች በኋላ፤ “ታዲያ ቫለንቲንን ልላክልዎ ?” ስትል ጠየቀች ።

“አዎ።” አሉ ኖርቲር ወዲያውኑ ዓይኖቻቸውን አንድ ጊዜ ብቻ በመክደን ። ባልና ሚስት እጅ ነስተው ከክፍሉ ወጡ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቫለንቲን ገባች ። ገና በጨረፍታ ስትመለከታቸው አያቷ ምን ያህል እንደበገኑና ብዙ የሚነግሯት ነገር እን ዳለ ተረዳች ። “አባባ !” አለች ቫለንቲን ቁጭታቸው እንዲብርድ የትጫ“ ምን ተፈጠረ ? የተናደድክበት ነገር አለ አይደለም ?”

“ አዎ !” አሉ ኖርቲር ዓይናቸውን ክደን በማድረግ ።

“ በማን ነው የተናደድከው ? በአባቴ ?”

“ አይደለም።” አሉ ሽማግሌው ዓይኖቻቸውን ደጋግመው በመ ጨፈን ።

“ በእንጀራ እናቴ ?”

“ አይደለም ። ”

“ በእኔ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እዎ ።" በማለት አሁንም ኖርቴር ዓይናቸውን ከደኑ ።

" እንዴት ያስገርማል።" አሉ ኑዛዜ ተቀባዩ ቪልፎርት እንዲ በአድናቆት ራሱን ሲነቀንቅ ተመልክተው ።

" እዎ፤ግን ኑዛዜው ደግሞ ይበልጥ የሚያስደንቅ ይመስለኛል ።" አለ ቪልፎርት " በኑዛዜው ላይ ሊሰፍር የሚችለው የእሱ ትክክለኛ ቃል ሳይሆን የልጅቷ ግምት ነው ። ልጅቷ ደግሞ የኖርቴርን ሃሣብ በትክክል ለመተርጐም የምትችል አይመስለኝም ። ወደ ራሷ ፍላጐት ልታጣምመው ትችላለች ።"

" የለም ፤ የለም !" በሚል ዓይነት ኖርቴር ዓይኖቻቸውን በፍጥነት ደጋግመው ጨፈኑ ።

" መሴ ቪልፎርት " አለ ኑዛዜ ተቀባዩ ይህንን ግራ የሚያጋባ ሁኔታ በማገናዘብ ፤" አሁን ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኖልኛል ። በሰባት ምስክሮች ፊት ተነቦ እነሱ ባሉበት በኑዛዜ ተቀባይ ሲፈረም ሕጋዊ ኑዛዜ ይሆናል ። በተጨማሪም ፍጹም የማይናወጥ ለማድረግ አንድ ጓደኛዬ እንዲረዳኝ ኑዛዜው ሲጻፍ እንዲገኝ ማድረግ አለብኝ ።ይህ ያረካዎታል መሴ ኖርቴር ?"

"እዎ።" አሉ ኖርቴር ሃሳባቸውን ስለተረዱላቸው ልባቸው በደስታ እየዘለለ ። ሁሉንም ነገር ሲያዳምጥ የነበረውና የጌታውን ፍላጐት በደንብ ያጤነው ባሮይስ ሁለተኛውን ኑዛዜ ተቀባይ ለማምጣት ጉዞውን ጀምሮ ነበር ።

ቪልፎርት ሚስቱ እንድትመጣ ላከ ። በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ሁለተኛውን ኑዛዜ ተቀባይ ጨምሮ ሁሉም ሰው በኖርቴር ክፍል ተሰበሰበ ።

" የሐብትዎን መጠን በዝርዝር ያውቃሉ ?" አለ የመጀመሪያው ኑዛዜ ተቀባይ ።

"እዎ።" ሲሉ ኖርቴር ምልክት ሰጡ ።

" አራት መቶ ሺህ ፍራንክ ይኖርዎታል ?"

የኖርቴር ዓይኖች ምልክት አልሰጡም ።

"አምስት መቶ ሺ ፣ ስድስት ፣ ሰባት፣ ስምንት ፣ ዘጠኝ ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘጠኝ ቁጥር ሲጠራ የኖርቴር ዓይኖች ተከደኑ ።

" ዘጠኝ መቶ ሺህ ፍራንክ አለዎ ?"

አሁንም ዓይኖቹ በእምንታ ተከደኑ ።

" ይህንን ሐብት ለማን ለማውረስ ይፈልጋሉ ?ለወይዘሪት ቫለንቲን ?"

የኖርቴር ዓይኖች በተቃውሞ ተርገበገቡ ።

" አለመሳሳትዎን እርግጠኛ ነዎ?" ሲል ጠየቀ ኑዛዜ ተቀባዩ ተገርሞ ።

"አይሆንም ።" በማለት ኖርቴር አይኖቻቸውን በተደጋጋሚ ጨፈኑ ።

ቫለንቲን ከውርስ በመገለሏ ሣይሆን አያቷን እንዲቀየሟት ያደረገ ጥፋት መች እንደሠራች በማሰላሰል በሃሣብ ተመሰጠች። ኖርቴር ግን ልጃገረዷን በአፍቅሮት አስተያየት ሲመለከቷት ልቧ ተነካ።"እሰይ አባባ ፣ ለካስ ሀብትህን እንጅ ፍቅርህን አልነፈግኸኝም።" አለች።

" አዎ ፣ አዎ ፣ያለጥርጥር " የሚሉት የኖርቴር ዓይኖች ለቫለንቲን አእምሮ ታላቅ እፎይታ ሰጡ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኑዛዜው አቅጣጫ በእመቤት ቪልፎርት ዘንድ ያልተጠበቀ ተስፋ ፈንጥቆ ነበር ። ወደ ሽማግሌው ጠጋ ብላ "ለኤድዋርድ ይሆን ሀብትዎን ሊሰጡ የፈለጉት?" ስትል በሹክሹክታ ጠየቀች ።

በዚህ ጊዜ ኖርቴር ዓይኖቻቸውን በሚያስፈራ ሁኔታ ደጋግመው ሲጨፍኗቸው ለተመለከተ ከተቃውሞ አልፈው ጥላቻን ያንጸባርቁ ነበር ።

" ለእርስዎ ልጅ ነው? ለመሴ ቪልፎርት ?" ሲል ጠየቀ ኑዛዜ ተቀባዩ ።

" አይደለም ።"

ሁለቱ ኑዛዜ ተቀባዮች በሁኔታው ግራ ተጋብተው እርስ በርሳቸው ተያዩ ። ቪልፎርትና ሚስቱም አንድም በሐፍረት ፣ በሌላ በኩልም በንዴት ጨሱ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ታዲያ ሁላችንስ ምን እያረግንህ አባባ ?” ስትል ጠየቀች ቫለንቲን ። ኖርቴር ዓይናቸውን በቫለንቲን እጅ ላይ ጣል አደረጉ።

“ የኔ እጅ ?” ስትል ጠየቀች ።

“ አዎ ።”

“ እዬ . . . እያችሁ ድካማችን ምን ያህል መና እንደሆነ፤ ምስኪን አባቴ አብዷል ። ” አለ ቪልፎርት ።

“ አሃ” ስትል ጮኸች ቫለንቲን በድንገት፤ “ገባኝ። ጋብቻዬ ነው አይደለም አባባ ?”

“ አዎ ! አዎ ! አዎ ! ”

“ የታቀደው ጋብቻ አስከፍቶሃል አይደለም ?”

“ አዎ ።”

“ ፍራንዝን እንዳገባው አትፈልግም አይደለም ?”

“ አዎ ።”

“ የልጅ ልጅዎን ከውርስ ያገለሏት ከፍላጐትዎ ውጭ ልታገባ በመሆኑ ነው ?” ሲሉ ጠየቁ ኑዛዜ ተቀባዩ ።

“ አዎ ።”

“ ታዲያ ወይዘሪት ቫለንቲን ፍራንዝን የምታገባ ከሆነ ሃብትዎን ለማን ያወርሳሉ ? ለሌላ የቤተሰብ አባል ?”

“ አይደለም ።”

“ ለድሃ እንዲመጸዎት ይናዘዛሉ ?”

“ አዎ ።”

“ በዚህ ሁኔታ ላይ እርስዎ የሚወስኑት ምንድን ነው መሴ ቪልፎርት ? ሲሉ ጠየቁ ኑዛዜ ተቀባዩ ።

“ ምንም ። አባቴ ሃሣቡን እንደማይለውጥ ስለማውቅ ራሴን ከውዝግቡ ውጭ አድርጌአለሁ ። ገና ለገና የሱ ዘጠኝ መቶ ሺህ ፍራንክ ለቤተሰቤ ይቀርበታል ብዬ ላንድ አዛውንት ግትር ሃሣብ አላጐበድድም ። ሁሉም ነገር በራሴ ፈቃድ መሠረት ይፈጸማል ፤ ፍራንዝን ታገባለች ታገባለች ።”

ቪልፎርት አባቱ የመሰላቸውን እንዲናዘዙ ትቷቸው ከሚስቱ ጋር ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 33

አውቴል የሚገኘውን የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ቤት ከውጭ ሲመለከቱት በአካባቢው ከሚገኙት ተራ ቤቶች የተለየ ውበት ስለ ማይታይበት ከበርቴው እንደራሴ ለምን እንደመረጠው ግራ ያጋባል ። ይሁን እንጅ ይህ ተራ ውጫዊ ገጽታ አንድም መሻሻል ሳይደረግበት በበፊቱ ሁኔታ እንዳለ እንዲቆይ ያደረገው የእንደራሴው ፍላጐት ነበር።

ልክ በሩ ሲከፈት ግን ሁኔታው ፈጽሞ የተለየ ይሆናል ። ቤር ቱሲዮ የተባለው ባለሟል በቤት እቃ አመራረጡና ሥራውን ሲያከናውን ያለውን ጥበብ ያሳየበት ታላቅ ተሰጥኦ በዚህ ቤት ክፍሎች ውበት ላይ ሙሉ በሙሉ ተንጸባርቋል ።

ሆኖም ብዛት ካላቸው የቤቱ ክፍሎች መካከል በተለይ አንድ የውስጥ ደረጃ ያለው የመኝታ ክፍል እድሳት አልተደረገለትም ። ይህም እንዲሆን ያደረገው እንደራሴው ነበር ። የቤቱ ሠራተኞች በዚህ ክፍል በኩል ሲያልፉ አንዳች ነገር ያለበት ይመስል በጉጉት ገልመጥ ብለው ሳይመለከቱት አያልፉም ። ቤርቱሲዮ ግን ሲያየው መላ መንፈሱን ስለሚያውከው ዓይኑን አሳርፎበት አያውቅም ።

በዚህ ቅጥር ግቢ ነበር የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ የራት ግብዣውን ያዘጋጀው ። ልክ አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ማክሲሚለን ሞረል ከፈረሱ ሲወርድ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ከፊት ለፊቱ ደረጃ ላይ እየወረደ በፈገግታ ተቀበለው ።

“ የቀደመኝ ሰው እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ።” አለ ማክሲሚለን፤ “ሌሎች ከመድረሳቸው በፊት ብቻችንን እንድንጫወት እፈልጋለሁ።” ሆኖም በዚያው ቅጽበት በሁለት ፈረሰኞች የሚታጀብ ሠረገላ ከግቢው ፊት ለፊት ቆመ ። ደብራይ የተባለው የአገር አስተዳደር ሚኒስትር ጸሐፊ በፍጥነት ከፈረሱ ወርዶ የሠረገላውን በር ከከፈተ በኋላ ለእመቤት ዳንግላር እጁን ዘረጋላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዳንግላር ከሚስቱ ቀጥሎ ወረደ ። መልኩ ከመለዋወጡ የተ ነሳ ከሠረገላ ሳይሆን ከመቃብር የሚወጣ ይመስል ነበር ። ወደ ግቢው ሲገባም ከሕልም የባነነ ይመስል ዓይኖቹን ማሻሸት ያዘ ።

ቀጥሎ ጂሙን አሳምር የተላጨው ሻለቃ ባርቶሎሚዮ በአዲስ ልብስ የተለበጠውን ልጁን አንድሪያን ከጐኑ አድርጐ ገባ ። ከፍሉ ውስጥ ቀደም ሲል የገቡት እንግዶች ሁሉ ዓይናቸውን በባርቶሎሚ ዮና በአንድሪያ ላይ አሳረፉ ።

" እነዚያ ሁለት ሰዎች ደግሞ እነማን ናቸው ? " አለ ዳንግላር እንደደራሲውን ።

" ሻለቃ ባርቶሎሚዮና ልጁ ።"

" አላውቃቸውም ። "

" አዎ ፤ ከኢጣሊያ መሳፍንት ጋር በደንብ ሳይተዋወቁ ይችላሉ። ባርቶሎሚዮ የመሳፍንት ዘር ነው ። "

" በሃብት በኩልስ ? "

" ተወዳዳሪ የላቸውም ። "

" የሚያንቀሳቅሱት ድርጅት አላቸው ? " ሲል ጠየቀ ዳንግላር ።

" ሐብታቸውን በሙሉ ለማንቀሳቀስ ይፈልጋሉ ። በነገራችን ላይ ከትናንት በስቲያ እንደነገሩኝ ከእርስዎ ድርጅት ጋርም ኢጣሊያ ውስጥ ሸርክና ሳይከፍቱ አይቀሩም ። በርግጥ ለርስዎ ስልም ነው ዛሬ እዚህ እንዲገኙ የጠራሁአቸው ። አስተዋውቃችኋለሁ ። "

" ፈረንሳይኛ አጣርተው ይናገራሉ ልበል ? "

" ልጅየው የተማረው ፈረንሳይ ወ ስጥ ነው ። በፈረንሳይ ሴቶች ላይ ታላቅ ፍላጐት አለው ። እንዲያወ ም ፓሪስ ወ ስጥ ሚስት የምት ሆነው ሴት በማፈላለግ ላይ ነው ። "

" በጣም ጥሩ ሃሳብ ነው ። " አለ ዳንግላር ሳቅ ብሎ ።

እመቤት ዳንግላር ባለቤቷን በቁጣ ዓይን ስትገላምጠው ብት ቆይም በተለይ በዚህ ንግግራቸው ዝም አለች ።

ቪልፎርት ከነሚስቱ ገባ ። ቪልፎርት ራሱን ለመቆጣጠር ጥረት ቢያደርግም ሃሳቡ በአንድ ነገር እንደተወጠረ ግልጽ ነበር ። እን



t.me/OLDBOOKSPDF

ደራሴው ቪልፎርትን በሚጨብጥበት ጊዜ እጁ ይንቀጠቀጥ እንደነበር ለማወቅ አላስቸገረውም ። ' ጭንቀታቸውን ማመቅ የሚችሉት ሴቶች ብቻ ናቸው ' ሲል አሰበ እንደራሴው እመቤት ዳንግላር ቪልፎር ትንና ሚስቱን በተዝናና አኳኋን ሰላምታ ስታቀርብላቸው ተመልክቶ።

እንደራሴው ዘወር ሲል እንግዶቹ ከሚስተናገዱበት ክፍል ቀጥሎ ባለችው አነስተኛ ሳሎን ውስጥ ቤርቱሲዮን ተመለከተው ። ወደሱ ሄዶ " የምትፈልገው ነገር አለ ቤርቱሲዮ ? " ሲል ጠየቀ ።

" ለራት ስንት ቦታዎች ማዘጋጀት እንዳለብኝ አልነገሩኝምኮ ?"

" አዎ ፣ ልክ ነህ ። ግን እንግዶቹን መቁጠርምኮ ትችል ነበር ።"

" ከእንግዱህ የሚመጣ ሰው የለም ክቡር እንደራሴ ? "

" የለም ።"

" ቤርቱሲዮ ገርበብ ብሎ በተከፈተው በር በኩል ተመለከተ ። የእንደራሴው ዓይኖች ግን ቤርቱሲዮ ላይ እንደተተከሉ ቀሩ ።

" እንዴ ፣ እንዴ ፡ " አለ ቤርቱሲዮ አፉን በእጁ ይዞ ።

" ምን ሆንክ ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

" ያች ሴት . . . . . "

" የትኛዋ ? "

" ነጭ ቀሚስና ብዙ አልማዞች ያደረገችው ።"

" እመቤት ዳንግላርን ነው ? "

" ስሚን እንኳ አላውቅም ፣ ግን ያች እኮ ነች ክቡር እንደራሴ ፣ በጓሮ በኩል ሳያት የነበረችው። ስትጠባበቀው የነበረችው ነፍሰጡር።"

" ማንን ስትጠባበቅ የነበረችው ?"

ቤርቱሲዮ መልስ ሳይሰጥ እጅግ በመገረም ወደ ቪልፎርት በመ ጠቆም " እግዚአ " ፣ ይል ጀመር " ያዩታል ? "

" ምኑን ? ማንን ? "

" እሱን !"



t.me/OLDBOOKSPDF

" እዚህ አገር ሕጻን የገደለ የሚፈረድበት ቅጣት ምንድን ነው ?" አለ ሻለቃ ባርቶሎሚዮ

"እንዴ... አንገቱን መቀንጠስ ነዋ ፡ ይህን ወልዶ በላ ! " ሲል መለሰ አንድሪያ ።

" አዎ መሆን አለበት ፡ አይደለም ወይ መሴ ቪልፎርት ?"እን ደራሲው ነበር ። ' አንገቱን መቀንጠስ ......... ' ሲል የመለሰው አንድሪያ በመሆኑ የኮረኮሩትን ያህል አሳቀው ።

" አዎ ክቡር እንደራሴ " ሲል መለሰ ቪልፎርት ከሰው እንደ በት የወጣ መሆኑ በሚያጠራጥር የሰለለ ድምፅ ።

እንደራሴው ለዚህ ትርኢት ያዘጋጃቸው ሁለት ወንጀለኞች ራሳ ቸውን መቆጣጠር ከማይችሉበት የመጨረሻ ጭንቀት ላይ መድረሳ ቸውን ስላስተዋለ የበለጠ ሊያስጨንቃቸው አልፈለገም ።

" ማን ቡናችንን ረሣን መሰለኝ " አለ እንግዶቹን በመናፈሻው መካከል ላይ ወደ ተዘጋጀው ስፈ ጠረጴዛ እየመራ ።

ቪልፎርት ወደ እመቤት ዳንግላር ጆሮ ጠጋ ብሎ " ነገ ላገኝሽ እፈልጋለሁ " አለ በሹክሹክታ ።

" የት ? "

" ቢሮዬ ድረስ ነይ ። እዚያ ይሻላል ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

# 34

ከራት ግብዣው ላይ መጀመሪያ ወደቤቷ ለመመለስ የተነሳችው እመቤት ቪልፎርት ነበረች ። ባሏ ተከተላት ። ሌሎችም እንግዶች መመለስ ጀመሩ ።

አንድሪያ ጋሪው ላይ ለመውጣት እንደተዘጋጀ ትከሻውን እንድ ነገር ነካ አደረገው ። ዞር ሲል አንድ በጺም የተሸፈነ ፀሐይ ያጠቆረው ፊት ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ፈገግ ሲል እንደቀበሮና እንደ ተኩላ ሹል የሆኑት ሰላሳ ሁለቱም ጥርሶቹ አገጠጡበት ። ይህንን ፊት በማወቁ ይሁን ወይም ድንገተኛው ፈገግታ ስላስደነገጠው ፣ አንድሪያ ሽምቅቅ ብሎ ወደ ኋላው ፈንጠር ካለ በኋላ “ ምን ፈለግህ ?” ሲል ጠየቀ ።

“ መሃል ከተማ በሰላም እንድታደርሰኝ እፈልጋለሁ ። ሰውነቴ ከመድከሙም በላይ እንዳንተ በራት ግብዣ ሆዴን ጠርቄ እርጥብ ቅል አልመሰልኩም ። መቆም እንኳ አቅቶኛል ። በሚያምረው ሠረገላህ አሳፍረህ ወደከተማው እንድታስገባኝ እፈልጋለሁ። ቂ ቂ ቂ ቂ ”

አንድሪያ የሰውየውን ማንነት ከአሳሳቁ አረጋገጠ ። በቁጣ ፊቱ ጥም ቢመስልም የሚናገረው አልነበረውም ። “ የራሴው ድክመት ነው ” ሲል ንግግሩን ቀጠለ ሰውየው ፡ እጆቹን በኪሶቹ ውስጥ ከትቶ አንድሪያን በሚያንገሪግር ሁኔታ እየተመለከተው ፤“ ይገባሃል አይደለም ቤኔዴቶ ? ”

ይህ ስም ሲጠራ አንድሪያ ሰውነቱ ከሁለት የተከፈለ መሰለው። በፍጥነት ወደ ሠረገላው ሾፌር ሄዶ “ ይህንን ሰው አንድ ቦታ ልኬው ልክ አሁን መመለሱ ነው ፣ የመልዕክቱን መልስ ለብቻዬ እንዲነግረኝ ስለምፈልግ አንተ ጋሪ ተከራይተህ ቤቴ ጠብቀኝ ” አለው ።

ሾፌሩ ሁኔታው አስገርሞት ከሠረገላው ወርዶ ሄደ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እንደራሴ ? ሃብቱ ግን ለመሥፍንም ሲበዛ ነው ። ” አለ ካድ ሮስ ።

“ እዎ ፡ ግን ከሱ ሰው ላይ ዓይንህን ብታነሳ ይበጅሃል ፡ የዋዛ ሰው እንዳይመስልህ ። ”

“ ባክህ እንደራሴህን አልነካብህም ፡ አሁን የምፈልገው ሁለ ታችን በሰላም እንድንኖር ጥቂት ገንዘብ ጣል እንድታደርግልኝ ነው።”

“ እሺ ፤ ምን ያህል ይበቃሃል ? ”

“ በወር መቶ ፍራንክ ይበቃኛል ግን ....... ”

“ ግን ምን ? ”

“ ግን አያዝናናኝም።መቶ ሃምሳ ቢሆን ግን በደስታ ያኖረኛል።”

“ ያውልህ ሁለት መቶ ። ” አለ አንድሪያ ሁለት ባለ መቶ ፍራ ንክ ኖት እየሰጠው ። “በየወሩ መባቻ ላይ ብቅ ብትል የኔ አበል እስ ካልተቋረጠ ድረስ ያንተውም ሁለት መቶ ይከፈልሃል ።”

“ እንዳልተሳሳትኩ ይገባኛል ” አለ ካድሮስ ፡ “ የአንተ ዓይነቱ ጥሩ ልጅ እድሉ ሲቃና እጅግ ደስ ይላል ። እስኪ አሁን ደግሞ ስለገጠመህ ዕድል አጫውተኝ ። ”

“ ብነግርህ ምን ያደርግልሃል ? ”

“ አሁንም አታምነኝም ፤ አይደለም ? ”

“ እንደዚያ እንኳ አይደለም .............. አየህ አባቴን አገኘሁት ። ”

“ ወላጅ አባትህን ? ”

“ ገንዘብ ይስጠኝ እንጅ ወለደ አልወለደኝ ምን አመራመረኝ ?”

“ ስሙ ማን ይባላል ? ”

“ ሻለቃ ባርቶሎሚዮ ። ”

“ ለመሆኑ ከዚህ አባት ጋር ያገናኘህ ማነው ? ”

“ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ጥሩ " አለ እንድሪያ በመጨረሻው ፡ " ወደ ከተማ አብረን እንሄዳለን ። ግን ኬላውን ስታልፍ አይጠረጥሩህም ? እንደሚመስለኝ ይህንን ልብስ ለብሰህ በሠረገላ መሄድ በእግር ከመሄድ የባሰ ያስጠ ረጥርሃል ። "

" ቆይ እስኪ " አለ ካድሮስ ቀበል አድርጐ ። ከዚያም የአንድ ሪያን ባርኔጣ አውልቆ በራሱ አደረገው ። ቀጠለና የሠረገላው ሾፌር ረስቶት የሄደውን ኮት ደረበ ።

" እኔስ ? " ሲል ጠየቀ አንድሪያ " ባዶ ራስ ቅሌን ልሄድልህ ነው ? "

" አየህ ዛሬ አየሩ ነፋሻ ነው ። ባርኔጣህን ነፋስ ነጠቀህ ሊባል ይችላል ። "

አንድሪያ " በል እስኪ እንሞክር " ከማለት ሌላ አማራጭ አል ነበረውም ። ኬላውን ያለችግር አለፉ ። ከኬላው ራቅ ብለው እንደሄዱ አንድሪያ ሠረገላውን ሲያቆምለት ካድሮስ ዘሎ ወረደ ።
" እንዴ ባርኔጣዬና የሠራተኛዬ ኮትስ ? " ሲል ጠየቀ አንድሪያ።
" እዩ ፡ እኔን ብርድ ቢመታኝ ደስ ይልሃል ? " አለ ካድሮስ እያ ሾፈ ። " ደህና ሁን ይልቅስ ቤኔዴቶ ! " መንገዱን ተሻግሮ ተሰ ወረ ።

አንድሪያ እንደመሳቅ እየቃጣው ።፡ " ወይ ጣጣ ! በዚህች ዓለም ፍጹም ደስተኛ መሆን አይቻልም ማለት ነው ? " አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 35

በሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ቤት የራት ግብዣ በተደረገ ማግሥት ስድስት ሰዓት ተኩል ላይ እመቤት ዳንግላር ከቤቷ ወጥታ በቀጥታ ወደ ቪልፎርት ቢሮ አመራች ።

የቪልፎርት ቢሮ የግቢው በረንዳ በሰው የተሞላ ቢሆንም እመ ቤት ዳንግላር ለሕግ አስከባሪው ስሟን ለማሳወቅ እንኳ ሳትጨነቅ በቀጥታ ግቢው ውስጥ ገባች ። ከዚያም አንድ ተቆጣጣሪ ቪልፎርት ቀጠሮ የሰጣት እመቤት እርሷ መሆኗን ለማረጋገጥ ከጠየቃት በኋላ በአንዲት ጠበብ ያለች መተላለፊያ በኩል ወደ ቪልፎርት ቢሮ ወሰ ዳት ።

ዓቃቤ ሕጉ ጀርባውን ለበሩ ሰጥቶ አንገቱን አቀርቅሮ ይጽፋል ። እመቤት ዳንግላርን ዞር ብሎ አላያትም ። የተቆጣጣሪውን ከቢሮው ወጥቶ ርቆ መሄድ እንዳረጋገጠ ግን ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በሩን ከውስጥ ከቀረቀረው በኋላ መጋረጃዎቹን ሸፈነ ። ከዚያም ወደ እመ ቤት ዳንግላር ዞር ብሎ እንዲህ አለ ። “ ከረጅም ጊዜ በኋላ በግል ለመነጋገር በታደልንበት በዛሬው ዕለት የመነጋገሪያችን ርዕስ እጅግ አሳሳቢና አስጨናቂ የሆነ ጉዳይ በመሆኑ አዝናለሁ ። ”

“ ምን እንደሚሰማኝ የሚገባህ ይመስለኛል ። ” አለች እመቤት ዳንግላር ፤ “ በዚህ ብዙ ወንጀለኞች በፍርሃት እየተርበደበዱ በሃ ፍረት ሲሸማቀቁ በሚታዩበት ክፍል እኔም ስርበደበድና ስሸማቀቅ ከአንድ አስፈሪ ዳኛ ፊት ለፊት የቆምኩ ወንጀለኛ እንደሆንኩ ይሰ ማኛል ። ሆኖም ለፈጸምኩት ወንጀል የማልችለውን ቅጣት ትናንት ማታ ስቀበል ያመሸሁ መሆኔን እንደተረዳህልኝ አምናለሁ ። ”

“ አዎ ፤ ያንቺ ጉልበት የሚችለው ቅጣት አልነበረም . . . ምስ ኪን” አለ ቪልፎርት እጆዋን ጭብጥ አድርጎ በመያዝ “እንዲያም ሆ ኖ ጣጣችን ገና አለማለቁን እንድታውቂው ። ያ አስከፊ ትርኢት እን



t.me/OLDBOOKSPDF

ችልም ነበር ። ”
“ አሁን ምን በጀ ? ” ስትል ጠየቀች እመቤት ዳንግላር በሚማ

ፀን ቃና ።

በበኩልሽ ለክፋም ፡ ለደጉም የሚሆንሽ ደህና ገንዘብ አዘጋጅ፡
ከባለቤትሽ ካዝና ወደ ጉያሽ ብትሸጉጭ ለመከራ ቀን ያገለግላል ። አስ
ፈላጊ ከሆነም ካገር ወጥተሽ ትኖሪያለሽ ፡ ቁርጠኛ ቀን ከመጣ ። ”

“ አንተስ ምን ለማድረግ ወሰንህ ? ” አለች ወንጀለኛዋ እመ

ቤት ።

“ በበኩሌ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ ። ” አለ
ቪልፎርት ። “ በሳምንት ውስጥ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ የሚሉት
ሰላቢ ማን እንደሆነ ፡ ከየት እንደመጣ ፡ ወዴት እንደሚሄድና በጓ
ሮው ውስጥ ስለተቀበረ ሕፃን ለምን እንዳወራ አጣራለሁ ። ”

በግድ የለሽነት የተዘረጋውን የእመቤት ዳንግላርን እጅ ጨብጦ
በሩን ከፈተላት ። እመቤት ዳንግላር እንዴት ወደ ቤቷ እንደደረሰች
ራሷም አታውቀውም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 36

እመቤት ዳንግላር ሠረገላዋ እንዲዘጋጅ አዝዛ ከግቢ ስትወጣ ዳንግላር በመጋረጃ ተከልሎ ሲጠባበቀው የነበረውን የሚስቱን መውጣት ተከታተለ ። እንደመጣች እንዲነግሩት ባለሚሎቹን ቢያዝዝም እስከስምንት ሰዓት ድረስ አልተመለሰችም ።

ስምንት ሰዓት ላይ መሐል ከተማ ወደሚገኘው የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ቤት አመራ ።

" ምን ሆነዋል ባሮን ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው ከመጀመሪያው የሠላምታ ልውውጥ በኋላ ። " የተረበሹ ይመስላሉ ። "

" ለመሆኑ እኒህ ሐብታም ጣሊያኖች ሲባሉ እርስ በርሳቸው ነው የሚጋቡት የሚባለው እውነት ነው ? " ሲል ጠየቀ ዳንግላር እንደ ዋዛ ፡ " ሐብታቸውን ለማዋሃድ የሚፈልጉ ይመስለኛል ። "

" ብዙ ጊዜ እንደዚያ ያደርጋሉ ። ግን ባልሳሳት ሊጠይቁኝ የፈለጉት ስለ ኻቪታ ባርቶሎሜዮ መሰለኝ ። ባርቶሎሜዮ የተለየ ሰው ነው ። እንዲያውም ልጁን ወደ ፈረንሳይ ያመጣው እዚሀ ሚስት እንዲያጭ ስለፈለገ ሳይሆን አይቀርም ። "

" እውነት እውነት ? "

" እርግጠኛ ነኝ ! "

" ስለ ሐብቱ የሚያውቁት ነገር ይኖራል ? "

" በውነቱ በጥልቀት አላውቀውም ። ስለሱ የማውቀው ነገር እሱ ራሱና ቄስ ቡሶኒ ስለሱ የነገሩኝን ብቻ ነው ። ዛሬ ጧት ቄስ ቡሶኒ እንደነገሩኝ ከሆነ ባርቶሎሜዮ ሐብቱን ኢጣሊያ ውስጥ ተወዝፎ ማየቱ ስለታከተው ፈረንሳይ ወይም እንግሊዝ ውስጥ ለማንቀሳቀስ ይፈልጋል ። ልጁ ካገባ ግን ምናልባት ሁለት ወይም ሦስት ሚሊዮን ፍራንክ ሳይሰጠው አይቀርም ። ለምሳሌ የባንክ ነጋዴ ልጅ ካገባ ባርቶ ሎሜዮ ከልጁ እጓት ድርጅት ጋር ንግድ ይከፍታል ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አዎ ከመሥሥፍት ከአሊ. ፓሻ ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው ። ”

“ አ . . . . . ዎ ! ”

“ ታላቅ ምስጢር ሳይኖርበት አይቀርም ። ” አለ ዳንግላር ፤ “ እኔም በዚያም በዚህ ብዬ ምስጢሩን ለማወቅ ስደክም ነበር የኖርኩ ። ”

“ ፍላጎቱ ካለ ምስጢሩን ማግኘት አድካሚ አይሆንም ። ግሪክ ውስጥ ተወካዮች አሉዎ አያደለም ? ”

“ እንዴታ ! የኔ ወኪሎች የማይገኙበት አገር የታለና ! ”

“ መልካም ፡ እንግዲያውስ በአሊ.ፓሻ ጉዳይ ላይ ሞርስፍ የተባለ ፈረንሳዊ ጄኔራል የተጫወተውን ሚና በሚመለከት መረጃ እንዲል ክልዎ ግሪክ ወ ስጥ ለሚገኝ ወኪልዎ ቴሌግራም ያድርጉ ። ”

“ ልክ ነዎ ” አለ ዳንግላር ከተቀመጠበት እየተነሳ ። “ ዛሬ ውኑ እጽፋለሁ ። ”

“ ታዲያ አንድ ደህና ዜና ከደረሰዎ . . . . ? ”

“ ወዲያውኑ ለርስዎ እነግርዎታለሁ ። ”

ዳንግላር ከእንደራሲው ቤት ወጥቶ ወደ ሠረገላው አመራ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 37

ቫለንቲንና እመቤት ቪልፎርት ወደ ዳንስ ቤት እንደወጡ ቪል ፎርት እጅግ በጣም አሳሳቢ ለሆነ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ማንም እንዳያናግረው አዝዞ የጥናት ክፍሉን ዘግቶ ብዛት ያለው ወረቀት ከተከመረበት ጠረጴዛ ፊት ለፊት ተቀመጠ ።

የወረቀቱ ክምር ጠረጴዛው ላይ ለይስሙላ ይቀመጥ እንጅ ቪል ፎርት ለሥራ የሚንቀሳቀስ ሰው አልነበረም ። እጁም አእምሮውም በነገር ተገንዟል ። ወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ባለፉት ተከታታይ ቀናት ስለተከሰቱት አስከፊ ትርኢቶች በማሰላሰል ከሃያ ዓመታት በፊት ወደ ተከናወነው ድርጊት በሃሳብ ዓለም ተዘፍቆ ያወጣ ያወርድ ገባ ።

ብዙም ሳይቆይ በግቢው ውስጥ የሠረገላ ድምፅ ይሰማ ጀመር ። ወዲያው በደረጃው ላይ የእግር እርምጃ ከለቅሶ ዓይነት ንግግር ጋር ተከተለ ። ቪልፎርት የክፍሉን በር እንደከፈተ ከእፍታ በኋላ አንዲት በዕድሜ ጠና ያሉ ሴት “ እግዚኦ . . . አይን አሳይ አይልም . . . . እኔስ ምኑን ተረፍኩት . . . . . ” እያሉ ገብተው በሩ አጠገብ ከሚገኝ ወንበር ላይ ዘፍ ብለው በመቀመጥ እንባቸውን ይለቁት ጀመር ። ቪል ፎርት ወደ ሴትየዋ ጠጋ አለ ፡ የመጀመሪያ ሚስቱ የሬኔ እናት ነበሩ ።

“ ምን ሆንሽ እመይቱ ? ምን እንዲህ የሚያንሰቀስቅ ችግር ደረሰብሽ ? አባባስ አብሮሽ መጥቷል ? ” የወንድ አማቱን ነበር የሚጠይቀው ።

“ ምን አብሮኝ ይመጣል ፡ ሞቱ እንጅ ፡ ጉድ . . . ጉድ . . . . ጉድ . . . . . ” ከእያንዳንዱ ቃል ጋር የሴትየዋ ድምፅ ከፍ እያለ ሄዶ በመጨረሻው በኃይል ጮህ ብለው “ ጉድ ! ” አሉ ።

“ ሞቱ ? እንዲህ በድንገት ? ” ሲል ጮኸ ቪልፎርትም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ቫለንቲንን ለፍራንዝ ልትድር ትፈልጋለህ አይደለም ? " አሉ አሮጊቷ ። ከሞት ጋር እሽቅድድም የገጠሙ ይመስል ጊዜ እንዳያጥራቸው በተጣደፈ አነጋገር ።

" አዎ እመይቴ ። " ሲል መለሰ ቪልፎርት ።

" ፍራንዝ ማለት ናፖሊዮን ከኢልባ ደሴት ከመመለሱ ጥቂት ቀደም ብሎ የተገደለው የጄኔራል ፍላቬን ልጅ አይደለም ? "

" አዎ ። "

" ታዲያ የናፖሊዮን ደጋፊ የኖርቲርን የልጅ ልጅ ለማግባት ፈቃደኛ ሆነ ? "

" የጥንቱ የፖለቲካ ቅራኔኮ አሁን አይሠራም እመይቴ ። ፍራንዝ አባቱ በሞተበት ወቅት ገና ልጅ የነበረ ከመሆኑም በላይ ስለ አባቱ እምብዛም ስለማያውቅ ያን ያህል ወግ አጥባቂ አይደለም ። "

" እና ጥሩ ጋብቻ ነው ትላለህ ? "

" ሃሳብ አይግባሽ እመይቴ ። ፍራንዝ እውቅ ከሚባሉት የፓሪስ ወጣቶች መካከል አንዱ ነው ። "

ይህ ሁሉ ሲሆን ቫለንቲን ዝም ብላ ትከታተላለች ።

" እንግዲያውስ ፤ " አሉ አሮጊቷ ጥቂት ሲያስቡ ከቆዩ በኋላ ፤ " ባሌን መከተሌ ነውና ፈጠን ብታደርጉት ። "

" ምነው እማማዬ " ስትል ቫለንቲን እያለቀሰች አያቷ ደረት ላይ ተለጠፈች ።

" የምናገረውን አውቃለሁ " አሉ አሮጊቷ " ፈጠን ብላችሁ ሠርጉን ደግሱና እናት የሌላትን ቫለንቲንን እኔ እያቷ ልመርቃት ።"

" ባስቸኳይ ይደገሳል " አለ ቪልፎርት " በተለይም ያንቺ ሃሳብ ከእኔው ጋር ስለተጣጣመ ልክ ፍራንዝ ወደ ፓሪስ እንደተመለሰ . . ."

" ግን እማማዬ " አለች ቫለንቲን አባቷን በማቋረጥ " አሁንኮ ሃዘን ላይ ነን ። በሐዘን ጊዜ ሠርግ ይደገሳል ? "

" አባክሽ እንዲህ ያለውን ድሮ የቀረ ወግ አጥባቂ ስንካላ አስተሳሰብ ወዲያ ጣይ " አሉ አሮጊቷ ቆጣ ብለው ፤ " እኔ ራሴ ያን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንባቸውን የመዋጥ ችሎታና ፍላጐት አላቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ የተጫናቸው መጥፎ ገጠመኝ ከጫንቃቸው ላይ ይወርድ ዘንድ ከዕድላቸው ጋር መታገልን ይመርጣሉ ። ከዕድልሽ ጋር ለመታገል ወስነሻል ፣ ቫለንቲን ? ዛሬ ልጠይቅሽ የመጣሁት ይህንን ነው ።”

የመጣቱ ያልተጠበቀ አነጋገር አስደንግጧት ቫለንቲን አይኖቿ በፍርሃት እየዋለሉ ማክሲሚለንን ተመለከተችው ። በአባቷና በአያቷ ላይ የማመጽ ነገር በሃሳብ ደረጃ እንኳ አልመጣላትም ነበር ።

“ የምትናገረው አልገባኝም ማክሲሚለን ? ” አለች “ የአባቴን ትዕዛዝ እንድጥስና ወደ መቃብር የተጠጋችውን አያቴን እንዳስቀይም ነው የምትጠይቀኝ ? ያ እንኳ አይቻልም ! የወላጆችን ትዕዛዝ መጣስ ቀዛ ነው . . . የኔ ጌታ ? የለም ፡ ከዕድሉ ጋርስ አልታገልም ። ከራሴው ጋር ለመታገልና አንተ እንዳልከው እንባዬን ለመዋጥ ያለ የሌለ ኃይሌን እጠቀማለሁ ። ”

“ ልክ ነሽ ! ” አለ ማክሲሚለን ተስፋው በተሟጠጠ ድካማ አነጋገር ። “ አባባልሽ ገብቶኛል ። አባትሽን ለማስደንገጥ ወይም አያትሽን ለማስከፋት ስለማትፈልጊ ነገ የጋብቻውን ውል ትፈርሚያለሽ ። ”

“ ታዲያ ሌላ ምን አማራጭ አለኝ ? ”

“ በቁም ነገር ምክር እንድሰጥሽ ትፈልጊያለሽ ? ”

“ አዎ ማክሲሚለን ፡ ካንተ የሚበልጥብኝ እንደሌለ ታውቅ የለም እንዴ ፤ ”

“ እንግዲያውስ ፡ ልብ ብለሽ ስሚኝ ። መጀመሪያ እህቴ ቤት ልውሰድሽና ከፈረንሳይ ወጥተን ወዳጆቻችን ወላጆችሽን እስኪያሳምኑ እንቆይ ። ከዚያም በዕርቅ እንመለስ ። ”

ቫለንቲን አይኖቿን ገርበብ እንዳደረገች ካዳመጠችው በኋላ ራሷን በአሉታ በመነቅነቅ፡“ ኮብልይ ማለትህ ነው ? . . . ይኸ እንኳ የዕብድ ምክር ነው ማክሲሚለን ፤ ‘ አይቻልም ’ በሚለው ቃል አንተን ጭምር ካልገታሁህ በስተቀር ካንተ የባሰ እንዳበድኩ ይቆጠራል” አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የተወረረ የሚመስለውን ሕንፃ ሲመለከት በአንድ በኩልመስኮት ሲከፈት አዩ። ወዲያው ከውስጥ የምትታይ ሻማ በፈነጠቀችው ደብዛዛ ብርሃን አንድ ነገር ከባንኮኒው በኩል ሲወጣ ተመለከተ። ቫለንቲን ነበረች ። ማክሲሚለን ሰው ያዩኛል ወይም ቫለንቲን በድንጋጤ ጮሀ ሰው ይመጣብኛል የሚል ጥርጣሬና ማመዛዘን ሲመጣለትም ሆነ ሊገታው አይችልም ነበር ። ከሕንጻው ጥግ በሥርዓት የበቀለውን ጨፌ እየረገጠ አቋርጦ ደረጃውን በሩጫ በመውጣት ያልተቆለፈውን በር በትክሻው ገፋ አደረገው ። ስሜቱ የሱ ስላልነበረ አባወራውን ቪልፎርትን ቢመለከት እንኳ ግድ አልነበረውም ። ደግነቱ ማንም አልነበረም ።

የደረጃዎቹን ጫፍ እንደደረሰ ደብዛዛ ብርሃን ከሚታይበት በኩል ገርበብ ብሎ የተከፈተ በር በኩል አንድ የለቅሶ ድምጽ ተሰማው ። የማን ድምጽ እንደሆነ ለማወቅ ግን ጊዜ አልፈጀበትም ። በሩን በር ግዶ ገባ ።

የሟችን ቅርፅ በግልፅ በሚያሳይ ነጭ አንሶላ ተሸፍና አስከሬኑ ተጋድሟል ። ከአስከሬኑ ጐን በባንኮኒው በኩል ያለፈችው ቫለንቲን ምንነቱ የማይታወቅ ጸሎት ታደርሳለች ። ለቅሶዋ ልብ ከመንካቱ የተነሳ ማክሲሚለን ዝም ብሎ የሚመለከተው አልነበረም ። የግዱን ፈገግ እንደማለት እየቃጣው በዝግታ ስሟን ጠራ ።ቀና ብላ ተመለከተችው ። ድንጋጤም ሆነ መገረም ግን አልታየባትም ። አንዳንድ ጊዜ በከፍተኛ ትካዜ ከተዋጠ ልብ ስሜት ገላጭ ምልክቶች ሊታዩ አይችሉም ።

" ቫለንቲን ! " አለ ማክሲሚለን በተቆራረጠ ድምጽ፤ "ሁለት ሰዓት ሙሉ ስጠብቅ አምሽቼ ስትቀሪ ራሴን መቆጣጠር አቃተኝ። የአጥሩን ግድግዳ ዘልዬ ወደ ዛፎች ተጠጋሁ ።እና እዚያ ስለ አሳዛኙ አደጋ የሚነጋገሩ ድምጾችን ሰማሁ ። "

" የማንን ድምጾች ? "

የቪልፎርትና የዶክተሩ ንግግር ሙሉ ለሙሉ ትዝ ሲለው ማክሲሚለን ሽምቀቅ አደረገው ። " የአሽከሮቹ ድምጾች ሁሉንም ፤ የደረሰውን ሁሉ ነገሩኝ " አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ማን እዚህ ከተገኘህ ዋ ! " አለች ። ንግግሯ ቁጣም ሆነ ፍር ሃት አልነበረበትም።"አሁን በፊት ለፊቱ በርም ሆነ በጓሮ በኩል መው ጣት አትችልም ። አመቺው መውጫ አንድ ብቻ ነው ። ና ላስወጣህ።"

" በዬት ? "

" በእያቴ ክፍል በኩል "

" ተጠንቀቂ ቫለንቲን ፡ " አለ ማክሲሚሊን ኢየቅማማ ። "እዚህ መምጣቴ እብደት መሆኑ አሁን ተገልጾልኛል ። አንችስ ቢት ክክል ለማሰብሽ እርግጠኛ ነሽ ? "

" ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ነኝ ። ምስኪኗን አያቴን ብቻዋን ትቸ መውጣቴ ብቻ ነው የሚያሳዝነኝ ። "

" ሞት በራሱ ቅዱስ ነው ፡ " የማክሲሚሊን መልስ ነበር ።

ቫለንቲን ስፊ አዳራሽ አቋርጣ ወደ ኖርቱር ክፍል የሚወስድ ደረጃ ስትወርድ ማክሲሚሊንም በጣቶቹ ጫፍ እየተራመደ ይከተላት ጀመር።

የደረሰው አደጋ ሁሉ በነባር ሠራተኞቸው የተገለጸላቸው ኖር ቴር ተሽከርካሪ ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ ቫለንቲንን ሲመ ለከቱ አይኖቻቸው አበሩ ።

" አባባዬ " አለች ቫለንቲን ከኖርቴር ፊት ለፊት ቆማ " በቅ ርቡ ከአንድ ሰዓት በፊት አያቴ መሞቷን ሰምተሃል ። እንግዲህ ለእኔ በዚህች ዓለም የቀረኸኝ ዘመድ አንተ ብቻ ነህ ። " የሽማግሌው አይ ኖች ወሰን የሌለው የእፍቅሮት ስሜት ያሳዩ ጀመር ። " ስለዚህ ላንተ ፍቅር ስል ደስታዬንና ሐዘኔን ሳልደብቅ መንገር አለብኝ ። አይደለም አባባዬ ? "

" አዎ " በሚል ምልክት የኖርቴር አይኖች ተከዱ ።

"እንግዲያውስ ይህንን ወንድሜን በደንብ ተመልከተው።"አለች ቫለንቲን የማክሲሚሊንን እጅ በእጅዋ ይዛ " ማክሲሚሊን ሞሪል ይባላል ። አባቱ በማርሴል የታወቁ ባለመርከብ ነበሩ ። ስለአባቱ ዝና ታውቃለህ ፣ አይደል ? "

" አዎ " አሉ የሽማግሌው አይኖች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ይህ ወንድሜም ስሙ የማያሳፍር ሲሆን በየጊዜው ታዋቂ እየ ሆነ በመምጣት ላይ በመሆኑ ገና በሰላሳ ዓመቱ የብርጌድ አዛዥ ሲሆን የክብር ሊሻን ሲሸለም በቅቷል ። "

ኖርቴር ይህንን ጉዳይ እንደሚያውቁ በሚገልፅ ሁኔታ በአይኖ ቻቸው ምልክት ሰጡ ።

" አባባዬ ፣ " አለች ቫለንቲን " ክልቤ ስለማፈቅረው ለሱ እንጅ ለማንም ራሴን አሳልፌ አልሰጥም ። ሌላ ሰው እንዳገባ የሚያስገድዱኝ ከሆነ ራሴን አጠፋለሁ ።"

ኖርቴር በታላቅ ትካዜ መዋጣቸውን አይኖቻቸው ተናገሩ ።

" ማክሲሚሊያንን ተቀብለኸዋል ፣ አይደለም ፣ አባባዬ ? "

" አዎ ። "

" እና የአባቴን ሃሳብ ታከሽፈዋለህ አይደለም ? "

ኖርቴር " እንደሁኔታው ይታሰብበታል " በሚል አስተያዩት ማክሲሚሊያንን በአትኩሮት አዩት ።

ነገሩ የገባው ማክሲሚሊያን " ቫለንቲን " አለ " ለሟች አያትሽ ጸሎት በማድረስ ላይ እንዳለሽ ነው ያቋረጥኩሽ ። ለአፍታ ከአባባ ጋር ብቻችንን እንድንነጋገር ትፈቅጅልናለሽ ? "

" አዎ አዎ ፣ ልክ ነው ፣ " አሉ የኖርቴር አይኖች ። ከዚያም ቫለንቲንን በጥያቄ ምልክት ተመለከቷት ።

" ሃሳቤን እንዴት ይረዳል በማለት ገርሞህ ነው አባባ ? " ስትል ጠየቀች ቫለንቲን ።

" አዎ ። "

"ስለሱ አትጨነቅ ፣ ስላንተ ብዙ ጊዜ ስለተነጋገርን እንዴት እንደማነጋግርህ ያውቃል ። " አያቷን ጉንጫቸው ላይ ስማ ማክሲ ሚሊያንን ከተሰናበተች በኋላ ከክፍሉ ወጣች ።

ቫለንቲን የተናገረችው ምን ያህል እውነት እንደሆነና ስለላቸው ምን ያህል እንደተነጋገሩ ለማረጋገጥ ማክሲሚሊያን የፊደል ሠሌዳ ፣ መዝገበ ቃላት ፣ ብዕርና ወረቀት አውጥቶ ፋኖስ ከተቀመጠበት ጠረ



t.me/OLDBOOKSPDF

" አይፈረምም ሊሉኝ ፈልገው ነው ፣ አባባ ? "

" አዎ ። "

" ምንጊዜም ቢሆን ውሉ አይፈረምም ? " አለ ማክሲሚለን ድምጹን ከፍ አድርጐ ። " ይቅርታ አድርጉልኝ አባባ ፣ እንዲህ አይነት ጥሩ ዜና ስሰማ ተጠራጣሪ መሆኔ አይቀርም ። እንደማይፈረም እርግጠኛ ነዎ ? "

" አዎ . . . . . . . ! "

ይህ ሁሉ ሲሆን ማክሲሚለን ሽማግሌውን በሙሉ ልብ ሊያምን አልቻለም ። ኃይሉ ከተኮላሸ አዛውንት የሚወጣው ቃል ኪዳን እንግዳ ከመሆኑ የተነሳ ነገሮችን በትክክል ከማወቅ ሳይሆን በእርጅናና በመዳከም ምክንያት የሚነገር አልባሌ ነገር ይመስል ነበር ።

የወጣቱን ጥርጣሬ በመረዳት ይሁን ወይም ባሳዩት ምልክት ግልጽነት ባለመርካት ኖርቲር ማክሲሚለንን ኮስተር ብለው ተመለከቱት።

" በትዕግሥት ለመጠባበቅ የገባሁትን ቃል እንዳድስ ፈለጉ አባባ ? " ሲል ጠየቀ ።

የኖርቲር አይኖች በኮስታራ አስተያየት ' ቃል መግባት ብቻውን አይበቃም ' ይሉ ይመስል በማክሲሚለን ፊት ላይ ተተክለው ከቆዩ በኋላ ወደ እጁ አመሩ ።

" መሐላ እንዳደርግ ይፈልጋሉ ? "

" አዎ ። "

ማክሲሚለን እጆቹን ከፍ አድርጐ " ማንኛውንም ተግባር ከመፈጸሜ በፊት እርስዎ ሊያደርጉት የወሰኑትን ነገር በመከታተል ታግሼ ለመጠባበቅ በክብሬ ስም እምላለሁ ! " አለ ።

" በጣም ጥሩ ! " አሉ የኖርቲር አይኖች ።

" አሁን እንድሄድ ይፈልጋሉ ፣ አባባ ? "

" አዎ ። "

" እንደገና ወይዘሪት ቫለንቲንን ሳላይ ? "

" አዎ ። "

ማክሲሚለን በአክብሮት ከአንገቱ ዝቅ በማለት እጅ ከነሳ በኋላ ከክፍሉ ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 38

ከሁለት ቀናት በኋላ ከጧቱ በ4 ሰዓት አካባቢ የቪልፎርት እማ
ቶች የቀብር ሥነሥርዓት ቪልፎርት ከረጅም ጊዜ በፊት በተለይ ለመላ
ቤተሰቡ መካነ መቃብር እንዲሆን ባዘጋጀውና ቫለንቲንን የወለደች
ለት የመጀመሪያ ሚስቱ ሬኒ በተቀበረችበት ሥፍራ ተከናወነ ።

የአስከሬኖቹ ፍቃት በቪልፎርት ቤት ቀደም ሲል የተጠናቀቀ
በመሆኑ በመካነ መቃብሩ ሥፍራ የተካሄደው ሥነሥርዓት እምብ
ዛም ጊዜ አልፈጀም ። አስከሬኖቹ በተዘጋጀላቸው ጉድጓዶች ውስጥ
አርፈው አፈር ከተመለሰ በኋላ ለቀብር የተገኘው ሕዝብ በመጣበት
መመለስ ያዘ ። ፍራንዝ ቪልፎርትን ተሰናብቶ ሊሄድ ሲል ቪልፎ
ርት " መቼ ነው እንደገና የምንገናኘው ፤ መሴ ፍራንዝ ? " ሲል
ጠየቀው ።

" በፈለጉ ጊዜ ። "

" እንግዲያውስ በሚቻልህ ፍጥነት እንገናኝ ። "

" አሁን አብሬዎ ብመለስ ምን ይመስልዎታል ? "

" ደስ ይለኛል ፡ ያንተን ፕሮግራም የማላዛባ ከሆነ ። "

" ኧረ ምንም አይደል ። "

ሁለቱ ሰዎች ወደ ቪልፎርት ቤት አብረው ሄዱ ። ቪልፎርት
ቫለንቲንንም ሆነ ሚስቱን ሳያነጋግር ወጣቱን ወደ ግል ክፍሉ ወስዶ
እንዲቀመጥ ጋበዘው ።

" እንደምታውቀው ፍራንዝ " በማለት ቪልፎርት ገለፃውን
ጀመረ ፡ " የሟች አያቷም ፍላጎት ሠርጉ በአፋጣኝ እንዲፈጸም ነበር።
ውሉ ከሶስት ቀናት በፊት እንደሚፈረም ታስቦ ስለነበረ ረቂቁ ቀደም
ሲል ተዘጋጅቷል ። ፊርማው ከዛሬ ማለፍ የለበትም ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እንግዲያውስ” አለ ባሮይስ፣“ ክቡር ኖርቴር ራሳቸው ወደ ሳሎኑ እንድወስዳቸው አዝዘውኛል ። ”

“ ቫለንቲን ” አለ ቪልፎርት በብሽቀት እርር ብሎ “ እስኪ እባክሽ ሂጂና ይኸ ገፊ አያትሽ አሁን ደግሞ ምን እንደሚፈልግ አነጋግሪው ። ”

ቫለንቲን ጣል ጣል እያለች ጥቂት እርምጃዎችን እንደሄደች ቪልፎርት ሃሳቡን ቀይሮ “ ቆይ ፡ ቆይ ” አለ “ አብሬሽ እሄዳለሁ ። ”

“ ይቅርታ ያድርጉልኝ መሴ ቪልፎርት ” አለ ፍራንዝ፣“ ሰውየው በተለይ እኔን እስከፈለጉ ድረስ ሃሳባቸውን መፈጸም የኔ ተግባር ነው ።በዚያውም እስካሁን እድል ባለማግኘቴ ላቀርብላቸው ያልቻልኩትን የአክብሮት ሠላምታ ማቅረብ አለብኝ ። ”

“ አዬ . . . እባክህ ራስህን አታስቸግር ” አለ ቪልፎርት የሚመጣ አደጋ መኖሩ የሚታየው ይመስል እየቀፈፈው ።

“ ይቅርታ እጠይቃለሁ ” አለ ፍራንዝ የማይበገር ውሳኔ ባላለፈ ሰው አነጋገር ፤ “ ለርሳቸው ያለኝን የልጅ ፍቅር በማሳየት በእኔ ላይ ያላቸውን አጉል ጥላቻ የምፍቅበት ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ አላገኝም ። ”

ቪልፎርት ሌላ ቃል ከመናገሩ በፊት ፍራንዝ ብድግ ብሎ ከስመጡች መርከብ አምልጦ ሰፊ ባሕር ካቋረጠ በኋላ በዋና የዛለ ሰውነቱ በመጨረሻ መሬት እንደነካለት ሰው በደስታ እየፈነደቀች ደረጃውን በመውረድ ላይ ያለችውን ቫለንቲንን ተከትሎ ሄደ ። ቪልፎርት ከሁለቱም ጀርባ ይራመድ ጀመር ።

ኖርቴር በተሽከርካሪ ወንበራቸው ላይ ተቀምጠዋል ። “ ትዕዛዝህን በአክብሮት በመቀበል ከሥነሥርዓቱ ላይ ተነስቶ ወዳንተ የመጣው ፍራንዝ ማለት ይህ ነው ። ” አለ ቪልፎርት ለአባቱ “ ሁለታችሁ እንድትገናኙና በወጣቱ ላይ ያለህ ጥላቻ መሠረተ ቢስ መሆኑን እንድትረዳ ለረጅም ጊዜ ስመኝ ነበር ። . . . . ”

ቪልፎርት ንግግሩን ለመጨረስ አልቻለም ። የአባቱ አስተያየት ጉሮሮ ከማነቅ የበለጠ ሽምቅቅ የሚያደርግ ኃይል ነበረው ። ቀጥሎም ኖርቴር ቫለንቲን እንድትጠጋ ቸው ምልክት ሰጡ ።ከጥቂት ጊዜ በኋላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያተለመደውን የመዝገበ ቃላት ሥርዓት በመከተል " ቁልፍ " የሚለውን ቃል አገኙ ። ከዚህ በኋላ የኖርቴር ዓይኖች በሁለቱ መስኮቶች መካከል በሚገኝ አነስተኛ ቁምሳጥን መሳቢያ ላይ ተተከሉ ። ቫለንቲን መሳቢያውን ስትከፍት ከውስጡ ቁልፍ አገኘች ።

የሚፈልጉት ቁልፍ እሱ መሆኑን የሚያረጋግጥ ምልክት ካሳዩ በኋላ ኖርቴር የማይጠቅሙ ወረቀቶች የሚያስቀምጡበት ነው ሲባል ወይንበረ አሮጌ የመጻፊያ ጠረጴዛ ዓይኖቻቸውን መለሱ ።

" የጠረጴዛውን መሳቢያ ልክፈት ? " ስትል ጠየቀች ፡ ቫለንቲን።

" አዎ " አሉ የኖርቴር ዓይኖች ።

ከመሳቢያው ውስጥ የተጠቀለለ ወረቀት አወጣች ። " ይህንን ነው የምትፈልገው አባባዬ ?"

" አይደለም " አሉ ሽማግሌው ዓይኖቻቸውን ደጋግመው በመጨፈን ። ከዚያም ዓይኖቻቸውን መዝገበ ቃላቱ ላይ ተከሉ ። ቫለንቲን መጀመሪያ በፊደል ሠሌዳው ላይ የተጻፉትን ፊደሎች ወደ ታች በተራ በመጠቆም " መ " ላይ እንደደረሰች የኖርቴር ዓይኖች "አዎ" የሚል ምልክት አሳዩ ። ቀጥሎ ደግሞ " መ " በሚለው ፊደል ትይዩ ወደጐን በመጠቆም "ሚ" ላይ ስትደርስ አሁንም " አዎ " አሉ የሽማግሌው ዓይኖች ። መዝገበ ቃላቱን ገልጣ " ሚ " በሚለው ፊደል ሥር ያሉትን ቃላት አንድ ባንድ ትጠቁም ገባች ። " ሚስጥር " ኖዥል ኖርቴር ሊናገሩት የፈለጉት ።

"ሚስጥር አለህ አባባዬ ? " ስትል ጠየቀች ቫለንቲን ።

" አዎ " አሉ የኖርቴር ዓይኖች ።

" ታዲያ ሚስጥሩን ማነው የሚያውቀው ? "

ኖርቴር ባሮይስ ወደ ወጣበት በር ዓይኖቻቸውን ወሰዱ ፡

" ባሮይስ ነው ? "

" አዎ ። "

" ልጥራው ? "

" አዎ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

ቫለንቲን ወደ በሩ ሄዳ ባሮይስን ጠራችው ። " ባሮይስ " አለች ታማኙ አሽከር እንደገባ ፤ " አባባዬ የመጻፊያውን ጠረጴዛ መሳቢያውን እንድከፍት አዝዞኝ ነበር ። በዚያ መሳቢያ ውስጥ ሚስጥር መኖሩን ይናገራል ፤ ሚስጥሩንም አንተ ታውቃለህ ይላል ። "

ባሮይስ በመጠይቅ አስተያየት ወደ ኖርቴር ተመለከተ ። "ታዘዝ" የሚል ምልክት ሰጡ የሽማግሌው ዓይኖች ። ባሮይስ ቀደም ሲል ቫለንቲን ከፍታው ከነበረው መሳቢያ ሥር ከታች በኩል የተደረበውን ሥውር መሳቢያ ከፍቶ በጥቁር ጨርቅ የታሠሩ ወረቀቶች ያሉበት ጥቅል አወጣ ። " ይህን አይደለም የሚፈልጉት ?" ሲል ጠየቀ ።

" አዎ ። "

" ለማን ልስጥ ? ለሙሴ ቪልፎርት ? "

" አይደለም ። "

" ለወይዘሪት ቫለንቲን ? "

" አይደለም ። "

" ለፍራንዝ ? "

" አዎ ! "

ፍራንዝ ግራ ተጋብቶ ወደፊት በመሄድ ወረቀቶቹን ከባሮይስ ተቀበለ ።

" ምን ላድርጋቸው ? " ሲል ጠየቀ ኖርቴርን ።

" ፍራንዝ ወረቀቶቹን እንዲያነብ ፈለግህ ? " አለች ቫለንቲን ቀበል አድርጋ ።

" አዎ ። " አሉ ሽማግሌው ።

" እኛም እንቀመጣ ! " አለ ቪልፎርት ብግን ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና ። " ያንን ሁሉ ቡትቶ ማንበብ ጊዜ ይወስዳል ። " ቪልፎርት ተቀመጠ ። ቫለንቲን ግን ከአያቷ ወንበር ጐን ቆማ ፍራንዝን ፊት ለፊት ታየው ጀመር ።

ፍራንዝ ጥቁሩን ጨርቅ ፈትቶ ማንበብ ጀ. ምረ ።

የቅዱስ ያዕቆብ በናፖርቲስት ክለብ የካቲት አምስት ቀን *1815* ከደረገው ስብሰባ የተወሰደ ቃለ ጉባኤ



t.me/OLDBOOKSPDF

## 39

ኖርቲር ማክሲሚለን በአስቸኳይ እንዲመጣ ባሮይስን ልከውበት ወደክፍላቸው እንደገባ ቫለንቲንም ለሰውነቷ ቀለም ልዩ ውበት የሰጣትን የሐዘን ልብስ እንደለበሰች ወደ አያቷ ክፍል ገባች ።

" እንድናገር የነገርከኝን ነገር በሙሉ እንድናገር ትፈልጋለህ አባባ?" አለች ቫለንቲን አያቷን ።

" አዎ " አሉ ኖርቲር ።

" ባለፉት ሶስት ቀናት ውስጥ አያቴ ብዙ ነገር ነግሮኛል ። " አለች ቫለንቲን ወደ ማክሲሚለን ዞር ብላ ። " ዛሬ አንተ እንድትመጣ የላኩብህም እነዚህን ነገሮች እንድነግርህ ነው ። እኔን ለአስተርጓሚነት ስለመረጠኝ እሱ ያለውን ነገር ሳልለውጥ እነግርሃለሁ ።"

" እሺ " አለ ማክሲሚለን ፤ የደስታ ብዛት ሰውነቷን ስላደከመው ዓይኖቿ ገርበብ ብለው በማየቱ በተስፋ ተሞልቶ ።

" አያቴ ከዚህ ቤት ለመውጣት ይፈልጋል ።" አለች ቫለንቲን፤ "ባሮይስ ደህና አፓርትማ እየፈለገለት ነው ። አባቴ ከአያቴ ጋር እንድኖር ከፈቀደልኝ ዛሬ ነገ ሳልል እኔም እለቃለሁ ። አለዚያ ግን በደንቡ መሠረት እድሜዬ እስኪፈቅድ ማለትም ለመጭዎቹ አሥራ ስምንት ወራት እዚሁ እቆያለሁ ። ከዚያ በኋላ ግን ነጻ ስለምሆን የራሴ ሃብት ይኖረኛል እና . . . . . "

" እና ምን ? " ሲል ጠየቀ ማክሲሚለን ።

" እና ፤ በአያቴ ፈቃድ ፤ ላንተ የገባሁትን ቃል እፈጽማለሁ ።"

እነዚህ የመጨረሻ ቃላት ከቫለንቲን አንደበት ሲወጡ እጅግ ለስለስ ከማለታቸው የተነሳ ማክሲሚለን ጆሮውን አቁሞ ባያዳምጥ ኖሮ ለመስማት እንኳ አስቸጋሪ ነበሩ ።

" ሐሳብህን በግልጽ ተናግሬአለሁ አባባዬ ? " ስትል ጠየቀች ቫለንቲን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቫለንቲን የዶክተሩ አነጋገርም ሆነ አስተያዩት አላምርሽ ብሏት በፉረፍታ ካየችው በኋላ አያቷን ማንባራቸው ላይ ስማ ወጣች ።

ዶክተር አብሪኝ በምሬት እየተመለከታት እንደወጣች በሩን ከጀርባዋ ዘጋባት ።

“ አሁን ምን ይሰማሃል ባሮይስ ? ” የዶክተሩ ጥያቄ ነበር ።

“ ትንሽ ይሻለኛል ዶክተር ። ”

“ ይህንን ብርጭቆ ውሃ መጠጣት ትችላለህ ? ”

“ እሞክራለሁ ፣ ግን እንዳይነኩኝ ። ”

“ ለምን ? ”

“ በጣትዎ ጫፍ እንኳ ቢነኩኝ ውጋቱ የሚመለስ ይመስለኛል።”

“ በል እስኪ ጠጣ ”

ባሮይስ ብርጭቆውን ተቀብሎ ግማሹን ውሃ ጠጣው ።

“ ውጋቱ ድንገት ነው የጀመረህ?” ሲል ጠየቀ ዶክተር አብሪኝ።

“ ልክ እንደ መብረቅ።”

“ ትናንት ወይም ከትናንት ወዲያ ጤናህን ነበርክ ? ”

“ ኧረ ቁርጠትም አልሞከረኝ ። ”

“ ዛሬ ምን በልተህ ነበር ? ”

“ ምንም ፣ ከነጋ የእሳቸውን የሎሚ ጭማቂ ብቻ ነው የጠጣሁት” አለ ባሮይስ ወይ ኖርቴር በክንፈሩ እያመለከተ።ኖርቴር አንዲትም ቃል ሆነች ድርጊት ሳታመልጣቸው ሁሉንም በጥሞና ይከታተላሉ ።

“ የታለ የሎሚው ጭማቂ?” አለ ዶክተሩ ተቻኩሎ ።

“ ምድር ቤት ነው ፣ ማብሰያ ክፍል ። ”

“ ሄጀ ላምጣው ? ” ሲል ጠየቀ ቪልፎርት ግራ ተጋብቶ ።

“ አይሆንም ፣ እዚሁ ይቆዩ እኔው አመጣዋለሁ ። ” ካለ በኋላ ዶክተር አብሪኝ ወደ ምድር ቤት እየተንደረደረ ሲወርድ ደረጃው ላይ እመቤት ቪልፎርትን ገጭቶ ሊጥላት ምንም አልቀረውም ። እመቤት ቪልፎርትም ወደ ማብሰያ ቤት በመውረድ ላይ ነበረች ። ማብሰያ ቤት እንደደረሰ የብርቱካን ጭማቂውን የያዘው እቃ ዝርግ ሳህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ን ላይ ባሮይስ እንዳስቀመጠው ነበር ። ሶስት አራተኛ ያህሉ ባዶ ነው ። ሚሴቴት ጠልፋ እንደምትበር ጭልፊት በቅልጥፍና ብድግ አድ ርጐ ደረጃውን በሩጫ ወደ ላይ ሲያያዘው ለተመለከተው ያስፈራ ነበር። ኖርቲር ክፍል ውስጥ ተመልሶ ሲገባም ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ሊያ ናግረው አልቻለም ። እመቤት ቪልፎርት እንደገና ተመልሳ ወደ ግል ክፍሏ ገባች ።

" ያ . . . . ገኘኸው ጠርሙስ . . . ይኸ . . . ነበር ? " ሲል ጠየቀ አቭሪኝ ።

" አዎ ጌታዬ ! " አለ ባሮይስ

" የጠጣኸው . . . . ጭማቂስ ይኸው . . . . ነበር ? "

" ይመስለኛል ።"

" ምን ምን አለህ ?"

" ትንሽ ኮምጥጦኝ ነበር ። "

ዶክተሩ ጥቂት ጠብታዎች በመዳፉ ላይ አፈሰሰና አፉን እስከ ከቶ ምድጃው ላይ ከተፋው በኋላ " አሃ " አለ " እርስዎስ ጠጥተ ውለታል መሴ ኖርቲር ? "

" አዎ " የሚል ምልክት ሰጡ ኖርቲር ።

" እርስዎንም ኮምጥጦዎ ኖሯል ? "

" አዎ ። "

" አ . . . ዶክተር " አለ ባሮይስ ዓይኑን እያስለመለመ " መጣ እንደገና ! አምላኬ . . . አ . . . ባክህ አውጣኝ ። "

" እስኪ የሚያስታውከው መድሃኒት ተገዝቶ እንደሆን ጠይቅ ?" አለ አቭሪኝ ለቪልፎርት ።

ቪልፎርት ወደ ውጭ እየተንደረደረ " የሚያስታውከውን መድ ሃኒት ? " ሲል ጮኸ ።

መልስ የሰጠ ግን አልነበረም ። ቤቱ በሙሉ በሽብር ተጨንቋል።

ባሮይስ ከመጀመሪያው የበለጠ ውጋት ያጣድፈው ጀመር ። ማስታገሻ ሊሰጠው እንደማይችል የተረዳው ዶክተር ወደ ኖርቲር



t.me/OLDBOOKSPDF

መለስ ብሎ “ ምን ይሰማዎታል ? ” ሲል ጠየቀ ዝቅ ባለ ድምጽ “ጤነ ኛ ነዎ ? ”

የሽማግሌው ዓይኖች በአዎንታ ተከደኑ ።

“ለሚውን የጨመቀልዎ ባሮይስ ነው ? ”

የኖርቴር ዓይኖች አሁንም ተከደኑ ።

“ ከጭማቂው ፡ እንዲጠጣለት የጠየቁትስ እርስዎ ነበሩ ? ”

“ አይደለሁም ። ”

“ መሴ ቪልፎርት ? ”

“ አይደለም ። ”

“ እመቤት ቪልፎርት ? ”

“ አይደለችም ። ”

“ ቫለንቲን ? ”

የሽማግሌው ዓይኖች በመከደን “ አዎ ” አሉ ።

አቭሪኚ ወደ ባሮይስ ዞር አለና “ ጭማቂውን የሠራው ማነው ?” ሲል ጠየቀ ።

“ እኔ ራሴ ። ”

“ እንደሠራኸው ወዲያውኑ ወደ መሴ ኖርቴር አመጣኸው ? ”

“ ኧረ የለም ፡ ምድር ቤት ጠርተውኝ ስለነበረ ዕቃ ቤት ትቸው ወረድኩ ። ”

“ ታዲያ እዚህ ማን አመጣው ? ”

“ ወይዘሪት ቫለንቲን ። ”

ዶክተር አቭሪኚ ግንባሩን በመዳፉ መታ አድርጐ “ እግዚኦ ፈጣ ሪዬ አምላኬ ” አለ ።

“ አ . . . . ዶክተር . . . ” ሲል አቃተተ ባሮይስ ሶስተኛው ውጋት ተነስቶበት ።

“ልቤ . . . ራ . . . ሴ . . ዶክ . . ተር ምን . . .ያህል . . ነው የ. .ም . . ሰቃ . . የው ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እይዞህ ፤ ጥቂት ጊዜ ነው የቀረህ ። "

" ገ. . . ብቶ . . ኛል " አለ ባሮይስ የግዱን ።

"ፈጣ. . ሪ . . . ዬ ፡ ነ. . ፍ . . . ሴን . . . ተ . . ቀ . . በላት እ. . . . " የባሮይስ ጩኸት ለጆሮ ይቀፍ ነበር ።

ዶክተሩ እጁን በባሮይስ ደረት ላይ አድርጐ ጥቂት ካዳመጠ በኋላ ወደ ቪልፎርት መለስ በማለት " እስኪ ምድር ቤት የረሳሁት ሽሮፕ አለ ፤ እስመጡልኝ ? " አለ ።

ቪልፎርት ወጣ ብሎ ከቆየ በኋላ ተመልሶ " አሁንም ራሱን እንደሳተ ነው ? " ሲል ጠየቀ ።

" ሞቷል " አለ ዶክተሩ ።

ቪልፎርት ራሱን በእጆቹ ይዞ ወደ ኋላ ከተንገዳገደ በኋላ ፍርሃት በተቀላቀለበት ሃዘኔታ " እንዲህ በድንገት ፡ እንዲህ በፍጥነት ?" አለ

" አዎ ፡ እጅግ ፈጣን ነበር አይደለም ? " አለ ዶክተሩ የምጸት ሳቅ ፈገግ ብሎ ። " ግን ይኸ ሊያስገርምዎ አይገባም ። አማቶችዎም በድንገት ነበር የሞቱት ። ቤትዎ ውስጥ ሰዎች በፍጥነት እየተቀሰፉ ናቸው መሴ ቪልፎርት ። "

" እች ናትና " አለ ቪልፎርት ድንጋጤውን በቁጣ ሊሸፍን እየሞከረ ። " አሁንም ያንን አስቀያሚ አስተሳሰብ አልተውክም ?"

"ለአንዲት ደቂቃ እንኳ አልተውኩም ። " ሲል መለሰ ዶክተር ብምሬት ። " ደግሞ ባሁኑ ጊዜ አለመሳሳቴን ለማስመስከር ያበቃሁ ሰው ነኝ።በጥሞና ያዳምጡኝ መሴ ቪልፎርት፡" ቪልፎርት መንፈሱም ሆነ አካሉ በመረበሹ መልስ ለመስጠት እንኳ የሚችል ሰው አልነበረም ። "ምልክት እንኳ ሳይሰጥ የሚገድል መርዝአለ።" በማለት ዶክተር ንግግሩን ቀጠለ ፤" ያንን መርዝ በጥልቀት ያጠናሁት በመሆኑ የሚያስከትላቸውን ውጤቶችም ጠንቅቄ አውቃለሁ ። ውጤቶቹ አሁን በምስኪኑ ባሮይስና ቀደም ሲልም ባማቶችዎ የታዩት ናቸው። ያ መርዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

# 40

መሸትሸት ብሏል ። አንድሪያ መስፍኖች ሆቴል ወደተባለው መኖሪያው ሲገባ ገና በረንዳው አካባቢ ሲደርስ መምጣቱን ሲጠባበቅ የነበረው ዘበኛ ባርኔጣውን አውልቆ፦

" ሰውየው ሲጠብቅዎ ነበር ጌታዬ " አለ ።

" የቱ ሰውዬ ? " አለ አንድሪያ ማንነቱን በሚገባ ቢያስታውስም ግራ የተጋባ ለመምሰል የማንባሩን ቆዳ በመከላተር ሽብሽብ አድርጎ ።

" ትንሽ አበል የሚሰጡት ሰውዬ ጌታዬ።"

" እሃ ገባኝ " አለ አንድሪያ " ያ የአባቴ አሽከር የነበረው ? ለመ ሆኑ የተውኩለትን ሁለት መቶ ፍራንክ ሰጠኸው ? "

" አልቀበልም አለ ጌታዬ "

" እንዴት ? "

የሚፈልገው እርስዎን ለማነጋገር ብቻ መሆኑን ነው የሚናገረው ። መጀመሪያ አለመኖርዎን ስነግረው አላምን ብሎኝ ነበር ። በኋላ ነው ይህንን ደብዳቤ ትቶልዎ የሄደው ። "

" እስኪ አምጣው " ካለ በኋላ አንድሪያ በቁራጭ ወረቀት የተ ጻፈችውን መልዕክት አነበበ ።

> የት እንደምኖር ታውቃለህ ። ነገ ጧት ልክ ሶስት ሰዓት ላይ እጠብቅሃ ለሁ ።

" ፈረሶቹን ካስገባህ በኋላ ወደኔ ክፍል ና " አለ አንድሪያ የሠ ረገላውን ሾፌር ።

የሠረገላው ሾፌር ሲገባ አንድሪያ የካድሮስን ደብዳቤ አቃጥሎ ጨርሶ ነበር ። " ቁመናህ ከኔ አይበልጥም አይደለም ?" ሲል ጠየቀ አንድሪያ ሾፌሩን ።

" ይመስለኛል ጌታዬ " አለ ሾፌሩ በጥያቄው ግራ ተጋብቶ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ዛሬ ማታ ከአንዲት ሴት ጋር ቀጠሮ ነበረብኝ ፡ ማን እንደሆንኩ እንድታውቅ አልፈልግም ። እስኪ ለዛሬ ሌሊት ልብስህን አውሰኝና ሌላ ሆቴል ሄጄ ልደር ? "

ሾፌሩ አላቅማማም ። ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ አንድሪያ ራሱን ፍጹም ሌላ ሰው አስመስሎ ከመስፍኖች ሆቴል እንደወጣ ጋሪ ተከራይቶ ገሰገሰ ። ያደረው ከአንድ አልባሌ ሆቴል ውስጥ ነበር ። በማግሥቱ ጧት ወደ ካድሮስ ቤት አመራ ።

" ሰው ጠፍቶብሃል እንዴ ? " አለ ከመንገድ ማዶ የተቀመጠ ፍራፍሬ ሻጭ ።

" ፓይለቲን የተባለ ሰው ፈልጌ ነበር ። "

" ጡረተኛው ዳቦ ጋጋሪ ? "

" አዎ ። "

" አራተኛ ፎቅ ላይ በስተግራ በኩል ባለው ክፍል ውስጥ ነው የሚኖረው ። "

አንድሪያ ጥቆማውን ተከትሎ አራተኛ ፎቅ እንደደረሰ ደወል ደወለ ። ብዙም ሳይቆይ ካድሮስ ብቅ አለ ። " ልክ በሰዓቱ ደረስክ" ካለ በኋላ አንድሪያን እንዲገባ ምልክት ሰጠው ። አንድሪያ በሩን አልፎ እንደገባ በብሽቀት የሾፌሩን ባርኔጣ አውልቆ ወደ ወንበሩ ሲወረውረው ፣ ባርኔጣው ወንበሩን አልፎ መሬት ላይ ወደቀ ። " አይዞህ አትናደድ የኔ ልጅ " አለ ካድሮስ በቀልድ ቀልምጫ " ይልቅስ የምትወደውን ቁርስ አዘጋጅቸልሃለሁና ወስደህ ብላ ። ቂ ቂ ቂ ቂ " አንድሪያ የሻጋታ ጠረን ያለው የዳቦ ፍርፍር ሲሸተው ከንፈሩን ወደላይ በመውሰድ አፍንጫውን አፈነና " አፈር ብላና እዚህ ድረስ እንድመጣ ያደከምከኝ ለቁርስ ብለህ ነው ? " በማለት በብሽቀት ጥርሱን አፋጨ ።

" የኔ ልጅ " አለ ካድሮስ ረጋ ብሎ " እየበሉ መጨዋወት ያስደስተኛል ። ደግሞስ የድሮ ጓደኛህን ለመጠየቅ እንዲሁ ብትመጣ ምን ነውር አለው ? በበኩሌ ናፍቆኸኝ ነበር ። "

" ጉረኛ " አለ አንድሪያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምን የስድስት ወር ፣ ቢያስፈልግህም ያመት አበልህን ሰጥቸህ ወደ እንዱ አገር አትጠፋም ? ”

“ በአንድ ሺህ ሁለት መቶ ፍራንክ አንድ ዓመት የምኖር ይመ ስልሃል ? ይልቅስ የተሻለ አንድ ሐሳብ ላውጣልህ ። ከራስህ አንድ ሳንቲም እንኳ ሳታወጣ ሰላሳ ሺህ ፍራንክ እንዳገኝ ትረዳኛለህ ? ”

“ አልችልም ፤ አላደርገውም ” ሲል መለሰ እንድሪያ ፈጠን ብሎ።

“ አባባሌ የገባህ አይመስለኝም ። ካንተ አንድም ሳንቲም ሳይ ነካ ነውኮ የምልህ ። ”

“ እንድሰርቅና የሁለታችንንም እድል አበላሽቶ ካመለጥነው እሥር ቤት ተመልሰን እንድንታጕር ትፈልጋለህ ? ”

“ ተያዝኩ አልተያዝኩ ጉዳዬ አይደለም ” አለ ካድሮስ “ እን ዲያውም እሥር ቤት የተውኳቸው ጓደኞች ትዝ እያሉኝ ተቸግሬአለሁ ። እኔ እንዳንተ ልበ ድፍን አይደለሁም ። አንተ እነሱን ዳግመኛ ማዬት አትፈልግም ። ”

በዚህ ጊዜ እንድሪያ ፣ ሽምቅቅ ማለት ብቻ ሳይሆን ፊቱ ቀላ ። “ ኧረ ተው እንዲህ ያለው ሞኝነት ይቅርብህ ካድሮስ ” አለ ።

“ አትጨነቅ ወዳጄ ቤኔዴቶ ፣ ካንተ የሚጠበቀው ራስህን ተሳ ታፊ ሳታደርግ እኔ ሰላሳውን ሺህ ፍራንክ የማገኝበትን መንገድ መጠ ቆም ብቻ ነው ። ”

“ ጥሩ ፣ እሞክራለሁ ። ሁኔታውን እከታተላለሁ ። ”

“ ደግሞም አበሌን አምስት መቶ ፍራንክ አድርግልኝ ፣ ሠራ ተኛ መቅጠር እፈልጋለሁ ። ”

“ እሺ ይሰጥሃል ፣ ግን ትንሽ አይከብደኝም ? ”

“ ምን ይከብድሃል አንት ጨቅ ? ” አለ ካድሮስ “ ገንዘብህን ከማይነጥፍ ምንጭ እያገኘህ ! ”

እንድሪያ ይህ አባባል እስኪነገረው ሲጠባበቅ የነበረ ይመስል ፈጠን ብሎ “ አዎ ” አለ ፤ “ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ በደንብ ነው የሚንከባከቡኝ ። ”

“ የናጠጠ ቱጃር ነው አይደል ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ምን ጥያቄ አለው ። ብዙ ጊዜ ቤቱ ስለምሄድ የሐብቱ ብዛት ይታየኛል ። ከትናንት ወዲያ እንኳ የባንክ ኒጋዴው ሂሳብ ሹም በቦርሳ አምሳ ሺህ ፍራንክ አመጣለት ፤ ትናንት ደግሞ አንድ ባለባንክ ሰውዬ አንድ መቶ ሺህ የወርቅ ገንዘብ ሰጠው ። ”

“ ቤቱ ትሄዳለሃ ? ” ሲል ጠየቀ ካድሮስ እቋርጦ ።

“ በፈለግሁ ጊዜ ! ”

ካድሮስ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ በድንገት “ መቸም ያ ቤት እጅግ ያማረ መሆን አለበት ። በምን አጋጣሚ ባየሁት ? መቸም አንድ ቀን ትወስደኛለህ ። ” አለ

“ ያ እንኳ እንደማይቻል የምታውቅ ይመስለኛል ። ”

“እሱስ ልክ ነህ ፤ ግን እስኪ ንገረኝ ። ትልቅ ቤት ነው ? ”

“ ትልቅም ትንሽም አይባልም ። ”

“ በሩ በየት በኩል ይሆን ? ”

“ ይህማ ንድፍ ማውጣት ይጠይቃል ። ”

“ ምናለበት አሳየኛ ? ” እያለ ካድሮስ ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ወረቀትና ብዕር አመጣ ።

አንድሪያ በቤቱ ፊት ለፊት የሚያልፈውን መንገድ በሥዕል በማሳየት በሩ ወዴት እንደሆን አመለከተው ።

“ የቤቱ ግድግዳ ረጅም ነው ? ”

“ አይ ከፍ ቢል ከስምንትና ካስር ጫማ አይበልጥም ። ”

በዚህ ሁኔታ በካድሮስ ወትዋችነት አንድሪያ የእንደራሴውን የመኖሪያ ሕንጻ ከውጭ አንስቶ የአትክልቱን ሥፍራ ፣ የሕንጻውን በሮች ፣ መስኮቶች ፣ ሳሎኑን ፤ መኝታ ቤቶቹን በዝርዝር አስረዳው ።

“ ሠራተኞቹ የት ነው የሚተኙት ? ” ሲል ጠየቀ ካድሮስ ።

“ የሠራተኞቹ መኖሪያ ከዋናው ሕንጻ በስተቀኝ የሚገኝ ሌላ ሕንጻ ነው ። እንዲያውም ባጋጣሚ ትናንት “ ለምን ግድየለሽ ይሆናሉ ፤ ለምንድን ነው ወደ ገጠር ቤትዎ ሲሄዱ ሠራተኞችዎን በሙሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይዘው የሚሄዱት ? አንድ ቀን ሲባ ያስጋምታል ?' በማለት ጠይቀ
ቻው ነበር ። ”

“ ታዲያ ምን መልስ ሰጠሀ ? ”

“ ብሰርቅ ምንቸገረኝ ? አሉኝ ”

“ አሃ ፣ የሚስጥር ቁም ሳጥን ይኖረው ይሆናል ፣ ” አለ ካድሮስ

“ የምን የሚስጥር ቁምሳጥን ? ”

“ ሊባን ሳይታሰብ ይዞ የጨኸት ድምጽ የሚያሰማ ። ”

“ ኧረ የሳቸው ቁምሳጥን ተራ ነው ። ”

“ እስካሁን ከቁምሳጥኑ የሰረቀው ሰው የለም ? ”

“ በፍጹም ፣ ሠራተኞቹ ሁሉ ለሰውየው በጣም ታማኝ ናቸው ።”

“ በዚያ ቁምሳጥን መሳቢያ ውስጥ መቸም ያለው ገንዘብ ቁጥር. . .”

“ ማን ያውቃል ፣ በውስጡ ምን እንዳለበት የሚያውቅ የለም ።”

“ ለመሆኑ ይህ ቁምሳጥን የት ነው ያለው ? ”

“ ሁለተኛው ፎቅ ። ”

“ በል እንደ አንደኛው ፎቅ የሁለተኛውንም ንድፍ ሳልልኝ ።”

አንድሪያ ሳያመነታ ብዕሩን አንስቶ እያንዳንዱን ክፍል በወ
ረቀቱ ላይ ካስቀመጠ በኋላ በመጨረሻው ቁምሳጥኑ ያለበትን የመ
ልበሻ ክፍል በትክክል አሳየው ።

“ መልበሻ ክፍሉ ውስጥ መስኮት አለ ? ”

“ ያውም ሁለት ” በማለት አንድሪያ የመስኮቶችን አቀማመጥ
በንድፉ ላይ ሳለ ።

ከዚህ በኋላ ካድሮስ ለጥቂት ጊዜ በሃሳብ ተመስጦ ቆየ ።

“ ወደ ገጠር ቤቱ ያዘወትራል ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ በሳምንት ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ። ነገ ለምሳሌ ቀን የወጡ
እዚያው ነው የሚያድሩት ። ”

“ እርግጠኛ ነህ ? ”

“ እዚያ ሄጄ እራት እንድጋበዝ ጠይቀውኝ ነበር ። ”

“ ትሄዳለህ ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ምናልባት ። "

" ከሄድክ ሌሊቱን እዚያው ታሳልፋለህ ? "

" ከመሰለኝ ። "

ካድሮስ የወጣቱን ልብ ሰንጥቆ እውነቱን የሚያወጣ ይመስል ጥርሱን አግጥጦ ዓይኑን አፈጠጠበት ። አንድሪያ ግን አንዳችም ለውጥ ሳይታይበት ረጋ እንዳለ ከኪሱ የሲጋራ ባኮ አውጥቶ ሲጋራ ያጨስ ጀመር ። ጥቂት ከቆየ በኋላ " አሁን አምስት መቶ ፍራንክህን ትፈልጋለህ ? " ሲል ጠየቀ ።

" ይዘህ ከሆነማ አሁኑኑ ስጠኝ ። "

" አምስት መቶ ፍራንክ በኪሴ ተሸክሜ አልዞርም ። "

" እንግዲያውስ ለዘበኛው ተውልኝና ብቅ ብዬ እወስደዋለሁ ።"

" ዛሬ ? "

" አይ ፣ ነገ ። ዛሬ ጊዜ የለኝም ። "

" ጥሩ ፣ ከእንግዲህ በዚህ ግባ በዚህ ውጣ እያልክ አታስቸግረኝም አይደለም ? "

" በፍጹም ፣ ግን አንድ የወዳጅ ምክር ልስጥህ ። "

" ምን ልትል ነው ? "

" ያንን የአልማዝ ቀለበት ብትተውልኝ ይሻልሃል ። እንዴት እንዲህ ያለ የጅል ሥራ ትሰራለህ ? ሁለታችንንም እንደገና ቢይዙን ይሻልሃል ? "

" ምን ማለትህ ነው ? "

" የአሽከርህን ልብስ ለብሰህ አራትና አምስት ሺህ ፍራንክ የሚያወጣ የአልማዝ ቀለበት ስታሥር አያስጠረጥርህም ? "

" ህ . . . . ምኝህን ፈልግ " አለ አንድሪያ ።

" ዋ . . . . ስለ አልማዝ ብዙ አውቃለሁ ። ባንድ ወቅት እኔም ነበረኝ ። "

አንድሪያ ብዙም አልተከራከረም ። ቀለበቱን አውልቆ ሰጠውና " ሌላስ ምን ቀረህ ? " አለው ። " ጃኬቱን አውልቄ ልስጥህ ? ቆቤን ? አትፍሪ ጠይቀኝ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በል አሁን ይበቃሃል ። በሩን ላስወጣህ ። ”

“ ምንም አይደል ፤ ራሴ እወጣለሁ ። ”

“ የለም መሸኘት አለብኝ ። ”

“ ለምን ? ”

“ ምክንያቱም በሩ አካባቢ ጥቂት ሚስጥር አይጠፋም ፤ ትንሽ መጠንቀቁ አይከፋም ። እነዚያን በሩ ላይ ያሉ ቁልፎች ቀጥ ቅጩ ለውጫቸዋለሁ ። ቴጃር ስትሆን ላንተም አንድ እሠራልሃለሁ። ቂ ቂ ቂ ቂ ቂ ”

“ እመሰግናለሁ ። ለቴጃርነት ልክ አንድ ስምንት ቀን ሲቀረኝ አሳውቅህና ትሠራልኛለህ ” አለ አንድሬያ እየሳቀ ። ተለያዩ ። ካድሮስ አንድሬያ መንገዱን አቋርጦ እስኪሄድ ድረስ በዓይኑ ከተከተለው በኋላ ወደ ቤቱ ተመልሶ በሩን ቆለፈና ወጣቱ የሳለለትን ንድፍ በተመስጦ ያጠና ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## 41

በእንድሪያና በካድሮስ መካከል ይህ ውይይት በተደረገ ማግ ሥት የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ አሊንና ሌሎች ጥቂት ባለሟሎችን አስከትሎ አውቲል ወደሚገኘው ቤቱ ሄዶ ነበር ። እዚያ እንዳለም ቤርቱሲዮ ኖርማንዲ በተባለው የባሕር ጠረፍ እንዲገዛ የተላከውን ቤት ስለማግኘቱ ለእንደራሴው አበሰረ ። እንደራሴው በባህሩ በፈ ለገ ጊዜ ሊንዝባቸው የሚያስችለው ወደብ ሳይቀር በመዘጋጀቱ መር ከቡ በተጠንቀቅ ላይ እንደምትገኝም ገለጸለት ።

እንደራሴው ቤርቱሲዮ በቅን ልቡና በመድከሙ አመስግኖ በአ ንድ ወር ውስጥ የፈረንሳይ ቆይታውን ስለሚያጠናቅቅ ለጉዞ ዝግጁ እንዲሆን ነገረው ። በዚህ ወቅት ባፕቲስቲን የተባለው ባለሟል በሩን ከፍቶ ገባ ። በእጁ ወረቀት ይዞ ነበር ።

"እዚህ ምን ታደርጋለህ ? እዚህ እንድትመጣ ጠይቄሃለሁ ?" ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

ባፕቲስቲን መልስ ሳይሰጥ ወደፊት ተራምዶ " አሳሳቢና አስ ቸኳይ " በማለት የያዘውን ወረቀት አቀረበ ። እንደራሴው ወረቀቱን ገልጠ ያነብ ጀመር ።

*በመልበሻ ክፍልዎ የሚገኙ አንዳንድ ሰነዶችን ለመስረቅ የሚፈልግ ሰው ዛሬ ማታ ቤትዎን ሰብሮ ስለሚገባ ይጠንቀቁ ። ማስጠንቀቂያውን አስመ ልክተው ለፖሊስ ቢነገሩ ግን ይህንን ደብዳቤ የፃፈልዎ ሰው ችግር ላይ ስለሚወድቅ እንዳያስቡበት ። ብዛት ያላቸው ሰዎች ተዘጋጅተው ቢጠ ብቁት ወይም ለእይታ ግልፅ የሆነ መሰናዶ ቢያደርጉ ሌባው እቅዱን ለሌላ ጊዜ በማስተላለፍ ይህንን ማስጠንቀቂያ የፃፈው ሰውም ሆነ እርስዎ በማያውቁበት ሰዓት የልቡን ሊሠራ ይችላል ።*

እንደራሴው ይህንን ደብዳቤ እንዳነበበ እነስተኛ ለሆነ አደጋ ማስጠንቀቂያ ጽፎ በማዘናጋት ለበለጠ አደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የታለመ ተራ የሌባ ስልት ነው ብሎ ገምቶ ነበር ። እናም ማስጠን



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀቂያውን የጻፈለትን ያልታወቀ ሰው ምክር ችላ በማለት ደብዳቤውን ለፖሊስ ጣቢያ ሲያቀርብ ወስኖ ጥቂት እንደቆየ ድንገት ይህ ሴባ ምናልባት የራሱ የግል ጠላት ሊሆን እንደሚችል አስተውሎ ሃሳ ቡን ለወጠ ።

‘ የሚፈልገው ወረቀቶችን ለመሥረቅ ሳይሆን እኔን ለመግደል ይሆናል ’ አለ በሃሳቡ ። ‘ ፖሊሶች በእኔ የግል ጉዳይ እንዲቸገሩ አልፈልግም ። ’

ደብዳቤውን ከሰጠ በኋላ ከክፍሉ የወጣውን ባፕቲስቲንን ጠራው ። “ ወደ ከተማ ሂድና ሁሉንም ሠራተኞቼን እዚህ አምጣቸው ። እያ ንዳንዳቸው ወዲህ እንዲመጡ እፈልጋለሁ ፤ ቤቱ ግን የምድር ቤቱን መስኮቶችና በሮች መከለያዎች ከመዝጋት በስተቀር እንደነበረ እን ዲተው ። ትዕዛዜ ግልጽ ነው ? ”

“ የፎቁ መከለያዎችስ ? ”

“ዘግቻቸው እንደማላውቅ ታውቅ የለም እንዴ ። በል ሂድ ።”

እንደራሴው እንደተለመደው ረጋ ብሎ ራቱን አነስተኛ ምግብ ከወሰደ በኋላ አሊ የተባለውን ባለሟሉን እንዲከተለው አዝዞ በአጥሩ የኋላ በር በኩል ሹልክ ብሎ ወጣ ። ጊዜው ለአይን ያዝ ሲያደ ርግ መሃል ከተማ ወደሚገኘው ቤቱ ደረሰ ። ከአንድ ዛፍ ሥር ተለጥ ፎ በአካባቢው የተደበቀ ሰው መኖር አለመኖሩን ለመለየት በመንገ ዱ ላይና ታች ተመለከተ ። ማንም ሰው አድብቶ እንደማይጠብቀው ካረጋገጠ በኋላ ከአሊ ጋር ወደ ኋላው በር ሮጦ ተጠጋና በሩን ከፍቶ መምጣቱን የሚያመለክት እንዳችም ምልክት ሳይተው ፎቅ ላይ ወጥቶ መኝታ ቤቱ ውስጥ ገባ ።

አሊ መኝታ ቤቱ ውስጥ እንዲቆይ በጥቅሻ ምልክት ከሰጠው በኋላ ወደ መልበሻ ክፍሉ ገብቶ ክፍሉን በጥንቃቄ መረመረው ። ሁሉም ነገር በበፊቱ ሁኔታ ነበረ ።

የበሩን ማጠፊያ ፈልቀቅ አድርጐ ወደ መኝታ ክፍሉ ተመለሰ ። እንደራሴው በቤቱ ባልነበረበት ጊዜ እንዲዘጋጁለት ባዘዘው መሠ ረት አሊ አጭሩን ካርባይን ጠመንጃውንና ሁለቱን ጥንድ ጉራሽ ሽጉ ጦች ጠረጴዛው ላይ አስቀምጧቸው ነበር ። በዚህ ትጥቁ እንደራ ሴው ባንድ ምት አምስት ሰዎች ሊጥል እንደሚችል አረጋገጠ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" እናያለን "

" ብቻዎን ነዎ አባቴ ወይስ እኔን ለማሳሰር ያዘጋጁዋቸው ወታደሮችም አሉ ? "

" ብቻዬን ነኝ " አሉ ቄሱ " ማንም እንኳ በራሴ ድካመት አንዳንድ ችግሮችን ሊያስከትልብኝ ቢችልም እውነቱን ከሰረ መሠረቱ ከነገርከኝ ላገንልህ እችላለሁ ። "

" እህ ቄስ ቡሶኒ " በማለት ካድሮስ በእጁ እያጨበጨበ በመሳቅ ወደ ቄሱ ተጠጋ ። ከጉኑ የሻጠው ትልቅ ጩቤ ስራውን መስራት እንዳለበት ተገንዝቧል ። " የሕይወቴ መድህን ነዎ ቂ ቂ ቂ ቂ ቂ "

" አንድ ሰው ከእሥር ቤት እንዳወጣህ ተናገርክ ። "

" አዎ ከፈለጉ እምልልዎታለሁ ። "

" ማን ነበር እሱ ? "

" አንድ እንግሊዛዊ ነው ። "

" ስሙስ ? "

" ሎርድ ዊልሞር ። "

" አሃ ፤ እሱንማ አውቀው የለም እንዴ ፤ ልብ አድርግ ። አንድ ውሸት ብትናገር እሱ ይነግረኛል ። "

" ኧረ እውነቱን ነው የምነግርዎ "

" ይህ እንግሊዛዊ ያንተ ተንከባካቢ ነበር ፤ አይደለም ? "

" አይ ፤ እሱ እንኳ አብሮኝ የታሰረ አንድ ወጣት ኮርሲካዊ ነበር የሚንከባከበው ። "

" የዚህ ወጣት ስምስ ማን ይባላል ? "

" ቤኔዴቶ "

" የአባቱ ስም ? "

" የአባት ስም የለውም . . . ዘላን ቢጤ ወጠጤ ነው ። "

" ታዲያ እሱም ካንተ ጋር አመለጠ ? "

" አዎ ። አንድ ቀን የጉልበት ሥራ ታዝዘን እንደወጣን እንግሊዛዊው በሰጠን የብረት ሞረድ ሰንሰለታችንን በጥሰን አመለጥን ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

" ቤኔዴቶስ የት ደረሰ ? "

" እኔ እንጃ ፣ ወዲያውኑ ነው የተለያየነው ። "

" አንት ቀጣፊ " አሉ ቄሱ አንዳች ኃይል ባዘለ ድንጋገር ቃና " ያ ወጠጤ አሁንም ጓደኛህ ነው ፡ "

" አይ ቄስ ቡሶኒ " አለ ካድሮስ አንገቱን አቀርቅሮ በሐፍረት እየተሽኮረመመ ።

" ከእሥር ቤት ከወጣህ ጀምሮ እንዴት ነበር የምትኖረው ? ተናገር "

" ድላላ ቢጤ እየሠራሁ ፡ "

" አንት የተረገምህ " አሉ ቄሱ እንደገና የበለጠ በሚያስፈራ ቃና ። ካድሮስ የሚያደርገው ጠፍቶት ቄሱን በሚማጸኑ አይኖች ይመለከት ጀመር ። " ቤኔዴቶ በሚሰጥህ ርዳታ አይደለም የምትኖረው ?"

" አዎ ፣ ልክ ነው " አለ ካድሮስ " ቤኔዴቶ የአንድ ሃብታም ሰው ልጅ ሆኖ ተገኝቷል ። "

" እንዴት የአንድ ሐብታም ሰው ልጅ ሊሆን ቻለ ? "

" እረ ዝም ብሎ ነው ፤ መላውም አልታወቀ ........."

" የዚህ ሐብታም ሰው ስም ማነው ? "

" የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ . . . . . . . የዚህ ቤት ባለቤት "

" ቤኔዴቶ ፣ የእንደራሴው ልጅ ? " አሉ ቄሱ በመገረም ።

" እንደዚያ ነው ፣ እንደራሴው እሱን በልጅነት ከተቀበሉ ጊዜ አንስቶ በወር የአምስት ሺህ ፍራንክ አበል ከመስጠታቸውም በላይ የግማሽ ሚሊዮን ፍራንክ ወራሽ አድርገውታል ። "

" አሃ " አለ አስመሳዩ ቄስ ነገሩ እንደገባው መስሎ " ያ ቤኔዴቶ በአባቱና በአካባቢው የሚታወቅበት ሌላ ስም የለውም ? "

" አዎ ፣ አንድሪያ እየተባለ ይጠራል ። "

" ታዲያ እሱማ እንደራሴው ወዳጅ በቤቱ የሚያስተናግደው የመሴ ዳንግላርን ልጅ ያጨው ወጣት አይደለም እንዴ ? "

" ልክ ነዎ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" አንተ የረከሰክ ወራዳ ፡ የበፊት ሕይወቱንና ወንጀሉን እያወቅህ ይህንን ሁሉ ሲያደርግ ዝም ብለህ አየኸው ? "

" ታዲያ ዓይኛ ጥሩ ዕድል ሲገጥመው መሰናክል መሆን ይገባል ? " አለ ካድሮስ

" እሱስ ልክ ነህ መሴ ዳንግላርን የምታስጠነቅቀው አንተ ሳትሆን እኔ ነኝ ። "

" ኧረረ . . . እንዲያስ አያድርጉ አባቴ ! "

" ለምን ? "

" ምክንያቱም እንዲያ ካደረጉ መተዳደሪያችን ይነጠቃል ። "

" እንደናንተ ያሉ ጥንድ ወንጀለኞች መተዳደሪያ እንዳይነጠቁ ብዬ በውንብድና ሥራቸው እየተሳተፍኩ የምንከባከባቸው ይመስልሃል ? የለም የለም ፡ ሁሉንም ነገር ለዳንግላር እነግረዋለሁ ። "

" ለማንም ምንም አትናገርም ፡ ወለወልዳ ቄስ " በማለት ከጮኸ በኋላ ካድሮስ አንድ ትልቅ ጩቤ አውጥቶ በኃይል በማንዘር በቄሱ ደረት ላይ አሳረፈው ። ሆኖም ረጅሙ ጩቤ በቄሱ ደረት ውስጥ በመስመጥ ፋንታ ጫፉ ታጥፎ ወደላይ ነጠረ ። በተመሳሳይ ጊዜ ቄሱ የተቀናቃኙን ክንድ በግራ እጃቸው በኃይል ሲቆለምሙት ካድሮስ ከተሰማው ሕማም የተነሳ ጩቤውን መሬት ላይ ጥሎ ይጮህ ጀመር ።

ቄሱ እንደገና የካድሮስን እጅ በኃይል ሲቆለምሙት ካድሮስ በጉልበቱ ተደፍቶ ፊቱ ከወለሉ ጋር ተላተመ ። ከዚያም ቄሱ እግራቸውን በሌባው ራስ ላይ አሳርፈው " ከነክህን እንዳላበግናው የሚያግደኝ ምን ኃይል እንዳለ አይገባኝም ፣ ነፍስ ገዳይ ። " አሉ ።

" ማሩኝ ፣ ማሩኝ " በማለት ተማፀነ ካድሮስ ።

ቄሱ እግራቸውን ከሌባው ላይ አንስተው " ተነስ ! " ሲሉ አዘዙ ። ካድሮስ ብድግ አለ ።

" ኧረ ያንተ ያለህ ፣ እንዴት ያሉ ጉልበታም ነዎ ጃል " አለ ካድሮስ የሚጠዘጥዘውን ክንዱን እያሻሸ። " እግዚኦ! በጣም ጠንካራ ነዎትና ቄስ ቡሶኒ ! "



t.me/OLDBOOKSPDF

" እግዚአብሔር ይቅር እንዳለህ ይቆጠራልና የበኩሌን ቂም እፍቃለሁ ። "

" ለምን እንደምሞት ሁሉ ያስፈራሩኛል አባቴ " አለ ካድሮስ ዓይኖቹን በጭንቀት እያቅበዘበዘ ።

" አሁን ውጣ ፡ " አሉ ቄሱ ወደመስኮቱ እያመለከቱ ።

የቄሱን አነጋገር ሙሉ ለሙሉ ማመን ያቃተው ካድሮስ በመስኮቱ በኩል ቮልኮ መሰላሉን መውረድ ጀመረ ። ቄሱም ሻማ እያበሩ አካሄዱን ይከታተሉ ጀመር ። ከመንገድ ቆሞ ለሚመለከት ካድሮስ በመሳሰሉ ሲወርድ ሌላ ሰው ሻማ እያበራ ቁልቁል እንደሚያየው በግልጽ ይታይ ነበር ።

" ምን ያደርጋሉ ? " አለ ካድሮስ " ሮንዶች ሲያልፉ ቢያዩኝስ ? "

ቄሱ ሻማውን አጠፉ ። ካድሮስ እግሩ መሬት እስኪነካ ድረስ የሰላም አየር መተንፈስ አቅቶት ነበር ።

ቄሱ ወደመኝታ ቤት ሄደው ካድሮስ ጓሮውን አልፎ መሰላሉን ከአጥሩ ግምብ ጋር ሲያስደግፍ ተመለከቱ ። ከዚያም ካድሮስን መንገድ ላይ ሲጠባበቅ የነበረው ሰው ከውጭ በኩል ካድሮስ ከሚወጣበት ቦታ ከግምቡ ጫፍ ላይ ከአንገቱ በላይ ብቅ ብሎ ተመልሶ ገባ ።

ካድሮስ ልክ የመሰላሉን የመጨረሻ መወጣጫ ረግጦ በግንቡ ጫፍ ላይ ሊወጣ እግሩን ብድግ ሲያደርግ ቢላዋ የጨበጠ እጅ ታየው ። ራሱን ለመከላከል ከመሞከሩ በፊት ባለቢላዋው እጅ መጀመሪያ ጀርባውን ቀጥሎም ሆድ እቃውን አገነፋው ። ካድሮስ ወደመሬ ሊወድቅ ሲል ሁለተኛ እጅ ጸጉሩን ጭምድድ አድርጐ በመያዝ ደረቱ ላይ ሰካበት ።

ካድሮስ ለአፍታ መሬት ላይ ተዘርሮ ከቆየ በኋላ ባለሃይሉ ከአንገቱ ቀና ብሎ " ድረሱልኝ ! ቄስ ቡሶኒ ! ሞትኩ " አለ በተዳከመ ድምጽ ።

ይህ የጣዕረሞት ጩኸት የጭለማውን ጸጥታ አደፈረሰው ። ወዲያው የእንደራሴው መኖሪያ ሕንጻ ጀርባ በር ተከፍቶ አሊና ጌታው ፋኖስ ይዘው እየሮጡ ደረሱ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ምን ሆንክ ? " አሉ ቄሱ ።

" እርዱኝ " አለ ካድሮስ " በጩቤ ተወግቻለሁ ። "

" አይዞህ ።"

" አየ ፡ በቃኮ ምንም ቢሆን አልተርፍም ። "

አሊና ቄሱ ቁስለኛውን ተሸክመው ወደቤት ወሰዱት ። ቄስ ቡሶኒ የቁስለኛውን ሰውነት አገላብጠው ሲመለከቱ ሶስቱን አሰቃቂ ቁስሎች አዩ ። አሊ " ምን መደረግ አለበት ? " በሚል የጥያቄ አስተያየት ጌታውን ይመለከታል ። " በአስቸኳይ ዓቃቤ ሕጉን ቪልፎርትን ጥራ " አሉ ቄስ ቡሶኒ ። " እግረ መንገድህንም የጽዳት ሠራተኛውን ሐኪም እንዲጠራ ንገረው ። "

አሊ እጅ ነስቶ ወጣ ። " አየ ፡ አሁን ዶክተር ቀርቶ እግዚአብሔር ራሱ ቢመጣ ያድነኛል ? " አሉ ካድሮስ " ባይሆን ትንሽ ጉልበት ሰጥቶኝ አንድ ኑዛዜ እንዳሰማ ጊዜ አገኝ እንደሁ እንጂ ። "

" የምን ኑዛዜ ? "

" በጩቤ ስለወጋኝ ሰው ።"

" ማን እንደሆነ ታውቀዋለህ ? "

" አውቀዋለሁ ፡ ቤኔዴቶ ነው ። "

" ወጣቱ ኮርሲካዊ ጓደኛህ ? "

" አዎ ። የእንደራሴውን ቤት ንድፍ የሰጠኝ እሱ ነበር ። አሁን ነገሩ ገባኝ ። ምናልባት እንደራሴውን ገድዬለት ቶሎ ለውርስ ለመብቃት ፤ አለዚያም እንደራሴው እኔን ገድለውኝ እንዲገላገለኝ ተስፋ አድርጎ ነበር የላከኝ ። ሁለታችንም አለመሞታችንን ሲያይ በጩቤ ወጋኝ ። "

" አሁን ዓቃቤ ሕጉ ሲመጣ ትናገራለህ ። "

" ደሜ ፈሶ እያለቀ ነው ። ዓቃቤ ሕጉ ሳይደርስ እሞታለሁ ። " አለ ካድሮስ ይበልጥ በተዳከመ ድምጽ እያጣጣረ ።

" ቆይ እስኪ " ካሉ በኋላ ቄስ ቡሶኒ ወጣ ብለው አንድ ብልቃጥ ይዘው ተመለሱ ። ከብልቃጡ ውስጥ ሶስት ጠብታዎች በቁስለኛው ከንፈር ላይ አንጠባጠቡ ። ካድሮስ ፈገግ ሲል እየሞከረ



t.me/OLDBOOKSPDF

" እዚህ ድረስ ተደብቆ እንደተከተለህ ፣ ቤት ውስጥ የምታደርገውን ሁሉ እንደተከታተለ ፣ ያለምንም ውጤት መመለስከን ሲያይ በሩጫ ሄዶ ከአጥሩ ግንብ በኩል እንደተጠባበቅህ ሁሉ እነግርበታለሁ ። "

" ይህንን ሁሉ ሲያዩ ነበር እንዴ ? "

" በሰላም ቤትህ ከገባህ እግዚአብሔር ይቅር እንዳለህ ይቆጠራልና የበኩሌን ቂም እፍቃለሁ ያልኩህን አስታውስ ። "

" እና ሳያስጠነቅቁኝ ቀሩ እ ? " አለ ካድሮስ በእጁ ተደግፎ ከተኛበት ለመነሳት እየሞከረ " ከዚህ ተመልሼ ስወጣ እንደምገደል እያወቁ ዝም አሉኝ ! "

" አዎ ! ምክንያቱም በቤኔዴቶ እጅ አንድ ትክክለኛ ፍትህ ይታየኝ ስለነበር ያንን ትክክለኛ ፍርድ ልጋፋ አልፈለግሁም ። "

" ወጊድ እባክህ ይህንን ትክክለኛ ፍትህ የሚባል ዲስኩር ተወኝ አንተ ቄስ ። ትክክለኛ ፍትህ የሚባል ነገር አለመኖሩን ስንት ቅጣት የሚገባቸው ሰዎች ተንደላቅቀው እንደሚኖሩ አንተ ራስህ ሳትታዘብ ቀርተህ ነው ? "

" አፍህን ዝጋ " በማለት ቄስ ቡሶኒ ሲጮሁ ቃናው ካድሮስን እንኳ ካንገበገበበት ሞት የበለጠ የሚያስፈራ ነገር ያለ ይመስል ስቅጥጥ አደረገው ። "እስኪ የረገጥከውን እድል ዞር ብለህ ተመልከት ። ጤንነት ፣ ጥንካሬ ፣ ደህና ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ፣ ባጭሩ ሰው በንጹህ ልቡና ተፈጥሮአዊ ፍላጐቶችን ለማርካት የሚያስፈልጉት ነገሮች በሙሉ ተሟልተውልህ ነበር ። አንተ ግን በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ተደስተህ ከመኖር ይልቅ ወደ ስንፍናና ወደ ጠጭነት አዘነበልህ። በጠጭነት መንፈስ ተነሳስተህም ከእውነተኛ ጓደኞችህ አንዱን ከዳህ ። "

" ኡ . . . . ኡ " ሲል ጮኸ ካድሮስ በሰለለ አንደበት " ቄስ አይደለም የምፈልገው ፣ የዶክተር ያለህ ፣ ልትረፍ የምችለውን . . . "

" ቁስልህ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ያንን ሶስት ጠብታ ፈሳሽ ባልሰጥህ ኖሮ እስካሁንም አትቆይም ነበር ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ቂስ ቡሶኒ ስው ሥራሽ ጸጉራቸውን አውልቀው ጥቁሩ ጸጉራቸው በርበሬ በመሰለው ፊታቸው ላይ ከንበል ብሎ እንዲደፋ አደረጉ።

" እንዴ ? " አለ ካድሮስ ልቡ በፍርሐት እየተናደ " ጸጉርዎ ጥቁር ባይሆን ኖሮ ከእሥር ቤት ያወጡኝ እንግሊዛዊ ሎርድ ዊልሞር ነዎ ባልኩ ነበር ! "

" ቄስ ቡሶኒም ሆነ ሎርድ ዊልምር አይደለሁም ። " አለ እንደራሴው " አሁንም በደንብ ተመልከተኝ ፣ እስኪ ወጣትነትህን አስታውስ ። ወደጥንቱ ተመልሰህ አሰላስል ። "

" አሃ ! ልክ ነዎ ! በፊት ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት ያየሁዎ ይመስለኛል ። "

" አዎ ካድሮስ ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት አይተኸኛል ። ባንድ ወቅት ጓደኛህ ነበርኩ ። "

" የማ ? የእኔ ጓደኛ ? ታዲያ እርስዎ ማን ነዎ ? ደግሞስ ጥንት የሚያውቁኝ ከሆነ ለምን ስሞት ዝም ብለው ያዩኛል ? "

" ምክንያቱም ቁስልህ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ምንም ነገር ሊያተርፍ አይችልምና ነው ፣ ካድሮስ ። ቢቻል ኖሮ የመጨረሻ ዕድል ሰጥቸህ ወደ ሕይወት ተመልሰህ ጥፋትህ እንደ እግር እሳት ሲለበልብህ ለማየት እሞክር እንደነበር በአባቴ መቃብር ስም እምልልሃለሁ ። "

" ታዲያ ለምን እከሴ ነኝ አይሉኝም ? "

እንደራሴው የካድሮስን የጤንነት ሁኔታ በደንብ ሲከታተል ስለነበር የሕይወቱ ፍጻሜ መቃረቡን አስተዋለ ። ጉንበስ ብሎ ወደተጻከመው ቁስለኛ ጆሮ ከተጠጋ በኋላ በሹክሹክታ እውነተኛ ስሙን ሲያሰማው ፣ ከቃላቱ መለስለስ የተነሳ እሱ ራሱ እንኳ የገዛ ስሙን መጠራት ለመስማት የፈራ ይመስል ነበር ።

ካድሮስ እንደምንም እጆቹን ዘርግቶ በማጋጠም ባለ ኃይሉ እንደመነሳት ብሎ " እግዚአ . . . . . . . . " አለ ። " የእውነትን አሸናፊነት አሁን ገና ማየቴ ነው ፣ ዎይ ነዶ ! . . . . "



t.me/OLDBOOKSPDF

የካድሮስ አይኖች ተከድነው የመጨረሻውን የማስረሞት ድም ጽና የመጨረሻውን የሕይወት አየር ተንፍሶ እንደገና በቻርባው ተዘረረ ።

“ አንድ ! ” አለ እንደራሴው ለራሱ ብቻ ግልጽ በሆነ ሚስጥ ራዊ አነጋገር አስከሬኑን በምሬት እየተመለከተ ።

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ዶክተሩና ዓቃቤ ሕግ ሲደርሱ ቄስ ቡሶኒ ለሟች ነፍስ ጸሎት ሲያደርሱ አገኙዋቸው ።

* * *

ለሁለት ሳምንታት ያህል የፓሪስ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በምንቴ ክሪስቶ እንደራሴ የመኖሪያ ሕንጻ ከተደረገው የሥርቆት ሙከራ ሌላ የመነጋገሪያ ርዕስ አልነበረውም ። ሟች በቢላዋ በተወጋበት ወቅት የገደለው ቤኔዴቶ የተባለ ሰው መሆኑን ስለገለጸ ፖሊስ በገጸዶ ላይ ክትትል ማድረጉን ተያያዘው ።

የካድሮስ ጩቤ ፥ ጢሻ ፥ ቁልፎቹና ልብሶቹ ኤግዚቢት ሆኑ ። አስከሬኑም ተባረ ዘመድ አዝማድ እስኪገኝ ድረስ በማዘጋጃ ቤት ልዩ የአስከሬኖች ክፍል ውስጥ ተቀመጠ ።

እንደራሴው ዝርፊያው በተሞከረበት ሌሊት አውቲል በሚገ ኘው የመናፈሻ ቤቱ ውስጥ እንደነበርና ስለሁኔታው ሊያውቅ የቻ ለው በአጋጣሚ በዚያ ሌሊት በግል መጻሕፍት ቤቱ ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ ከቤቱ ለማደር ፈቃድ የጠየቁት ቄስ ቡሶኒ አደጋውን ካብራሩለት በኋላ መሆኑን አሳወቀ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 42

“ ወረቀቶችዎን በሥርዓት በማስቀመጥ ላይ ሳሉ መጥተን ረበሽንዎ ” አለ አልበርት ፤ አንድ ቀን በጧት ቡቻምፕ ከተባለው ጋዜጠኛ ጓደኛው ጋር እንደራሴውን ሊጠይቅ መጥቶ ተገቢው የሰላምታ ልውውጥ ከተደረገ በኋላ ።

“ ኧረ የለም አልረበሻችሁኝም ፤ ወረቀቶቹም ቢሆን የአንድሪያ እንጅ የእኔ አይደሉም ” ሲል መለሰ እንደራሴው ።

“ የማነው አንድሪያ ? ” ጋዜጠኛው ቡቻምፕ ጠየቀ ።

“ ክቡር እንደራሴ ከፓሪስ ህብረተሰብ ጋር በማስተዋወቅ ላይ ያሉትን ወጣት እስካሁን አታውቀውም ? ” አልበርት ነበር ።

“ ይቅርታ ፤ እዚህ ላይ ላቋርጥህ ” አለ እንደራሴው “ እኔ አንድሪያን ይቅርና ማንንም ቢሆን ከፓሪስ ህብረተሰብ ጋር የማስተዋውቅ ሰው አይደለሁም ። ”

“ ታዲያ ወይዘሪት ኢዩጊን ዳንግላርን በእኔ ፋንታ ሊያገባ ያጨው ማነው ? ” አለ አልበርት ።

“ ምን ? ” አለ ቡቻምፕ ነገሩ አዲስ ሆኖበት “ አንድሪያ ኢዩጊንን አጨ ? ”

“ ጋዜጠኛ አይደለህም እንዴ ? እንዴት ሁሉም የሚቀባበለው ወሬ እስካሁን ሳይደርስህ ይቀራል ? ” አለ እንደራሴው ግንባሩን ቋጥር አድርጎ ።

“ እና ጋብቻውን ያቀናጁት እርስዎ ነዎ ? ” ሲል ጠየቀ ቡቻምፕ ። በዚህ ጊዜ እንደራሴው ኮት ብሎ ሳቀ “ እኔ ጋብቻ አቀናጀሁ ? ያንት ያለህ ፤ ለካ አታውቀኝም ። እኔ እንዲያውም ጋብቻውን ከሚቃወሙት ውስጥ አንዱ ነኝ ፤ በሽምግልናው እንኳ ልገባ አልፈለግሁም ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እሃ ! በጓደኞችን በአልበርት ምክንያት ነው የተቃወሙት ? " አለ ቡቻምፕ ።

" በእኔ ምክንያት ? " አለ አልበርት ቀበል አድርጎ " በፍጹም ሊሆን አይችልም ። እንዲያውም ከጋብቻው እንዲገላግሉኝ ስለም ናቸው እንደነበርና ምስጋናዬን ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆኑም በመ ጨረሻው ከማልፈልገው ጋብቻ እንደገላገሉኝ እንደራሴው ራሳቸው ሊነግሩህ ይችላሉ ። "

" ያም ሆነ ይህ የተጠበቀውን ያህል በነገሩ የተደሰትክበት አት መስልም አልበርት " አለ እንደራሴው ። " ምናልባት ለራስህ ሳይታወቅህ ከወይዘሪት ኢዩጊን ፍቅር ይዞህ ይሆን ? "

" እኔ እንጃ " አለ አልበርት ሳቅ እየዳዳው ።

" ግን ዛሬ የወትሮው አይደለህም ፤ " ሲል ጠየቀው " ምን ሆነሃል ? "

" ራስ ምታት አሞኛል ። "

" እኔ እንደ ህመም ሲሰማኝ የምጠቀምበት ፍቱን መድ ሃኒት ልጠቁምህ ። "

" ምንድን ነው እሱ ? "

" ሽርሽር ። እኔ ራሴ ሰሞኑን ትንሽ ህመም እየተሰማኝ ስለተ ቸገርኩ ሽርሽር ወጣ ብዬ አካባቢውን ቀይሬ ለመስንበት ወስኛ ለሁ ። አብረኸኝ ብትሰነብት ምን ይመስልሃል ? "

" በጣም ደስ ይለኛል ። ግን የምንሄደው የት ይሆን ? "

" አየሩ ንጹህ ፤ አካባቢው ጸጥ ያለ ፤ ሰዎች የፈለገውን ያህል ቢኩራሩም ኢምንትነታቸውን የሚያስተውሉበት ፤ ባጭሩ ወደ ባህር ጠረፍ ። ይገርምሃል አንድ ሰው የቤት እመቤቱን እንደሚያፈቅርና ለጥቂት ጊዜ ስትለዬው በናፍቆት እንደሚያሰቀልል ሁሉ እኔም ለባህር ተመሳሳይ ፍቅርና ናፍቆት አለኝ ። "

" በጣም ጥሩ ክቡር እንደራሴ ፤ እንሂድ ! " አለ አልበርት በጉጉት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ግብዣዬን ትቀብለሃላ ? "

" አዎ ። "

" መልካም እንግዲህ ፤ ዛሬ ማታ ግቢዬ ውስጥ ልክ አሊጋህ ላይ እንደተጋደምህ ሁሉ የምትንፈላሰስበት የጉዞ ሰረገላ ይዘጋጅል ሃል ። ቡቻምፕ፣ ሰረገላው አራት ሰዎችን አዝናንቶ ይይዛል ። አብረ ኸን ለመጓዝ ትፈልጋለህ ? "

" አመሰግናለሁ ። ሆኖም እኔ ዛሬ ከሽርሽር መመለሴ ነው ። "

" ግን የትኛው ጠረፍ ነው የምንሄደው ? " ሲል ጠየቀ አል በርት ።

" ኖርማንዲ ። አይስማማህም ? " በማለት እንደራሴው ጥያቄ ውን በጥያቄ አስከትሎ መለሰ ።

" በጣም ይስማማኛል ። በርግጥ ገጠር መግባታችንን የምናው ቅበት ሥፍራ ነው ። ግርግር የለ ፤ ጐረቤት የለ ፤ ለመሆኑ አብረውን የሚጓዙ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ ? "

" የግልቢያ ፈረሶች ፣ የአደን ውሾችና የአሳ ማስገሪያ ታንኳዎች ብቻ ። "

" ልክ እኔም የምፈልጋቸው እነዚህን ነበር ። በቃ ለእናቴ አሳ ውቄ በፈለጉ ሰዓት ለመንቀሳቀስ ተዘጋጅቻ እጠባበቃለሁ ። "

" ደህና ፤ በአሥራ አንድ ሰዓት ስለምንነሳ ተዘጋጅተህ እዚህ ድረስ መምጣት ትችል ይሆን ? "

" በሚገባ ፣ ለጉዞ ከመዘጋጀት በስተቀር ሌላ ሥራ የለኝም ። " አልበርት ወደ ቤቱ ጉዞ ሲጀምር ሲነሳ እንደራሴው ፈገግ ብሎ ካሰና በተው በኋላ በአንዳች ሀሳብ የተመሰጠ መስሎ እንደቆመ ቀረ ። ከዚያም ሃሳቡን ይጠርግ ይመስል ግንባሩን በእጁ ዳሰስ ካደረገ በኋላ ደወል ደውሎ ቤርቱሲዮን ጠራ ።

"ቤርቱሲዮ" አለ እንደራሴው ፤ " መጀመሪያ እንዳሰብኩት ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ሳይሆን ዛሬውኑ ወደ ኖርማንዲ መሄዴ ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ጊዜ ጠብቆ ጉዞ በማሳደርግበት ወቅት ቤርቱሲ ዮ ይሸጣቸ ዋል ። ስለሳና አርባ ሺህ ፍራንክ እንደሚያወጡ ሲናገር የሰማሁት ይመስለኛል ። »

« ግን ድንገት የመጣልኝ አንድ ሃሳብ ብገልጽልዎ ይፈቀድል ኛል ፣ ክቡር እንደራሴ ? »

« ምን ገዶኝ »

« መቼም በመላ አውሮፓ ክርስዎ ቀጥሎ ያለው ክበርቱ ቤር ቱሲዮ ለመሆን እወራረዳለሁ ። »

« በጣም ተሳስተሃል ፣ አልበርት » ሲል መለሰ እንደራሴው ።

« የቤርቱሲዮን ኪሶች ብትዘቀዝቃቸው የገንዘብ ዘር ጠብ እንደማ ይላቸው እርግጠኛ ነኝ ። »

« እረ በሕግ ? » አለ አልበርት ጆሮውን ማመን አቅቶት ። « ይኼ ከሆነማ ከዓለም አስደናቂ ነገሮች ስምንተኛው የርስዎው ሲኞር ቤርቱሲዮ መሆን አለበት ! አሁንስ በዛ ፣ ክቡር እንደራሴ ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ሌላ ተአምራዊ ነገሮች ቢነግሩኝ እንደማላምንዎ ይወቁ ። »

« እኔን በሚመለከት አንድም ተአምራዊ ነገር የለም ፣ አልበርት ። የመረጃና የሎጂክ ጥያቄ ነው ። እስኪ መልስልኝ ፣ አሽከር ለምን ይሠ ርቃል ? »

« እንዴ ፣ ተፈጥሮው ስለሆነ ነዋ ፣ ለመስረቅ ሲል ይሠር ቃል ፣ አመል አይደል ። »

« የለም ፣ ይኼ እንኳ ከእውነት የራቀነው ። ሚስትና ልጆች ቢኖሩት ፣ ለርሱና ለቤተሰቡ ሲያደርግ የሚያቅደው አንድ ውጥን ቢኖረው ፣ ከሁሉም በላይ ከጌታው ጋር ዕድሜ ልኩን እንደሚኖር እርግጠኛ ባይሆን በርግጥ ለወደፊት ሕይወቱ ዋስትና ለማመቻቸት ሲል ሊሰርቅ ይችል ነበር ። ቤርቱሲዮ ግን በዚህች ዓለም ብቻውን ያለ ምስኪን ነው ፣ ለኔ ሳያሳውቅ ገንዘቤን እንደፈለገው ይጠቀማል ፣ እንደፈለገው ያወጣል ። የካዝናዬ ቁልፍ በጁ ሲሆን እንዲያውም



t.me/OLDBOOKSPDF

ያሳይ ሥፍራ ላይ ሆነው ራት ከበሉ በኋላ በግል ቢተመጻህፍት ጥቂት ጊዜ አሳለፉ ።

በዚህ ዓይነት እንደሰዓት የፈጠኑ ሁለት ቀናት ከነፉ ።

በሦስተኛው ቀን መሸትሸት ሲል እንደራሴው እንደ ልጅች ጨዋታ ሲያዩው የነበረው ስፖርት ጡንቻዎቹን ያዛለበት አልበርት ወደመኝታ ክፍሉ ሄዶ የደከመ ሰውነቱን ለማሳረፍ ጋደም እንዳለ ከመንገዱ አካባቢ የፈረስ ኮቴ በመስኮቱ በኩል ተሰማው ። ብድግ ብሎ አንገቱን በማስወጣት ሲመለከት የራሱን የቤት ባለሟል ተመ ለከተ ። ይህንን ባለሟል በጉዞው ስላላስከተለው ግራ ተጋብቶ በቅ ጽበት መንፈሱ ተረበሸ ።

“ እንዴት ሊመጣ ቻለ ? ” እያለ በጭንቀት የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ ። “ እናቴ አንድ ነገር ሆና ይሆን ? ” በሩጫ ሄዶ ባለሟሉ አጠገብ እንደደረሰ ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ከላይ ከላይ መተንፈሱን ያልቀነሰው ባለሟል በውስጡ ጋዜጣና ደብዳቤ የያዘ ትልቅ ፖስታ ሰጠው ።

“ ደብዳቤው ደግሞ ከማነው የተላከው ? ” አለ አልበርት ተቻ ኩሎ ።

“ ከጋዜጠኛው ባልንጀራዎ ፡ ከቡቻምፕ ” ሲል መለሰ ባለ ሟል ።

“ ቡቻምፕ ነው የላከህ ? ”

“ አዎ ጌታዬ ፡ ለጉዞው ገንዘብ ሰጥቶኝ ፈረስ ከተከራዩልኝ በኋላ እዚህ እስከደርስ ድረስ ለአፍታ እንኳ እንዳልቆም ቃል አስገ ብቶ ላከኝ ። በአሥራ አምስት ሰዓት የጥድፊያ ጉዞ ነው የደረስኩት ።”

አልበርት ደብዳቤውን ገለጠ ። የመጀመሪያዎቹን ጥቂት መስ መሮች እንዳነበበ ልቅሶ አይሉት ኡኡታ በግልጽ የማይታወቅ ጩ ኸት የመሰለ ድምፅ አሰምቶ ደብዳቤውን ከእጁ ጣለና ጋዜጣውን ሊዘረጋ ሞከረ ። ይሁንና በድንገት አይኖቹን አንዳች ነገር ጋርዶት የሚንቀጠቀጡ እግሮቹ ተብረከረከው ሊደግፈው እጆቹን ከዘረጋለት ባለሟሉ ጫማ ስር ድፍት አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" አይ አለመታደል ! " አለ የወጣቱን ሁኔታ ከሩቅ ሲከታተል የነበረው እንደራሴ በዝቅተኛ ድምጽ " የአባት ኃጢአት ለልጅና ለልጅ ልጅ ይተላለፋል የሚሉት እውነት ይሆን ? "

ከጥቂት ቆይታ በኋላ አልበርት ልብ ገዝቶ ጋዜጣውን ያነብ ጀመር ። ከዚያም ጋዜጣውን ጭምድድ አደረገና " ፈረስህ ወደ ፓሪስ ሊመልሰኝ ይችላል ? " ሲል ባለሟሉን ጠየቀው ።

" ኧረ በጣም ደክሟል ፤ እኔንም በስንት እሻር ነው እዚህ ያደረሰኝ ። "

" ወየው ጉዴ ፤ ለመሆኑ ወዲህ ስትመጣ ቤታችን እንዴት ነበር ? " ሲል ጠየቀ አልበርት ።

" ጸጥ ያለ ነበር ፤ ግን ወደዚህ ለመምጣት ከመነሳቴ በፊት ከመሴ ቡቻምፕ ቤት እንደተመለሱ እናትዎ በእንባ እየታጠቡ እር ስዎ የሚመለሱበትን ጊዜ እንዳጣራ ላኩብኝ ። እኔም መሴ ቡቻምፕ እርስዎን እንዳመጣ የላኩኝ መሆኑን ነገርኳቸው ። መጀመሪያ እጇን ያዝ አድርገው ሊያስቀሩኝ ከከጀሉ በኋላ ጥቂት አሰቡ ' በቃ ሂድና ቶሎ እንዲመጣ ንገረው ' አሉኝ ። "

አልበርት ዞር ብሎ እንደራሴው ሁኔታውን ወደሚከታተልበት ክፍል በሩጫ አመራ ። " ክቡር እንደራሴ ፤ " አለ " ላደረጉልኝ እን ክብካቤ እጅግ አመሰግንዎታለሁ ። ብዙ ጊዜ አብሬዎ ብሰነብት ደስ ባለኝ ነበር ። ሆኖም አሁኑኑ ወደ ፓሪስ መመለስ አለብኝ ። "

" ምን ችግር ተፈጠረ ? " እንደራሴው ለነገሩ እንግዳ መስሎ ግንባሩን ሽብሽብ አደረገ ።

" እጅግ የመረረ እክል ደርሶብኛል ፤ ግን እባክዎ አሁኑኑ እን ድሄድ ይፍቀዱልኝ ። . . . ከህይወቴ የበለጠ ትልቅ ነገር አደጋ ላይ ወድቋል። ክቡር እንደራሴ ሌሎች ጥያቄዎችን ከሚያቀርቡልኝ ይልቅ ፈረስ እንዲሰጡኝ እለምንዎታለሁ ። "

" ከግምጃ ቤት የመረጥከውን ፈረስ ልትጠቀም ትችላለህ " አለ እንደራሴው ።

" ግን ያን ሁሉ መንገድ በፈረስ ብትጓዝ በድካም ዝለህ ትሞ ታለህ ፤ ሰረገላ ብትጠቀም ነው የሚሻለው ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

# 43

አልበርት በሚቀጥለው ቀን ጧት ላይ ፓሪስ እንደደረሰ የቡቻምፕን ቤት የመኝታ ክፍል በር በርግዶ ገባ ።

" ስጠብቅህ ነበር ክልታማው ጓደኛዬ " አለ ቡቻምፕ ።

" እኔም መጥቻለሁ ። " አለ አልበርት ፤ " የላክህልኝ መልዕክት ታማኝነትህንና ተቆርቋሪነትህን ያረጋግጣል ፣ እስኪ ጊዜ ሳናጠፋ የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ንገረኝ ። "

አልበርት በቁጭትና በሐፍረት እየተሸማቀቀ ጋዜጠኛው ጓደኛው የሚያቀርብለትን ገለጣ በተመስጦ ያዳምጥ ጀመር ።

ለጋዜጣው የቀረበው ጽሁፍ ቡቻምፕ ሳያውቅ ታትሞ ከወጣ ሁለት ቀን አልፎት ነበር ። ቡቻምፕ ጽሁፉን በሚያነብበት ወቅት ቁርስ ላይ ነበር ። ምግቡን ሳይጨርስ ወደ ጋዜጣው ዝግጅት ቢሮ እየተጣደፈ ሄደ ። ምንም እንኳ የአዘጋጁ የፖለቲካ አቋም ከቡቻምፕ ጋር የሚፃረር ቢሆንም የቀረበ የጓደኝነት ግንኙነት ነበራቸው ።

" የመጣሁት ስለሞርስፍ እንደራሴ የወጣውን ጽሁፍ በተመለከተ ላነጋግርህ ነው " አለ ቡቻምፕ እንደደረሰ ።

" አ ፣ አዎ . . . አነጋጋሪ ጉዳይ ነው ፣ አይደለም ? " አለ የጋዜጣው አዘጋጅ ።

" በጣም አነጋጋሪ ከመሆኑ የተነሳ በስም አጥፊነት ከመጠየቅ የምታመልጥ አይመስለኝም ። "

" ማ እኔ ? በፍፁም እንድም አደጋ አይገጥመኝም ። ጽሁፉን የሰጠን ሰው ጠንካራ ማስረጃ ስላለው ጄኔራል ሞርስፍ አንድም ቃል እንደማይተነፍሱ እርግጠኞች ነን ። ከዚህም በተጨማሪ ለያ ዙት ሹመት ብቁ ያልሆኑ ከሃዲዎችን ማጋለጥ ለአገር ታላቅ ግልጋሎት ማበርከት ነው ። "

" ጽሁፉን ማን ሰጠህ ? "



t.me/OLDBOOKSPDF

« ትናንት አንድ ሰው ከያኒና ከተማ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሰነዶችን በመያዝ ሊያነጋግረን መጣ ። ነገሩን እንደውንጀላ ቆጥረን ሳለማተም ስናመነታ ሰውየው እኛ እምቢ ካልን ለሌላ ጋዜጣ ዝግጅት ጽሑፉን አቅርቦ እንደሚያሳትመው ነገረን ። ቡቻምፕ ጋዜጠኛ እንደመሆንህ መጠን አንድ ጠቃሚ ጽሁፍ ማውጣት ምን ያህል ትልቅ ነገር እንደሆነ ታውቀዋለህ ። በዚህም መሠረት ጽሁፉ በእጃችን ከገባ በኋላ እንዲነጥቀን አልፈለግንም ። አሁንማ አንድ ጊዜ ምላጩ ስለተሳበ የተኮሱ ድምጽ በመላ አውሮፓ እንዳያስተጋባ የሚያግደው ነገር የለም ። ” አለ የጋዜጣው አዘጋጅ ። ቡቻምፕ ምንም ማድረግ እንደማይችል ተረዳ ። ያለው አማራጭ ወደ አልበርት መልዕክት መላክ ነበር ።

ጉዱ ይህ ብቻ አልነበረም ። ነገሩ የተፈፀመው መልእክተኛው ጉዞውን ከጀመረ በኋላ በመሆኑ ቡቻምፕ ለአልበርት ሊገልጽለት ያልቻለው አንድ ሌላ ህዝበፓሪስን ያንቀጠቀጠ ሁኔታም ተከስቷል ። በዚያው ዕለት የአልበርት አባት በአባልነት በሚሠራበት ምክር ቤት ኃይለኛ ቅስቀሳ በመካሄድ ላይ ነበር ። የምክር ቤት አባላት ከእውቅ ጓደኞቻቸው መካከል ባንዱ ላይ በማንገርበብ ላይ ስለሚገኘው አስጊ ሁኔታ ለመነጋገር ከመደበኛው የሥራ ሰዓት ቀደም ብለው ሥፍራቸውን ይዘዋል ። አንዳንዶቹ ጓደኞቻቸው በጋዜጣ ላይ የቀረበበትን የውንጀላ ጽሑፍ ያነባሉ ፤ ሌሎቹም ለውንጀላው ተጨማሪ ክብደት በመስጠት ላይ ስለሚገኘው የሌተና ጄኔራል ሞርሰፍ የጥንት የሕይወት ታሪክ ይነጋገራሉ ። ጄኔራል ሞርሰፍ በጓደኞቹ ዘንድ የሚወደድ ሰው አልነበረም ። ክብሩን ለማስጠበቅ የሚያደርገው ከልክ ያለፈጥረት ግትርና ጉረኛ አድርጎታል ።

ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ጋዜጣውን ያላነበበ ሰው ቢኖር ጄኔራል ሞርሰፍ ራሱ ብቻ ነበር ። ጋዜጣው ታትሞ በወጣበት ጧት ጄኔራሉ ደብዳቤ በመጻፍና ፈረስ በመግራት ሥራ ላይ ተጠምዶ ስለነበር በተለመደው ሰዓትና በወትሮው ኩራት ወደምክር ቤቱ አዳራሽ ሲገባ የጓደኞቹን የቀዘቀዘ ሰላምታም ሆነ የአስተናጋጆችን ሽሙጥ ሊያስተውል አልቻለም ። እሱ በገባበት ወቅት ስብሰባው ከተጀመረ ግማሽ ሰዓት አልፎታል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይመስል በፍርሃት አቀረቀረ ። ቀጥሎም ትንፋሹን እንዳፈነው ሁሉ የተቆለፈ ኮቱን በኃይል ከፈተና እብደት እንደጀመረው ሰው እየቀባዠረ ከአዳራሹ ወጣ ። አዳራሹን እስኪወጣ ድረስ የእርምጃው ድምፅ ሐዘኑን በማስተጋባት ሙሾ እንደሚያወርድ ለቀስተኛ አጀበው ። ሰረገላው ውስጥ እንደገባ በከባድ ፍጥነት ወደቤቱ ገሰገሰ ።

“ ወንድሞቼ ” አሉ ሊቀመንበሩ አዳራሹ መልሶ ፀጥ ማለት ሲጀምር ፤ “ ሌተና ጀኔራል ሞርስፍ የዝርፊያ ፣ የነፍስ ግድያ ፣ የክህደትና በሥልጣን የመባለግ ወንጀለኛ ሆኖ አግኝተነዋልን ? ”

“ አዎ . . . .! ” በማለት የኮሚሽኑ አባላት ባንድነት ሲጮኹ ግድግዳው ድምጻቸውን እየተቀባበለ ሲያቀናቅን ቆየ። “ አዎ . . . .! ”

ሃይዲ ቃሉን ስታዳምጥ የደስታም ሆነ የሐዘኔታ ምልክት አልታየባትም ። ጥቂት እንደቆየች ፊቷን መልሳ በሻሹ ከሸፈነች በኋላ በታላቅ ግርማ ሞገስ ለስብሰባው እጅ ነስታ ረጋ ባለ የንግሥት አረማመድ ከአዳራሹ ወጣች ። ያችን የግሪክ እሸት ሁሉም አይኖች በአድናቆትና በአክብሮት እንደፈዘዙ እስከበር ድረስ ሸኟት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በርግጥ እኔ ነኝ ፣ ግን አንድ ሰው ማደጐ ልጁን ለአንድ ጐረ ምሳ ሲድር ሲታጭ ስለሙሽራው ቤተሰብ ማጣራት የለበትም ? ይህ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም መሰለኝ ? ” አለ ዳንግላር የበለጠ እየተረጋጋ ።

“ ወዶ ያኒና በጽሁፍ ስትጠይቅ የምትቀበለውን መልስ በደ ንብ ታውቅ ነበር ። ” አለ አልበርት ።

“ ባውቅ ኖሮ ምን አጻፈኝ ? ስለ አሲ ፓሻ አወዳደቅስ እንዴት ላውቅ እችላለሁ ? ”

“ ታዲያ ሌላ ሰው እንድትጠይቅ ገፋፋህ ? ”

“ አዎ ። ”

“ ማነው እሱ ? . . . ንገረኝ ? ”

“ ባንድ ወቅት ስለአባትህ የሕይወት ታሪክ ካንድ ሰው ጋር ስንጨዋወት አባትህ ሐብቱን ከዬት እንዳገኘው እስካሁን ሚስጥር መሆኑን ስናገር ሰውየው የአባትህ ሐብት ከዬት አገር እንደመጣ ጠየ ቀኝ ። እኔም ከግሪክ እንደሆነ ነገርኩት ። እሱም ’ እንግዲያውስ ለአ ስፈላጊው መረጃ ወደ ያኒና ጽፈህ ጠይቅ ‘ አለኝ ። ”

“ ያሰው ማነው ? ”

“ የራስህ ጓደኛ ፣ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ። ”

አልበርትና ቡቻምፕ ተፋጠጡ ።

“ መሴ ዳንግላር ” አለ እስካሁን በዝምታ ሁኔታውን ሲከታ ተል የቆየው ቡቻምፕ “ እንደራሴውን እየወነጀልህ ነው ፣ እሱ ግን አሁን ፓሪስ ውስጥ ስለማይገኝ ራሱን ሊከላከል አይችልም ። ”

“ እኔ ማንንም አልወነጅልም ! ” ሲል መለሰ ዳንግላር “ እኔ የምናገረው የሆነውን ብቻ ነው ። ካስፈለገም ሰውየው ሲመለስ አሁን የተናገርኩትን በፊቱ ልደግምላችሁ እችላለሁ ። ”

“ እንደራሴው ከያኒና የደረሰህን መልስ ያውቃል ? ” ሲል ጠየቀ አልበርት ተቻኩሎ ።

“ አሳይቸዋለሁ ። ”

“ የአባቴ የቀድሞ ስም ፈርናንድ ሞንዴጐ መሆኑንስ ? ”

“ አዎ ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት ነግሬዋለሁ ። እኔ ያደረግሁት ማን ም ሰው በኔ ቦታ ቢቀመጥ የሚያደርገውን ፣ እንዲያውም ከዚያ ያነሰ



t.me/OLDBOOKSPDF

# 45

ከዳንግላር ግቢ ወጣ እንዳሉ ቡቻምፕ ስሜቱ ገንፍሎ የሚዋከበውን ጓደኛውን አስቀድሞ “ አልበርት ፣ ወደ እንደራሲው መኖሪያ ቤት ከመሄዳችን በፊት ጥቂት ብታስብበት አይሻልም ? ” አለው ።

“ ስለምን ? ”

“ ስለምታደርገው ነገር አያገኙት ? ”

“ አፋ ! እኔ የምፈራው አንድ ነገር ፣ ፍልሚያ ለመግጠም የማይፈልግ ሰው እንዳላገኝ ብቻ ነው ። ”

“ አዬ ፣ ስለሱስ አታስብ ” አለ ቡቻምፕ ፤ “ እርግጠኛ ነኝ እንደራሲው ይፋለማል ፣ እንዲያው ም ከጠበቅኸው በላይ ሳይፋለም አይቀርም ። ተጠንቀቅ ! ”

“ ወዳጄ ፣ ” አለ አልበርት ከፈገግታ ጋር ፤ “ በኔ ላይ ሊደርስ የሚችለው ግፋ ቢል ለአባቴ ክብር መሞት ነው ። ያ ደግሞ ሁላችንንም ከውድቀት ያድነናል ። ”

“ ግን እናትህም እንደምትሞት አትርሳ ። ”

“ ያልታደለች እናት ” አለ አልበርት ለእፍታ አይኖቹን በእጁ ሸፍኖ ፤ “ ያንን አውቃለሁ ። ሆኖም ተዋርዳ ከምትኖር ሃዘን ቢገድላት እመርጣለሁ ። ”

“ እስከዚህ ቆርጠሃል አልበርት ? ”

“ አፋ ፣ አዎ . . . ! ”

“ እንግዲያውስ እንሂድ ። ሰውዬውን ኖርማንዲ የምናገኘው ይመስልሃል ? ”

“ እኔ ስመለስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚመጣ ሲናገር ነበር ። እስካሁን ተመልሶ መሆን አለበት ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሃል ከተማ ወደሚገኘው የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ መኖ ሪያ እየተጣደፉ ሄዱ ። በር ላይ ያገኙት ባፕቲስቲን የተባለውን ባለ ሟል ነበር ። በርግጥም እንደራሴው ከጥቂት ሰዓቶች በፊት ከኖርማ ንዲ ተመልሶ ኖሯል ። ይሁንና ማንም ሰው እንዳያነጋግረው ትዕዛዝ ሰጥቶ ወደ ሰውነት መታጠቢያው ገብቷል ።

" ሰውነቱን ከታጠበ በኋላ ምን ያደርጋል ? " አለ አልበርት ኃይል በተቀላቀለበት አነጋገር ።

" ራት ይበላሉ ፤" ሲል መለሰ ባፕቲስቲን ፣ አልበርት እንደራሴ ውን ዘልፎ በመናገሩ ግራ ገብቶት ሲስቅ እየከጀለው ።

" ከራት በኋላስ ? "

" ለአንድ ሰዓት ያህል ይተኛሉ ። "

" ከዚያስ ? "

" ኦፔራ ይመለከታሉ ። "

" እርግጠኛ ነህ ? "

" መቶ በመቶ ። እንደራሴው ሁለት ሰዓት ላይ ሰረገላቸው ዝግጁ እንዲሆንላቸው አዝዘዋል ። "

" በጣም ጥሩ !" አለ አልበርት ፤ " ይህን ብቻ ነው ማወቅ የም ፈልገው ። " ቀጥሎም ወደ ቡቻምፕ ዞር አለ ። " የምትሰራው ሥራ ካለህ አሁኑኑ ጨርስ ። ለዛሬ ማታ የያዝከው ቀጠሮ ካለም ለነገ አስተ ላልፈው ። ዛሬ ማታ አንተን እስከትዬ ለምን ወደ ቲያትር ቤት እን ደምሄድ የሚገባህ ይመስለኛል ። ከቻልህ ሬናውድንም ጭምር ይዘህ ና ። "

አልበርት ቤቱ እንደደረሰ ፍራንዝ ፣ ደብሬይና ማክሲሚሊን በ ዚያ ምሽት ቲያትር ቤት ድረስ በጥብቅ እንደሚፈልጋቸው መልዕ ክት ላከ ። ከዚያም በጋዜጣ የታተመው አሳዛኝ ዜናና የምክር ቤቱ ጉድ ከተፈጸመ ጀምሮ ማንንም ሳለመቀበል እምቢ ብላ በግል ክፍሏ እንደተቀመጠች ያለችውን እናቱን ሊያይ ሄደ ።

እመቤት ሞርስፍ ልጇዋን ስታይ እጇን ጭብጥ አድርጋ ተንሰቀ ሰቃ ታለቅስ ጀመር።አልበርት እናቱን ትኩር ብሎ እያዩ ለአፍታ ዝም ብሎ ቆየ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" መልካም ቡቻምፕ" አለ አንድራሴው ፤ " አሁን ሁሉም ነገር ተወስኗልና የቀረውን ተውኔት እንድመለከት ፍቀድልኝ ። በነገራችን ላይ ጓደኛህን ዳግመኛ ተመልሶ እንዳይመጣ ምከረው እባክህ ። በገዛ ራሱ ጉሬ ጉሮሮውን አይሰንጥቅ ። ወደ ቤት ሄዶ ጥቂት እንቅልፍ ቢያገኝ ነው የሚበጀው ። "

ቡቻምፕ ሲያነጋግረው የነበረው ሰው ተራ ጉረኛ ይሁን ወይም ከሰው የተለየ ፍጡር ተምታቶበት እየተገረመ ወጣ ።

አንድራሴው ወደ ማክሲሚለን መለስ ብሎ " ባንተ ልተማመን እችላለሁ ። አልችልም ? " ሲል ጠየቀ ።

" ያለጥርጥር " ሲል መለሰ ማክሲሚለን " ግን . . . . ? "

" ግን ምን ? "

" የአምባጓሮውን እውነተኛ መንስኤ ባውቅ እጅግ ደስ ይለኛል ። "

" የኔ ደጀን ለመሆን አለመፈለግህን ልትነግረኝ ነው ? "

" ኧረ አይደለም ። "

" እውነተኛው መንስኤ ? " አለ አንድራሴው " አልበርት ራሱ እንኳ አያውቀውም ። በዚህች ምድር ላይ እውነተኛውን መንስኤ የማውቀው ሰው እኔ ብቻ ነኝ ። ግን ልነግርህ አልችልም ። እንኳን ላንተ ለገዛ ራሴ ጆሮዎች ስለሚዘገንን ከፌ ማውጣት አልችልም ። ሆኖም ቃሌን ልስጥህና ትክክለኛው ፍርድ ለእኛ ይፈረድልናል ። "

" ለእኔ ይህ ይበቃኛል ክቡር አንድራሴ " አለ ማክሲሚለን ። "ሌላው ደጀንዎስ ማን ይሆን ? "

" ፓሪስ ውስጥ ያንን ክብር ልሰጣቸው የምፈልገው ላንተና ለእህትህ ባል ለአማኑኤል ነው ። አማኑኤል ይቀበለዋል ትላለህ ? "

" በራሴ እርግጠኛ የሆንኩትን ያህል ለእሱም አፌን ሞልቼ መናገር እችላለሁ ፤ ክቡር አንድራሴ ። "

" ጥሩ እንግዲያውስ ነገ ልክ በአንድ ሰዓት ቤቴ ድረስ ብቅ በሉ ። "

" እንቀርም ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

# 46

ኦፔራው እንዳበቃ እንደራሴውና ማክሲሚለን ተለያይተው ወደ የቤታቸው ሄዱ ። እንደራሴው አሁንም ርጋታውና ፈገግታው ያል ተለየው ሰው መስሎ ይታያል ። ይሁን እንጂ መኝታ ቤቱ ውስጥ እን ደገባ አሊን ጠርቶ በረጅሙ ተንፈስና “ እስኪ ባለዝሆን ጥርስ እጀታ ሽጉጤን አምጣልኝ . . . . አሊ ? ” ብሎ ሲያዝዝ ለሰማው የድምጹ ቃና ሰውዬውን በደንብ ለሚያውቀው የታከተ ትላጼ ያዘለ መሆኑ ግልጽ ነበር ።

አሊ ሽጉጡን አቅርቦ ከመውጣቱ እንደራሴው ትክዝ እንዳለ በጥንቃቄ አገላብጦ መረመረው ። ሽጉጡን በእጁ እንደያዘ በሩ ተከፍቶ ቤርቱሲዮ ገባ ። ሆኖም እንደራሴው አፉን ለመክፈት እንኳ ጊዜ ከማግ ኘቱ በፊት ከሠራተኛው ኋላ በሩ ላይ የተሸፋፈነችቤት መቆሟን አስተ ዋለ ። ቤርቱሲዮ እንዲወጣ ምልክት ሰጥቶ ት እንደወጣ በሩን ዘጋው ።

“ ማን ልበል እመቤት ? ” አለ እንደራሴው ትካዜ እንደዋጠው ፣ የተሸፋፈነችውን ሴት ። ሴትዮዋ እጆቿን ግጥም አድርጋ ልትንበረከክ እየቃጣት ሆድ በሚበላ ሆደ ባሻ እንደበት “ ልጄን አትግደልብኝ ፣ ኢድመንድ ! ” አለች ።

እንደራሴው ከቁጥጥሩ ውጭ በሆነ መንገድ ሽምቅቅ ብሎ ወደ ኋላ ሲያፈገፍግ ሽጉጡ ከእጁ አምልጦ እንዴት እንደወደቀ አልታ ወቀውም ። ሊያነሳውም አልሞከረም ። “ የምን ስም ነው የጠራሽው እመቤት ሞርሰፍ ? ” አለ በተለመደው ቀዝቀዝ ብሎ ሆድ የሚረ ብሽ ቃና ።

“ ያንተን ! ” አለች ሴትዮዋ ሽፋኗን ወደ ኋላዋ እየገለጠች ። “ ያንተን እውነተኛ ስም ። እኔ ብቻ የማስታውሰውን ! ኤድመንድ ፣ የምታነጋግርህ እመቤት ሞርሰፍ አይደለችም ፤ ሜርሲደስ ነች ! ” እንደራሴው በረጅሙ ተነፈሰ ። “ ሜርሲደስ ሞታለች እመቤት ፣ በዚያ ስም የምትጠራ ሌላ ሴት አላውቅም ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ንቃቄ የተዘጋጀ ሥነጽሁፍ የሚያነብ ተራኪ እንጅ አእምሮው የሚያፈልቅለትን በሜት እንደቀልድ የሚወረውር ሰው አይመስልም ።

“ ኢድመንድ ” አለች ሜርሲደስ በመጨረሻው ፤ “ የቀረኝን አንድ ነገር ልንገርህ ፣ እንደምታዬው ቁንጅናዮ ፈዟል ፣ ውበቴ ጠውልጓል ። ይሁን እንጅ በኔ ይሁንብህ ፣ ሜርሲደስ ገጽታዋ የወትሮው ባይሆንም ልቧ ግን እንዳለ ነው ። በል እንግዲህ ደህና ሁንልኝ ኢድመንድ ፣ ካሁን በኋላ መንግሥተ ሰማያትን እንኳ አልመኝም ። አንተን እንደወትሮው ክቡርና አስተዋይ ሆነህ ለማዬት በቅቻለሁ ። ደህና ሁንልኝ ፣ ኢድመንድ ። ከልቤ አመሰግንሃለሁ ። ”

እንደራሴው መልስ አልሰጠም ። ነገሩ ሁሉ ሕልም መሰለው ። አይኖቹን ጭፍን አደረገ ። የሰረዘው የብቀላ ቃልኪዳን ከከተተው ቅዠት የመሰለ ሰመመን ብንን ሲል አይኖቹን ቢገልጥ ሜርሴደስ የለችም ። “ ወይኔ አረንዛው ! ” ሲል አንጓሩ አገጩን በእጁ አስደግፎ በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ ። “ ብቀላ ብሎ መሃላ ። እንዴት ያለሁት ደደብ ኖሬአለሁ ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

## 47

ማክሲሚሊንና ኢማኑኤል ከቀጠሮው ሰዓት ፂያ ደቂቃውን ቀደም ብለው ደረሱ ። “ ቀደም ብዬ በመምጣቴ ይቅርታ ይደረግልኝ ” አለ ማክሲሚለን “ ይሁንና እኔም ሆንኩ ቤቴ ውስጥ ያለው ሰው በሙሉ ለእጥቃ እንቅልፍ ኸልብ አላደረገንም ነበር ። እርስዎን እተካ ዘንድ የርስዎን ወኔና ልበ ሙሉነት ለማየት ችኩያለሁ ። ”

እንደራሴው በዚህ አነጋገር ልቡ ከመነካቱ የተነሳ እጁን በመጨበጥ ፋንታ ክንዶቹን ዘርግቶ ተጠመጠመበት ። “ ማክሲሚለን ” አለ “ የእንተ ዓይነቱ ወጣት ሰው ሲወደኝ የሚሰማኝ ስሜት የዛሬዋ ዕለት ለእኔ እንጸባራቂ መሆኗን ያሳዩኛል ። እና እውነት የእኔ ደጀን ለመሆን ወስናችኋል ? ”

“ አሁንም ይጠራጠራሉ ? ”

“ ግን እኔ ከተጠቃሁ ። . . . . ”

“ ኧከከ . . . . እኤኮ ትናንት ማታ በቲያትር ቤቱ የታየውን ሁሉ አስተውያለሁ ። ሌሊቱን ሙሉ ስለርስዎ በራስ መተማመን ሳስብ ፍርድ ለርስዎ እንደሚበየን ለራሴ ስናገር ነበር ያደርኩት ። አለዚያማ የሰውን ገጽታ አይቶ ምንም ነገር መናገር አይቻልም ማለት ነው ። ”

“ አመሰግናለሁ ማክሲሚለን ፤ ” ካለ በኋላ እንደራሴው ደወል ደውሎ አሊን ጠራና “ ይህን ወደኔ ኑዛዜ ተቀባይ ውሰድልኝ ” አለ “ ኑዛዜዬ ነው ማክሲሚለን ። ከሞትኩ በኋላ አንተን ይመለከታል ።”

“ እረረ . . . ” ሲል ጮኸ ማክሲሚለን “ የእርስዎ ሞት ? ”

“ ይሆናል ብሎ መጠንቀቅ ፤ ሲሆን ላለመደናገጥ ሳይሆን ለመደሰት ይረዳል ። የኔወንድም ፤ ግን እስኪንገረኝ ትናንት ከኔ ከተለየህ በኋላ ምን አደረግህ ? ”

“ ቡቻምፕንና ሬናውድን ፍለጋ ሄድኩ ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እንዴ ለምን ? ሥፍራው ፡ ሰዓቱ ፡ የመሳሪያው ዓይነት ሁሉ ም ተወስኖ የለም እንዴ ? ”

“ የመሳሪያውን ዓይነት ከሽጉጥ ወደ ጦር እንዲለውጡ ለማድ ረግ ፈልጌ ነበር ። ሽጉጥከ እውር ነው ። ”

“ ታዲያ ተሳካልህ ? ” ሲል ጠየቀ እንደራሴው በቃላት የማይ ገለጥ የተስፋ ጭላንጭል በዓይኖቹ እየታየ ።

“ በጦር ግጥሚያ እንዴት ራስዎን መከላከል እንደሚችሉ አገር አውቆልዎታል ። ”

“ እንዴት ታወቀ ? ”

“ አለልጣኞችን ባንድ ወቅት እንዳሸነፉ ታይቷል ። ”

“ ታዲያ አልተሳካልህማ ? ”

“ በፍጹም እሽ አላሉኝም ። ”

“ ለመሆኑ ሽጉጥ ተኩስ ላይስ አይተሽኝ ታውቃለህ ? ” ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

“ እረ የለም ። ”

እንደራሴው በአራት ማዕዘን የተቀረጸች አልማዝ ከጣውላ ጋር አጣበቀና ከሩቅ ሆኖ ሽጉጥ በማንሳት በአራቱም ማዕዘን መሐል ላይ አነጣጥሮ መታት ። “ ያንት ያለህ ” አለ ማክሲሚለን በእንደራሴ ው ቅልጥፍናና ትክክለኛነት ከመደንቅ አልፎ በፍርሃት እንደተዋጠ ። “ ስለእናት አንጀት ብለው ክቡር እንደራሴ ፤ አልበርትን አይግደሉ ት ፣ ያ ምስኪን ልጅ እናት አለችው ። ”

“ እውነት ነው ” አለ እንደራሴው” የእኔ ግን የለችኝም ። ” የእ ነዚህ ቃላት አነጋገር ማክሲሚለንን ሽምቅቅ አደረገው ።

“ የተበደሉት እርስዎ ነው ፡ ጌታዬ ። ”

“ አዎ ። ታዲያ ያ ምን ማለት ነው ? ”

“ ያ ማለት መጀመሪያ የሚተኩሱት እርስዎ ይሆናሉ ። ከልጁ ጓደኞች ጋር ብዙ ድርድር ካደረግን በኋላ ባይሆን ርቀቱ ትንሽ እን ዲጨምር ተስማምተናል ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እንዴት ወጣት ልጃገረድ አፈቅራለሁ ፤ ክቡር እንደራሴ ። ”

“ በጥልቅ ታፈቅራታለህ ? ”

“ ከሕይወቴ አስበልጨ ”

“ ሌላ ካብ ተናደ ። ” አለ እንደራሴው ። ከዚያም ተከዝ ብሎ ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምጽ “ ምስኪን ሃይዲ ” አለ በዚህች ዓለም ብቻዋን የምትቀረው ባይተዋር ባሪያው ትዝ ብላው ።

“ በደንብ ባላውቅዎ ኖሮ ክቡር እንደራሴ ” አለ ማክሲሚለን ፤ “ ለጉብዝናዎ ምስክር መሆን ያዳግተኝ ነበር ። ”

“ ትቸው ስለምሄደው ሰው እያሰብኩ በመተከዜ ነው የማት መሰክርልኝ ? ማክሲሚለን አንድ ነገር ልንገርህ ። ይህ ዓለም እዳዎቻችንን በሙሉ ክፍለን ፤ የውለታዎቻችንን አጸፋ መልሰን ፤ በትህትናና በንጽሕና እጅ ነስተን ልንሰናበተው የሚገባን ትርክርክ ባሉን ነው ። ”

ለአፍታ ሁለቱም ዝም አሉ ።

“ በነገራችን ላይ መሳሪያዎችዎን አምጥተዋል ? ”

“ የለም ፤ እኒያ ወንድሞቼ የራሳቸውን እንደሚያመጡ እጠብ ቃለሁ ። ”

“ ልጠይቃቸው ” ካለ በኋላ ማክሲሚለን በርቀት ከዛፎች ሥር ቆመው ወደሚያወሩት ወደ ቡቻምፕና ወደ ሬናውድ ሄደ ። ሶስቱ ወጣቶች በወዳጅነት መንፈስ እንኳ ባይሆን በአክብሮት ሰላ ምታ ተለዋወጡ ።

“ ይቅርታ አድርጉልኝ ጉብዝ ” አለ ማክሲሚለን ፤ “ምነው አልበርት በመካከላችሁ የለም ? ”

“ እዚህ ድረስ ራሱ እንደሚመጣ ዛሬ ጧት ልኮብናል ። ” አለ ቡቻምፕ ። “ ገና ሁለት ሰዓት ተኩልኮ ነው ፤ ብዙም ጊዜ አልባከ ነም መሰ. ማክሲሚለን ። ”

“ እንዲያውም ያው ሠረገላ እየመጣ ነው ። ” አለ ሬናውድ ፤ ወደ.ቆሙበት ሥፍራ ከሚያደርሱት አቋራጭ መንገዶች በአንዱ ፈጣን ሠረገላ ይገሰግሳል ። “ ግን አልበርት አይደለም ” አለ ሬና ውድ “ ፍራንዝና ደብራይ ናቸው ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣቶቹ በመካከላቸው መብረቅ ቢጥል እንኳ ከዚያ ተውኔት መስል ትርኢት የበለጠ አያስደነግጣቸውም ። እንደራሲው ግን ወሰን በሌለው አድናቆት ዓይኖቹን በዝግታ ወደሰማይ ቀና አደረገ ። ያስደነቀው ከኢጣሊያ ሽፍቶች ሊያድነው ሲደርስለት እንኳ መንፈሱ ቅንጣት ያልተረበሸው ፤ ወኔ የተሞላው አልበርት እንዲያ ራሱን ዝቅ አድርጐ ለውርደት ማጎብደዱ አልነበረም ። የሚርሲዲስ ተጽእኖና ሕይወቱን በልጅዋ ሕይወት እንደሚለውጥላት ሲነግራት ዝም ብላ የሄደችበት ምክንያት ገብቶት ራሱን ነቀነቀ ።

" እንግዲህ " አለ አልበርት " አሁን የጠየቅሁዎ ይቅርታ በቂ ሆኖ ካገኙት እጅዎን ለእርቅ ይዘርጉልኝ ። "

የእንደራሲው ዓይኖች በእንባ ረጠቡ ፤ ደረቱ በሲቃ ተጨነቀ ። እጁን ወደ አልበርት ሲዘረጋ አልበርት በቃላት አክብሮት ደረቱ ሥር ሸጉጣቸው ። " ወንድሞቼ " አለ አልበርት ። " የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሲ ይቅርታዬን ተቀብለውታል ። ህሊናዬ ያዘዘኝን በማድረጌ ዓለም ከሃዲ እንደማይለኝ ተስፋ አለኝ ። ግን " የሚናገረው ለጓደኞቹ ሳይሆን ለጠላቶቹ ይመስል ከአንገቱ በኩራት ቀና አለ ። " ግን አሁን ያደረግሁትን ተግባር እንዳደርግ ስለገፋፋኝ ምክንያት አንድ ሰው የተሳሳተ ግምት ቢሰጥ ሃሳቡን ለማስተካከል ዝግጁ ነኝ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

## 48

አልበርት ወደ ቤቱ እንደተመለሰ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር የእናቱን ፎቶ ከተሰቀለበት አውርዶ መጠቅለል ነበር ። ከዚያም ምርጥ ምርጦቹን የቱርክ የጦር መሳሪያዎች ፣ የእንግሊዝ ጠመንጃ ዎችና የጃፓን ሰኢፎች ፣ ቅርሳ ቅርሶችና የነሐስ ቅርጾች ካሰባሰበ በኋላ በኪሱ ያለውን ገንዘብ በሙሉ በቦርሳ ውስጥ ፣ በመደርደሪያ ውና በሳጥን ውስጥ ያለውን ጌጣጌጥ ጭምር ክፍቱን በተወው የቁም ሳጥን መሳቢያ ላይ ወርውሮ ሁሉንም ነገር አንድ ባንድ ቆጠረና የንብረቱን ዝርዝር ጽፎ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ ።

ይህንን ሥራ በማገባደድ ላይ እንዳለ የፈረስ ኮቴ ድምጽ ተሰ ማው ። ወደ መስኮቱ ሄዶ ወደውጭ ሲመለከት አባቱ ሠረገላው ላይ ሆኖ ከግቢ ሲወጣ ተመለከተ ።

ከዚህ በኋላ አልበርት ወደ እናቱ ክፍል ሄደ ። ሆኖም በእናቱ ክፍል በር ላይ ሲደርስ ባየውና በጠረጠረው ነገር ክው ብሎ ቆመ ። የእናትና የልጅ ሕሊና ባንድ መንፈስ ይመሩ ይመስል ሜርሴዲስም በክፍሏ ውስጥ ልክ አልበርት ሲያደርግ የነበረውን ታደርግ ኖሯል። የምትዘጋጅበትን ምክንያት በማረጋገጡ “ እናቴ ! ” ሲል እየጮኸ ዘሎ አንገቷ ላይ ተጠመጠመባት ። “ ምንድን ነው የምታደርጊው ? ”

“ አንተስ ምን ነበር የምታደርገው ? ”

“ እናቴ ? ” አለ አልበርት ድምጹ ከአንደበቱ አልወጣልህ ብሎት እየተናነቀው ። “ ነገሩ ለኔና ላንቺ አንድ አይደለም ። ”

“ በቃ መውጣቴ ነው ” አለች ሜርሴዲስ “ ልጄም እንደሚ ከተለኝ እተማመንበታለሁ ። ተሳሳትሁ ? ”

“ እናቴ ” አለ አልበርት ያለልቡ ኮስተር ሊል እየሞከረ “ እኔ ልኖረው የወሰንኩትን ሕይወት እንድትመሪ አልፈቅድልሽም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ገንዘብ የምትቀበል ከሆነ ለባቱ በአባትህ በረካብ የተገደለበት ሰው ለእናትህ የለገሳትን አዲስ ሕይወት እንዳትመሪ ብትከለከላት ትልቅ ስህተት እንደሠራህ ይቆጠራል ።

ሜርሲደስ ይህንን ደብዳቤ አንብባ እንደጨረሰች አልበርት ሳይንቀሳቀስ ቆሞ ውሳኔዋን ይጠባበቅ ጀመር ። ዓይኖቿ እንባ እንዳቀረሩ ደብዳቤውን ሳም ካደረገች በኋላ “ ተቀብዬዋለሁ ” አለች ። “ ለገዳም የሚሰጠውን የመግቢያ ክፍያ የመክፈል መብት አለው ። ” ደብዳቤውን በልቧ ሸጉጣ የልጅዋን ክንድ ተደግፋ ወደ ደረጃው ታመራ ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## 49

እንድራሴው ከፍልሚያው ቦታ የተመለሰው ከአማኑኤልና ከማክሲሚለን ጋር ነበር ። ግማሽ መንገድ ከተጓዙ በኋላ አማኑኤል ወደ ቤቱ ለመግባት ከሠረገላው ወረደ ።

" ምሳ ከኔ ጋር ነህ ፡ አይደለም ? " አለ እንድራሴው ማክሲሚለንን ።

" የለም ፡ አራት ሰዓት ላይ እለይዎታለሁ ። "

" የምሳ ቀጠሮ አለብህ ? "

ማክሲሚለን ራሱን በመነቅነቅ ቀጠሮው የምሳ አለመሆኑን ገለጸ ።

" ያም ሆነ ይህ አንድ ቦታ ምሳ ትበላለህ ፡ አይደለም ? "

" ምናልባት ካልራበኝስ ?

" እሃ ፡ " አለ እንድራሴው " የምግብ ፍላጐትን የሚዘጉ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው ፡ ትካዜና ፍቅር ። አንተ ደግሞ ትካዜ የተጫነህ አይደለህም። ይልቅስ ጧት የነገርከኝ ነገር ትዝ አለኝ ። ፍቅር . . . ?"

" አዎ ! እሱን መካድ አልችልም ። " አለ ማክሲሚለን ፊቱ ወገግ ብሎ ።

" ታዲያ ዝርዝሩን መቼ አጫወትኸኝ ? " አለ እንድራሴው ሚስጥሩን ለማወቅ መጓጓቱን በሚያሳይ ስሜት ።

" ጧት እንደነገርኩዎ አሁን ልቤ ከርስዎ ጋር ባለመሆኑ እርሱን ፍለጋ መሄድ አለብኝ ። "

" በል ሂድ " አለ እንድራሴው በቀስታ ። " ግን በዚህ አለም ላይ ጠንከር ያለ ኃይል ስላለኝ ፡ ያንን ኃይልም የምመካባቸውን ሰዎች ብረዳበት ደስ ስለሚለኝና አንተም ከምመካባቸው ሰዎች መካከል



t.me/OLDBOOKSPDF

" እንዲያም ሆኖ አሁንም የአባቴ ውርደትና በቤቴ የደረሰው አሳዛኝ ውድቀት መንስኤ አድርጐ ነው የሚቆጥርዎ ። "

" ትክክል ነው " አለ እንደራሴው በተለመደው መንፈስ የሚያውክ ርጋታ ። " የመጀመሪያው ባይሆንም በሁለተኛ ደረጃ የግጭቱ መንስኤ ይኸው ጉዳይ ነበር ። "

" እንግዲያውስ እርግጠኛ ነኝ ወይ ይቅርታ ጠይቀውታል ፤ አለዚያም አንድ ማብራሪያ አቅርበውለታል ። "

" ይግረምዎትና የተገላቢጦሽ ነበር ፡ ይቅርታ ጠያቂውም ሆነ ማብራሪያ አቅራቢው እሱ ነበር ። "

" ግን ይህን ሥነምግባር ከምን ያመነጨው ይመስልዎታል ? "

" ምናልባት የእውነተኛውን ኃጢአተኛ ማንነት ተረድቶ ይሆናላ ። "

" ማነው እውነተኛው ኃጢአተኛ ? "

" አባቴ ። "

" ግን ምንም ቢሆን " አለ ሞርስፍ በጥፊ ያጮሉትን ያህል ዞሮበት ፤ " ጥፋተኛም ሰው ጥፋቱ ፊቱ ላይ ሲወረወርበት እጁን አጣጥፎ አይመለከትም ። "

" እዎ አውቃለሁ ፤ የምጠብቀውም እሱን ነበር ። "

" ልጅ አልበርት እንደሚፈራ ነበር የሚጠብቁት ? " አለ ጄኔራሉ በቁጭት ።

" መሴ አልበርት ፈሪ ሰው አይደለም ። " አለ እንደራሴው ።

" ባገሬ ፤ ጦር የጨበጠ እጅ እያለው ከፊት ለፊቱ ቆሞ ምራቁን ጢቅ የሚልበትን ጠላቱን ደረቱ ላይ የማይሸቀሽቅ ልጅ ልጅ ሳይሆን የእንግዴ ልጅ ነው ! እሱም እዚህ ቢኖር ይህንኑ ነበር የምንገረው ። "

" ታዲያ ምን ያደርጋል ። " አለ እንደራሴው እንደወትሮው ቀዘቀዝ ብሎ ፤ " እንኳን ደረት በጦር ሊሸቀሽቅ ጀርባ በጡጢ አል ደለቀም ። . . . መሴ ሞርስፍ ። ግን ቤቱ የመጡት የቤተሰብዎን ስን



t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ማንንም ለመጠየቅ ሳይደፍር ወደ ውስጥ ገብቶ ወደራሱ ክፍል ይሮጥ ጀመር ።

ሁለት ሰዎች ደረጃውን ይወርዳሉ ። ፈጠን ብሎ ራሱን በመጋረጃው ከደበቀ በኋላ ማርሲደስ የአልበርትን ክንድ ተደግፋ ከቤት ሲወጡ ተመለከተ ። " አይዞሽ እናቴ " ሲል ሰማው አልበርት " ካሁን በኋላ ይህ ቤት የኛ አይደለም ። "

የቃላቱና የእርምጃቸው ድምጽ ከርቀት ጋር እየቀነሰ ሄደ ። ፈርናንድ መጋረጃውን እቅፍ አድርጎ ይዞ በራሱ ፈቃድ ከሚወርደው እንባው ጋር ቢታገልም ሚስቱና አንድ ልጁ በአንድጊዜ የከዱትን ሰው ፈንቅሎ የሚወጣውን ሲቃ መቆጣጠር ባለመቻሉ እንደሕጻን ልጅ ስቅስቅ ብሎ ለቅሶውን ለቀቀው ።

ወዲያውኑ የሠረገላው በር ሲዘጋና ጉዞ ሲጀምር ተሰማው ። የግዙፏ ሠረገላ እንቅስቃሴ የመስኮቱን መስታወት አንቀጠቀጠው ። ወደ መኝታ ቤት ሮጦ ገባና በምድር ላይ ከሁሉ አብልጦ የሚወዳቸውን ሁለት ነገሮች ለመጨረሻ ጊዜ በርቀት እያዩ ለመሰናበት እንገቱን በመስኮት ቢያስወጣም ሠረገላው እንጂ በውስጡ ያሉት ሰዎች ግቢያቸውን ለመሰናበት በመስኮቱ ብቅ ብለው አልታዩም ።

ልክ ሠረገላው የበሩን ደፌባል ማለፍ እንደጀመረ ከቤት ውስጥ የተኩስ ድምጽ ተሰምቶ በፍንዳታው ኃይል በተሰነጠቀ አንድ የመኝታ ቤት መስኮት በኩል የባሩድ ጭስ ሲወጣ ታዩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 50

ከሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ እንደተለያየ ማክሲሚሊን በቀጥታ ያመራው ወደ ቪልፎርት መኖሪያ ነበር ። ኖርቲርና ቫለንቲን በሳምንት ሁለት ጊዜ እየመጣ እንዲያነጋግራቸው ስለፈቀዱለት ማክሲሚሊን ይህንን መብት መጠቀም ጀምሯል ።

ቫለንቲን በጭንቀት እየተርበተበተች ስትጠባበቀው ስለነበር እጁን ይዛ ወደ አያቷ ክፍል ወሰደችው ። አልበርት በቲያትር ቤት የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴን ለፍልሚያ እንደገፋፋው ስለሰማች ማክሲሚሊን ደጀን እንደሚሆን በመገመቷና በተለይም ለእንደራሴው ካለው ፍቅር የተነሳ ጥቃታቸውን ዝም ብሎ እንደማይመለከት ተጠራጥራ ስትጨነቅ ነበር የጠበቀችው ። በዚህም የተነሳ ሁኔታው በምን እኳኋን እንደተከናወነ በታላቅ ጉጉት ጠየቀችው ። ማክሲሚሊን ፍልሚያው ባልተጠበቀ መንገድ ወደ እርቅ ተለውጦ ተፋላሚ ወገኖች በሙሉ በሰላም ወደየቤታቸው መመለሳቸውን ሲነግራት በፍቅረኛው ዓይኖች ላይ ይታይ የነበረው ወሰን የሌለው ደስታ እጅግ አስገረመው ።

“ በል አሁን ደግሞ ስለግል ጉዳዮቻችን እንጫወት ” አለችው፣ ከአያቷ ጐን እንዲቀመጥ በመጠቆም ራሷ በድንክ በርጩማ ላይ አረፍ ብላ ። “ እንደምታውቀው አያቴ ባንድ ወቅት ይህንን ቤት ለቆ ለመውጣትና አፓርታማ ተከራይቶ ለመኖር ሃሳብ ነበረው ። አሁንም በሃሳቡ እንደጸና ነው ። ”

“ በጣም ግሩም ! ” አለ ማክሲሚሊን ።

“ ግን ይህንን ቤት ለመልቀቅ ምን እንዳነሳሳው የሰጠውን ምክንያት ታውቃለህ ? ”

ኖርተር የልጅ ልጃቸው ዝም እንድትል ምልክት ሊሰጡ ቢፈልጉም ቫለንቲን ልብ አላለቻቸውም ። ዓይኖቿና ቀልቧ በሙሉ ወደ ማክሲሚሊን ተጉዘዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" የመጣሁት እየተጣደፍኩ ነው ፤ የማነጋግርዎ ጉዳይ አለኝ ።"

" ቤተሰብ ደህናም አይደል ?" ሲል ጠየቀ እንደራሴው ከልቡ መሆኑን በማያጠራጥር የተቅርቋሪነት ገጽታ ግንባሩን ከስክስ አድርጎ ።

" ደህና ነው ፤ አመሰግናለሁ ።" አለ ወጣቱ ንግግሩን የሚጀምርበት መነሻ የጠፋው ይመስል እየተቅለሰለሰ ። " ቤተሰቡስ በሙሉ በጣም ደህና ነው ።"

" ትልቅ እፎይታ ። ታዲያምንድ ነው ልትነግረኝ የፈለግኸው ? የምረዳህ ነገር አለ ?"

" አዎ ጌታዬ ፤ እንደ እብድ እየዛከርኩ የመጣሁት የርስዎን እርዳታ ፈልጌ ነው ፤ጧት የነገሩኝን አስታውሸ።"

" ያም ሆነ ይህ ንገረኝ ።"

" እንዲህ ያለውን ሚስጥር ለሰው ጆሮ አውጥቶ መናገር ጥሩ ይሁን መጥፎ አጣርቼ አላውቅም ክቡር እኔደራሴ ፤ ግን ምንም ነገር ልደብቅዎ አልፈልግም ። አልችልምም ።"

" ልክ ነህ ማክሲሚለን ፣ " አለ እንደራሴው " በሃሳብህ የሚጉላላውን ንገረኝ ። "

" ክቡር እንደራሴ ፣ ቤርቱሲዮ ስለአንድ ስለሚያውቁት ሰው ሁኔታ ጠይቆልኝ እንዲመጣ ብልከው ይፈቅዱልኛል ? "

" እንዴታ ፣ ደውዬ ልጥራው ? "

" አይ ራሴ ባናግረው ይሻላል ። "

ማክሲሚለን ከክፍሉ ወጥቶ ቤርቱሲዮን ከጠራ በኋላ በሹክሹክታ ጥቂት ቃላት ሲነግረው ቤርቱሲዮ ከግቢው ወጥቶ ይገሰግስ ጀመር ።

" ላከኸው ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው ማክሲሚለን ተመልሶ እንደገባ ።

" አዎ ፣ አሁን የሚያስጨንቀኝ ነገር አይኖርም ። "

" በል እንግዲህ የሚረብሽህን ነገር ንገረኝ ። " አለ እንደራሴው ፈገግ ብሎ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቪልፎርትን ፣ አፈቅራታለሁ ። እባክዎ እንዴት እንደማድናት ይንገሩኝ ? ምን እንደማደርግ ቅጡ ጠፍቶብኛል ። ”

እንደራሴው የቆሰለ አንበሳ የሚያሰማውን በመሰለ ድምጽ አዝ ገመገመ ። “ ቫለንቲንን ታፈቅራታለህ ? ” ሲል ጮኸ “ ያችን ያሪምስ ሽንት ? ”

ማክሲሚሊን በሰው ፊት ላይ እንዲያ ያለ ገጽታ አይቶ አያውቅም ። በፍርሃት ሽምቅቅ ብሎ ወደኋላው ሊያፈገፍግ ሞከረ ። እንደራሴው እንዳች ውስጣዊ ብልጭታ ቦግ ያለበት ይመስል ዓይኑን ጭፍን አድርጐ ከደረቱ ውስጥ የታመቀውን ንጐድጓድ ለማፈን ይታገል ጀመር ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ እንደገና ሰከን ባለ ድምጽ እንዲህ አለ “አቅሙ እያላቸው ግፍ ሲሰራ እያዩ ዝም የሚሉ ቸልተኞች ከግፈኞቹ ከራሳቸው ተነጥለው አይታዩም ። ጠንካራ ሁን ፣ ተስፋም አትቁረጥ ። እስከመጨረሻው የቅርብ ክትትል እንደማደርግልህ እምነትህ ይጽና ። ”

ማክሲሚሊን የእንደራሴው ንግግር ግራ ስሲጋባው ራሱን በአሉታ ነቀነቀ ።

“ ተስፋ አትቁረጥ ነው የምልህ ” አለ እንደራሴው ፤ “ ልብ ብልህ አዳምጠኝ ። አሁን ቫለንቲን ሞታ ቢሆን እንኳ የመትረፍ ተስፋ አለ ። አሁን ወደቤትህ ሂድ ፣ እኔ ካላኩብህ ብቅ እንዳትል ። ”

“ የአነጋገርዎ ቃና አስፈራኝ ጌታዬ ” አለ ማክሲሚሊን ። “ በሞት ላይም ኃይል አለዎ እንዴ ? ከሌላው ሰው በምን ይለያሉ ? ”

እንደራሴው ወጣቱን ከላይ እስከታች ከቃኘው በኋላ “ ብዙ ማድረግ እችላለሁ ወዳጄ ፣ አሁን ወደቤትህ ሂድ ። ብቻዬን መሆን እፈልጋለሁ ። ” አለው ።

ማክሲሚሊን እንደራሴው ዙሪያውን ባሉ ሰዎች ላይ ሁሉ ሲፈልግ በሚሰነዝረው የገጽታ ጫና የሕሊናው ትክሻ ስለተሰበረ ቃላት እንኳ ሊናገር አልከጀለም ። ከእንደራሴው ጋር እጅ ለእጅ ተጨባብጦ በዝግታ ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በሩ ላይ እንደደረሰ ቤርቱሲዮ ከውጭ እየተጣደፈ ሲመጣ አየው ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቪልፎርት ዶክተር አቭሪኝን ይዞ ወደ ቤቱ ተመልሶ ነበር ። ቫለንቲን አሁንም ራሷን እንደሳተች ሲሆን ዶክተሩ በከባድ ጥንቃቄ ምርመራ ሲያደርግላት ቪልፎርትና ኖርቴር ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ ይከታተላሉ ። “ ነፍሷ አልወጣችም ” አለ ሐኪሙ በመጨረሻው ።

“ አልወጣችም ? ” አለ ቪልፎርት ከው ብሎ “ ወይ ጉዴ ፤ ምን መዓት ነው የምታወራው ዶክተር ? ጥያቄው የመውጣትና ያለ መውጣት ሆኗል እንዴ ? ”

“ አዎ ፤ አሁንም እደግመዋለሁ ፤ ነፍሷ አልወጣችም ። ይህም ማመን እስኪያቅተኝ ድረስ እጅግ ያስደንቀኛል ። ”

“ ግን ታድናታለህ ? ”

“ አዎ ፤ እስካልሞተች ድረስ ፤ ” ልክ ይህንን ሲናገር ዶክተሩ የኖርቴር ዓይኖች በደስታ እንባ ተሞልተው እንዳሉ ይንጸባረቅባቸው የነበረውን ሁኔታ አይቶ ልቡ ተነካ ። “መሴ ቪልፎርት” አለ “እባክዎ የቫለንቲንን ሞግዚት ያስጠሩልኝ ”፤

ቪልፎርት ሞግዚቷን ራሱ ሊያመጣ እየተጣደፈ እንደወጣ ዶክተሩ ወደ ኖርቴር ጠጋ አለና “ ሊነግሩኝ የሚፈልጉት ነገር አለ ? ” አለ ።

ኖርቴር በእዎንታ አይናቸውን ከደን አደረጉ ።

“ ለእኔ ብቻ የሚነግሩኝሚስጥር ነው ? ”

“ አዎ ” አሉ የኖርቴር አይኖች ።

“ በጣም ጥሩ ፤ እዚሁ አብሬዎ እቆያለሁ ። ”

በዚህ ጊዜ ቪልፎርት ሞግዚቷን አስከትሎ ገባ ። እመቤት ቪልፎርት ከኋላቸው ነበረች ። “ ደግሞ አሁን ምን ሆነች ? ” አለች እመቤት ቪልፎርት “ምነው እንዲህ ጣጣዋ በዛ ? ጤንነት አይሰማኝም ስትል ነበር ፤ እስከዚህ ጠንቶባት ኖሯል ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" አልጋዋ ላይ ስናደርጋት ይሻላታል " ካለ በኋላ ቪልፎርት ወደ ሞግዚቷ መለስ ብሎ " ነይ እንቺ ፣ እንሽና እንውሰዳት " አለ ።

ዶክተር አቭሪኝ ከኖርቴር ጋር ብቻውን ለመቆየት አመች ሁኔታ ስለሚፈጥርለት በሽተኛዋን ይዘው እንዲወጡና እሱ ካላዘዘ በስተቀር ምንም ነገር እንዳይሰጧት ነገራቸው።ተሸከመዋት በመሄድ ላይ እንዳሉ ዶክተሩ ወደ መድኃኒት ቤት ራሱ ሄዶ ያዘዛላትን መድኃኒት ማዘጋጀታቸውን እንዲከታተል ለቪልፎርት ነገረው ።

ከዚያም አቭሪኝ በሩን በጥንቃቄ ዘጋና ማንም እንደማያዳምጣቸው ካረጋገጠ በኋላ ወደ ኖርቴር ቀረብ ብሎ " ስለልጅቷ ሕመም የሚያውቁት ነገር አለ ? " ሲል ጠየቃቸው ።

" አዎ ! "

አቭሪኝ ለአፍታ ሲያሰላስል ቆየና እንዲህ ሲል ጠየቀ ። "ለምናገረው ነገር ይቅርታ ያድርጉልኝ። በዚህ አስቃቂ ሁኔታ ቅንጣት ቸል የምንለው ነገር ስለሌለ ነው ። ባሮይስ ሲሞት አይተዋል ፣ አሟሟቱ የተለመደ ዓይነት የእግዚር ሞት የሚሉት ይመስልዎታል ? "

በኖርቴር ከንፈሮች ላይ ፈገግታ የመሰለ ነገር ታየ ።

" ታዲያ ባሮይስ በመርዝ መሞቱን ቀደም ብለው ያውቁ ነበር ? "

" አዎ ። "

" መርዙ እርሱን ለመግደል ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ይመስልዎታል ? "

" አይደለም ። "

" ቫለንቲንን የመረዛት የባሮይስ ገዳይ ይመስልዎታል ? "

" አዎ ። "

" ታዲያ እርሷም ትሞታለች ? "

" የለም " አሉ የአዛውንቱ አይኖች በድል አድራጊ ሰው ገጽታ ።

" መርዙ በቫለንቲን ላይ ያለው ጉልበት የመግደል ያህል አይደለም ? " አለ አቭሪኝ ።

" አዎ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" ለምን ይመስልዎታል የማትሞተው ? "

የኖርቴር አይኖች ወደ ግራ ጐን ገልበጥ ብለው አንድ ነገር ላይ ተተከሉ ። አብሪኝ የአይኖቹን አቅጣጫ ተከትሎ ሲመለከት አዛውንቱ የሚመለከቱት ሁልጊዜ መድኃኒት ይዞ የሚቀርብላቸውን ብልቃጥ መሆኑን ተረዳ ።

" አሃ ! " አለ አብሪኝ አንድ ሃሳብ ድንገት ድቅን ብሎበት ፤ " ቀደም ብለው ልጅቷን ከመርዙ ጋር ለማለማመድ ሞክረው ኖሯል ? "

" አዎ ! "

" በተከታታይ መጠኑን ከፍ እያደረጉ ሲሰጧት ለንብተው ኖሯል ? "

" አዎ ፡ አዎ ! " አሉ አዛውንቱ በአይኖቻቸው ፣ ሃሳባቸውን ስለተረዳላቸው በደስታ ተውጠው ።

" ልክንዎ ተሳክቶለዎታል ! " አለ አብሪኝ " ያ ቅድመ ዝግጅት ባይደረግላት ኖሮ ቫለንቲን እስካሁን ባልቆየች ነበር ። መርዙ በኃይል የጐዳት ቢሆንም ታንሠራራለች ። "

በዚህ ጊዜ በሩ ተከፍቶ ቪልፎርት ገባ ። " ይኸውና ያዘዝከው መድኃኒት ዶክተር "አለ ቪልፎርት ።

" እርስዎ እያዩ ነው የተዘጋጀው ? "

" አዎ !"

" እዚህ እስኪመጡ ድረስ ከእጅዎ አልተለየም ?

" በጭራሽ ! "

አብሪኝ ብልቃጡን ተቀብሎ ጥቂት ጠብታዎች በእጁ መዳፍ ላይ ካፈሰሰ በኋላ በምላሱ ቀምሶ አጣጣመውና " ጥሩ" አለ " አሁን እስኪ ወደ ቫለንቲን እንሂድ ። ትዕዛዜን ለሁሉም እሰጣለሁ ። ሙሴ ቪልፎርት ትዕዛዜ አለመጣሱን ራስዎ በቅርብ እንዲከታተሉ እፈልጋለሁ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

* * *

ዶክተር አቨሪኝና ቪልፎርት ወደ ቫለንቲን ክፍል በመግባት ላይ እንዳሉ አንድ በገጽታቸው ኮስታራና አስተዋይ፣በአነጋገራቸው ረጋ ያሉና ጭምት ኢጣሊያዊ ቄስ ከቪልፎርት ግቢ ቀጥሎ ያለውን ቤት ይከራዩ ነበር ። በቤቱ ውስጥ ቀደም ሲል ይኖሩ የነበሩት ሶስት ተከራዮች ለምን ከሁለት ሰዓት በፊት ቤቱን ለቀው እንደሄዱ በውል የሚያውቅ ባይኖርም ሰዎቹ የለቀቁት የቤቱ መሰረት የተናጋና ሊፈርስ የደረሰ ስለነበረ ነው የሚል ወሬ በጐረቤቶች ዘንድ ይናፈሳል ። ይሁንና ወሬው ቄሱ ይህንን ቤት ተከራይተው የቤት እቃቸውን ከማስገባት አላገዳቸውም ። የበፊቶቹ ተከራዮች እንደለቀቁ በአምስት ሰዓት አካባቢ ቄሱ የስድስት ወር ኪራይ በቅድሚያ ከፍለው ገቡበት ። እኚህ ኢጣሊያዊ ቄስ ፣ ቄስ ቡሶኒ ናቸው ።

በዚያው ቀን አናጢዎችና ግንበኞች መሰረቱን በመሥራት ሲዋከቡ እያየ አላፊ አግዳሚው ሁሉ በመገረም አፉን ይይዝ ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 51

ይህ ከሆነ ከሶስት ቀናት በኋላ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ የዳንግላር መኖሪያ ቤት ዋናው ሳሎን በታላላቅ ሰዎች ተሞልቶ ነበር ። ሰዎቹ በሳሎኑ የተገኙት ለዳንግላር ቤተሰብ ባላቸው ልባዊ ፍቅር የተነሳ ሳይሆን በዚያ ወቅት ሊደረግ የታቀደውን ፕሮግራም መመልከቱን እንደ አዲስ ነገር በመቁጠራቸው ነበር ። እናም ዋናው ሳሎን ከሚችለው በላይ ሆነና የሚቀጥለው ጠበብ ያለ ሳሎንም በሰዎች ተጨነቀ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በወይዘሪት ኢዩጊን ዳንግላርና በአንድሪያ ባርቶሎሚዮ መካከል የጋብቻ ውል ስለሚፈጸም እንደሚስተናገዱበት ሰዎች ሁሉ ሳሎኑም ራሱ እጅግ ተውቧል ። ውድ የሆኑት የከት እቃዎች ወጭተው ሳሎኑን የቤት እቃዎች ትርኢት የሚታይበት አዳራሽ አስመስለውታል ።

ወይዘሪት ኢዩጊን ዳንግላር ውብና ነጭ የሃር ቀሚስ ለብሳለች ። ሆኖም አለባበሷ ቀለል ያለ ከመሆኑም በላይ በከፊል ወደ ትከሻዋ ሊወድቅ ከቃጣው ነጭ ባርኔጣዋ በስተቀር አንድም ጌጥ አላደረገችም ። አልተኳኳለችም ።

እመቤት ዳንግላር ከወንድ ጓደኞቿ ጋር የሞቀ ወሬ ከፍታለች ። አባዎራውም እንደዚሁ ዙሪያውን ከተቀመጡት ቱጃሮች ጋር የሰሞኑን ንግድ ወሬ አንስቶ ይጫወታል ። በንግድ ዓለም ፣ በጦር ግንባርና በስነጽሑፍ ስማቸውን ገናና ያደረጉ ሰዎች ወደ ሳሎኑ መግባታቸውን እንደ ቀጠሉ ናቸው ። ግዙፉ የግድግዳ ሰዓት ልክ ሶስት ሰዓት ላይ ሲደውል የሳሎኑ አስተናጋጅ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ መምጣቱን አስታወቀ ። ወዲያውኑ በሳሎኑ የተሰባሰበው ሰው በሙሉ ወደ በሩ አተኮረ ። እንደራሴው ገባ ። ነጩ ሸሚዙ የኃያልነት ምልክት የሚያንጸባርቀውን ደረቱን የበለጠ ያሰፋው ይመስላል ። ያደረጋት ጌጥ ግን በአንገቱ ላይ ያሰራት የወርቅ ሃብል ብቻ ነበረች ።

በአፍታ ጨረፍታ እንደራሴው እመቤት ዳንግላርን ከሳሎኑ በአንድ ጥግ ፣ ባለቤቷን ደግሞ በሌላው በኩል አያቸው ። ወይዘሪት



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ነገሩ ቀላል ፤ እመቤት ፣ ” አለ እንደራሴው “ ሽሚዙና ደብ ዳቤው ለወንጀሉ መጣራት ማስረጃዎች ከለሚሆኑ ሁለቱንም ወደ አቃቤ ሕግ ላክሁ ። በወንጀል ጉዳዮች ህግ የያዘው ነገር ለሁሉም ይበጃል ። ምናልባት በርስዎ ላይ የተቀናጀ ሴራ ሳይኖር አይቀርም ። ”

እንድሪያ እንደራሴውን በልቡ እየተራገመ በምሬት ገልመጥ አድርጎ ወደሚቀጥለው ክፍል መሰለ ብሎ ሄደ ።

“ አይደረግም አይባልም ፣ ” አለ ዳንግላር ፤ “ ሚች ከወሀኒ ያመለጠ ወንጀለኛ ነበር ፣ አይደለም ? ”

“ ትክክል ነው ። ካደሮስ የተባለ ያመለጠ ወንጀለኛ ። ”

ዳንግላር ይህን ስም ሲሰማ ፊቱ ፍም መሰለ ። በዚሁ ጊዜ እንድሪያ ከሚቀጥለው ክፍል ወደ ውጭ በመውጣት በረንዳው ላይ ደርሷል ።

“ ግን እባካችሁ ውሉን ፈርማችሁ ጨርሱ ” አለ እንደራሴው “ የኔ ቤት ታሪክ ሁሉንም ሰው አዘናጋውኮ ፣ ይቅርታችሁን እለም ናለሁ ። ”

በዚህ ጊዜ ፊርማዋን አሳርፋ የነበረችው እመቤት ዳንግላር ብዕሩን ለውል ሰሚ መልሳ ሰጠች ። “ አሁን ደግሞ መስፍን አንድሪያ ” አለ ውል ሰሚው ። “ የት ነህ ፣ መስፍን እንድሪያ ? ”

“ እስኪ ሂድና ከሚቀጥለው ክፍል ጥራው ። ተራው ደርሷል ። ” አለ ዳንግላር ለአንደኛው ባለሚሉ ።

በዚህ አፍታ አንድ እስፈሪ አውሬ ያስበረገጋቸው ይመስል በሚ ቀጥለው ክፍል የነበሩ ብዙ ሰዎች እየተንጋጉ ወደ ዋናው ሳሎን ግር ብለው ገቡ ። ለካስ በርግጥም የሚያስበረግግ ነገር ኖሩአል ። አንድ የፖሊስ መኰንን በሁለቱም ክፍሎች በሮች ሁለት ወታደሮች አቁሞ ሌላ ኮሚሳር ከፊቱ አስቀድሞ ወደ ዳንግላር ያመራል ።

እመቤት ዳንግላር በጀርባዋ ወደቀች ። አደጋው ለሱ መሆኑን የጠረጠረው ዳንግላር በፍርሃት እየተቀለሰለሰ እንግዶቹን ይመለከ ታል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" የትኛው ነህ አንድሪያ ባርቶሎሚዮ ? " ሲል ጠየቀ ኮሚሳሩ እንደገባ ። ሳሎኑ በአድናቆት ጉርምርምታ ተዋጠ ። ሁሉም ዙሪያውን ተገላመጠ ።

" ግን ማነው እሱ አንድሪያ ባርቶሎሚዮ ? " ሲል ጠየቀ ዳንግላር ፤ የሚናገረው ጠፍቶበት ።

" ከቱሎን ወህኒ ያመለጠ ወንጀለኛ ነዋ ፣ አሁን ደግሞ ካደሮስ የተባለ ሌላ ያመለጠ እስረኛ መግደሉ ተደርሶበታል ። "

የሞንቴ ክሪስቶ እንዴራሲ በፍጥነት ዙሪያውን አማተረ ። አንድሪያ አምልጧል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 52

የፖሊሶቹ ድንገተኛ ፍተሻ በባሮን ዳንግላር ስሬ ሳሎን መደና ገጥና ትርምስ እንደፈጠረ ወዲያውኑ ለስነስርዓቱ ተጠርተው የነበሩት እንግዶች በመሉ ከመካከላቸው አንደኛው ኮሌራ ወይም ሌላ ተላላፊ ተውሳክ የያዘው ይመስል ሹልክ እያሉ ወጡ ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥም ሳሎኑ እና ሆነ ። የቀሩ ቢኖሩ ለኮሚሳሩ ቃሉን የሚሰጠው አባዎሬ፣ በፍርሃት የምትንቀጠቀጠው ባለቤቱና ጊዜ ሳታጠፋ ከማትለያት ጓደኛዋ ከወይዘሪት አርሚሊ ጋር ወደ ግል መኝታ ክፍሏ የገባችው ሙሽራ ኢዩጊን ዳንግላር ብቻ ነበሩ ።

ኢዩጊን መኝታ ክፍሏ ውስጥ እንደገባች በሩን ከውስጥ ስትቆልፍ ጓደኛዋ ወንበሩ ላይ በቁሟ ዘፍ አለችበት ። "ጉድ እያልቅ" አለች የሙዚቃ መምህሯ አርሚሊ በረጅሙ ተንፍሳ "መስፍን እንድሪያ ባርቶሎሚዮ . . . . ያመለጠ እስረኛ . . . ነፍሰ ገዳይ ?! "

" ድሮም ሳውቀው ነው " አለች ኢዩጊን በንዴት እርር ብላ ከላይ ከላይ እየተነፈሰች ፤ " ከአልበርት አመለጥኩ ስል እንድሪያ ላይ ልውደቅ ፤ ? "

" ባክሽ ሁለቱን አታወዳድሪ ፣ ኢዩጊን ? "

" ኧረ ወደዛ ፣ ወንዶች ሲባሉ ሁሉም ያው ናቸው ! እኔማ አንዳንዴ ሳስበው በተፈጥሮዬ ለነሱ ያለኝ ጥላቻ ያስደስተኛል ። ዛሬስ ከጥላቻ አልፈው ቋቅ አሉኝ ። "

" አሁን ምን ወሰንሽ ? " ስትል አርሚሊ ጠየቀች ።

" እንዴ ፣ ያው እቅዳችንን መፈጸም ነዋ ፣ መውጣት ! "

" አሁንም እዚያው ነሽ ? ውሉ ፈርሶም . . . . ? "

" ለምን እዚህ እንዘላዘላለሁ ? ደሞ የዛሬ ሳምንት እንዳሁን ጉትተው ፈርሚ ይበሉኝ ? እንዲያውም ዛሬ በኔ የደረሰው ጥሩ ሰበብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆነኛል ። ነገሮች ከተገጣጠሙልኝ እድሉ ሊያመልጠኝ አልፈል ግም ። ”

“ አይ አንቺ . . . አይ ልቢቱ ! ” አለች አርሚሊ ኢዩጊንን ።

“ እስካሁን አታውቂኝም ? በይ አሁን ይልቅስ ወደ ነጥቡ ። ለጉዞው መሰናዶ አድርገሻል ? ”

“ አዎ ። ”

“ ፓስፖርታችንስ ? ”

“ ይኸው ። ”

ኢዩጊን በተለመደው ችኮላዋ ፡ ፓስፖርቱን ገልጣ ታነብ ጀመር ።

መሲ ሊዮን አርሚሊ
እድሜ ሃያ ፣ ሥራ ክየኒ ፤ የጸጉር ቀለም ጥቁር ፤ የዓይን ቀለም ጥቁር ፤
ከእህቱ ጋር የሚጓዝ ።

“ አንቺ ጉደኛ ! እንዴት አገኘሽው ? ”

“ የጥንቱ ክሪስቶ እንደራሴ ከሮምና ከኔፕልስ ቲያትር ቤቶች ስራ አስኪያጆች ጋር የምተዋወቅበት ደብዳቤ እንዲጽፉልኝ ልጠ ይቃቸው ሄጄ ሳለ መንገዱ ለሴት ልጅ አስቸጋሪ ነው የሚባለውን ወሬ አዋዩሁአቸው ። እሳቸውም ችግሬን ተረድተው የሀገር ፓስ ፖርት አገኙልኝ ። “ ከእህቱ ጋር የሚጓዝ ” የሚለውን ግን ራሴ ነኝ የጨመርኩበት ። ”

“ ጐሽ ፡ እንግዲያውስ ፡ ” አለች ኢዩጊን በደስታ እየተፍለቀለ ቀች ። “ አሁን የቀረን ሻንጣዎቻችንን ማዘጋጀት ነው ! ጉዟችን እን ዳሰብነው በሰርጌ ምሽት ሳይሆን ዛሬ ማታ ነው ። ”

“ ግን ጥቂት ብታስቢበት ፡ ኢዩጊን ? ”

“ መጣብሽ እንግዲህ ፡ ሺ ጊዜ አስቤበታለሁ ። እድሜ ላባቴ ካዝና ፤ ለአራት አመታት እንደ ንግስት አንቀባሮ የሚያኖረን ገንዘብ አጭቄአለሁ ። ካስፈለገም የዛሬ ስድስት ወር እጥፍ እናደርገዋለን ። አንቺ በመሳሪያ ፡ እኔ በድምጼ ። ”

“ በጣም ትገርሚያለሽ ፡ ኢዩጊን ፡ ”

ሁለቱ ልጃገረዶች ለጉዞአችን ያስፈልጉናል የሚሏቸውን እቃ ዎች በሙሉ በትልቅ ሻንጣ ይከቱ ጀመር ። ይህንን አድርገው



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደጨረሱ ኢዩጊን ከቦት ጫማ እስከ ኮት ድረስ የወንድ ልብስ ለበ ሰች ። ሱሪዋን ፣ ጫማዋንና ሸሚዟን ስትለብስ ለተመለከታት የወንድ ልብስ የመልበስ የረጅም ጊዜ ልምድ ያላት ትመስል ነበር ።

"ነገሩስ ይሄዳል ፣ " አለች አርሚሊ ጓደኛዋን በአድናቆት ስት መለከታት ቆይታ ።

" ግን በዚያ ረጅም ጸጉርሽ ላይ የወንድ ባርኔጣ . . . . ? "

"ቆይ ታያለሽ" ካለች በኋላ ኢዩጊን ወገቧ ድረስየወረደውን ጸጉ ሯን በግራ እጅዋ ግምድ አድርጋ ወደፊት ካመጣችው በኋላ በቀኝ እጅዋ መቀስ አነሳች ። ብዙም ሳይቆይ ያ የሚያሳዝን ጸጉር በብዙ ጥይት እንደተመታ ቲሰለኛ ዝንጥፍ ብሎ እግሯ ስር ተጋደመ ። ጓደ ኛዋ በሃዘን ራሷን ነቀነቀች ። ኢዩጊን ግን ቅንጣት ቅሬታ አልተሰ ማትም ። እንዲያውም በደማቆቹ ቅንድቦቿ ስር የሚብለጨለጩት አይኖቿ ከመቼውም የበለጠ ያበሩ ጀመር ።

" ግን አሁን የት ነው የምንሄደው ? " አርሚሊ ነበረች ።

" ወደ በልጅግ ፣ የሚቀርበን ጐረቤት አገር እሱ ነው ። ከዚያ በኋላ በብራስልስ አድርገን ስዊዘርላንድን እናቋርጥና ጣሊያን ጥልቅ ነዋ ! ምን ይመስልሻል ?"

" በጣም ጥሩ ! "

ሁለቱ ጓደኞች የክፍሉን ሸማዎች ካጠፉ በኋላ በጥንቃቄ በሩን ከፈቱ ። መጀመሪያ የወጣችው ኢዩጊን ነበረች ። የሻንጣውን ማን ጠልጠያ ካንድ ጫፍ ይዛለች ። ከሌላ ጫፍ ጓደኛዋ ይዛ ተከትላ ቻት ። በረንዳው ጭር ብሏል ። የግድግዳው ሰዓት መንፈቀ ሌሊት ላይ ደወለ ።

ጉዞውን ተያያዙት ። ከሩብ ሰዓት ጉዞ በኋላ ሲጠባበቃቸው የነ በረውን ሰረገላ አገኙት ።

ሌላ ሩብ ሰዓት አለፈ ፣ ሰረገላው ከፓሪስ ወጣ ።

መሴ ዳንግላር ልጁንና ከፊል ሃብቱን አጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## 43

የአንድሪያ ዕድል እንደ እንቢይ ካብ በቅጽበት ተናደ ። በሳሎኑ ያለው ሁኔታ አዝማሚያው አላምርህ እንዳለው ጊዜ ሳያጠፋ ወደ በሩ ቹልክ ካለ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ሌላ ክፍል ዘው አለ ። በዚህ ጊዜ ነበር ሁለት ወታደሮች የሳሎኖቹን በሮች ያጠሩአቸው ።

አንድሪያ እድሜው ገና ለጋ ቢሆንም ፈጠራው የሚደንቅ ፣ ቅል ጥፍናውና ፍጥነቱም የማይታመን ነበር ። እሳት የላሰው ወጣት በዚያች ቀውጢ ደቂቃ በመስኮት ዘሎ በረንዳው ላይ ዱብ ካለ በኋላ ለሙሽርነቱ በወርቃማው ስጋጃ ላይ ተቀምጦ ከነበረው የወ ርቅና የአልማዝ ገጸ በረከት ውስጥ ጥቂት ዘገነለት ። ከዚያም በተ ለመደው ፍጥነቱ ወታደሮቹ ሳሎን ውስጥ መኖር አለመኖሩን ከማ ረጋገጣቸው በፊት ከግቢ ወጥቶ ሰፊውን ጐዳና ተያያዘው ።

አንድ ጊዜ ከግቢ ከወጣ በኋላ ጊዜ ሊያባክን አልፈለገም ። ሊታሰርበት በነበረው ስፍራና በራሱ መካከል ያለውን ርቀት በተቻ ለው መጠን ማስረዘም ነበረበት ። እናም ለሩብ ሰዓት ያህል ልቡ እስኪጠፋ ሮጠ ።

ለአፍታ ትንፋሹን ለማረጋጋትና ዙሪያውን ለመቃኘት ቆም አለ ። ብቻውን ነበር ። ብዙም ሳይርቅ ወደሱ የሚመጣ ጋሪ አየ ። በጥቅሻ ጠራውና "ፈረስህ ደክሟል ?" ሲል ጋሪ ነጅውን የመስሪ ጥያቄ አቀረበለት ።

"ወይ ድካም !" አለ ባለጋሪው ። "ቀኑን ሙሉ ቦዝኖ ነው የዋ ለው ። ሰባት ፍራንክ ሰርቷል ፣ ከነዚያውም ስድስቱ ለባለቤቱ ይሰ ጣል !"

"ሃያ ፍራንክ ቢሰራ ምን ይመስልሃል ?"

"ደስታውን አልችለው ። ግን ምን ሰርቶ ነው ሃያ ፍራ ንክ . . . ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠር ጊዜ የፖሊስ መኮንኑ ከሆቴል ዴ ቪል መስኮቶች በአንደኛው አን ገቱን ብቅ አደረገ ። ከአንድሪያ ሆቴል ጣራ ላይ ማንም የለም ። ጥቂት ጊዜ ዝግ ብሎ ሲመለከት ከቆየ በኋላ በቅሬታ ራሱን እየነቀነቀ ተመ ልሶ ገባ ።

ጠንካራው የፖሊስ መኮንን የሚበገር አልሆነም ። ከሆቴል ዴ ቪል ሲወርድ መንገዱ ላይ ብዙ ህዝብ ተሰብስቦ ስለ ሁኔታው በጥ ያቄ ሲያዋክበውም መልስ ሳይሰጥ ወደ አንድሪያ ሆቴል ተመልሶ ገባ ።

" እህስ ? " አሉት ሁለቱ ወታደሮች ።

" በጢት ገስግሶ ሳይሄድ አልቀረም ። " ሲል መለሰ መኮንኑ ፤ " ያም ሆኑ ይህ አውራ መንገዶችንና ጫካውን በደንብ እናስስ ። ብዙም ሳይርቅ ሲልከሰከስ እንይዘዋለን ። "

ይህ ውሳኔ ለአንድሪያ ትልቅ እፎይታ ነበር ። ግን መኮንኑ አረ ፍተ ነገሩን እንኳ ሳይጨርስ ጆሮ የሚበሳ ጩኸትና ኃይለኛ የደወል ድምጽ በግቢው አስተጋባ ።

" ምንድን ነው እሱ ? " ሲል ጮኸ መኮንኑ ።

" የችኮላ እንግዳ ይሆናል ። " አለ የሆቴሉ ተቆጣጣሪ ፤ " ግን ደወሉ ከየትኛው ክፍል ነው ? "

" ከሶስት ቁጥር " አለ አንድ ሰራተኛ ።

" ሶስት ቁጥር የተከራየው ማነው ? " መኮንኑ ነበር ።

" ትናንት አመሻሽ ከእህቱ ጋር መጥቶ ሁለት አልጋ ያለው ክፍል የጠየቀ ልጅ እግር ሰው ነው ። "

ደወሉ በድጋሚ በኃይል ይጮህ ጀመር ። " ተከተለኝ ! " አለ መኮንኑ ኮሚሳሩን ። ከዚያም ወደ ወታደሮቹ ዞር አለና " እናንተ ደግሞ አድፍጣችሁ ተጠባበቁ ። ሊያመልጥ ከሞከረ በጥይት እግሩን ሰበሩት ! አደገኛ ወንጀለኛ መሆኑ በቴሌግራሙ ተገልጿል " ብሎ አስጠነቀቃቸው ።

መኮንኑና ኮሚሳሩ በደረጃዎቹ ወደላይ በሩጫ ወጡ ፤ ከውጭ ብዛት ያለው ሰው ይከተላቸዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙም ሳይቆዩ በሩ በኃይል ተበርግዶ ተከፈተ ። አንድሪያ አሁንም አንድ ሌላ አማራጭ ታዬው ። በበረንዳው ዙሪያ ወደከበበው መጋዘን ወደሚያስወጣው በር ሮጠ ። በዚያው ቅጽበትም እጁን በጀርባው በሸጕጠው ጩቤው ላይ አሳርፎ ኖሯል ። ይሁንና ከውጭ ሲጠባበቁ የነበሩት ወታደሮች መሳሪያቸውን ደግነው አስቆሙት ።

መኮንኑ ቆመጡን አውጥቶ ወደ አንድሪያ ተጠጋ ።

" ባክህ ዱላህን መልስህ ና ይልቅስ ። " አለ አንድሪያ በመጨረሻው ። " እጄን ስለሰጠሁ እንዳትመታኝ ። " እጆቹን ዘርግቶ ለወታደሮቹ አስረከበ ።

ወዲያው ግን ወደ ሁለቱ ሴቶች ዞር አለና እየሳቀ " ላባትሽ የማደርሰው መልእክት ይኖርሻል ወይዘሪት ኢዩጊን ? ወደ ፓሪስ መመለሴ ነው ። " አለ ። ኢዩጊን ሃፍረቱን አልቻለችውም ። ፊቷን በእጆቿ ሸፈነች ። " አይ . . . . ምን ያሳፍርሻል ? " አለ አንድሪያ ቀጠለና ።

" ተከትለሽኝ መምጣትሽን ሰው ስላወቀብሽ ደስ አላለሽም ? ድሮስ ከባልሽ ተለይተሽ ልትቀሪ ኖሯል ? "

አይን አውጣው ወንጀለኛ ይህን ተናግሮ ሴቶቹን የከበባቸው ህዝብ ማጠቋቆሚያ አድርጓቸው ሄደ ። ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ሴቶቹ ሰረገላቸው ላይ ወጥተው ጉዟቸውን ቀጠሉ ። በዚህ ጊዜ ግን ሁለቱም የሴት ልብስ ነበር የለበሱት ።

አንድሪያ ወደ ፓሪስ ተወስዶ በተለየ ጥቢቃ ወህኒ ወረደ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 54

ቫለንቲን አሁንም አልጋ ላይ እንደተዘረረች ናት ። ሕመሙ ካላደረባት ሰመመን ብንን ብላ አይኗን ገለጥ ስታደርግ ራቢ ከፍል ድረስ ሄደው በአፍቅሮት አስተያዩት አይናቸውን የጣሉባትን አያ ቷን ትመለከትና ልቧ በአዘኔታ ናድ ይላል ። አልፎ አልፎም ቪልፎ ርት ከትሎት በሚመለስበት ጊዜ አሥራ ሁለት ሰዓት ሆኖ ወደ ጥናት ክፍሉ ከመሄዱ በፊት ከእሷና ከእባቱ ጋር ሲጫወት ጥቂት ጊዜ ያሳ ልፋል ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ዶክተር አቭሪኚ የበሽተኛዋን የሌሊት መድኃኒት ይዞ ይመጣል ፡ ኖርቴርም ወደ ክፍላቸው ይመ ለሳሉ ። ከዚያ በኋላ በዶክተሩ የተመረጠች ነርስ አራትና አምስት ሰዓት ላይ እንቅልፍ እስኪጥላት ድረስ ቫለንቲንን ስትጠብቅ ታመ ሻለች ።

ሁልጊዜ ጧት ማክሲሚለን ሞረል ወደ ኖርቴር በመምጣት ስለ ቫለንቲን ይጠይቃል ። የሚያስገርመው ጭንቀቱ በየቀኑ እየቀነሰ መምጣቱ ነው ። በመጀመሪያ ደረጃ ቫለንቲን በመጀመሪያ የተሰማት የነርቭ መናጋት ሕመም ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሲሆን በሌላ በኩልም እንደራሲው ልጅቷ በሁለት ሰዓታት ውስጥ ካልሞተች እንደምት ተርፍ የነገረውን በማስታወስ ነበር ።

የቫለንቲን የነርብ መታወስ ብዙ ጊዜ በእንቅልፍና በመባንን መካ ከል በሰመመን እንድትገኝ ያደርጋት ነበር ። በተለይም ጭልጥ ካለ እንቅልፍ ከባነነች በኋላ የሚከተለው ሁኔታ የህልም ይሁን የእውን አይታወቃትም ። በጀርባዋ እንደተኛች አይኖቿን ገርበብ አድርጋ እንቅልፍ ሳይወስዳት ቅገርት የምታይ ይመስላታል ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች ነበር ግርማ ሞገስ በተጎናጸፈው የሌሊት ጸጥታና በርቀት የምትበራው ፋኖስ በምትፈነጥቀው ደካማ ብርሃን አይኗን ገለጥ ስታ ደርግ ወደ በሽተኞች ክፍል ይመጣሉ የሚባሉት ምስሎች የሚታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከማክሲሚለን ጋር እየጠበቁኝ ናቸው ።' የሚል አረፍተ ነገር በሀ ሲናሽ ያስተጋባ ።"

" እንዴት የሚያስጨንቅ መዓት ነው? "

" ታዲያ እንጀራ እናትሽን በሕግ ፊት ለማቅረብ ትመርጫለሽ?"

" ኧረረ . . . . . ያን ከማድረግስ ሞት ይሻለኛል ። "

" አትሞችም ቫለንቲን ! ግን የፈለገው ነገር ቢደርስብሽ ተስፋ ላለመቁረጥ ቃል ግቢልኝ ። በማክሲሚለን ፍቅር የምታምኚውን ያህል በእኔ ተንከባካቢነት ላይም ጽኑ እምነት ይኑርሽ ።"

ቫለንቲን እንደራሲውን በሀዘኔታ ተመለከተችው ። እንደራሲው ትንሿን የእንቁ እቃውን ከኪሱ አውጥቶ ከከፈታት በኋላ አተር የም ታክል ክኒን በቫለንቲን እጅ ላይ አስቀመጠ ።

ቫለንቲን በጥያቄ አስተያየት እንደራሲውን ተመለከተች ። እንደ ራሴው ክኒን የያዘውን የበሽተኛዋን እጅ ወደ አፏ እያስጠጋ " አዎ ! " አለ ። በሽተኛዋ ክኒኗን ወደ አፏ አስገብታ አኘከቻት ።

" በይ እንግዲህ ደህና ሁኚ ቫለንቲን " አለ እንደራሲው ። " አሁን ከሞት ተርፌሻልና እንቅልፍ ማግኘት ይኖርብኛል ።"

ቫለንቲን በዋጠችው ክኒን ኃይል ቀስ በቀስ ሰውነቷ ዝሎ አይ ኖቿ ሲከደኑ እንደራሲው ተመለከታት ። ቀጥሎም በብርጭቆው ተቀ ድቶ የነበረውን መርዝ ቫለንቲን የጠጣችው እንዲመስል ብዙውን ምድጃው ላይ ከደፋ በኋላ ወደ ጠረጴዛው መልሶ በቀትር ጸሐይ የምት ለበለብ ድመት መስሏ የተዘረጋችውን በሽተኛ ለመጨረሻ ጊዜ በጨ ረፍታ አዩት አድርጎ በቤተ መጻሕፍቱ በኩል ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 55

መደርደሪያው ላይ የተቀመጠው ፋኖስ መብራቱን ቀጥሏል ። ከረጅም ጊዜ በኋላ በኤድዋርድ ክፍል በኩል አንድ ሰው ብቅ አለ። እመቤት ቪልፎርት የመርዟን ውጤት ለማዬት መምጣቷ ነበር ።ግድ ግዳው ላይ ተለጥፋ ቆመች ። ነዳጁን በመጨረስ ላይ ያለው የፋ ኖስ መብራት ከሚያሰማው ድምጽ በስተቀር ሁሉም ነገር ፀጥ ረጭ ብሏል ። በቀስታ እየተራመደች ከቫለንቲን አልጋ ጐን ባለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠው ብርጭቆ ባዶ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ወደ በሽተኛዋ አልጋ ጠጋ አለች ። ብርጭቆው ከሞላ ጐደል ባዶ ነበር ። እመቤት ቪልፎርት ብርጭቆው ላይ የቀረውን ጥቂት መርዝ ወደ ምድ ጃው ከፈነጠቀች በኋላ እመዱን ወዲያ ወዲህ አመሰቃቅላ ብርጭ ቆውን በመሃረቧ ወልውላ አደረቀችና ጠረጴዛው ላይ መልሳ አስቀመ ጠችው ።

በዚያች ደቂቃ ወደዚያ ክፍል ለሚመለከት እመቤት ቪልፎርት ቫለንቲንን ለማዬትም ሆነ ወደ አልጋዋ ለመጠጋት ምን ያህል እንደ ፈራች በግልጽ ያስታውቅ ነበር ። ነፍሰ ገዳይዋ በራሷ ተግባር ተርበ ትብታለች ። በመጨረሻ የግዷን ደፈር ብላ ወደ አልጋው በማንንበስ ተመለከተች ። ቫለንቲን መተንፈሷን አቁማለች ። በእንቅልፍ ልቧም ቢሆን መንቀሳቀሳቸውን የማያቆሙት ከንፈሮቿ እንኳ ፀጥ ብለዋል ። እመቤት ቪልፎርት እጇቿን በቫለንቲን ደረት ላይ አስቀምጣ የልብ ትርታዋን ለማዳመጥ ሞከረች ። የበሽተኛ እንቅስቃሴ ግን ፈጽሞ በድን ሆኗል ። እሳት እንዳቃጠለው ሰው በድንጋጤ ሽምቅቅ ብላ እጅዋን መለሰች ። የቫለንቲን ክንድ ከአልጋው ጠርዝ አልፎ ተንጠ ልጥሏል ። ክርኗ መገተር የጀመረ ሲሆን ጥፍሮቿም ወደ ነጭነት እየ ተለወጡ ነው ።

እመቤት ቪልፎርት ምንም ጥርጣሬ አልነበራትም ። አሁን ሁሉም ነገር ተጠናቋል ። የመጨረሻው ተግባሯ በተሳካ ሁኔታ ተከ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠጡ ። " እዎ እነዚያን ቃላት ሰምቻቸዋለሁ ፤ " ሲል ቀጠለ ማክ ሲሚለን ። "እነዚያን ቃላት በህግ ፊት ደግሜ እናገራቸው ነበር ።እንዳ ልሰማሁ አፌን ይገፍ የቫለንቲን ገዳይ ተባባሪ ሆኛለሁ ። አሁን ግን ደሟን እመልሳለሁ ። የዚህ አራተኛ ግድያ ምንነት በማንም ዓይን ቁልጭ ብሎ እየታየ የሚች አባት የልጁን ህይወት ካልተበቀለ ማክሲ ሚለን ሞረል እንደሚበቀለው እምላለሁ ። "

" እኔም ይህ ፍትህ እንዲበዬን ከማክሲሚለን ሞረል ጋር እተባ በራለሁ ። " አለ አብሪኝ ግንባሩን ቁጥር አድርጐ ፤ " እኔም በንዝሀ ላልነቴ ነፍሰ ገዳዩን የልብ ልብ ስለሰጠሁት ልቤ በጸጸት ጦር ተወግ ቷል ።"

" ወይ መከራዬ " ሲል አጉረመረመ ቪልፎርት የሚሆነውን እጥቶ ። ማክሲሚለን ዞር ሲል የኖርቲር እይኖች በአንዳች ኃይል ሲያ በሩ አያቸው ።

" ነፍሰ ገዳዩ ማን እንደሆነ ያውቃሉ ?" ሲል ጠየቀ ማክሲ ሚለን ።

" እዎ ። "

" ይጠቁሙናል ?" አለ ማክሲሚለን ቃሉን በጉጉት ጫን አድ ርጐ ።

ኖርቲር ወጣቱን በተመስጦ አስተያዬት ከተመለከቱት በኋላ አይኖቻቸውን ወደ በሩ ዘወር አደረጉ ።

" እንድወጣ ይፈልጋሉ ?" ሲል ጠየቀ ማክሲሚለን ተስፋ በቆ ረጠ ገጽታ ።

" እዎ ። "

" ጥቂት ቆይቶ ልመለስ እችላለሁ ?"

" እዎ ። "

" ብቻዬን ነው የምወጣው ?"

" አይደለም ። "

" ማነው ከኔ ጋር እንዲወጣ የሚፈልጉት ? መሴ ቪልፎርት ?"

" አይደለም ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" ታዲያ ብቀላውን ለኔ ለመተው ትምላላችሁ ፤ ጉበዝ ?" ሲል ጠየቀ ቪልፎርት ።

አብሪኝ ፊቱን በሽሙጥ ዞር አድርጐ በቀስታ "አዎ" ሲል አጉተመተመ ። ማክሲሚለን ግን ወደ አልጋው እየተንደረደረ ሄዶ የቫለንቲንን ቀዝቃዛ ከንፈሮች ስሞ አንጀት የሚያላውስ የትካዜ ሲቃ እያሰማ ከክፍሉ ወጣ ።

" ለቫለንቲን የሚጸልይ የሚያውቁት ቄስ አለ ?" ሲል ጠየቀ አብሪኝ ቪልፎርትን ።

" እረ የለም ።" ሲል መለሰ ቪልፎርት በረጅሙ ተንፍሶ " በቅርብ የሚገኘውን ጥራ ።"

" በቅርብ የሚገኘውማ ከዚህ ግቢ ጐን ሰሞኑን የተከራዩው ኢጣሊያዊ ቄስ ነው ። ወደ ቤቱ ስሄድ እግረ መንገዴን ጉራ ብዬ ላነጋግረዋ ?"

"አዎ ፤ እዚህ ከቫለንቲን ጋር ሲቆይ ይችል እንደሆነ ጠይቀው።"

" ሊያነጋግሩት ይፈልጋሉ ?"

" አይ ፤ ብቻዬን መሆን ነው የምፈልገው ። ይቅርታ ጠይቀው ፤ ደግሞም ቄስ የሰው ሃዘን የሚገባው ሰው ነው ። "

አብሪኝ ወደ ቤቱ ማምራት እንደጀመረ በኢጣሊያዊው ቄስ መኖሪያ ቤት በረንዳ ላይ ካባ የለበሰ ሰው ቆሞ አየ ። ወደ ሰውዬው ሄዶ " ልጁ ለተቀጠፈችበት አንድ ምስኪን አባት ታላቅ አገልግሎት ሲፈጽሙ ይፈቅዳሉ አባታችን ? ለጐረቤትዎ ፤ ለመሴ ቪልፎርት ማለቴ ነው ።" አለ ።

" አዎ ፤ የሱን ቤት ሞት ደጋግሞ እንደጐበኘው አውቃለሁ ። " ሲሉ መለሱ ቄሱ በኢጣሊያዊ የአነጋገር ቃና ፤ " በራሴ ፍላጐት እገልግሎቱን ለሰግስ ሳመነታ ነው የመጣሁት ። ተግባሮቼን ቀደም አድርጐ ማወቅ የቄስ ተልእኮ ነው ።"

" ለግላጋ ልጃገረድ ነበረች ።"

" አዎ ፤ ያንንም አውቃለሁ ፤ ቤቱን ለቀው ከሚወጡ አሽከሮች ተነግሮኛል ። ስሟም ቫለንቲን መሆኑ ስለተገለጸልኝ ቀደም ብዬ ጸሎቱን ሳደርስላት ነበር ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አመሰግናለሁ አባታችን ።” አለ አብሬኝ ፤ “ የተቀደሰውን ተግባርዎን ቀደም ብለው እስከጀመሩ ድረስ እባክዎ ይቀጥሉበት ? እባክዎ ይሂዱና ከእድለቢሷ ልጃገረድ ጐን ይቀመጡ ? መላ ቢተሰቧ ከልብ ያመሰግንዎታል ።”

“ እሄዳለሁ ። ” አሉ ቄሱ ።

አብሬኝ የቄሱን እጅ ይዞ በቀጥታ ወደ ቫለንቲን ክፍል ወሰዳቸው ።

የኖርቲር አይኖች የቄሱን አይኖች ሲመለከቱ አንድ ነገር ያነበቡባቸው ይመስል በአትኩሮት እንዳፈጠጡባቸው ቀሩ ።

አብሬኝ ወጣ ። ቪልፎርት በፊትም ወደ ግል ክፍሉ ገብቶ ነበር ። ቄሱ ፀሎታቸው እንዳይረበሽ ! ኖርቲርም ሃዘናቸውን በጸጥታ ያገኙ ዘንድ በሩን ከውስጥ አጥብቀው ቀረቀሩት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 56

በማግሥቱ ዳንግላር የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ሠረገላ ወደ ግቢው ሲገባ በመስኮት እንደተመለከተ እንደራሴውን ለመቀበል ከቢሮ ወጣ ። የእንደራሴው ፊት ቆጣ ያለ ቢመስልም የትሁትና ገጽታ ይነበብበታል ።

" የሐዘን ተካፋይነትዎን ለመግለጽ እንደመጡ አልጠራጠርም ።" አለ ዳንግላር " ኧረ እባክዎ ጥንቃቄ አይጉደልዎ ክቡር እንደራሴ ? የእኛ ትውልድ ሰዎች ዘንድሮ ቀናቸው አይደለም ። ቪል ፎርት መላ ቤተሰቡን በድንገተኛ ሁኔታ ማጣቱና ጄኔራል ሞርሰፍ እንደውሻ ተዋርዶ መሞቱ ሲገርመኝ እኔም ራሴ ቤኔዴቶ የሚሉት ሰላቢ መሣለቂያ አደረገኝ ። ይባስ ብሎ . . . "

" ይባስ ብሎ ምን ?" ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

" አልሰሙም እንዴ ? ልጄ ደግሞ ቤቴን ጥላ ሄደችኮ ። "

" አይደረግም !"

" ተደረገ ፤ ክቡር እንደራሴ ። ያ ውቃቤ የራቀው ጉረምሣ ባደረሰብን ውርደት ሞራሏ በመነካቱ በውጭ ሀገር ሽርሽር ለማድረግ ፈቃድ ጠይቃኝ ከትናንት በስቲያ ማታ ሄደች ።"

" ታዲያ ፈቃድ ጠይቃ ከሄደች ምኑ ነው ጥፋቷ ? ለመሆኑ ከእመቤት ዳንግላር ጋር ነው ወይስ ? "

" አይ ፤ ከሌላ ዘመድ ጋር ። የምትመለስ አይመስለኝም ። ወይኔ ልጄን ። ጸባይዋን አውቀዋለሁ ፤ በፍጹም ወደ አገሯ አትመለስም ።"

" እንዲህ ያለውን ሃዘን በምድር ላይ ያለችው ንብረት አንድ ልጁ የሆነች ሰው ሊሸከመው አይችልም ።" አለ እንደራሴው " ለአንድ ቱጃር ግን ከምንም ላይቆጠር ይችላል ። ፈላስፋዎች ምንም ይበሉ ገንዘብ ታላቅ ካሣ መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው ። እንደርስዎ ያለው የቱጃሮች ንጉሥ ደግሞ ከየትኛውም ሰው የበለጠ ካሣ አለው ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሌ . . . . . ገባ . . . . ኝም" አለ ቦቪል ተምታቶበት በተ ቆራረጠ ድምጽ ። "አ . . . ልገባ . . . ኝም ለዚያ በረንዳው እካ ባቢ እንደሚያውቀኝ ሁሉ እጅ ነስቶኝ ለሄደው ሰው አምስት ሚሊዮን ፍራንክ ሰጠሁ ነው የሚሉኝ ?"

" ይሄ አይደል ደረሰኙ ፤ ራስዎ ይመልከቱት ። "

ቦቪል ደረሰኙን ተቀብሎ በታላቅ አድናቆት አመልካች ጣቱን አፍንጫው ላይ እንዳሣረፈ ያነብ ጀመር ። " ይህንን ሰው ማነጋ ገር አለብኝ ። " አለ ፤ " የበገ አድራጎት ችሮታ እንዲሰግስ እጠይቀ ዋለሁ ። እመቤት ሞርሰፍንና ልጅዋን እንደምግሌ እጠቅስለታለሁ ።"

" እነሱ ምን አደረጉ ?"

" መላ ሀብታቸውን ለሆስፒታሎች ለገሱ ! "

" የትኛውን ሃብት ?"

" የሟቹን የጄኔራል ሞርሰፍን ነዋ ። "

" ግን ለምን እንደዚያ አደረጉ ?"

" በዚያ በወራዳ ተግባር ከተገኘ ገንዘብ ቅንጣት እንደማይጠ ቀሙ ተናገሩ ።"

" ታዲያ እንዴት ይኖራሉ ?"

" እናት መንኩሳ ገዳም ገብታለች ፤ ልጅ ደግሞ በውትድርና ተመልምሏል ። . . . . ግን አሁን ስለራሳችን አምስት ሚሊዮን ፍራ ንክ እንነጋገር ።"

"በደስታ" አለ ዳንግላር እንደበቱ እንደወትሮው ጥርት ለማለት እየሞከረ ። " ገንዘቡን ለማግኘት ይቸኩላሉ ?"

"አዎ . . . . . የሂሣብ ሰነዶቻችን ነገ በኦዲተሮች ይመረመራሉ።"

" ነገ . . . . . ? እሱማ ሰፊ ጊዜ ነው ። በስንት ሰዓት ነው የሚመ ረመሩት ?"

" በስምንት ። "

" ጧት ሰው ይላኩ ፤ ቼኮቹን አዘጋጅቼ እቆይዎታለሁ ። "

ቦቪል እያመነታ ራሱን ከነቀነቀ በኋላ ቦርሣውን እያነሣ ፤ " ግዴ ለም እኔው እመጣለሁ ። " አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣም ወረደ ከለመዱ ንስናሽ ውስጥ ጥቂት ወርቅ ሳታገኝ እንደትማ
ቀሪ ተስፋ አለኝ ።

በዚህ ተስፋ ነው ውዳጅዋንና ብልጧን ሚስቴን ያለአንዳች ማመንታት
ትቸሽ የሄድኩት ። በእኔ ምትክ አንዳንድ ጓደኞች ፣ የጠቀስኩልሽ ወርቅና
ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደፈለግሽው የመሆን ነፃነት አሉሽ ።

አሁን ደግሞ እስኪ አንዳንድ የውስጥ ጉዳዮችን ላንሳልሽ ። ለቤተሰባ
ችንና ለልጆቻችን መበልጸግ ስትደክሚ ባለ ሙሉ ሥልጣን የሰጠሁሽ ቢሆ
ንም ለውድቀታችን ስትሯሯጭ እያዩሁ ዝም ማለት አቃተኝ ። ሳገባሽ
ሃብታም ብትሆኚም ተገቢው ክብር አልነበረሽም ። ለአሥራ አምስት
ዓመታት ሃብታችን ሲዳብር ኖሮ ባላወቅሁት ምክንያት ድንገት ማሽቆልቆል
ያዘ ። በሌላ በኩል ግን አንቺ የግል ሃብትሽን ስታደላድይ ኖረሻል ። ስለዚህ
የተውኩሽ ልክ ባገኘሁበት ሁኔታ ነው ፣ ማለትም ደህና ሐብት ከጥቂት ክብር
ጋር ። ካሁን በኋላ እኔም ለራሴ የግል ብልፅግና መልፋት እጀምራለሁ ።
ላሳዩሽኝ ምሣሌነት ሳላመሰግንሽ አላልፍም ።

የትናንቱ ባልሽ

ባሮን ዳንግላር



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ ጥንቃቄ የተሞላበት መሆኑ ከሌሎች እስረኞች ለየት አድር ጉታል ።

አንድ ቀን ይህ ሰው ቀስ በቀስ ቀለሟን እየለወጠች የመጣች ውን ሸሚዝ ኮሌታ ካስተካከለ በኋላ በጥራቱ የሌሎች እስረኞች መጠ ቃቀሻ የሆነውን ቦታ ጫማውን በመሃረቡ ጫፍ በመጥረግ ላይ እን ዳለ የቲያትር ቤት ቲኬት መቁረጫ ከምትመስለው ጠባብ መስኮት በኩል አንድ ድምጽ በድንገት “ ቤኔዴቶ ” ሲል ተጣራ ።

“ እኔን ነው ? ” ሲል ጠየቀ እስረኛው ማመን አቅቶት

“ ወደ እንግዳ ማነጋገሪያው ” ብሎ መለሰ ድምጹ ።

አንድሪያ ለጥቂት ጊዜ በመገረም ፈዞ ቀረ ። እንደሌሎች እስ ረኞች የሚጎበኘው ዘመድ አዝማድ አልነበረውም ። “ አንድ ታላቅ ሰው እንደሚንከባከበኝ አልጠራጠርም ። ” አለ ለራሱ “ ሁሉ ነገር ይህን ያረጋግጥልኛል ። በድንገት የቀረበልኝ ሃብት ፣ ሁሉንም እንቅፋቶች በቀላሉ መወጣቴ ፣ ሳላስበው የመጣልኝ ከበ ርቱ ቤተሰብ ፣ አዲሱ ስሜና ከሃብታም ቤተሰብ ጋር ልጋባ ቀርቦልኝ የነበረው እድል ሁሉ ይመሰክርልኛል ። ተንከባካቢዬ ለጊዜው ቸልብ ሎኛል። ቸልታው ግን ዘላቂ አይደለም ። ምን ያንቀዠቅዠኛል ? ራሴን ከተንከባካቢዬ ለማግለል ? ግን አሁንም በሁለት መንገዶች ሊያድነኝ ይችላል ። ለዘቦች ጉቦ ሰጥቶ በሚስጥር እንዳመልጥ ማድረግ ወይም በሆነው መንገድ ዳኞች በነጻ እንዲለቁኝ ማስፈረድ ። ተንከባካቢዬ ሙሉ ለሙሉ እንደከዳኝ ሳላረጋግጥ ምንም ነገር አላደርግም ። ከከዳ ኝ ግን ራሴው . . . ”

ልቡ በደስታ ነጠር ነጠር ይል ጀመር ። በከፊል በሽቦ ወደተከለለ ክፍል ተወሰደ ። ከሽቦው ማዶ ቤርቱቺዮ ፈርጠም ብሎ ይታያል ።

“ እህሳ ቤኒዴቶ ” አለ ቤርቱቺዮ ጥርት ባለ አንደበት ።

“ እንዴ ? ” አለ አንድርያ ራሱን ይዞ ዙሪያውን በፍርሃት እያ ማተረ ።

“ አላወቅሽኝም ቤኔዴቶ ? ”

“ ኧረ ቀስ ብለህ ተናገር ?” አለ አንድሪያ ግድግዳዎቹ ድምፅ የማያስቀሩ መሆናቸውን በደንብ ያውቅ ስለነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ማንም ሳይሰማን ብቻችንን ብንነጋገር ትመርጣለህ አይደ ለም ? ” ሲል ጠየቀ ቤርቱሲዮ

“ አዎ ”

ቤርቱሲዮ ከኪሱ አንድ ነገር አውጥቶ በሽቦው አጥር ጥግ ለቆመው ዘብ ከሰጠ በኋላ “ አንብበው ” አለ ።

“ ምንድን ነው ? ” ሲል ጠየቀ አንድሪያ ተጠራጥሮ ።

“ የራስህ ክፍል እንዲኖርህና በዚያ ክፍል እንዳነጋገርህ የሚ ያዝዝ ደብዳቤ ።”

“ አሃ ” አለ አንድሪያ በደስታ እየፈነደቀ ። ወዲያው ደግሞ ለራሱ “ አሁንም ያልታወቀው ተንከባካቢዬ ለካስ አልረሳኝም ። ቤርቱስዮንም የላከው እሱው ነው ” አለ ።

ዘቡ አንድሪያን ወደ ሁለተኛው ክፍል ወስዶ ከበረንዳው ትይዩ በሚገኝ ክፍል አስገባው ። የክፍሉ ግድግዳ በነጭ ቀለም የተቀባ ነው ። ለአንድሪያ ያ ክፍል የሚያፈዝ ውበት ያለው ነበር ። ምድጃ፣ አልጋ ፣ ጠረጴዛና ወንበር አሉት ።

ቤርቱሲዮ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። አንድሪያ ደግሞ ዘቡ እንደ ወጣ አልጋው ላይ እግሩን ዘርግቶ ተጋደመ ።

“ የምታናግረኝ ነገር አለ ? ” በማለት ጠየቀ ቤርቱሲዮ ።

“ አንተስ ? ”

“ አይ ፣ መጀመሪያ አንተ ”

“ ልትጠይቀኝ የመጣኸው አንተ እስከሆንክ ድረስ የምትነግ ረኝ ነገር አዘጋጅተሃል ። ”

“ እረ ለመሆኑ አሁንም ወንጀል መፈጸምህን አልተውህም ? ደሞ በስርቆት በግድያ ተይዘህ ትታሰር? መቼ ይሆን እርም የሚልህ?”

“ ይህንን ልትነግረኝ ነው እንዴ የመጣኸው ? ” አለ አንድሪያ ፤ “ እሱ ጠፋኝ ብዬሃለሁ ? ይልቅዬ እኔ የማላውቀው ነገር አለ ፣ እሱን ንገረኝ ። ማነው የላከህ ? ”

“ ማንም ። ”

“ ታዲያ መታሰሬን ማን ነገረህ ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ወደ እንደራሴው ቤት ስትቀላውጥ አንድ ቀን ይህ እንደማ ይቀርልህ አውቅ ነበር ። "

" የእንደራሴው ቤት . . . . . ስመሆኑ አባቴ ምን አለ ? "

" እኔ ምንህ ነኝ አንተ ? "

" አንተማ የእንጀራ አባቴ ነህ ። ግን በአራትና በአምስት ወራት የተጠቀምኩበትን አንድ መቶ ሺ ፍራንክ ስትሰጠኝ የነበርከው አንተ አትመስለኝም ። ሃብታም ኢጣሊያዊ አባት የፈጠርክ ልኝ አንተ አልነበርህም ። በአውቲሉ የራት ግብዣ ከታወቁ የፓሪስ ሰዎች ጋር ያስተዋወቅሽኝ አንተ አልነበርህም . . . . . . . . "

" ስመሆኑ ምንድን ነው ልነግርህ የምትፈልገው ? " ሲል በርቱ ሲዮ አጳረጠው ።

" ፍንጭ ልስጥህ ? አሁን ስለ እንደራሴው ቤት ስታወራ ነበር አይደለም ? "

" እና ? "

" እንደራሴው በጣም የተከበሩና ሃብታም ነበሩ ። "

" በቤታቸው ስርቆትና ግድያ የፈጸምክባቸው ? "

" አ . . . ነው መሰለኝ ። ግን አሁን እስኪ በሞቴ ንገረኝ ፣ እግራቸው ስር ተደፍቼ ' አባቴ ማረኝ ' ብዬ ልለምናቸው ? "

" ቀልዱ ይቅርብህ " አለ ቤርቱሲዮ ምርር ብሎ " ዳግመኛም እንዲህ ያለ ነገር ካፍህ አይውጣ ። "

" ለምን ቢባል ? " ሲል ጠየቀ አንድሪያ በቤርቱሲዮ መኮሳተር በሽቆ ።

" ምክንያቱም የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ እንዳንተ ያለው ርጉም ወንጀለኛ አባቴ የሚላቸው ሰው አይደሉም ። "

" ጥሩ ብለሃል ። ግን . . . "

" ካልተጠነቀቅህ ሌላም ይከተልሃል ። "

" ኢዲያ ፣ ምን ታንገራግረኛለህ። እኔ እንደሁ ሁሌም ያው ነኝ።"

" ብትጠነቀቅ አይሻልህም ቤኔዴቶ ? አሁንም የቸርነት እጅ ተዘርግቶልሃል ። ብትጠቀምበት ይሻልሃል ። ጥጋብህ አልበረደ ድልህ ከሆነ ግን ያው . . . . . "



t.me/OLDBOOKSPDF

" አባቴ ማን እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ " አለ እንድሪያ ተሰላችቶ እንደ ሕጻን ልጅ እግሩን ሲያፈራግጥ እያጣረ ። " የፈለገው ይሁን አባቴን ፈልጌ ማግኘት አለብኝ ። ማነው አባቴ ? "

" እሱን ልነግርህ ነው የመጣሁት ። "

" እሻ " አለ እንድሪያ አይኖቹ በደስታ እያበሩ ።

በዚህ ጊዜ በሩ ተከፍቶ ዘቡ ገባ ። " ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ " አለ ዘቡ ቤርቱሲዮን ። " ቃል ተቀባይ እስረኛውን እየጠበቀ ነው ።"

" ነገ ተመልሼ እመጣለሁ ። " አለ ቤርቱሲዮ

" ጥሩ " አለ እንድሪያ ። " ታዲያ እግረ መንገድህን አንድ ሁለት መቶ ፍራንክ ያህል ተውልኝ ፣ ስንት አለ ? አንዳንድ ነገር እንኳ ቢያስፈልገኝ . . . . "

" እተውልሃለሁ ። " ሲል መለሰ ቤርቱሲዮ ።

ዳሩ ግን እንድሪያ እጁን ቢዘረጋም ቤርቱሲዮ እጁን ከኪሱ አላወጣ አለ ።

እንድሪያ ፈገግ ለማለት ሞከሮ ግን የቤርቱሲዮ ያልተለመደ ጸጥ ያለ ገጽታ መንፈሱን ረበሸው ። " ተሳስቼ ይሆን ? " ሲል አሰበ ። " እስቲ ለሁሉም እናያለን ። " ከዚያም ድምፁን ከፍ አድርጎ " መቼ እንገናኛለን ?" አለው ቤርቱሲዮን ።

" ነገ ። " ነበር የቤርቱሲዮ መልስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብለው እሳት የሚተፉ እስኪመስሉ ድረስ ቪልፎርትን ገረመሙት ። ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲገባ በቀስታ መራመድ ሲጀምርም እነዚያው አስፈሪ አይኖች ተከተሉት ። በመጨረሻም የእነዚያውንቱ አይኖች ልጃቸው ያቀረበውን መሐላ የሚያስታውሱት ይመስል ወደ ሰማይ ተመለከቱ ።

“ ታገሰኝ ! ” አለ ቪልፎርት ፤ ከአባቱ ክፍል ቤታች እንደ ደረሰ ። “ አንድ ቀን ብቻ ታገሰኝ ። ቃሌን አላጥፍም ! ”

የኖርቴር አይኖች ቁጣቸው በቪልፎርት ቃላት ረገብ ብለው ወደ ሌላ አቅጣጫ ይመለከቱ ጀመር ። ቪልፎርት እንደታፈነ ሁሉ ኮቱን በፍጥነት አውልቆ እጁን ግንባሩ ላይ እንዳደረገ ወደ ራሱ ክፍል ገባ ።

እንደወትሮው ሁሉ በዚያ ምሽትም ሌሎች የቤተሰቡ አባላት ወደየመኝታቸው በገቡበት ሰዓት ቪልፎርት በሥራ እንደተጠመደ ነበር ያነጋው ። እስከ ንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ የመሃል ዳኛው ስለ ቤኔዴቶ ጉዳይ ያቀረቡትን ዘገባ ፤ የአይን ምስክሮችን ቃልና እሱም ለሚቀጥለው ችሎት በከባድ ጥንቃቄ ያዘጋጀውን የውሳኔ ሃሳብ ሲመረምር አደረ ። ከዚያም ለጥቂት ጊዜ በሚሠራበት ጠረጴዛ ላይ ተደፍቶ ካሸለበ በኋላ በመጀመሪያው የወፎች ጫጫታ ብንን አለ ። ወደ መስኮቱ ሄዶ ከፈተው ። በምሥራቁ አድማስ ዙሪያ ፍም የመሰለ ብርሃን ተዘርግቷል ። የንጋቱ ቀዝቃዛ አየር ፊቱን ሲዳስሰው ትውስታውን ቀሰቀሰበት ። “ ዛሬ ” አለ የታችኛውን ከንፈሩን ነክሶ ከቆየ በኋላ “ የፍትህን ጦር የጨበጠው ሰው ወንጀል በተሠራበት ቦታ ሁሉ ከንዱን መሰንዘር አለበት ። ”

ሳይታወቀው አይኖቹ ትናንት ኖርቴርን ወዳዩበት መስኮት አማተሩ ። መስኮቱ በመጋረጃ የተሸፈነ ቢሆንም የአባቱ ገጽታ በአይነ ሕሊናው ቁልጭ ብሎ ይታየው ስለነበር የእነዛውንቱ ቁጡ አይኖች ከዚያው ሥፍራ ያሉ ይመስል ፤ “ አይዞህ ፤ እታስብ ። ” ሲል አጉረመረመ ።

በክፍሉ ብዙ ጊዜ ከዳር እስከዳር ሲንጐራደድ ከቆየ በኋላ የእደ ባባይ ልብሱን ለብሶ ሶፋው ላይ ተዝናንቶ ተቀመጠ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀስ በቀስ ቤቱ ራሱ ከሌሊቱ እንቅልፉ የሚነቃ መሰለ ። በሮች እየተከፈቱ ሲዘጉ ፣ ሚስቱ ሠራተኛዋን ደወል ደውላ ስትጠራ ፣ ሕጻኑ ኤድዋርድ ሲጫወት ይሰሙታል ።

ቪልፎርት ደወል ደወለ ። አዲሱ ባለሟሉ የጧት ጋዜጣና ቸኮሌት ይዞ መጣ ።

"ምንድን ነው እሱ ደግሞ ?" ሲል ጠየቀ ቪልፎርት በሽሙጥ ።

"ቸኮሌት ነው ጌታዬ ።"

" መች ጠየቅሁ ፣ ዛሬስ ማነው እንዲህ ያሰበልኝ ? "

" እመቤት ቪልፎርት ናቸው ፣ ጌታዬ ። የዛሬው የግድያ ክስ ምናልባት በኃይል ሳያደክምዎ አይቀርም ፣ ኃይል ያስፈልግዎታል ብለው ነው እንዳመጣልዎ ያዘዙኝ ። "

ባለሟሉ ስኒውን አስቀምጦ ወጣ ። ቪልፎርት ስኒውን የጉድን ሲያዬው ከቆየ በኋላ ድንገት ብድግ አድርጐ ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው። ሁኔታው ቸኮሌቱ እንደተመረዘ ተስፋ አድርጐ ከሞት ከበለጠው አስቸጋሪ ሥራው ይገላግለው ዘንድ ሞትን በደስታ በመቀበል የሚ ጠጣ ይመስል ነበር ። ብድግ ብሎ ለሚያየው ሁሉ በሚዘገንን ሁኔታ ፈገግ እያለ ክፍሉን ደጋግሞ ዞረው ።

ቸኮሌቱ አልተጠናወተውም ፣ የሕመም ስሜት አልተሰማውም። በምሳ ሰዓት ወደ ሳሎን አልወጣም ። በመጨረሻው ባለሟሉ በሩን ከፍቶ ከአንገቱ ብቻ ገባ በማለት ፣

" ጌታዬ ፣ እመቤት ቪልፎርት ' አምስት ሰዓት ሆኗል ፣ ችሎት የሚከፈተው ከሰዓት በኋላ ነው ' ይላሉ " አለ ።

" ታዲያ ምን ይሁን ? " ኃይለኛ ጩኸት ነበር ።

" አሳቸውም ከእርስዎ ጋር ለመሄድ ይፈልጋሉ ጌታዬ ፣ ፈቃ ደኝነትዎን እንድጠይቅ ነው የላኩኝ ። "

" የት ? "

" ችሎት ። "

" ለምን ? "

"በዛሬው ክስ ላይ ለመገኘት በጣም እፈልጋለሁ ነው ያሉት ።"



t.me/OLDBOOKSPDF

ኤድዋርድ እጆቹን እያፍተለተለ እንደወጣ ቪልፎርት በሩን ከው ስጥ ቀረቀረው ።

" ምንድን ነው ጉዳዩ ? " ስትል ጠየቀች ወጣቷ እመቤት ባሏን በሚመራመር አስተያየት ስትመለከተው ቆይታ የታከተ ገጽታውን የምታካክስ ይመስል ፈገግ ልትል እየሞከረች ። " ዛሬስ ተሹሞብ ሃል ። "

" ያ መርዝ የታለ ? " አለ ቪልፎርት በሚስቱና በበሩ መካከል እንደቆመ ጥርሱን እያንቀረጨጨ ።

እመቤት ቪልፎርት የተሰማትን ስሜት በቃላት መግለፅ ያዳግ ታል ። ከጉሮሮዋ አካባቢ ለቅሶ ይሁን ሳቅ የማይታወቅ ሻካራ ድምፅ አመለጣት ። " አ . . . . አልገባኝም ፥ " አለች ።

" እንዴት አይገባሽም ?" አለ ቪልፎርት ፍጹም ጥርት ባለ ድምፅ " ሁለት አማቶቼን ፥ ባሮይስንና ልጄን ቫለንቲንን የገደልሽበትን መርዝ የት ነው የደበቅሽው ? "

" እንዴ . . . ምንድን ነው የምታወራው ? " ስትል ጮኸች እመ ቤት ቪልፎርት እጆቿን እያወናጨፈች ።

" መልሽ እንጂ ጠይቂ አልተባልሽም ! "

" ከማን ጋር ነው የምነጋገረው . . . . . ከባለቤቴ ወይስ ከዳኛ ? " አለች ሚስት ልብ ልትገዛ እየሞከረች ።

" ከዳኛ ጋር እመቤት ፥ ከዳኛ ! "

" እንዴ " ከማለት ሌላ እመቤት ቪልፎርት የምትናገረው ቃል አጣች ።

" አልመለስሽኝም እመቤት ! " አለ አስፈሪው ቃል ተቀባይ ። ከዚያም ከቁጣ የበለጠ በሚያሸብር ፈገግታ ፤ " በርግጥ የምትክጅው ነገር የለሽም ። " አለ ።

እመቤት ቪልፎርት ሳታውቀው ወደ ኋላ አፈገፈገች ። "መካድም አት ችይም ! " አለ ቪልፎርት ቀጠል አድርጐ ፥ በፍትህ ስም የሚያንቃት ይመስል እጁን ወደ አንገቷ አካባቢ እያሳረፈ ። " ወንጀልሽን የምት ፈጽሚበት የራስሽ ሐፍረተ ቢስ ጥበብ ቢኖርሽም ወጥመድሽ ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልሻል ? የለም ፣ ግንም ይሁን ግን ገመዱ የወንጀለኛውን እንገት መጠባበቁን አይተውም ። ”

እመቤት ቪልፎርት ድንጋጤ ከሰውነት ወደ አውሬነት የለወጣት መሰለች ። በማትችለው ጭንቀት እንደተዋጠች ፊቷ ይመሰከራል ።

“ ገመድ እንኳ አትፍሪ ። ” አለ ዓቃቤ ሕጉ ፤ “ ያንቺን ክብር ማበላሸት ራሴንም ጭምር ማዋረድ ነው ። የተናገርኩትን በጥሞና አዳምጠሽ ቢሆን ኖሮ በገመድ ታንቀሽ እንደማትሞች ትረጂ ነበር።”

“ ምን ለማለት እንደፈለግህ አላወቅሁም ። ” አለች ወንጀለኛዋ እመቤት ፍጹም በተብረከረከ አንደበት ።

“ የምለውማ የስመጥሩ ዓቃቤ ሕግ ፣ ተወዳዳሪ የሌለው የሕግ ሰው ፣ የቪልፎርት ባለቤት በራሷ ወንጀል ባሏን ጨምራ አትበክልም ፤ ባንድ ጊዜ እሷንም ባሏንም አታቀልም . . . ነው ። ”

“ እዎ ፣ እዎ አታቀልም ! ”

“ እንግዲያውስ የበኩልሽን በመወጣትሽ እጅግ አመሰግናለሁ።”

“ ታመሰግነኛለህ ? ምን ስላደረግሁልህ ? ”

“ እሁን የተናገርሽውን ስለተናገርሽ ። ”

“ ምን ተናገርኩ ? ናላዬ ዞሮብኛል . . . ተምታቶብኛል . . . ወይ አሳሬ ! ”

“ ገና ስገባ የጠየቅሁሽን ጥያቄ አልመለስሽልኝምኮ ! መርዝሽ የታለ? ”

እመቤት ቪልፎርት እጆቿን ወደላይ ዘርግታ ጣቶቿን አቆላለፈች “ እረ ፣ እረ ፣ ” አለች ግራ በተጋባ ቃና ፤ “ ያንን እንዳደርግ በፍጹም አትፈርድብኝም ። ”

“የማልፈርድብሽ የስቅላት ሞትን ነው ። ተግባባን ? ”

“ ማረኝ ! ”

“ መች ጨከንኩብሽ ? እኔ የምፈልገው ትክክለኛ ፍርድ ሲፈጸም ማየት ነው ። ” አለ ቪልፎርት ፣ “ የተፈጠርኩት ወንጀለኛን ለመቅጣት ነው ” አለ ቀጠለና ። “ ማንኛዋንም ሴት ፣ ንግሥትም



t.me/OLDBOOKSPDF

ብትሆን ፥ በቀጥታ ወደ ችሎት አቀርባታለሁ ። እንቺን ግን ምሬሻ ለሁ ። ለአንቺ የምናገረው ቃል ‘ ከመርዝሽ ጥቂት አስተርፊሻል ? ’ የሚል ብቻ ይሆናል ። ”

“ ኧረ . . . ኧረ ይቅርታ አድርግልኝ ፥ አትጨክንብኝ . . . ጥቂት ልቆይ ? ”

“ ነፍሰ በላ ! ”

“ ተው ሚስትህ መሆኔን አስብ ? ! ”

“ ጭራቅ ነሽ ! ”

“ በፈጠረህ . . . . . ?”

“ አይቻልም ! ”

“ በድሮው ፍቅራችን . . . . . ? ”

“ አይቻልም ፥ አይቻልም ! ”

“ በልጃችን ሞት ! እባክህ ለልጃችን እንኳ ልኑርለት ? ! ”

“ አይቻልም ! ያንቺ ሕይወት ከተራዘመ አንድ ቀን እሱንም ታርጅዋለሽ ። ”

“ እኔ ? ልጄን ልገድል ? ” በማለት እንደ እብድ ያደረጋት እመ ቤት ዘላ ቪልፎርት ላይ ተከመረችበት ። “ እኔ የእኔን ኤድዋርድ እገ ድላለሁ ? ” ከንግግሯ መጨረሻ የእብድ ሰው አይነት ሳቅ ከሳቀች በኋላ እንደገና በባሏ እግር ሥር ተደፍታ ጫማውን ሙጭጭ አድርጋ ያዘች ።

“ ልብ አድርጊ ” አለ ቪልፎርት ፥ “ከችሎት ስመለስ ፍትህ ተበ ይኖ ባላገኝ ዋ ! በገዛ ራሴ ከንፈሮቼ ወንጀሎ በገዛ ራሴ እጆች ጠፍሬ እንደማሥርሽ ፥ በአረመኔአዊ የነፍሰ ግድያ ወንጀል ተከሠሽ በሕ ዝብ ፊት ቅጣት እንደሚፈጸምብሽ እወቂ ። ”

እየተንቀጠቀጠች አዳመጠችው ። በድን ከሆነው መላ ሰውነቷ ውስጥ ሕይወት የሚታይባቸው አይኖቿ በሚዘገንን ሁኔታ ደም ለብ ሰዋል ።

“ ተግባብተናል ? ” አለ ቪልፎርት ። “ አሁን ወደ ችሎት የም ሄደው አንድ ነፍሰ ገዳይ የሞት ቅጣት እንዲበየንበት ለመጠየቅ መሆ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነን ታውቂያለሽ ። ልክ ስመለስ በሕይወት ባገኝሽ ማታውኑ ወሀኒ አስጨምርሻለሁ ። ነገውኑ በዛሬው ነፍስ ገዳይ ላይ የጠቀስኩትን እንቀጽ ጠቅሼ እገትርሻለሁ ! ”

እመቤት ቪልፎርት የማታዝገበት ሰውነቷ ወለሉ ላይ ተዘረረ ። በደመነፍስ ፈገግ አለች ። ቪልፎርት ሁኔታዋን ሲያይ መጠነኛ የእዘኔታ ስሜት ከጀለው ። አጐንብሶ በአትኩሮት ከተመለከታት በኋላ “ ደህና ሁኚ እመቤት . . . . ደህና ሁኚ ! ” አለ በዝግታ ። ቃላቱ እንደ ቢላዋ ቀደዋት ገቡ ። ራሷን ስታ ተስለመለመች ።

ዓቃቤ ሕጉ በሩን በባለቤቱ ላይ ከውጭ ቆልፎባት ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## 60

የቢኔዴቶ ጉዳይ በሚታይበት ችሎት ብቻ ሳይሆን በመላ ፓሪስ ታላቅ የመነጋገሪያ ርዕስ ከሆነ ውሎ አድሯል ። የባርቶሎሚዮ ልጅ አንድሪያ በፓሪስ ከተማ በቅንጦት ሲንፈላሰስ በነበረባቸው ጥቂት ወራት ከብዙ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ ችሎ ነበር ። ጋዜጦች አንድሪያ በእሥር ቤትም ሆነ በፓሪስ ሕብረተሰብ ዘንድ ያሳለፈውን የጉደፈ ሕይወት እየፈለፈሉ ይፋ በማውጣት በተለይ አንድሪያ ባር ቶሎሚዮን በሚያውቁ ሰዎች ዘንድ መጨረሻውን ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት እንዲያድርባቸው አደረጉ ። ብዙ ሰዎች ግን አንድሪያን የሚያውቁት በተጫዋችነቱና በለጋስነቱ ስለነበር የሚወራበት ሁሉ አንድ ከባድ ባላንጣ የሸረበበት ተንኮል እንጂ በርግጥ አንድሪያ የፈጸመው ወንጀል ነው ብለው ማመን አዳግቷቸዋል ።

በዚህ የተነሳ ነበር በአንድሪያ ላይ በሚቀርበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ አስተያየቱን ለመስጠትም ሆነ እንዲሁ ትርኢቱን ተመልክቶ ለመዝናናት የችሎቱን አዳራሽ ሕዝብ ያጨናነቀው ። ገና ከጧቱ በአንድ ሰዓት ችሎቱ ከመሰየሙ አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ የፍርድ ቤቱን በር ዙሪያ ሕዝብ አጣቦት ነበር ።

ዳኞችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሕግ ባለሙያዎች ሥፍራቸውን እንደያዙ አዳራሹ በወረቀቶች መገላበጥ እንኳ የሚረበሽ እስኪመስል ድረስ ጸጥ አለ ። የተመልካቾችን አትኩሮት ብቻ ሳይሆን አድናቆት በመሳብ ዝነኛ የሆነው ቪልፎርት ወንበሩ ላይ በኩራት እንደተቀመጠ እንደተለመደው ገልመጥ ብሎ አዳራሹን በአይኑ ገረመመው ። አሁንም እንደተሾመበት ነው ።

“ ወታደሮች ” አለ የመሐል ዳኛው ፤ “ ተከሳሽ ይቅረብ ። ”

እነዚህ ቃላት ሲነገሩ የተመልካቹ ሕዝብ ትኩረት የበለጠ ጨምሮ ሁሉም አይኖች ቤኔዴቶ ወደሚገባበት በር አተኮሩ ። በሩ ወዲያውኑ



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ምን ፣ የማታውቃቸው ጠላቶች ያቀነባበሩብህ ደባ ተጠቂ ላለመሆንህ እርግጠኛ ነህ ፣ መሴ ቪልፎርት ? የማመዛዘን ችሎታህ ተዛባብህ ? እንዲህ ያለው ድንገተኛ ፣ ያልተጠበቀና አስደንጋጭ ውንጀላ በርግጥ አእምሮን ሊረብሽ ይችላል ። ሁላችንም ይህ ይገባናል። አደብ እስክትገዛ ጊዜ ልንሰጥህ እንችላለን ። ”

ቪልፎርት በእሉታ ራሱን ነቀነቀ ። ወባው እንደተነሳበት በሽተኛ ጥርሶቹ በኃይል ተፋጩ ። “ እእምሮዬ ፍጹም እንደወትሮው ነው ፣ ጌታዬ ” አለ ። “ ይህ ወጣት በእኔ ላይ ያቀረባቸው ነጥቦች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን ቢመሳበል ካሁን በኋላ በሚተካኝ ዓቃቤ ሕግ ፊት ራሴን ለፍርድ አቅርቤአለሁ ። ”

እነዚህን ቃላት ቢታፈንና በግልጽ በማይሰማ ድምጽ ከተናገረ በኋላ ቪልፎርት እየተንገዳገደ ከአዳራሹ ወጣ ።

ባለፉት ሁለት ሳምንታት የፓሪስን ነዋሪ ሕዝብ ግራ ሲያጋቡ የነበሩት ክስተቶች በዚህ ወቅት ከተፈጠረው አዲስ ዱብዳ ጋር ተዳምረው አዳራሹን በቃላት በማይገለጽ ሽብር አንቀጠቀጡት ።

“ችሎቱ ተዘግቷል ። ” አለ የመሃል ዳኛው ፣ ከየግራ ቀኙ ዳኞች ጋር ለብዙ ጊዜ በሹክሹክታ ሲነጋገር ቆይቶ ። “ ጉዳዩ ለሚቀጥለው ችሎት ተላልፏል ። ”

አንድሪያ የተረጋጋው ገጽታው ሳይለየው አንዳች አክብሮት ያሳዩት በጀመሩት ሁለት ወታደሮች እንደታጀበ ከአዳራሹ ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## 61

ተደጋጋሚ አደጋ አትሉን ያሳጣው ቪልፎርት ከችሎት ሲወጣ ይታይበት የነበረውን ድንግርግሩ የወጣ ሁኔታ ፣ የደም ሥሮቹን እስኪቀረተሩ ድረስ የወጠራቸውን ትኩሳት ፣ መላ ሰውነቱን የወረረውን የጭንቀት ሁኔታ ፣ ደረጃውን በቃላት ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው ። ዙሪያው ስለጨለመበት ከአዳራሹ እንደወጣ ወደ ኮሪደሩ የሄደው በደመ ነፍስ ነበር ። የወቶት ስልባቦት የመሰለ አረፋ በአከናፍሩ ይኩረፈረፋል ። ደጋግሞ በረጅሙ እንደተነፈሰ ሠገረላውን አዬው ። ያለወትሮው በሩን ራሱ ከፍቶ ከገባ በኋላ ወንበሩ ላይ በኃይል ወደቀበት ። ሲናገር ሲያስብ እንደበቱ ተሰልቦበታል ። የሠረገላውን ሾፌር ወደ ቤቱ አቅጣጫ አመለከተው ።

የሕይወቱ ውድቀት የመላ ከብደቱን ናዳ በቪልፎርት ራስ ላይ ጭኗል ። በከብደቱ የተጨፈለቀ ቢሆንም ቪልፎርት መዘዙን ገና አልተረዳም ፣ ቢረዳም ምን ያህል መራራ እንደሚሆን አልለካም ። አልፎ አልፎ ብቻ “ በስመ አብ ፣ በስመአብ ፣ ” ይላል ፣ የሚናገረው ሳይታወቀው ።

ሠረገላው ገሰገሰ ። ቪልፎርት በመቀመጫው ላይ ሊጋደም ሲሞክር ድንገት አንድ የሚያስጨንቀው ነገር በእጁ እንደነካ ተሰማው ። ሚስቱ ሠረገላ ላይ አስቀምጣ የረሳችው የአየር ማራገቢያ ነበር ። በውድቅት ሌሊት ድንገት ቦግ እንደሚል የመብረቅ ብልጭታ ማራገቢያው ትዝታውን አፈለቀበት ። ስለሚስቱ አሰበ ።

“ አ ! ” ሲል ጮኸ ልቡ በጋለ ብረት እንደተወጋ ሁሉ ። ለአንድ ሰዓት ያህል ሕሊናውን ሲበጠብጠው የነበረው የሃጢአቱ አንድ ዘርፍ ብቻ ነበር ። ሌላው አስከፊ ዘርፍ ደግሞ ትውስ አለውና አይኖቹን በኃይል ጭፍን አደረገ ። ጧት በሚስቱ ፊት የማይበገር ዳኛ ሚና እንደሚጫወት ራሱን አወድሶ የሞት ቅጣት ፈርዶባት ነበር ከቤት የወ



t.me/OLDBOOKSPDF

" ያኔ የመጣሁት ለልጅህ የነፍስ ይማር ጸሎት ላደርስ ነበር ፡"
ሲሉ መለሱ ቄሱ ።

" ዛሬስ ? "

" ዛሬ ኢንኳ እዳህን እንደከፈልከኝ ልነግርህና ካሁን በኋላ ሌላ ቅጣት እንዳይፈጽምብህ ልጸልይልህ ብዬ ነው የመጣሁት ። "

" ኧረረ . . . . . " አለ ቪልፎርት ሽምቅቅ ብሎ ወደኋላው እያፈገፈገ " ይኸ የቄስ ቡሶኒ ድምጽ አይደለም ። "

" አልተሳሳትህም ! " ቄሱ ጥምጥማቸውን በቅጽበት አውልቀው ራሳቸውን ነቅንቅ ሲያደርጉት ከተተበተበበት ጨርቅ ነጻ የወጣው ጸጉር ፈርጠም ባለው ፊት ላይ ተመሰቃቅሎ ወረደ ።

" የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ፊት አይደለም እንዴ ? " ሲል ሙሽ እንደ እንስሳ ሊሆን የተቃረበው ቪልፎርት ራሱን ይዞ ። ተሳስተሃል ። አይደለም ፤ ሙሴ ቪልፎርት . . . . እስኪ ራቅ አድርገሎ አስብ ። "

" ይህ ድምጽ ! የት ነበር መጀመሪያ የሰማሁት ? "

" ከሃያ ሶስት ዓመታት በፊት ማርሴል ላይ ነበር የሰማኸው ። ከሬኔ ጋር የጋብቻ ውል ያሰርክ ቀን ። "

" ቡሶኒም ፤ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴም አይደሉም ? ወይ አጋጣሚ ! እርስዎ ነዎታ ድብቁ ባላንጣዬ ! ማርሴል ባንድ ጉዳይ በድየ ዎታለሁ ልበል ? "

" አዎ ! እጅግ አድርገህ ! " አለ እንደራሴው እጆቹን በሰፊው ደረቱ ላይ አጣምሮ ። " መለስ ብለህ አሰላስል ። "

" እኮ ምን አደረግሁዎ ? " ሲል ሙሽ አእምሮው በእብደትና በቁጭት መካከል የሚዋዥቀው ቪልፎርት ። " ምን አደረግሁዎ ? ይን ገሩኝ ? ! ይናገሩ ? ! "

" ባልሞት ቀበርከኝ ። በሰቆቃ ማቅቄ በአዝጋሚ ሞት እንዳልፍ ፈረድህብኝ ። አባቴን በረሃብ ገደልክብኝ ። ፍቅሬን አስነጠቅኸኝ ። ወለል ብሎ የተዘረጋውን እድሌን በግፍ አጠፍክብኝ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ንላተ . . . . ይብላኝ ላንተ ” ከእያንዳንዷ ይብላኝ ላንተ ጋር መሬቱ ላይ ያንዘራል ።

እንደራሴው ቅናፍ ብሎት ወደ ኋላው መለስ አለና “ ወቻ ጉድ ” አለ ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምጽ ። “ አበደኮ ! ”

ከዚያም የዚያ የተረገመ ሕንጻ ግድግዳ ተደርምሶ ራሱ ላይ እንዳ ይፈረካከስ የፈራ ይመስል ጣል ጣል እያለ ወደ መንገዱ ሲወጣ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ያደረገውን ለማድረግ መብቱ የሚፈቅድለት ተበዳይ መሆን አለመሆኑን በጥርጣሬ ያምሰለስል ነበር ።

ቤቱ እንደደረሰ ማክሲሚለን በሃሳብ ተመስጦ በበረንዳው ወዲያ ወዲህ ሲንጐራደድ አገኘው ።

“ ራስህን አዘጋጅ ፡ ማክሲሚለን ። ” አለ እንደራሴው ፈገግ ብሎ “ ነገ ፓሪስን እንለቃለን ። ”

“ እዚህ የቀረም ጉዳይ የለም ማለት ነው ? ” ሲል ጠየቀ ማክ ሲሚለን ።

“ እንዲያውም ከሚገባኝ በላይ ሳልሠራ አልቀረሁም ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

# 62

ድፍን ፓሪስ ጉድ አለ ። በየጊዜው አንድ የሚያሸብር ነገር ሰምቶ አፉን የማይዝ የፓሪስ ነዋሪ አይገኝም ። እማኑኤልና ሚስቱ ዡሊዩም በቤታቸው በሦስቱ ስመጥር የፈረንሳይ ሰዎች በዳንግላር፣ በሞርሰፍና በቪልፎርት ላይ የደረሱትን ሦስቱን ያልተጠበቁና ድንገተኛ ፍርጃዎች ጸሩ ሲወያዩባቸው ነበር ። ሊጠይቃቸው የመጣው ማክሲሚለን እያነጻ በውይይታቸው ሳይሳተፍ በታዛቢነት በመወሰን በራሱ የትካዜ ባሕር ይዋኝ ነበር ።

“ አቤት ፣ እንዴት ፈረደባቸው ! ” አለ እማኑኤል ስለሞርሰፍና ስለ ዳንግላር ሲያስብ ቆይቶ ።

“ ወይ መዓት ። ” አለች ዡሊዩ ። ንግግሯ ስለቫለንቲን ቢሆንም ስሟን በወንድሟ ፊት ላለመጥራት ፈልጋ ።

“ የመታቸው ሲያደባቸው የኖረ ተበዳይ ከሆነ ” አለ እማኑኤል ፤ “ እንዲህ የጨከነባቸው ካለፈው ሕይወታቸው ቅጣታቸውን የሚያቀልላቸው በጐ ተግባር አላገኘላቸው ብሎ ይሆናል ። ”

እማኑኤል ገና ንግግሩን ሳይጨርስ የሳሎኑ በር ተከፍቶ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴን መምጣት አበሰረ ። ዡሊዩና እማኑኤል በደስታ ብድግአሉ ። ማክሲሚለን ከአንገቱ ቀና ካለ በኋላ ተመልሶ አቀረቀረ ።

“ ማክሲሚለን ” አለ እንደራሴው የእሱ መምጣት በሰዎቹ ዘንድ የፈጠረውን ስሜት ልብ ሳይል “ ከእኔ ጋር ልወስድህ ነው የመጣሁት ። ”

“ ከእርስዎ ጋር ሊወስዱኝ ? ” አለ ማክሲሚለን ከቅዠቱ የባነነ መስሎ ።

“ አዎ ፣ እንድትዘጋጅ አልነገርኩህም ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

" ታዲያ ተዘጋጅቻለሁ ! " ሲል መለሰ ማክሲሚለን ። " እዚህ የመጣሁትም ልሰናበት ነው ። "

" የት ነው የምትሄዱት ፤ ክቡር እንደራሴ ? " ስትል ጠየቀች ዡሊዬ ።

" መጀመሪያ ወደ ማርሴል ። "

" ወደ ማርሴል ? " ሲሉ ባልና ሚስት ቃሉን ደገሙት ።

" አዎ ፤ ወንድማችሁንም ልወስድባችሁ ነው ። "

" በፈጠረዎ አድነው ይመልሱልን ? " አለች ዡሊዬ ።

ማክሲሚለን ስሜቱን ለመደበቅ ዞር አለ ።

" ሃዘኑን አውቃችሁለታላ ? " እንደራሴው ነበር ።

" አዎ ፤ እረ እንዲያውም እኛን ሳይቀር የሰለቸን ይመስለኛል።"

" ዞር አድርጌው ልሰንብት እስኪ ። " ሲል መለሰ እንደራሴው

" ዝግጁ ነኝ ክቡር እንደራሴ ፤ " አለ ማክሲሚለን ። " ደህና ሁኑ ዘመዶቼ ! ደህና ሁን አማኑኤል ! ደህና ሁኚ ዡሊዬ ! "

" ምን ማለትህ ነው ? " ስትል ዡሊዬ ወንድሟ ላይ ሙኘች ። " እንዴት እንዲህ በድንገት ትለየናለህ ? ሳትሰናዳ ? ያለ ፓስፖርት?"

" ዳተኛነት የመለያዬትን ሃዘን ያራዝመዋል ። " አለ እንደራ ሴው ፤ " ማክሲሚለን ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ እርግጠኛ ነኝ ። "

" አስቀድሜ ነግሬዎታለሁ ። ፓስፖርቴም ሆነ ጓዜ ተሰናድ ቷል ። " አለ ማክሲሚለን ቀልጠፍ ብሎ ።

" እና እንዲህ በድንገት ነው የምትለዩን ? " ስትል ጠየቀች ዡሊዬ ።

" ከግቢያችሁ በር ላይ ሠረገላዬ እየተቁነጠነጠ ይጠባበቃል ። በአምስት ቀናት ውስጥ ሮም መድረስ አለብኝ ። "

" ማክሲሚለንም ሮም ሊሄድ ነው ? " ሲል አማኑኤል ጠየቀ ።

" እንደራሴው ሊወስዱኝ በሚፈልጉት ቦታ ሁሉ እንዛለሁ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

" እንዲህ አትበል " አለ እንደራሴው መከራከሩ እንደማያዋጣው ገምቶ " የለም ፤ እኔ እንኳ ሰው ነኝ። " ሙሉ ለሙሉ ፈገግ አለ።

እንደራሴው የእማኑኤልንና የዡቢዩን እጆች አጣምሮ ከያዘ በኋላ እንባ በአይኑ እንደተሞላ ሳማቸውና ከዚያ ደስታ ድንኳኑን የተከለበት ከሚመስለው ቤት ፈጠን ብሎ ሲወጣ ፈልጐ ማክሲሚለንን ገኑ አደረገው። ማክሲሚለን ቫለንቲን በሞተችበት ዕለት ይታይበት የነበረው የትካዜ ገጽታ ይነበብበታል ።

" የወንድማችንን ነገር እንግዲህ አደራ ! " ስትል ዡሲዬ በእንደራሴው ጆሮ ሹክ አለች ።

እንደራሴው ከአሥራ አንድ ዓመታት በፊት ወደ አባቷ ክፍል በሚያስወጣው ደረጃ ላይ ሲያገኛት እንዳደረገው እንግሊዛዊ እጅዋን ጭምቅ አደረገና ። " አሁንም በመርከበኛው ሲንባድ ላይ እምነት አለሽ ? " አለ ሳቅ ብሎ ።

" ሙሉ ለሙሉ !"

" እንግዲያውስ አታስቢ ። "

እንደራሴው እንደተናገረው እውነትም አራቱ የሠረገላው ፈረሶች እየተቅበጠበጡ ልጓማቸውን እየነቀነቁ ፤ ጭራቸውን እየቆሉ ይጠባበቁ ኖሯል ። ከደረጃው በታች በኩል አሊ ላቡ እየተንዠበዠበ ይጠባበቃል ። መልእክት ለማድረስ ሳይሆን አይቀርም ፤ ከረጅም ጉዞ እንደተመለሰ ያስታውቃል ።

" አዛውንቱን አገኘሃቸው ? " ሲል ጠየቀ እንደራሴው በአረብኛ ። ዓሊ በአወንታ ራሱን ነቀነቀ ።

" እንዳዘዝኩህ ደብዳቤውን አይናቸው እያዩ ከፈትክላቸው?" አሊ ራሱን በድጋሚ በአዎንታ ነቀነቀ ።

" ምን አሉ ? "

አሊ ኖርቴር 'አዎ ' ሲሉ ሲፈልጉ እንደሚያደርጉት አይኖቹን ከደነ ።

" በጣም ጥሩ ፤ ተስማምተዋላ " አለ እንደራሴው " እንሂድ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

እንድራሴው ግን ከፓሪስ እየራቀ በሄደ መጠን እንዳች ኃያል ርካታ መንፈሱን ይመግብለት ነበር ። ወደትውልድ ሃገሩ እንደሚመለስ ስደተኛ ነበር ልቡ የሚፈንድቀው ።

ወዲያውኑ በነጫጭ ሕንፃዎች የተገነባችው ማርሴል ለእይታ በቃች ። እንደወትሮዋ ሕይወት ሙሉ ለሙሉ እስትንፋሱን እራግቦ ባታል ። ሁለቱም መንገደኞች ከልጅነታቸው ጀምር ያሳደገቻቸውን ይህችን የወደብ ከተማ ሲመለከቱ በአእምሮአቸው የትዝታ ጐርፍ ሰረገበት ።

መቆጣጠሪያ ሠገነቱ ላይ ሲደርሱ በደመ ነፍስ ቆሙ ። አንዲት መርከብ ወደ አልጀሪያ ልትጓዝ እየተዘጋጀች ናት ። መርከቧ ላይ የወጡት ተሳፋሪዎችና ዘመዶቻቸው የስንብት ቃላት ሲለዋወጡና ሲላቀሱ መመልከት ልብ የሚነካ ትርኢት ነበር።ማክሲሚለን ግን እእምሮውን ካጣበበው ሃሳብ ሊነቃ አልቻለም ።

“ ይመልከቱ ” አለ ማክሲሚለን የእንድራሴውን እጅ ይዞ “እዚህ ላይ ሆኖ ነበር አባቴ ፋራኦን ስትነሳና ስትደርስ ቆሞ የሚመለከታት። እዚህ ነበር ከሞትና ከውርደት ያዳኑት አባቴ የሰጠመችው መርከብ ስትመለስ አንገቴ ላይ የተጠመጠመብኝ ። እሱ ብቻ አልነበረም በሲቃ ያለቀሰው ፤ በዙሪያችን የከበቡን ሁሉ እንባቸውን ያፈሱልን ነበር ። ”

እንድራሴው ፈገግ አለ ። “እኔም እዚያ ቦታ ሆኘ በደስታ እልቅ ሸላችኋለሁ ” አለ ወደ መንገዱ ጠርዝ እያመለከተ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ከዚህ እሥር ቤት ጋር የሚገናኙ ታሪኮች የሉም ? ” ሲል ጠየቀ እንደራሴው ።

“እሉ እንጂ ጌታዬ ” ሲል መለሰ አስጐብኚው ፤ “በተለይ ከዚች ክፍል ጋር የተገናኘ አንድ የሚገርም ታሪክ እንደተሠራ የቀድሞው የዚህ ክፍል ዘበኛ አጫውቶኛል ። ሊሰሙት ይፈልጋሉ ? ”

“ አዎ” አለ እንደራሴው ፤ “ንገረኝ።” የራሱ ታሪክ ሲነገር ለመስማት የፈራ ይመስል በኃይል የሚመታውን ልቡን በእጁ ደገፍ አደረገው ።

“ ይህ ክፍል ” በማለት አስጐብኚው ንግግሩን ጀመረ ። “እንደ ተነገረኝ አንድ በጣም አደገኛ እሥረኛ ተመድቦበት ነበር ። ሌላ እሥረኛም በዚያው ጊዜ በሚቀጥለው ክፍል ይኖር ነበር ፤ እሉኛው ግን ቀውስ ቢጤ ቄስ ነበር ። ”

“ አሃ ፤ ” አለ እንደራሴው ፤ “ እንዴት ቀውስ ማለት ? ”

“ ከእሥር ቢፈታ ብዙ ሚሊዮን ፍራንክ እንደሚሰጥ ይደሰኩር ነበር እሉ ። ”

“ ሁለቱ እሥረኞች ይገናኙ ኖሯል ? ”

“ አዬ ! እሱማ ክልክል ነበር ጌታዬ ። እነሱ ግን የኋላ ኋላ የሚሥጥር መተላለፊያ ሠርተው ተገኙ ። ”

“ ማንኛቸው ነበሩ መተላለፊያውን የሠሩት ? ”

“ እንዴ ፣ ያው ወጣቱ ነዋ ፤ በጣም ኃይለኛና ጠንካራ ነበር ይባላል ። ምስኪኑ ቄስማ አርጌና ደካማ ከመሆኑም በላይ ቀውስ ስለሆነ አንድ ሃሳብ የሚከተል ጭንቅላት አልነበረውም ። ”

“ ደንባሮች ! ” አለ እንደራሴው ለራሱ ።

“ ያ ወጣት መተላለፊያውን እንዴት እንደሠራው ማንም አያውቅም ። ” ሲል አስጐብኚው ንግግሩን ቀጠለ ። “ እሱ ለመሥራቱ ግን ጥርጥር የለውም ። ይመልከቱ ፣ ምልክቱን ማየት ይችላሉ ። ” አስጐብኚው የያዘውን ጧፍ ከፍ አድርጐ ወደ ግድግዳው አስጠጋው።

“ አሃ ! አዎ ! ” አለ እንደራሴው ከራሱ ጋር እየታገለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ስሙ ማን ነበር ? "

" አይ ፤ ቁጥር 34 በሚል መጠሪያ ብቻ ነበር የሚታወቀው ።"

' ቪልፎርት ! ቪልፎርት ! ' ሲል የእንደራሴው ልብ ከውስጥ ጮኸ ። ' አንተ ርጉም . . . ምስሌ ከእንቅልፍህ ሊያባንንህ ሲያገጥ ብህ ለራስህ ደጋግመህ የነገርከው ይህን መሆን አለበት ። '

" ሌሎቹን ክፍሎች ማዬት ይፈልጋሉ ጌታዬ ? " በሚል ጥያቄ አስጎብኚው እንደራሴውን ከሃሳቡ መለሰው ።

" አዎ ፤ በተለይ የቄሱን ክፍል ብታሳዬኝ ። "

" ይከተሉኝ ። "

" አንድ ጊዜ ታገሰኝ ።" አለ እንደራሴው ፤ " ይህንን ክፍል ለመ ጨረሻ ጊዜ ላዬው እፈልጋለሁ ። "

" ይኸማ ለእኔም ተመቸኝ።"አለ አስጎብኚው፤ " እስከዚያ የ ቄ ሱን ክፍል ቁልፍ አመጣለሁ ። "

"ሂድና አምጣው እንግዲያውስ ። "

" ጧፉ እዚሁ ይሁንልዎ ። "

" አይ ፤ ውሰደው ። "

" እንዴ ፤ በጨለማ ይዳፈናሉ ። "

" ግዴለህም ፤ በጭለማ ማየት እችላለሁ ። "

" እንግዲያውማ እንደ ቁጥር 34 ነዎ ማለት ነዋ ። እሱኮ ጥቅ ጥቅ ባለ ጨለማ መድፌ ማዬት ይችላል ይሉታል ። "

' ውለናሞች ። ይህን ችሎታ ለመቀዳጀት አሥር ዓመት ፈጅቶበ ታል ። ' አለ እንደራሴው ለራሱ ። አስጎብኚው ጧፉን ይዞ ወጣ ።

እንደራሴው እውነቱን ተናግሯል ። ለጥቂት ሰኮንዶች በጭ ለማው እንደቆዬ ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ይታዬው ጀመር ። "አዎ።" አለ ፤ " ይህ ድንጋይ ነበር መቀመጫዬ ፤ አንድ ቀን ጭንቅላቴን በድንጋይ ልፈረክስ ከግድግዳ ጋር ተጋጭቼ ሳለ የፈሰሰኝ ደም ነጠ ብጣብ እንኳ እንዳለ ነው ። እነዚያ ቁጥሮች . . . አዎ አዎ አስታወ ስኳቸው ፤ አንድ ቀን አባቴን በሕይወት ፤ ሜርሲደስን ሳታገባ አገ ኛቸው እንደሁ ዕድሜአቸውን ሳሰላ የጻፍኳቸው ናቸው ። እነዚያን



t.me/OLDBOOKSPDF

" ተሳስተዋል መሰለኝ ጌታዬ ? "

" እንዴት ? "

" የወርቅ ሳንቲሞች ናቸውኮ ። "

" አውቃለሁ ። "

" እያወቁ ነው የሰጡኝ ? "

" አዎ ። "

አስጐብኚው እንደራሴውን እየተሽከረመመ ከተመለከተው በኋላ " ጌታዬ " አለ ፤ " ልግስናዎ አልገባኝም ። "

" ይህን ያህል የሚያደናግር አይደለም ። አዬህ ፡ እኔም ባንድ ወቅት መርከበኛ ስለነበርኩ የነገርከኝ ታሪክ መንፈሴን አውኮታል ።"

" እንግዲያውስ ጌታዬ እንዲህ ያሉ ሲጋስ ከሆኑ እኔም የበኩሌን ላበረክትልዎ ። "

" ምን የምታበረክትልኝ ነገር አለህ ? "

" አሁን ከነገርኩኝ ታሪክ ጋር የሚናገናኝ ነገር ። "

" እረ ? ምንድን ነው እሱ ? " አለ እንደራሴው በጉጉት ።

" ልነግርዎ አይደል ፡ አንድ ቀን ' አንድ እሥረኛ አሥራ አምስት ዓመት ካሳለፈባት ክፍል ውስጥ አንድ ነገር አይጠፋም ' እያልኩ ከራሴ ጋር እነጋገር ነበር ። ግድግዳዎቹን መታ መታ አደረግሁ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአልጋው ራስጌ አጠገብ ወለሉ ሥር አንድ የተነደለ ነገር ድምጽ ተሰማኝ ። ድንጋዮቹን ብድግ ሳደርግ ምን አገኘሁ መሰለዎ . . . . . . ? "

" የገመድ መሰላልና አንዳንድ እቃዎች ? " ሲል እንደራሴው ጮኸ ።

" እንዴ ፡ እንዴት ሊያውቁ ቻሉ ? " አለ አስጐብኚው በመገረም አፉን ይዞ ።

" እንዴት አውቃለሁ ብለህ ነው ፣ በግምት ነው እንጂ ። መቼም አንድ እሥረኛ በክፍሉ ውስጥ የሚደብቀው እንዲህ ዓይነት ነገሮችን መሆን አለበት ብዬ ነው ። . . . . ለመሆኑ አትረሃቸዋል ? "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አዎ ፤ ግን አደራህ ከዚህ እስካልሄድኩ ድረስ ፊተህ እንዳታ ዬው ። ”

ብርቅዬውን ቅርስ በደረቱ ሸጉጦ ከጨለማው እሥር ቤት እየ ተጣደፈ ከወጣ በኋላ ወደ ጀልባዋ ሄደ ። “ ወደ ማርሴል ! ” አለው መርከበኛውን ።

ጀልባዋ ጉዞዋን እንደጀመረች እንደራሴው ቻቲዩዲፍን ገል መጥ አድርጎ እያዩ “ ወዮላቸው በዚህ አሰቃቂ ወህኒ ያጐሩኝ ! ” አለ ለራሱ ።

ድሉ ሊጠናቀቅ ይሆን ? የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ ለሁለተኛ ጊዜ ጥርጣሬውን አስወገደ ። ብቀላው አገረሸበት ። የልቡ ውስጥ እቶን እንደሚገራር ፍም ተንተርክኮ ፈጀው ። “ ሂድ ሂድ ” አለው ፤ ወደ ባላጋራው ። እንደገና ድል ሳይነሳ ላይመለስ ማለ ።

ማርሴል እንደደረሰ ማክሲሚሊንን ወደ ቀጠረበት የመከነ መቃ ብር ሥፍራ ሄደ ።

እንደራሴውም እንደ ማክሲሚለን ከእሥር ዓመታት በፊት ወደዚያ የመቃብር ሥፍራ ሄዶ እንባውን የረጨ ቢሆንም ያ ባለብዙ ሚሊ ዮን ፍራንክ ቱጃር በረሃብ አለንጋ ተገርፈው የሞቱ አባቱ ያረፉበትን መቃብር ሊያገኝ አልቻለም ።

ማክሲሚለን እንደ ዛፍ ተደግፎ የአባቱንና በሁለት ዓመት ቀድ ማው ያረፈችው እናቱን መቃብር ሐውልቶች በትካዜ ፍዝዝ ብሎ ይመ ለከታል ።

“ማክሲሚለን” አለ እንደራሴው ፤ “ በጉዟችን ወቅት እዚህ ማር ሴል ብዙ ቀናት መቆየት እንደምትፈልግ ስትናገር ነበር ። አሁንም በውሳኔህ እንደጸናህ ነህ ? ”

“ ምን ውሳኔ አለኝ ክቡር እንደራሴ ? እንዲያው ከሌላው ቦታ ሁሉ እዚህ ብሆን ጥቂት ቀለል ይልልኛል ብዬ ነው እንጅ ። ”

“ ጥሩ ፤ በል እንግዲህ ለአጭር ጊዜ ልለይህ ነው ። ግን ቃል ህን ታከብራለህ አይደለም ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣቱ ራሱን ደፋ አደረገ ። " አከብራለሁ " አለ ለአፍታ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ ። " ግን እንዳይረሱ . . . . . "

" ልክ ጥቅምት አምስት ቀን በሞንቴ ክሪስቶ ደሴት ላይ እጠብቅሃለሁ ። ጥቅምት አራት ቀን በዚሁ በማርሴል አንድ ባርካ ተዘጋጅታ ትጠብቅሃለች ። የጀልባዋ ስም ኢዩረስ ይባላል ፤ ለካፒቴኗ ስምህን ስትነግረው ያሳፍርሃል ። "

" እንዳሉኝ አደርጋለሁ ክቡር እንደራሴ ። ብቻ ጥቅምት አምስት ቀን ያሉኝን እንዳይረሱ . . . . "

" በዚያ ዕለት ቃሌ ከፈረሰ ሕይወትህን እንዳታጠፋ መከልከል ቀርቶ እንደማግዝህ ሃያ ጊዜ አልነገርኩህም ? በል ይልቅስ አሁን ደህና ሁን ። "

" መሄድዎ ነው ? "

" አዎ ፤ ኢጣሊያ አንድ ጉዳይ አለኝ ። አሁኑኑ መሄድ አለብኝ።"

ማክሲሚለን እንደራሴውን ተከትሎ ወደብ ድረስ ሄደ ። እንደራሴውን የምትጠብቀው መርከብ ጢስ መትፋት ጀምራለች ። ወዲያውኑ ጉዞዋን ቀጥላ ከአንድ ሰዓት በኋላ በምሥራቁ አድማስ በኩል ተሰወረች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" በል እስኪ አሁን ፈረንሳዊው የገንዘቡን ትክክለኛ መጠን ከማወቁ በፊት እንዳያወራርድ ሄጀ ልመልከተው ። "

ፔፒኖ መስማማቱን ገለጸ ።

የሂሳብ ሠራተኛው ዳንግላርና ተሳላኪው በገቡበት በር በኩል ሄዶ ጥቂት ከቆየ በኋላ እየሳቀ መጣ ።

" እህሳ ? " ሲል ጠየቀ ፔፒኖ ።

" ተዘጋጁ.......... እህያ የማይችለው ገንዘብ ነው ። "

" አምስት ሚሊዮን አይደለም ? "

" አዎ ፣ ግን እንዴት አወቅህ ? "

" ከከቡርነታቸው ከሞንቴ ክሪስቶ እንደራሲ ከተቀበለው ደረሰኝ ነዋ ! "

" አሃ ፣ ልክ ነህ " አለ የሂሳብ ሠራተኛው ። " ግን ካወቅህ እንዴት ልትጠይቀኝ መጣህ ? "

" ሰውዬው በትክክል እሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ። "

" እሱው ነው የምትፈልገው........ሽ.......ያው እየ ጦጣ ነው ። "

የሂሳብ ሠራተኛው ብዕሩን ብድግ ሲያደርግ ፔፒኖም ወረቀት ቢጤ አንስቶ ያነብ ጀመር ። ዳንግላር የድርጅቱን ተቆጣጣሪ አስከትሎ ሲወጣ ፊቱ በፈገግታ ፈክቶ ነበር ። ፔፒኖ ከዳንግላር ጀርባ ወጣ ።

በንግግራቸው መሠረት በድርጅቱ በር ላይ ለዳንግላር ሠረገላ ተዘጋጅቶ ይጠብቅ ነበር ። አስጎብኚው በሩን ከፈት አድርጎ ሲይዝለት ዳንግላር ሠረገላው ውስጥ ገባ ። አስጎብኚው በሩን ዘግቶ ከአሽከርካሪው ጎን ሄዶ ተቀመጠ ። ፔፒኖም ከኋላው መቀመጫ ዘሎ ቁብ አለ ።

" ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል መሄድ አይፈልጉም ጌታዬ ? " ሲል ጠየቀ አስጎብኚው ።

" ለምን ቢባል ? " ነበር የዳንግላር ኩስታራ መልስ ።

" እንዴ ፣ ለመጎብኘት ነዋ ! "



t.me/OLDBOOKSPDF

በእጁ ያለው አነስተኛ ገንዘብ እስከሆነ ድረስ በመያዝ ከማሥር በስተቀር የሚያደርጉት ነገር የላቸውም ። አልበርትን የያዙት ለሃያ አራት ሺህ ፍራንክ እንደሆነ ትዝ አለው ። የኢሱን መያዣ ደግሞ ምናልባት በእጥፍ ከፍ ቢያደርጉ ነው ፣ በአርባ ስምንትና በአምሳ ሺህ ፍራንክ ። ግን አሁንም ከከሰረትና ከሚስቱ የተረፈ አምስት ሚሊዮን አምሳ ሺህ ፍራንክ ያለው ሰው ስለሆነ የተጠየቀውን ከፍሎ እግሩ ወዳደረሰው መሄድ ይችላል ። መቸም ምንም ቢሆን በአምስት ሚሊዮን ፍራንክ አይዙትም ።

ዳንግላር እነዚህን ሃሳቦቹን ከደረደረ በኋላ እፎይታ ተሰምቶት ጉዝጓዙ ላይ በጀርባው ተንጋለለበት ። ሁለትና ሦስት ጊዜ እንደተገላበጠ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዶት ያኳርፍ ገባ ።

‘ በሆነ አጋጣሚ የሚለው ቃል ሃያ አራት ሰዓት ጠሙን ለሚ ጠራሞት ሰው እጅግ የሚያስቅ ነው ። ’ አለ ዳንግላር በሃሣቡ ። ከዚ ያም ጮህ ብሎ “ አዎ በጣም ርቦኛል ፤ በርግጥ እጅግ በጣም ርቦኛል ” አለ ።

“ ታዲያ መቼ ነው ምግብ ለመውሰድ የሚፈልጉት ጌታዬ ? ” ሲል ጠየቀ ፔፒኖ ።

“ አሁኑኑ ነዋ ፤ ከተቻለ ።”

“ ከዚህ የበለጠ ቀላል ነገር የለም ። ” አለ ፔፒኖ ፤ “ የሚፈል ጉት አይነት ይቀርብልዎታል . . . በርግጥ ሁሉም ትክክለኛ ሰው እንደ ሚያደርገው ከከፈሉ ። ”

“ ምን ይደረግ ” አለ ዳንግላር ፤ “ በርግጥ እውነት ለመና ገር ያፈኑና ያሠሩ ሰዎች እሥረኞቻቸውን ራሣቸው መመገብ ቢኖርባ ቸውም ።”

“ አይ ፡ ያ አልተለመደም ጌታዬ ። ”

“ አግባብ እንኳ አይደለም ፤ እኔ ግን መቸስ ልከፈል ። ” አለ ዳንግላር በቅንነቱ የዘበኑን ልብ ሊጋራ ፈልጎ ።

“ ምን ዓይነት ምግብ ነው የሚፈልጉት ጌታዬ ? ማዘዝ ብቻ ነው ከርስዎ የሚጠበቀው ።”

“ እዚህ ማብሰያ ቤት አላችሁ ማለት ነው ?”

“ እንዴ ፤ ታዲያስ !”

“ አብሳዮችም ?”

“ ምርጥ አብሳዮች !”

“ እንግዲያውስ ዶሮ . . . . ጥቂት አሣ . . . ሥጋ . . . የተገ ኘውን አምጣልኝ ።”

“ እንደፈለጉ ጌታዬ ፤ ዶሮ ላዝዝልዎ ?”

“ አዎ ዶሮ ! ” ዳንግላር ምራቁን ዋጠ ።

ፔፒኖ ወደ ውጭ ሄዶ “ ለክቡርነታቸው ዶሮ !” ሲል ጮኸ ። ወዲያውኑ አንድ ለግላጋ ወጣት ከብር በተሠራ ውብ ሣህን ዶሮ ይዞ መጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ስድሣ ፍራንክ ይቀራል ።” አለ ፔፒኖ ፤ “ እያዘገምን መቶሺ መድረሳችን አይቀርም ማለት ነው ።”

“ የማነህ እኛ ? ” አለ ዳንግላር በፔፒኖ ድርቅ ያለ ማሾፍ ደሙ ፈልቶ ። “ ስትፈልግ ጃንብ ግባ ፤ ማን እንደሆንኩ አታውቀኝም ።”

ፔፒኖ ምልክት እንደሰጠ ለግላጋው ወጣት ሣህኑን አንስቶ ይዞት ሄደ ። ዳንግላር አንዛው ላይ በቁሙ ወደቀበት ፤ ፔፒኖ በሩን ዘግቶ ቆለፈው ። ጨንራው ባዶውን ከመቅረቱ የተነሣ ዳንግላር እስከ መቼውም የሚሞላው ባይመስለውም ለግማሽ ሰዓት ያህል በትዕግሥት ጠበቀ ። ከዚያም በተዳከመ ሰውነቱ እንደምንም ብድግ ብሎ ወደ በሩ ከሄደ በኋላ ሆዱን እከክ እከክ እያደረገ ፤ “ እባካችሁ እዚህ አትራችሁ አትጫወቱብኝ ። ለምን ከኔ ምን እንደምትፈልጉ አትነግሩኝም ?” አለ በሰለለ ድምጽ ።

“ ከእኛ ምን እንደሚፈልጉ መናገሩ የርስዎ ፋንታ ነው ጌታዬ ” ሲል መለሰ ፔፒኖ ። “ ያዝዙን ፤ እንፈጽማለን ! ”

“ መጀመሪያ በሩን ክፈትልኝ ” አለ ዳንግላር ። ፔፒኖ በሩን ከፈተ ። “ ምግብ እፈልጋለሁ ! ” ሲል ጮኸ ዳንግላር ።

“ ርቦዎታል ጌታዬ ?”

“ አሹፍብኝ ግዴለም ። እንደራበኝ በደንብ ታውቃለህ !”

“ ምን ይምጣልዎ ?”

“ ዳቦ አምጣልኛ ፤ ዶሮማ ብርቃችሁ ነው ።”

“ ዳቦ ቶሎ ! ” ሲል ጮኸ ፔፒኖ ። ወጣቱ አንስተኛ ዳቦ ይዞ ቀረበ ።

“ ይኸስ ስንት ነው?”

“ አርባ ፍራንክ በቅድሚያ ከፍለዋል ፤ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ስድሣ ይቀራል ።”

“ ከሁለት ጉራሽ ለማታልፍ ዳቦ መቶ ሺህ ፍራንክ !”

“ ይኸው ነው ጌታዬ ።”

“ ግን የዶሮው ዋጋም ተመሣሣይ ነበር ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እዚህ ዶሮ ዳቦ ፣ እሚ . . . እያሉ ዋጋ መንቀስ የለም ። ምግም ይብሉ ምን ተመኑ ያው ነው ።"

" አሁንም ይኸን የማይረባ ቀልድህን አላቆምህም ! በረሀብ ልትገድሉኝ እንደፈለጋችሁ ለምን በግልጽ አትነግሩኝም ?" ረሃብ ሕጻን ያስመስላል ። ዳንግላር ሁኔታው ሁሉ የሕጻን መሰለ ።

" በጭራሽ ጌታዬ . . . . እንዲያውም እርስዎ ነዎት ራስዎን ለመ ግደል የሚፈልጉት ። ከከፈሉ ይቀርብልዎታል ።"

" ግን እንዴት አድርጌ ነው የምከፍለው አንት ደደብ?" ሲል ባረቀ ዳንግላር ። " መቶ ሺህ ፍራንክ በኪሴ ይዤ የምዞር ይመስል ሃል ?"

" ስድስ ይቆዩኝና በኪስዎ አምስት ሚሊዮን አምሳ ሺ ፍራንክ ይዘዋል ፣ ጌታዬ " አለ ፔፒኖ " በመቶ ሺህ ፍራንክ ሂሣብ ለሃምሣ ዶሮዎች ፣ በአምሳ ሺ ደግሞ ለግማሽ ዶሮ የሚበቃ ገንዘብ ነው ።"

ዳንግላር ሽምቅቅ አለ ። አይኖቹ በኃይል ተከፈቱ ። አፍን ጫው ተነፋ ። አሁንም ነገሩ ቀልድ ቢሆንም በመጨረሻ ሃሣባቸው ግልጽ ሆነለት ። " ይሁና ! " አለ በረጅሙ ተንፍሶ " መቶ ሺህ ፍራንክ ብሰጥህ የምፈልገውን ምግብ ታቀርብልኛለህ ?"

" ያለጥርጥር !"

" ግን እንዴት ነው ልሰጥህ የምችለው ?" ሲል ጠየቀ ዳንግላር በረጅሙ እየተነፈሰ ።

" ቀላል ነው ። ቼክዎ ላይ ፈርመው ይስጡንና የኛ ሂሣብ ሠራተኛ ሄዶ ገንዘቡን ያወጣል ።"

ፔፒኖ ብዕር አውጥቶ ሲሰጠው ዳንግላር ቼኩ ላይ ፈረመና " ይኸው ልሀ " አለ ።

" ይኸው ዶሮውም !"



t.me/OLDBOOKSPDF

# 66

በማግሥቱ ዳንግላር እንደገና ቢርበውም በዚያ ቀን ሌላ ገንዘብ ወጭ አደርጋለሁ ብሎ አላመነም ። ከትናንት ራቱ ዶሮ አስተርፎ በአንድ ጥግ በኩል ደብቆት ነበር ።

ነገር ግን ያሳደረውን ምግብ ተመግቦ እንደጨረሰ ውሃ ጥም ያንገበግበው ጀመር ። ፈጽሞ ያላሰበው ሌላ ፈተና ። ምላሱ ተናጋው ውስጥ ተሰንቅሮ እስኪቀር ድረስ ከጥማቱ ጋር ተሟገተ ። የኋላ ኋላ ግን መቋቋም አቅቶት ተጣራ ። ዘቡ በሩን ከፈተ ። አዲስ ሰው ነበር ። ከለመዱት ሰው ጋር መደራደሩ እንደሚመረጥ ገምቶ ፔፒኖ እንዲመጣለት ለመነ ።

" አቤት ጌታዬ ! " አለ ፔፒኖ ፈጠን ብሎ በመቅረብ ። " ምን ልታዘዝ ?"

" እባክህ የሚጠጣ ነገር . . . ? " አለ ምላሱ የተወተፈበት እሥረኛ

" እንደሚያውቁት ጌታዬ በሮም ዙሪያ ባለው የገጠር ክፍል ወይን ጠጅ በጣም ውድ ነው ።"

" በል ውሀ አምጣልኝ እንግዲያውስ " አለ ዳንግላር ፤ የሱ ቅስም እንደተሰበረ ብድሩን ለመመለስ ፈልጐ ።

" አዬ . . . ዘንድሮ የገባው ድርቅ ውሃን ከወይን ጠጅ የበለጠ እንዳስወደደው አልሰሙ ? "

" አሁንም ጥቂት ልንቀላለድ ነው አይደል ? " አለ ዳንግላር። እሥረኛው ይህን እየተናገረ የግዱን ሊስቅ ቢሞክርም ግንባሩን ላብ ሲያጠምቀው ተሰማው ፤ " በላ ወዳጄ" አለ ቀጠለና የፔፒኖን ግድ የለሽ አኳኋን ተመልክቶ ። " የምጠይቅህ አንድ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ብቻ ነው ። ልትከለክለኝ ነው ? "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በብርጭቆ አንሸጥም ጌታዬ ” ሲል መለሰ ፔፒኖ ተስላችቶ።
“ እሽ ጠርሙስ ወይን ጠጅ አምጣ ! ”
“ ምን ዓይነት ?”
“ የመጨረሻውን ርካሽ ።”
“ ሁሉም ዋጋቸው አንድ ነው ።”
“ ስንት?”
“ ጠርሙሱ ሃያ አምስት ሺህ ፍራንክ ።”

“ ያለህን በሙሉ ልንወስድብህ እንፈልጋለን ብላችሁ ለምን በግልጽ አትነግሩኝም ?” አለ ዳንግላር ምርር ብሎ ። “ እያለሳለሳ ችሁ ከምትቀልዱብኝ ቁርጡን አሳውቁኝ ።”

“ ያ ምናልባት የአለቃ እቅድ ይሆናል ፤ ” አለ ፔፒኖ ።
“ ማነው አለቃ ?”
“ ትናንት የተወሰዱበት ሰው።”
“ የታለ ?”
“ እዚሁ ። ”
“ ላየው እፈልጋለሁ ።”
“ ችግር የለውም ።”

ከአፍታ በኋላ ሉዊጊ ቫምፓ ከዳንግላር ፊት ለፊት ቆመ ። “ ፈለጉኝ ?” ሲል ጠየቀ ቫምፓ ።

“ እዚህ ያመጡኝ ሰዎች አለቃ እርስዎ ነዎት ?”
“ አዎ ፤ ጌታዬ ።”
“ ምን ያህል ገንዘብ ነው ከኔ የምትሹት ?ይንገሩኝ ! ”
“ እንዲ ፤ ያለዎትን አምስት ሚሊዮን ፍራንክ በሙሉ ነዋ!”

ዳንግላር ልቡ በኃይል ሲከማተር ተሰማው ። “ በዚህ አለም ያለኝ አንጡራ ሃብት እሱኮ ነው ። ” አለ በሚማጸን አኳኋን “ ለዚያ ውም ከብዙ ሃብት ውስጥ የተረፈኝ ገንዘብ ነው ። እሱን ከወሰዳች ሁብኝ ሕይወቴንም ውሰዱት ።”

“ ደምዎን እንዳናፈስ ተከልክለናል ጌታዬ ።”
“ በማን ነው የተከለከላችሁት ?”
“ በምናከብረው ሰው ።”



t.me/OLDBOOKSPDF

" እናንተም የምታከብሩት ነገር አላችሁ ?" እንጀት ቢርቀውም ሳቁን ሊቆጣጠር አልቻለም ።

" አዎ ! "

" እሱስ ? የሚያከብረው ነገር አለው ?"

" አዎ ! "

" ምንድን ይሆን? "

" ቃል ኪዳኑን ! "

ዳንግላር ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ተውጦ ቆየ ። " አልገባኝም " አለ በመጨረሻው ።

" የርስዎ ፋንታ ነው ።"

" ለመሆኑ ሰውዬው በዚህ መንገድ " እንድታንገላቱኝ ያዘዛችሁ ለምንድን ነው ?"

" እኔ የማውቀው ነገር አይደለም ።"

" እስኪ ይስሙኝ ፤" አለ ዳንግላር ፤ አንድ ሚሊዮን ፍራንክ ይፈልጋሉ ?"

" አልፈልግም ። "

" ሁለትስ ?"

" አልፈልግም ። "

" ሶስት ? . . . .አራት ? . . . ከእስር ከፈቱኝ አራት ሚሊዮን ፍራንክ እሰጥዎታለሁ ።"

" አምስት ሚሊዮን ፍራንክ ለሚያወጣ ነገር ለምን አራት ሚሊዮን እቀበላለሁ ?" ሲል ጠየቀ ቫምፓ ።

" በሉ ገንዘቡን ውሰዱና ግደሉኝ እንግዲያውስ !" ሲል ጮኸ ዳንግላር ጸጉሩን ሊነጭ እየከጀለ ።

" ረጋ ይበሉ ጌታዬ ፤ በዚህ አያያዝማ በቀን የአንድ ሚሊዮን ፍራንክ ምግብም አይመክትዎ ። ቁጠባ ነው የሚያዋጣዎ !"

" ግን ገንዘቤ ሲያልቅ ምን እሆናለሁ ?" ዳንግላር ተወራጨ ።

" ጥያቄው ቀላል ነው ። ይራባሉ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ተሳስተሃል ፤ የሞንቴ ክሪስቶ እንደራሴ አይደለሁም ።”

“ ታዲያ ማንነዎ ?”

“ የከዳኸውና የወነጀልከው ፤ እጮኛውን አቃጥረህ ያሸረምጥከበት ፤ ይህን እንደጤዛ የረገፈ ሀብትህን ለማግበስበስ ስትጣደፍ የእግርህ ጉዝጓዝ ያደረግኸው ፤ ከርሰ ምድር ውስጥ ከነሕይወቱ ያስቀበርከው ፤ አባቱን በረሃብ የገደልግበት ፤እሱ ግን ራሱ ይቅርታ እንዲያደርግልት ስለሚፈልግ የምህረት እጁን የሚዘረጋልህ ፤ ኤድመንድ ዳንት ማለት እኔ ነኝ ።” እንደራሴው ወንጀለኛውን ሊጨብጥ እጁን ዘረጋ ።

ዳንግላር ግን አንገርቶ ወለሉ ላይ ወደኋላው ወደቀ ።

“ ተነስ !” አለ እንደራሴው ። “ ሕይወትህ ይተርፋል ። ሶስቱ ጓደኞችህ እንዳንተ እድለኞች አልሆኑም ፤ የተረፈህ ሃምሣ ሺህ ፍራንክ ካንተው ጋር ይቆይ ፤ በስጦታ አበርክቼልሃለሁ ። አምስቱን ሚሊዮን ፍራንክ ግን ላጭበረበርከው የሆስፒታሎች ኮሚሽነር መልሼለታለሁ ! በል አሁን ምግብና መጠጥ ይቀርብሃል ፡ ዛሬ ምሽት የእኔ እንግዳ ነህ ። ቫምፓ . . . ይህ ሰው ከድካሙ ሲያገግም ልቀቁት ። ”

እንደራሴው ተመልሶ ሲሄድ ዳንግላር ከተጋደመበት አልተነሣም ። እንግቱን ቀና ሲያደርግ ማዬት የቻለው በመተላለፊያው በኩል ውልብ ብሎ የጠፋ ጥላ ብቻ ነበር ።

በእንደራሴው ትዕዛዝ መሠረት ቫምፓ ምርጥ የወይን ጠጅና ከአትክልት የተዘጋጀ ምግብ አስመጣለት ። ከዚያም ከዋሻው ካስወጣው በኋላ ሽፍን ሠረገላ ውስጥ አስገብቶ አውላላ ሜዳ ላይ ሲደርስ ትቶት ተመለሰ ።

ዳንግላር ያለበትን ቦታ ማወቅ ባለመቻሉ እስኪነጋ ዝም ብሎ ቆየ ። ከጧት ውርጭ ጋር የብርሃን ውጋጋን መታዬት እንደጀመረ በአጠገቡ ትንሽ ኩሬ መኖሩን አየ ። ውሃጥሙ እንደገና ያንገበግበው ስለነበር ወደ ኩሬው አጐነበሰ ። የራሱን መልክ በውሃው ውስጥ ሲያዬው ሊያምን አልቻለም ፤ ጸጉሩ የተባዘተ የጥጥ አመልማሎ እስኪመስል ሸብቶ ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 67

ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ሆኗል ። በቀለማት የተሽኰረኰረች ባርካ ባህሩን እየሰነጠቀች በዝግታ ትንሣለች ። ጸጉሩ ማጅራቱ ሥር የወረደ ረዘም ያለ ወጣት እንደኛውን አውታር ተደግፎ ቆሞ ባርካዋ የጐጆ ቤት ክዳን መስላ ከባሕሩ መሐል ጉብ ያለችውን ደሴት ስትጠጋ ያስተውላል ። " ምንቱ ክሪስቶ የተባለችዋ ደሴት ያች ናት እንዴ ?" አለ ወጣቱ ጥልቅ ሐዘን በተቀላቀለበት ድምጽ ።

" ያች ናት ጌታዬ ። " የጀልባዋ ካፒቴን ነበር ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የእሣት ብልጭታ ከደሴቷ ላይ ቦግ አለ ። ወዲያውኑ የተኩስ ድምጽ ተሰማ ። " ምልክት ተሰጠን ጌታዬ" አለ ካፒቴኑ ፤ " የመልስ ተኩስ ይፈልጋሉ ? "

" አዎ ! "

ካፒቴኑ የጐረሰ ጠመንጃ ለወጣቱ ሲሰጠው ወጣቱ ጠመንጃውን በዝግታ ከራሱ በላይ ከፍ አድርጐ ወደ ሰማይ ተኰሰ ።

ብዙም ሳይቆይ ወደ ደሴቷ ደርሰው ከጀልባዋ ወረዱ ። ወጣቱ የደሴቷን አሸዋ እንደረገጠ ጊዜው በጣም መሽቶ ስለነበር መንገድ የሚመራው ሰው ፍለጋ የያዘ ይመስል ዙሪያውን ያማትር ገባ ። ወዲያው አንድ ነገር ትከሻው ላይ ሲያርፍ ዞር አለ " ታዲያስ ማክሲሚሊን ፤ ቀጠሮ በማክበርህ አመሰግናለሁ ።" የደሴቷ እንደራሴ ነበር ።

" እንዴ ፤ እርስዎ ነዎት እንዴ ?" ማክሲሚሊን የእንደራሴውን እጅ ጨበጠ ።

" አዎ እኔ ነኝ ። እንዳንተ ቀጠሮ አክባሪው ።"

" ክቡር እንደራሴ " አለ ማክሲሚሊን ፤ ከረጅም ጉዞ በኋላ በመምጣቱ እረፍት እንኳ ሊያደርግ ሳይፈልግ ፤ " እመጣጤ በወዳጄ ክንድ ላይ ለመሞት ነው ። አሁንም በዚህች ምድር ላይ የማፈቅራ



t.me/OLDBOOKSPDF

## የተርጓሚው ሌሎች የትርጉም ሥራዎች

# ጉድ ሲናጥ

# *Des perfume*

## *Patrick SÜbkind*

መጽሐፍ አንብቦ ፊልሙን ማፈላለግ የሁሉ ነገር ነው። ለምሳሌ የKunderaን «The unbearable lightness of being» ካነበብኩ በኋላ ፊልሙን አፈላልጌ አይቼዋለሁ። የFyodor Dostoevskyን «The Gambler»ን እንዲሁ። ከእነዚህ ሁሉ የተለየብኝ «ጉድ ሲናጥ» (Des perfume) ነው። መጀመሪያ ፊልሙን «The Perfume» በሚል ርዕስ አየሁት። ወደድኩትም። መጽሐፉ ከፊልሙ በላይ እንደሚሆን አልተጠራጠርኩም። አፈላለግኩ፤ አፈላለግኩ . . . አጣሁት። በመጨረሻ ግን «በፈረሰ የፈለግኩት . . .» እንዲሉ ከእናት ቋንቋው ከጀርመንኛ ወደ ቋንቋዬ አማርኛ ተመልሶ በእጄ ደረሰ መሰለ። አንብቤ ጨረስኩት። በእርግጥም ግምቴ ይዞልኝ ሞጋል። መጽሐፉ ከፊልሙ በላይ የላቀ ነበር። ደገምኩት. . . ;

. . . . «ጉድ ሲናጥ» የሰው ልጅ ሕሊሙና አፍንጫ «ጓዳ» ተንጠልጥሎ ሁሉመና በጠረን ኃይል ሥር የሚሆድቅበትና መሥሥቱን የሚቀርብበት፣ እንኳን ሲሞክር ታሪክ የሚያውቀው ድንቅ ሥራ ነው። ይኸን መጽሐፍ አንብቦ ለሌላችን ሳይጋብዙ ማለፍ የሚያቻል ቢሆንብኝ «እነሆ» አልኳችሁ። አንብቡትና መጽሐፉን ከእኔ ጋር እማምራችሁ ፍርዳችሁን ወዲያው . . .

ዓለማየሁ ገላጋይ
ደራሲና ሐያሲ

t.me/OLDBOOKSPDF

[illegible] ... ቶች [illegible]
[illegible] ናቸው ።

ተ[illegible]

[illegible]— ፈረንሳዊው ደራሲ አሌክሳንደር ዱማስ [illegible] ዘመናዊ አውሮፓ " የድርሰት ፋብሪካ " [illegible] ሊጠራ ያደረገ ብርቅ መጽሐፍ ነው ።

[illegible]— እውቅ ሃያሲያን " የዱማስን ድርሰቶች [illegible] ነበረም ፣ የለም ፣ ሊኖርም አይችልም ። " ብለው [illegible] እንዲቀበሉለት ያደረገ ተዓምረኛ ድርሰት ነው ።

[illegible]— ደራሲዎን " የሥነ ጥበብ ቁንጮ " ከሰኙት [illegible] ምቹ ውስጥ የጕላውን ድርሻ የያዘ ስሜት [illegible] ልቦለድ ነው ።

[illegible]— ፈረንሳውያን ነጮች ፣ ደራሲውን ባንድ ወገኑ [illegible] ቁር በመወለዱ እንዳያንቋሽሹት ጨንቋቸው " [illegible] ቱን አስረሳንከ ! " እንዲሉ ያስገደደ [illegible] ሲዝ ጽሑፍ ነው ።

ንግድ ማተሚያ ቤት

ዋጋው ብር 9:50

t.me/OLDBOOKSPDF